Good Governance Africa



# ወጣትና ፖለቲካ በኢትዮጵያ

ዓርታኢ ዘሪሁን መሐመድ

RESEARCH REPORT

# ወጣትና ፖለቲካ በኢትዮጵያ

ዓርታኢ

ዘሪሁን መሐመድ

መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ

Goog Governance Africa (GGA)

© 2016 ዓ.ም መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ

አዲስ አበባ

ማንኛውም የአሳታሚው መብቶች በሕግ የተጠበቁ ናቸው

መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ

ፖ.ሣ.ቁ 46214

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ኢሜይል፡ info.easternafrica@gga.org

ድረ-ገጽ፡ www.gga.org

በዚህ ህትመት ውስጥ የተገለጹት አስተያየቶች የመልካም ስተዳደር አፍሪካን፣ የመልካም አስተዳደር አፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካን፣ የሥራ አመራር ቦርዱን፣ የድርጅቱን አጋሮች አቋምና አመለካከት ላያንጸባርቅ ይችላል፡፡

# ማውጫ


መግቢያ ........................................................................................ V

ወጣቱና ፖለቲካ በኢትዮጵያ፡- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ..............................1

ባሕሩ ዘውዴ

ትምህርትና የወጣት ስብዕና ልማት በኢትዮጵያ................................................21

የቆየዓለም ደሴ

ወጣትነት፣ግብረገብና ሥነ-ምግባር በኢትዮጵያ...................................................43

ጠና ደዎ

ወጣቶች እና የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም በኢትዮጵያ ...................................71

ዑርጌሳ ዴሬሳ ጉቱ

የወጣቶች ፖለቲካዊ አደረጃጀት እና የመንግስት ግንኙነት በድህረ-2010 ኢትዮጵያ .99

አስናቀ ከፋለ እና አማኑኤል ተስፋዬ

# መግቢያ

ወጣትነት በልጅነትና ጎልማሳነት መካከል የሚገኝ የዕድሜ ክልል ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ይሁን እንጂ ወጣት ማነው ለሚለው ጥያቄ ወይንም ወጣትነት ምንድነው ለሚለው መሠረታዊ ሀሳብ ሁሉንም የሚያስማማ ቀጥተኛ ትርጉም መስጠት አስቸጋሪ ነው። ይህም የሚሆነው የወጣትነት ትርጉም ምንም እንኳን በአብዛኛው ጊዜ በዕድሜ ላይ የተመሰረተ ቢሆንም ባህላዊ መገለጫዎችም ያሉት በመሆኑ ጭምር ነው። በወጣትነት የዕድሜ ማዕቀፍ ላይም በተለያዩ አገራት፣ አለም አቀፍ ተቋማት እና ድርጅቶች መካከል ልዩነቶች ይስተዋላሉ። ለምሳሌ ተ.መ.ድ. (አባል አገራት በየአገራቸው የሚሰጡት ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ) ወጣት ማለት ከ15 እስከ 24 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ሰው ነው በማለት ይተረጉመዋል። የአፍሪካ ሕብረት በበኩሉ ***የአፍሪካ የወጣቶች ቻርተር*** (*African Youth Charter*) በተባለውና እ.ኤ.አ በጁን 2006 በፀደቀው ሠነዱ የዕድሜ ማዕቀፉን በማስፋት ወጣትን ከ15 እስከ 35 ዕድሜ ክልል ያለ ማንኛውም ሰው ሲል ትርጉም ይሰጣል።

የተ.መ.ድ ትርጉምን ብቻ ወስደን ብንመለከት በአሁኑ ጊዜ ከ15-29 ዓመት ዕድሜ ውስጥ ያሉ ሰዎች ብዛት 1.8 ቢሊዮን ሲሆን፤ ከነዚህ መካከል ደግሞ 87 ከመቶ ያህሉ በታዳጊ አገሮች የሚኖሩ መሆናቸውን የተ.መ.ድ የፖፑሌሽን ፈንድ መረጃዎች ያሳያሉ። የአፍሪካን ሁኔታ በተለይ ስንመለከት አህጉሪቱ ወደ 400 ሚሊዮን የሚጠጋ ዕድሜው ከ15 እስከ 35 ዓመት የሆነ ሕዝብ በመያዝ ዓለም ላይ ወጣት በብዛት የሚኖርባት ቀዳሚ አህጉር ለመሆን መቻልዋን የአፍሪካ ልማት ባንክ መረጃ ያመለክታል። በአንድ አገር በወጣትነት ዕድሜ ክልል ላይ ያለ ህዝብ በብዛት መያዝ የራሱ አዎንታዊ ጎኖች እንዳሉት ጥናቶች ያመለክታሉ። ከነዚህ መካከል ለብሔራዊ ኢኮኖሚ ትልቅ ሚና ሊጫወት የሚችል ጠንካራና አምራች የሰው ኃይል መኖሩና ይህም ሰፊ የኢቨስትመንት ዕድል መሳብ መቻሉ በዋናነት ይጠቀሳል። በሌላ በኩል ወጣት የሚበዛበት አገር ሰፊ የስራ ዕድል እና ትምህርትና ጤናን የመሳሰሉ ማኅበራዊ ግልጋሎቶች የማዳረስ ኃላፊነት በመንግስታት ላይ ያሳድራል።

በኢትዮጵያ እንደሌሎች ታዳጊ አገራት ሁሉ በህዝብ የዕድሜ ስብጥር ውስጥ ህፃናት፣ አፍላ ወጣቶች (adolescents) እና ወጣቶች ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛሉ። የኢትዮጵያ ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ከ15 እስከ እስከ 29 ዓመት ዕድሜ ክልል ያለውን የህብረተሰብ ክፍል በሙሉ በወጣትነት ይፈርጀዋል። የማዕከላዊ ስታቲስቲክ ባለስልጣን መረጃዎች እንደሚያሳዩት ወደ 125 ሚሊዮን ከሚገመተው ህዝብ መካል በፖሊሲው ወጣት የተባለው ከ15 እስከ 29 ዕድሜ ያለው 30 በመቶ ይሆናል ተብሎ ይገመታል።

ይሁን እንጂ ይህ ሰፊ የህብረተሰብ ክፍል የተለያዩ ተግዳሮቶች ተጋርጠውበት ይገኛሉ። የገጠርና የከተማ ስራ አጥነት፣ ጥራት ያለው ትምህርት አለማግኘት፣ በቂ የማኅበራዊ ግልጋሎት ዕጥረት፣ ለአደገኛ ዕፅ ሱስ ተጋላጭነት፣ በቂ የፖለቲካ ተሳትፎ ዕድል አለማግኘት ወጣቱን ሰንገው ከያዙት ችግሮች መካከል በቅድሚያ የሚጠቀሱ ናቸው። አማራጭ ያጣ ቀላል ቁጥር የሌለው ወጣት ፍልሰትን እንደብቸኛ አማራጭ በመውሰድ በተለያዩ መደበኛ ባልሆኑ (irregular) መንገዶች ወደተለያዩ አገራት ለመሰደድ በሚያደርገው ጥረት ከፍተኛ ችግር እየደረሰበት እንደሚገኝ የየዕለት ዜና ከሆነ ሰንብቷል። ከአገር የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር ያልተመጣጠነ ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ዕድገት፣ የኢኮኖሚ መሠረት የሆነው ግብርና እስከ አሁንም እጅግ ኋላ ቀር ደረጃ ላይ መገኘት፣ የሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎችም አለማደግ፣ የትምህረርት መስፋፋት ከጥራት ጋር አብሮ አለመሄድ፣ ያልተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ እና የሰላምና ደህንነት ስሜት ማጣት የወጣቱን ፍላጎት ለማሟላት እንዳይቻል ካደረጉ መሠረታዊ ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ።

ይሁን እንጂ ወጣቱ የአገርን ዳር ድንበር እና ሉዓላዊነት ለማስከበር በየዘመኑ ከከፈለውና በመክፈል ላይ ከሚገኘው መስዋዕትነት በተጨማሪ ለአገር ዕድገት፣ ማኅበራዊ ፍትህና ዕኩልነት ታግሏል፤ በመታገል ላይም ይገኛል። ከ1950ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ያለውን ብቻ ብንመለከት ወጣቱ እጅግ በዝባዥና ኢ-ፍትሀዊ የነበረውን ፊውዳላዊ ስርዓት በጽኑ ታግሏል። በገዛ አገሩ ባይተዋር ተደርጎ ለብዝበዛ የተዳረገው አርሶ አደር ስቃይ እንዲያበቃና የመሬት ባለቤት እንዲሆን ‹‹መሬት ላራሹ›› የሚል መፈክር በማንገብ ታግሏል። በመጨረሻም ምንም እንኳን የድሉን ፍሬ ሌሎች ቢቀሙትም ወጣቱ በተለይም ተማሪው የአፄ ኃይለ ሥላሴን መንግስት ከነአስከፊ ስርዓቱ ላንዴና ለመጨረሻ እንዲያከትም አድርጓል። በተለይም በ1960ዎቹ መጨረሻና 1970ዎቹ መጀመሪያ ላይ ከአብዮቱ ፍንዳታ ጋር ተያይዞ በነበረው የፖለቲካ ሽኩቻ በተለያዩ ጎራዎች ተሰልፎ ከፍተኛ ዋጋ የከፈለው ወጣት ለከፍተኛ ዕንግልት፣ ስደትና ሞት ምክንያት የሆነውን የፖለቲካ ትግል ቢያንስ በከተሞች ርቆ የቆየ ይመስል ነበር። በመሆኑም ወጣቱ በመንግስት ላይ ሊያነሳ የሚፈልገውን የፖለቲካ ጥያቄ በትጥቅ ትግል መስክ ብቻ የተወሰነ ለመሆን ተገደደ። በዚህም ሳቢያ በደርግ መውደቂያ የመጨረሻ ዓመታት በብሔር፣ በርዕዮተ-ዓለምና በአገራዊ አጀንዳ የተደራጁ ነፍጥ ያነገቡ ተቃዋሚ ድርጅቶች እንደአሸን እንዲፈሉ ምክንያት ሆነ።

የደርግ መንግስት ተወግዶ ህወሓት መራሹ ኢህአዴግን ሲተካ በኢትዮጵያ የፖለቲካ አካሄድ ውስጥ መልካም ለውጥ ይመጣል፣ የነፍጥ ፖለቲካ ለውይይት ፖለቲካ ስፍራውን ይለቃል ተብሎ ተስፋ ቢደረግም የፖለቲካ ጥያቄና ትግልን በተመለከተ በመሠረታዊነት የተለወጠ ነገር አልነበረም። እንደ ደርግ ሁሉ ኢህአዴግም

ለሚቀርቡለት ለእርሱ የማይጥሙት የፖለቲካ ጥያቄዎችና ተቃውሞዎች ምላሹ መረር ያለ ነበር:: ለምሳሌ በኤርትራ ሊካሄድ የታቀደው ሕዝበ-ውሳኔ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስጠብቅ አይደለም በማለት ታሕሳስ 26 ቀን 1985 ለሰላማዊ ሠልፍ በወጡ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ላይ የወሰደው እርምጃ አገዛዙ ለዚህ አይነቱ ተቃውሞና ጥያቄ ስፍራ እንደሌለው ገና በጥዋቱ ያሳየበት አጋጣሚ ነበር::

በቅጡ ያልተደራጀ ነገር ግን ጠንካራ የወጣቶች የፖለቲካ ተቃውሞ ከታየባቸው የድህረ-1983 ጊዜያት መካከል የ1997 ምርጫ ውጤትን ተከትሎ በመንግስትና በተቃዋሚ ወጣቶች መካከል የተደረገው ፍጥጫ በዋናነት ይጠቀሳል:: ኢህአዴግ በራስ መተማመኑ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ እና ዲሞክራት መስሎ ለመታየት በነበረው ፍላጎት ይሁን ወይም በሌላ ምክንያት የፖለቲካ ምሕዳሩን በአንፃራዊነት ባልተለመደ መልኩ ሰፋ አድርጎት ነበር:: ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች በግል እና በቅንጅትባደረጉት የፖለቲካ ቅስቀሳ ከፍተኛ መጠን ያለው ሕዝብ በተለይ በከተሞች አካባቢ ከጎናቸው ማሰለፍ ቻሉ:: የተቃዋሚ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ በጊዜው በነበረው የፖለቲካ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ የተከፉ ወጣቶችን ቀልብ መሳብ ቻለ:: በዚህ ረገድ የተለያዩ ፓርቲዎች ውሕድ የነበረው ቅንጅት ለአንድነትና ለዲሞክራሲ ስሙ በስፋት ይነሳል::

ይሁን እንጂ ኢህአዴግ በብዙ ዜጎች ዘንድ በጉጉት ይጠበቅ የነበረው ምርጫ ውጤት እንደጠበቀው አለመሆኑን ሲረዳ ሁኔታዎችን ለራሱ በሚያመች መንገድ በፍጥነት በመለዋወጥ አሸናፊነቱን አወጀ:: ይህንን የተቃወሙ ወጣቶች በተለይ በአዲስ አበባና ሌሎች የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች ከፍተኛ ተቃውሞ አሰሙ:: መንግስትም ተቃውሞውን ለመቆጣጠር የብዙ ዜጎችን ሕይወት የቀጠፉ አስከፊ የተባሉ እርምጃዎችን ወሰደ:: ተቃውሞው የኢህአዴግ መንግስት ያለበትን የቅቡልነት ዕጥረት በግልጽ ያመለከተ ነበር:: ይሁን እንጂ በኋላ ላይ እንደታየው ምርጫ 97ን ተከትሎ የተካሄደው ተቃውሞ ‹‹ምርጫው ተጭበርብሯል፣ ይስተካከል›› ከማለት ባለፈ የጠራ አመራር፣ ርዕዮተ ዓለም እና በተለይም አደረጃጀት ስላልነበረው በቀላሉ በሚገባ ለተደራጀውና ለታጠቀው የኢህአዴግ የፀጥታ ኃይል የጭካኔ አፀፋዊ እርምጃ ሠለባ ሆኗል::

ከምርጫ 97 ‹‹ትምህርት›› የወሰደው ኢህአዴግ ለምርጫው ሲል በመጠኑ ከፈት አድርጎት የነበረውን የፖለቲካ ምሕዳር በአስፈሪ ሁኔታ መዘጋጋት ጀመረ:: በነፃነት የመደራጀት፤ ሀሳብን በነፃ የመግለፅ፣ የመንቀሳቀስ እና የመሳሰሉ ሰብዓዊና ሕገ-መንግስታዊ መብቶችን የሚገድቡ አዋጆችና ሕጎችን በብዛት ማውጣት ጀመረ:: በዚህ ረገድ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ (662/2002)፣ የፀረ ሽብርተኝነት አዋጅ (652/2001)፣ የበጎ አድራጎትና ማሕበራት አዋጅ (621/2001)

እና የመገናኛ ብዙሀንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ (500/2000) በዋናነት የፖለቲካ ተቃውሞን ለመገደብ፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ዜጎች በመንግስት ላይ ማንኛንም አይነት የተቃውሞ እንቅስቃሴ እንዳያስቡ ከመነሻው ለመከላከል ታቅደው የወጡ አፋኝ ሕጎች ናቸው በማለት ምሁራን ይጠቅሳሉ።

ኢህአዴግ መራሹ መንግስት በአንድ በኩል የሚነሱበትን ተቃውሞዎች በሀይል እያስወገደ እና ወደፊት ሌሎች እንዳይነሱም ጥብቅ የመከላከያ ህጎችን በማውጣት እየተከላከለ፤ በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪል ተቃውሞ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይችላሉ የሚላቸውን ወገኖች የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችና መደለያዎችን በመስጠት እንዲሁም የድርጅቱ አባል በማድረግ ለመቆጣጠር ጥረቱን ተያያዘው። በዚህም በድህረ-1997 ምርጫ በመንግስት መ/ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ ዩኒቨርስቲዎች እና በመሳሰሉ ተቋማት የጅምላ ኢህአዴግ አባልነት ምልመላ ተካሄደ። በተለያዩ መንግስታዊና ሕዝባዊ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የስራ ዕድልና ዕድገት ወጣቶችን ወደ ኢህአዴግ ለመሳብ ጥቅም ላይ ከዋሉት መደለያዎች መካከል በዋናነት ይጠቀሳሉ። ለምሳሌ ከዩኒቨርስቲዎች የሚመረቁ የኢህአዴግ አባል ወጣቶች በተለያዩ የፌዴራልና የክልል መንግስታዊና ህዝባዊ መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ውስጥ የስራ ዕድል እንዲያገኙ ይደረግ ነበር። ይህን የተመለከቱ አዲስ ገቢ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ወደ ፊት ስመረቅ የስራ ዕድል እንዳገኝ ይረዳኝ ይሆናል በማለት ከዩኒቨርስቲ ምዝገባ ፎርማቸው ጋር እንደ ‹‹ማንነታቸው›› የአንዱ የኢህአዴግ አባል ድርጅት አባል ለመሆን የአባልነት ጥያቄ ፎርም ለመሙላት ይሯሯጡ ነበር በማለት የጊዜው ተማሪዎች ይገልፃሉ። እንዲሁም በየመ/ቤቱ የተሻለ የስራ ዕድል፣ ዕድገትና ሹመት በመመኘት የኢህአዴግ አባል ለመሆን ይደረግ የነበረው ሩጫ ቀላል እንዳልነበር ይነገራል። በተመሳሳይ ሁኔታ ኢህአዴግ ወጣቱን ከሌሎች ‹‹ተቀናቃኝ›› የፖለቲካ ኃይሎች ‹ለመንጠቅ›› እና የራሱ ለማድረግ በራሱ አምሳል የተሰራ እና ለራሱ በቀጥታ ተጠሪ የሆነ በመንግስት መዋቅሮች በማቴሪያልና ገንዘብ የሚደገፍ ከታችኛው የቀበሌ ዕርከን እስከ አገር አቀፍ ደረጃ የተዘረጋ ‹‹የወጣቶች ሊግ›› በ2001 በመመስረት ወጣቶችን በውዴታ-ግዴታ በገፍ በመመልመል በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ ጥሯል።

ይሁን እንጂ እነዚህ ጥረቶች ሁሉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለጊዜው ረገብ ከማድረግ ባለፈ በዘላቂነት የወጣቱን እንቅስቃሴ ለማዳፈንና ሰጥ ለጥ ብሎ ለስርዓቱ እንዲገዛ ለማድረግ አላስቻሉም። ወጣቱን በጥቅማ ጥቅም በመደለል ለመያዝ የተደረገው ጥረት በገፍ አባል ለሆነው ወጣት ሁሉ ማዳረስ የማይቻልበት ደረጃ በመድረሱ ጉዞው በአጭሩ የተቀጨ ነበር። እንዲሁም እየተባባሰ የመጣው ስራ አጥነት (የከፍተኛ ትምሕርት ተቋማት ተመራቂዎችን ጨምሮ)፣ ሙስና፣ የኑሮ ውድነት፣ የማኅበራዊ አገልግሎቶች አለመሟላት፣ የገጠር መሬት አልባነት፣ በልማት ስም የሚደረጉ መፈናቀሎች፣ በተለይም የዜጎች የፖለቲካ ተሳትፎ ዕድል

መጣበብ በኢህአዲግ ድርጅታዊ ጥላ ስር የነበሩትን ጨምሮ በአብዛኛው ወጣት ዘንድ ተስፋ መቁረጥን አስከተለ። በዚህም ቀደም ሲል በተለያዩ መደለያዎች እና በጥብቅ የጸጥታ ቁጥጥር ተይዞ የነበረው የጠቅላላው ህብረተሰብ (በተለይም የወጣቱ) ብሶት አገዛዙ ከሚወስዳቸው ጭካኔ የተሞላባቸው ዕርምጃዎች ጋር ተዳምሮ ገንፍሎ መውጣት ጀመረ።

በመንግስት ላይ የሚደረጉ ሕዝባዊ ተቃውሞዎች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች የተነሳሱ ቢሆንም በተለይ ሠፊ የአገሪቱን ክፍል በሚሸፍኑት በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች ይበልጥ የተባባሱ ሆኑ። በኦሮሚያ በከተሞች መስፋፋት ሳቢያ ከመሬታቸው የሚፈናቀሉ ገበሬዎች ብሶት ስር እየሰደደ የመጣ ሲሆን፣ በተለይ በ2006 አዲስ አበባን ወደ አጎራባች የኦሮሚያ አካባቢዎች የማስፋት ማስተር ፕላን ለክልሉ ወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴ ዋና መነሻ ሰበብ ለመሆን ቻለ። ፕላኑ በወጣቶቹ የመረረ ተቃውሞ ሳቢያ ብዙም ሳይቆይ ቢሰረዝም ተቃውሞው ግን እየተባባሰ በመምጣት የቄሮን እንቅስቃሴ ሊወልድ እንደቻለ ይጠቀሳል[1]። የቄሮ ተቃውሞ በመጠናከር በተለያዩ የክልሉ ከተሞች ጠንካራ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በገዢው ኢህአዴግ ላይ ሊያካሄድ ቻለ። በተመሳሳይ ሁኔታ በአማራ ክልል የወጣት የሲቪክ እንቅስቃሴዎች እየተጠናከሩ መጡ። እንቅስቃሴዎቹ በአብዛኛው ከክልሉ ውጪ በሚኖሩ የአማራ ተወላጆች ላይ የሚደርሰው በደልና ጥቃት ይቁም፣ አማራ በማንነቱ መገፋቱ ያብቃ፣ የሕወሓት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ይገደብ፣ በተለይም በትግራይ ክልል ስር የሚገኙት፣ ነገር ግን በታሪክ የአማራ አካል ናቸው የሚሏቸውን እንደ ወልቃይት፣ ጠገዴ እና ሁመራ የመሳሰሉት አካባቢዎች ወደ አማራ ክልል ይካለሉ በሚሉ ጥያቄዎች ላይ የሚያጠነጥኑ ነበሩ። በገዢው የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች መካከል ከተፈጠረው መከፋፈል ጋር ተዳምሮ በአመዛኙ በወጣቱ የተመራው ሕዝባዊ ተቃውሞ በመጨረሻ የኢህአዴግ አገዛዝ እንዲያበቃ ማድረግ ችሏል። በዚህም በተለይ ሕወሓት ይዞት የነበረው የፌዴራል መንግስት የበላይነት እንዲያከትምና ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አሕመድም ወደ ስልጣን እንዲመጡ አስችሏል።

ሕወሓትን ቀንሶ ከኢህዴግነት ወደ ብልፅግናነት በተቀየረው አዲሱ አመራር ዘመንም የወጣቱ የፖለቲካ ተሳትፎ አዲስ ምዕራፍ ይዞ ይገኛል። በድሕረ-ኢህአዴግ ዓመታት በኦሮሚያና በአማራ ክልል የነበሩት ቄሮ እና ፋኖ በመጠናከር የከፊል መደበኛ አደረጃጀት መልክ ሲይዙ፣ ተመሳሳይ ኢ-መደበኛ ወጣት አደረጃጀቶች በተለያዩ

[1] Thea Forsén and Kjetil Tronvolld (2021) ***Protest and Political Change in Ethiopia: The Initial Success of the Oromo Qeerroo Youth Movement*.** **Nordic Journal of African Studies.** Vol. 30, No 4. እንዲሁም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የአስናቀ ከፋለና አማኑኤል ተስፋዬን ጽሁፍ ይመልከቱ።

ክልሎችና ብሔረሰቦች ብቅ ብቅ በማለት በአመዛኙ ብሄር ተኮር የሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎችን ማንሳት ጀመሩ። በዚህ ረገድ በሲዳማ ኢጀቶ፣ በጉራጌ ዘርማ እና በሶማሌ በርበርታ በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ከ2010 ወዲህ ያለው የወጣቶች የፖለቲካ ዕንቅስቃሴ መንግስትን ጨምሮ የሌሎች አካላት ተሳትፎ እና የፖለቲካ ፍላጎቶች ተፅዕኖ የሚታይበት ሲሆን፤ ዓይነቱና መልኩም እንደወቅቱ የፖለቲካ ሁኔታ ተለዋዋጭነት ተስተውሎበታል። ከዚህ አልፎም ኢ-መደበኛ የወጣት አደረጃጀቶች የተለያዩ የፖለቲካ ኃይሎች ለዓላማቸው ማስፈጸሚያነት ከጎናቸው ለማሰለፍ የሚጎትቷቸው በመሆናቸው የጥፋት መሣሪያ ሆነዋል የሚሉ ክፍሎችም አሉ። ታዋቂው የኦሮሞ ፖለቲከኛ ጃዋር መሐመድ በመንግስት ኃይሎች ቤቴ ተከብቧል በማለት በጥቅምት 2012 በማኅበራዊ ሚዲያ ያስተላለፈውን መልዕክት ተከትሎ[2]፤ እንዲሁም የታዋቂው አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ በሰኔ 22 ቀን 2012 መገደል ሳቢያ በተከሰተው ሁከትና ብጥብጥ በኦሮሚያ ከተሞች በመንግስት እና በሕዝብ ንብረት በተለይም ኦሮሞ ባልሆኑ ሰዎች ላይ የደረሰውን ጥፋት[3,4] በማመልከት ወጣቱ እና አደረጃጀቱ በፖለቲካ ቡድኖች ተጠልፏል ብለው የሚከራከሩ ወገኖችም አሉ።

በመንግስት በኩልም ከነዚህ ወጣት አደረጃጀቶች ጋር ያለው ግንኙነት በየጊዜው ሲቀያየር ይስተዋላል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዓቢይ ወደ ስልጣን እንደመጡ መንግስታቸውና ባለስልጣኖቻቸው ቄሮን ‹‹ሀቀኛ የህዝብ አለኝታና ተቆርቃሪ›› በማለት ሲያንቆለጳጵሱ የነበረ ቢሆንም፤ ቆየት ብሎ ቡድኑ ‹‹ለመግራት የሚያስቸግር መረን ሀይል›› ተደርጎ ሲወቀስ ተሰምቷል። በተመሳሳይ ሁኔታ በሠሜኑ የአገሪቱ ክፍል በፌዴራል መንግስት እና በትግራይ ክልል መካከል በተካሄደው ጦርነት ከመንግስት ጋር አብሮ ሲዋጋ እና ሲወደስ የነበረው ፋኖ ከመንግስት ጋር ለመጋጨትና ወደ ትጥቅ ትግል ለመግባት ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም።

በአጠቃላይ ሲታይ በአሁኑ ጊዜ ወጣቱ በአንድ በኩል ከሌላ ጊዜ በተለየ የፖለቲካ ጥያቄዎችን በማንሳት ለመብቱ እና ለማኅበራዊ ፍትህ የሚታገልና በዚህ ሳቢያም

---

[2] ***Ethiopia: Justice Needed for Deadly October Violence*** (Human Rights Watch, (1, 04, 2020) available at Ethiopia: Justice Needed for Deadly October Violence | Human Rights Watch (hrw.org)

[3] ‹‹Hachalu Hundessa: 'Eighty-one killed' in protests over Ethiopian singer's death››. BBC News website July 2, 2020. Available at https://www.bbc.com/news/world-africa-53243325.

[4] Violence & Human Rights Violations following Musician Hachalu Hundessa's Assassination (Investigation Report) Ethiopian Human Right Commission (EHRC) (available at Violence & Human Rights Violations following Musician Hachalu Hundessa's Assassination - Investigative Report - Ethiopian Human Rights Commission - EHRC)

ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሰነዘሩ በትሮችን ቀማሽ፣ በፖለቲካ ትርምስ ውስጥም ሊያገኝ የሚገባውን ጥራት ያለው የትምህርት ዕድል፣ ተገቢ የሥራ ዕድል፣ የፖለቲካ ተሳትፎ እና ማኅበራዊ አገልግሎቶች የተነፈገውና የተገፋ የህብረተሰብ ክፍል ተደርጎ ሲወሰድ፤ በሌላ በኩል ወጣቱን ለትምህርትና ስራ ብዙም ትኩረት የማይሰጥ፣ ለጽንፈኛ ፖለቲካ የተመቻቸ፣ በፖለቲካ ትርምስ ለማትረፍ የሚሯሯጥ፣ በአቋራጭ ለመክበር የሚጣጣር አድርገው የሚመለከቱት ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። እነዚህ ጽንፍ የያዙ አመለካከቶች አከራካሪነታቸው እንዳለ ሆኖ አንድ መካድ የማንችለው ሐቅ ግን የዛሬው ወጣት ከዚህ ቀደም ከነበረው የተለየ የፖለቲካ አዝማሚያዎች፣ አመለካከቶችና ድርጊቶችን የያዘ መሆኑ ነው። እነዚህ አዝማሚያዎች፣ አመለካከቶችና ድርጊቶች በበኩላቸው የጊዜው የፖለቲካና ኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ሉላዊነትና (globalization) ያመጣቸው ለውጦችና ሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ነፀብራቆች እንደሆኑ ይታመናል።

በነዚህ ሁኔታዎች ላይ በመመርኮዝ ***መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ*** ቢሮ የወጣቱን አሁናዊና ቀጣይ የፖለቲካ ሚና ለመረዳትና በፖለቲካው ሂደት የሚጫወተውን ሚና ገንቢ ለማድረግ በአሁን ጊዜ በወጣቱ የፖለቲካ አመለካከት እና ድርጊት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶችን መዳሰስና ያሳደሯቸውን በጎና ጎጂ ተፅዕኖዎችን መገምገም አስፈላጊ እንደሆነ በማመን በዚህ ላይ ያተኮረ ***ወጣቱና ፖለቲካ በኢትዮጵያ*** በሚል መሪ ርዕስ ስር ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች አዘጋጅቶ ከሐምሌ 7 ቀን 2014 እስከ ጥቅምት 3 ቀን 2015 አካሂዷል። በአምስት ክፍሎች ተከፋፍለው በተካሄዱት በነዚህ መድረኮች ላይ አግባብ ካላቸው የመንግስት መ/ቤቶች ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ ፖሊሲ አውጭዎችና አስፈጻሚዎች፣ የሲቪል ማህበረሰብ አባላት፣ ምሁራን እና የወጣት ተወካዮች የተሳተፉ ሲሆን፤ የውይይት መነሻ ጥናታዊ ፅሁፎችም በመስኩ ብቃትና ልምድ ባላቸው ምሑራን ቀርበዋል። በውይይት መድረኮቹ ላይ የቀረቡት ፍሬ ሀሳቦች በስብሰባ አዳራሽ ብቻ ተወስነው እንዳይቀሩ በማሰብ እነሆ በመድረኮቹ ላይ በምሑራኑ የቀረቡት የውይይት መነሻ ጥናታዊ ጽሁፎች አርትዖት ተደርጎባቸው ቀርበዋል።

ሐምሌ 7 ቀን 2014 በተካሄደው የመጀመሪያው የውይይት መድረክ ላይ ***ወጣቱና ፖለቲካ በኢትዮጵያ፡- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ*** በሚል ርዕስ የውይይት መነሻ ጥናታዊ ጽሁፍ የቀረበው በታዋቂው የታሪክ ምሁር ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ሲሆን በጽሁፋቸውም ወጣቱ ትኩስ ኃይል እንደሆነ በመጥቀስ በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የተካሄዱ የማኅበራዊ ለውጥ እንቅስቃሴዎች በአብዛኛው በወጣቶች የተመሩ እንደነበሩ፤ በተለይም ሉላዊ ስድሳዎቹ (global sixties) የተሰኘው የወጣቶች ንቅናቄ በዓለም ላይ እንደምን እንደናኘ ምሳሌዎችን በመጥቀስ ያስረዳሉ። በአገራችንም

ማኅበራዊ ለውጥ እንዲመጣ ጥረት የሚያደርጉ ወጣት ተማሪዎች ብቻ እንዳልነበሩ እና እርሳቸው ‹‹የለውጥ ፊር ቀዳጅ›› ያሏቸውን ቀደምት ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸውን ወጣት የለውጥ ሐዋሪያት እና ስራዎቻቸውን ያመለክታሉ። በንጉስ ኃይለ ስላሴ አገዛዝ ዘመን የተማሪዎች እንቅስቃሴ እንዴት እንዳቆጠቆጠ፣ ይከተለው የነበረውን ርዕዮተ ዓለም፣ አደረጃጀት እና ለዛሬው ትውልድ ትቶ ያለፈውን አሻራ በዝርዝር ይተነትናሉ። በመደምደሚያቸውም የኢትዮጵያ ተማሪዎች የፖለቲካ እቅስቃሴ ከከሰመ ከአራት አስረት ዓመታት በኋላ ዛሬም ወጣቱ ዋና የማኅበራዊ ለውጥ አንቀሳቃሽ ሆኖ መገኘቱ ‹‹በደል እስካለ ድረስ ወጣቱ ምንጊዜም ከመቃወም ወደኋላ እንደማይል ያመለክታል›› በማለት ያጠቃላሉ።

***የትምሕርት ስርዓትና ስብዕና ግንባታ በኢትዮጵያ*** የተሰኘው ጥናታዊ ጽሁፍ በዶ/ር የቆየዓለም ደሴ የቀረበው ሲሆን፤ በጽሁፉ ወጣትነት ምን ማለት ነው ከሚለው መሠረታዊ ጥያቄ በመነሳት የወጣት ስብዕና ዕድገት የሚካሄድባቸውን አውዶችና የአዎንታዊ ስብዕና መገለጫዎችን ይተነትናል። እንዲሁም ትምህርት በስብዕና ቀረፃ ውስጥ ያለውን ጉልህ ድርሻ በማንሳት በኢትዮጵያ በተለይ በድህረ-1983 ያለው የትምህርት ስርዓት ለውጥ፣ ያስመዘገባቸውን ስኬቶችና፣ ያሉበትን ጉድለቶች በዝርዝር ይተነትናል። በመጨረሻም በወጣቶች ስብዕና ግንባታ ውስጥ የትምህርት ስርዓቱ አሉበት ያላቸውን እንደ ብቃት ማነስ፣ የስነ-ምግባር መላላትና መውረድ፣ የክህሎት በበቂ ሁኔታ አለመኖር እና የመሳሰሉትን ችግሮች በአሀዝ በተደገፈ መረጃ በመጥቀስ፤ የአገራችን የትምህርት ስርዓት ጠንካራ ስብዕና ያለው፣ ታታሪ፣ አምራች እና በክህሎት የተሞላ ወጣት ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት ውስጥ የሚጠበቅበትን ሚና እንዲጫወት ሊስተካከሉና ሊሟሉ ይገባቸዋል ያላቸውን ጉዳዮች የያዘ ምክረ-ሀሳብ አካትቷል።

በዶ/ር ጠና ደዎ የቀረበውና የወጣቶች ግብረገብነትና ስነ-ምግባር ጉዳይን የሚመለከተው ***ወጣትነት፣ ግብረ-ገብና ስነ ምግባር በኢትዮጵያ*** የሚለው ሦስተኛው ጥናታዊ ጽሁፍ ነው። ጽሁፉ ግብረ-ገብ ምን ማለት ነው? ስነ ምግባርስ? በሚሉ ጠቅለል ያሉ ጥያቄዎች ተነስቶ የግብረገብና ስነ-ምግባር ምሠሦዎች ናቸው የሚላቸውን አንኳር ጉዳዮችን ይመለከታል። ግብረገብና ስነ-ምግባር በአገራችን ወጣቶች ማንነት ውስጥ ያላቸውን ቦታ፣ ህብረተሰቡ ለወጣቶች ግብረገብና ስነ-ምግባር ሁኔታዎችና ድርጊቶች ያለውን አመለካከት፤ እንዲሁም ወጣቶች መሆንና ማድረግ ስላባቸው ነገሮችና ሁኔታዎች በጥልቀት ያብራራል። በመደምደሚያውም ለአገርና ሕዝብ ዕድገት ይበጃሉ የሚላቸውን ጉዳዮች በምክረ-ሀሳብነት ያቀርባል።

በአሁኑ ጊዜ እጅግ እየተስፋፋ የመጣውን የማኅበራዊ ሚዲያ ጉዳይ የሚዳስሰው አራተኛው እና በዑርጌሳ ደሬሳ የቀረበው ***ወጣቶች እና የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም***

***በኢትዮጵያ*** የሚለው ሲሆን፤ ጽሁፉ በማኅበራዊ ሚዲያ ምንነት፣ ትርጉም፣ ባህሪያትና ሚና ላይ ሰፊ ትንታኔ ያቀርባል። ጽሁፉ ‹‹ባለ ሁለት አፍ›› በማለት የሚጠራው ማኅበራዊ ሚዲያ ለወጣቶች ይዞ የመጣውን በረከትና እያስከተለ ያለውን ፈተና ከማመልከቱም በላይ አሁን የሚታየውን አሉታዊ ጎን ለመቆጣጠር፤ ካልሆነም ለመቀነስ እስካሁን የተወሰዱ እርምጃዎችን ያብራራል። በመደምደሚያው ማኅበራዊ ሚዲያ የሰው ልጅ የወደ ፊት ዋና የመግባቢያና መገናኛ መሣሪያ ሆኖ መቀጠሉ የማያጠራጥር በመሆኑ አጠቃቀሙን በተመለከተ ወጣቶች ሊከተሏቸው የሚገቡ ጥንቃቄዎችን፤ ወላጆችና መንግስት ሊወስዱ የሚገባቸውን የመከታተያ፣ የመቆጣጠሪያና የማረሚያ ዘዴዎችን በምክረ-ኃሳብነት ያቀርባል።

በድህረ-2008 የሚታየውን የወጣቶች አደረጃጀትና የፖለቲካ እንቅስቃሴ የሚመለከተው በዶ/ር አስናቀ ከፋለ እና አማኑኤል ተስፋዬ የቀረበው አምስተኛው ጥናታዊ ወረቀት ኢህአዴግ ከፖለቲካ ስልጣን እንዲነሳ ያደረገውን ለውጥ ዋና አንቀሳቃሽ የሆኑት ወጣቶችን የፖለቲካ አደረጃጀትና የትግል ስልት፤ እንዲሁም ከመንግስት ጋር ያላቸውን መስተጋብር በጥልቀት ይፈትሻል። ጽሁፉ በተለይ በኦሮሚያ እና አማራ ክልሎች በኢ-መደበኛነት የተደራጁት ቄሮ እና ፋኖ ላይ ትኩረቱን አድርጎ አመሰራረታቸውን፣ እንቅስቃሴያቸውና ህልውናቸውን ይመለከታል። በተለይ ከ2010/11 ወዲህ መንግስት ቡድኖቹን እንደወቀቱ የፖለቲካው ሁኔታና ፍላጎቱ በተለያየ ሁኔታ አንዴት አንደሚፈርጃቸውና፣ ወደራሱ በማምጣት የፖለቲካ ድጋፍ ለማግኘት የሚጠቀምባቸውን ስልቶች እንዲሁም በቡድኖቹ ውስጥ የተከሰቱትን ውስጣዊ ለውጦች ይመለክታል። በማጠቃለያውም እነዚህ የወጣት አደረጃጀቶች ተዋረዳዊ መዋቅር፣ ግልጽ አመራር እና ርዕዮተ-ዓለም የሌላቸው በመሆኑ የተነሱለት የስርዓት/አገዛዝ ለውጥ ከመጣ በኂላ ላለው ጊዜ የጠራ አጀንዳ እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል በማለት ይደመድማል።

በአጠቃላይ በዚህ ጥራዝ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሁፎች አገራዊ መግባባትን ለመፍጠር በሚደረገው ጥረት የወጣቱን የፖለቲካ አቅጣጫ አዎንታዊ መልክ በማስያዝ አጋዥ ኃይል እንዲሆን ጥረት ለሚያደርጉ አስተዋጽኦ ከማድረጉ ባሻገር በመስኩ ለሚደረጉ ጥናትና ምርምር በማጣቀሻነት ያገለግላል ተብሎ ይታመናል።

አርታዒው

# ወጣቱና ፖለቲካ በኢትዮጵያ፡- የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ[5]

## ባሕሩ ዘውዴ

### መግቢያ

ወጣት ትኩስ ኃይል ነው ይባላል። በደልና ግፍ አይቶ ማለፍ አያስችለውም። ስርየትን ሲፈልግ ሞትን አይፈራም። የዓለም ታሪክ የሚያረጋግጠውም ይህን ሐቅ ነው። በ19ኛው መቶ ዓመት የአውሮፓ ታሪክ ወጣቶች ከምንጊዜውም በጋለ ሁኔታ ለለውጥና ስርየት የታገሉበት ወቅት ነበር። ለዚህም ዓላማ ‹‹ወጣት›› የሚለውን ስያሜ ያነገቡ ድርጅቶች በየቦታው ብቅ ብለው ነበር። ‹‹ወጣት አውሮፓ››፣ ‹‹ወጣት ኢጣልያ›› በሚል አርማ በአህጉርም በአገርም ደረጃ ለውጥ አቀነቀኑ። የመጀመሪያዎቹ በ1848[6] አውሮፓን ያጥለቀለቃትን የአብዮት ማዕበል አቀጣጠሉ። በ1831 የኢጣልያ አንድነት ነቢይ በሚባለው ጁሴፔ ማዚኒ የተመሠረተው ‹‹ወጣት ኢጣልያ›› ደግሞ ከአንድ አርባ ዓመት በኋላ በጁሴፔ ጋሪባልዲ አዝማችነት የኢጣልያን አንድነት አረጋገጠ።

በሀያኛው መቶ ዓመት ይህ የ‹‹ወጣት›› አዘል እንቅስቃሴ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ ተዛምቶ በአንዳንድ አገራት መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት ቻለ። በዚህ ረገድ በተለይ የሚጠቀሰው ዘመናዊት ቱርክን ለመመሥረት መረማመጃ የሆነው የ‹‹ወጣት ቱርክ›› እንቅስቃሴ ነው። ይህ እንቅስቃሴ በ1908ቱ አብዮት አማካይነት ፈላጭ ቆራጭ የሆነውን የኦቶማን አገዛዝ በማስወገድ በአንደኛው የዓለም ጦርነት ማግስት ከማል አታቱርክ ለመሠረተው ዘመናዊ ቱርክ መንገዱን ጠረገ።

ወጣቶች በሀያኛው መቶ ዓመት መባቻ በሩሲያና ቻይና በተካሄዱት አብዮቶችና የለውጥ ንቅናቄዎችም ጉልህ ሚና ነበራቸው። በተለይ በ1917 ለተካሄደው ታላቁ የሩሲያ አብዮት መቅድም በሆነው የ1905ቱ አብዮት የወጣቶችና ተማሪዎች ድርሻ ትልቅ ነበር። በ1919 ቻይናን ያጥለቀለቀው “May Fourth Movement” በመባል የሚታወቀው ንቅናቄ የተቀጣጠለውም በተማሪዎች አመፅ ነበር። ይህ ንቅናቄ ነው በሚከተሉት ዐሠርቶች መሪ የፖለቲካ ተዋናይ ለመሆን ለበቁት የኮሚንታንግና የቻይና ኮሙኒስት ፓርቲ አዋላጅ የሆነው። በተመሳሳይ መንገድም በደቡብ አሜሪካና

---

[5] በዚህ ጽሑፍ የሠፈሩት ሐሳቦች *The Quest for Socialist Utopia: The Ethiopian Student Movement ca. 1960-1974* (Woolbridge: James Currey, 2014) ላይ በስፋት ከቀረበው ትንተና የተቀነጨቡ ናቸው። አንባቢ የንቅናቄውን ሙሉ ታሪክ ለማወቅ ከፈለገ መጽሐፉን ሊያነብ ይችላል።

[6] የተጠቀሱት ዓመታት ሁሉም እ.ኤ.አ. መሆናቸው ይታወቅ። በኢትዮጵያ አቆጣጠር ሲሆን ዓ.ም. የሚለው መገለጫ ይከተላቸዋል።

በአህጉራችን አፍሪካም ተማሪዎችና ወጣቶች ለመንግሥትና ሥርዓት ለውጥ ታግለው ውጤት አምጥተዋል። በ1964 በሱዳን፣ በ1991 ደግሞ በማሊ ወታደራዊ አምባገነን አገዛዝን በአመፅ አስወግደው ሲቪል አስተዳደር በምርጫ እንዲመሠረት የአንበሳውን ድርሻ ወስደዋል።

**‹‹ሉላዊ ስድሳዎቹ››** ("The Global Sixties")

ነገር ግን እንደ 1960ዎቹ ያለ የተማሪዎችና ወጣቶች የለውጥ እንቅስቃሴ ጫፍ የረገጠበት ዘመን ለማሰብ ያዳግታል። እንቅስቃሴው በአንዳንድ አገራት ሳይታጠር ከጽንፍ እስከ አጽናፍ ስለናኘም ‹‹ሉላዊ ስድሳዎቹ›› የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል። እንቅስቃሴው የጀመረው በ1967 የኢራኑ አምባገነን ንጉሠ ነገሥት በጀርመን አገር የሚያደርገውን ጉብኝት በመቃወም ተማሪዎች ባካሄዱት ሰላማዊ ሰልፍ ነው። የተቃውሞ ሰልፉ ሩዲ ዱሽከ የተባለውን ዝነኛ መሪያቸውን ሲያፈራ፣ አንድ ተማሪም የተሰዋበት ቦታም ዘላለማዊ መዘክር ሆኖ ቆይቷል። በዓመቱ ደግሞ አመፁ ወደ ፈረንሣይ ተዛምቶ በዳንኤል ቤን ኮንዲት መሪነት ዝግባ-አከሉ ፕሬዚዳንት ደ ጎል ከሥልጣን ሊገረሰስ ቻለ።

በአጠቃላይ 1968 የሉላዊ አመፅ ዓመት ነበር ማለት ይቻላል። በወግ አጥባቂነቷ በምትታወቀው እንግሊዝ ሳይቀር በተለይ የለንደን ስኩል ኦፍ ኤኮኖሚክስ የተቃውሞ ማዕከል ሆነ። በተመሳሳይ መንገድም በአሜሪካ የካሊፎርኒያ ዩኒቨርሲቲ በርክሌ ተማሪዎች የሕዝብ መናፈሻን ባለቤትነት ለማስከበር ከፀጥታ ኃይሎች ጋር በ1969 የጀመሩት ትግል ዓመታትን አስቆጠረ። ከአሜሪካ በስተደቡብ በምትገኘው ሜክሲኮ ደግሞ 1968 በተማሪዎችና መንግሥት መካከል ደም ያፋሰሰ ፍልሚያ ተካሄደ። መንግሥት በዚያ ዓመት የሚያስተናግደውን 16ኛውን የኦሎምፒክ ውድድር አስመዝግቤያለሁ ብሎ የሚያምንበትን ዕድገት ለዓለም ለማሳየት ሽር ጉድ ሲል፣ ተማሪዎች ደግሞ ከ‹‹ዕድገቱ›› ጀርባ ያሉትን ችግሮች ለማጋለጥ አደባባይ ወጡ።

የ1960ዎቹ የወጣቶች እንቅስቃሴ ፖለቲካዊ ብቻ ሳይሆን ባሕላዊ አንድምታም ነበረው። ወጣቱ የተነሳው ፖለቲካዊ አብዮት ብቻ ሳይሆን ባሕላዊ አብዮትንም ለማካሄድ ነበር። በዚህ ረገድ ጥያቄ ውስጥ ያልገባ ባሕላዊ አስተሳሰብና ዘይቤ አልነበረም፦ አለባበስ፣ ፀጉር አቆራረጥ፣ የሙዚቃ ምርጫ፣ ፆታዊ ግንኙነት፣ ወዘተ። በርዕዮተ ዓለም ደረጃም በአብዛኛው ግራ-ዘመም ሲሆን በተለይም አዲሱ ግራ (The New Left) የሚባለው ቅኝት የገነነበት ጊዜ ነበር። የፖለቲካ ትግሉም በአንድ አገር ብቻ የተከለለ ሳይሆን ዓለም አቀፍ ባሕሪም ነበረው። በተለይ የአሜሪካን ኢምፔሪያሊዝምን በመታገል አኩሪ ገድል እየጻፉ የነበሩት እንደ ቬየትናም ያሉ አገሮች ዓለም አቀፍ ድጋፍ ተቸራቸው። የአውሮፓና አሜሪካ ከተሞች ለቬየትናም

በሚደረጉ የድጋፍ ሰልፎች ተናጡ። ሌላ የአኩሪ ትግል ተምሳሌት የሆነችው ደግሞ አሜሪካ አፍንጫ ስር ቁጭ ብላ ኃያሉን መንግሥት የምትገዳደረው ኩባ ነበረች። በተለይም ከፊደል ካስትሮ ጋር ሆኖ የኩባን ትግል ለድል ያበቃው ድንበር የለሹ አብዮተኛ ቼ ጉቬራ፣ ቀይ ኮከብ ከተፈነጠቀበት ጥቁር ቤሬቱ ጋር እስካሁንም ዓለም አቀፍ ክብርን ሲያገኝ ቆይቷል።

ከአውሮፓና አሜሪካ ውጪ ጠንካራ የተማሪዎች ንቅናቄ ለመፍጠር የቻሉት የኢራንና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ናቸው። ለዚህም ዋነኛ ምንጩ ሁለቱም አገሮች ፈላጭ ቆራጭ በሆነ ንጉሠ ነገሥታዊ አገዛዝ ስር መሆናቸው ነው። የሁለቱም አገሮች ተማሪዎች ከአገራቸውም ዘልቀው በአውሮፓና አሜሪካ ግዙፍ የተማሪዎች ማኅበራት ለመፍጠር ቻሉ። ከታሪካዊ መመሳሰላቸው ባሻገር ሁለቱም በጠንካራ ማኅበራት መደራጀት ስለቻሉም ውጭ አገር በሚያደርጉት እንቅስቃሴ በእጅጉ ይደጋገፉ ነበር። ሁለቱም ንቅናቄዎች የማታ ማታ አብዮትን ወለዱ፤ ኢትዮጵያ በ1974፣ ኢራን በ1979። የሚያሳዝነው ነገር ግን ሁለቱም ያቀጣጠሉትን አብዮቱን በዘላቂነት መቆጣጠር አልቻሉም። የኢትዮጵያ አብዮት በወታደራዊው ቡድን ሲጠለፍ የኢራኑን ደግሞ ሙላዎቹ ወረሱት።

## ፋና ወጊዎቹ

የለውጥ ሐሳብ በተማሪዎች እንዳልተጀመረ *Pioneers of Change in Ethiopia: The Reformist Intellectuals of the Early Twentieth Century* የተሰኘውን መጽሐፌን ያነበበ ሁሉ በቀላሉ ይረዳዋል። ስለሆነም እዚህ ዝርዝር ውስጥ መግባት አልፈልግም። ይልቁንስ ላተኩር የምፈልገው ከነዚያ የለውጥ አቀንቃኝ ምሁራን መካከል ብዙዎቹ በወጣትነት የዕድሜ ክልል ውስጥ እንደነበሩ ማሳየቱ ላይ ነው። የሚገርመው ነገር በተለይ የውጭ አገር ጸሐፊዎች ይህን የለውጥ አቀንቃኝ ቡድን፣ ከአውሮፓ ታሪክ በመዋስ ይመስላል፣ ‹‹ወጣት ኢትዮጵያ›› (Young Ethiopia) በሚል ስያሜ ይጠሩት እንደነበር ነው። ማለትም ልክ በአውሮፓ በ19ኛው፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ደግሞ በሀያኛው መቶ ዓመት መባቻ እንዳየነው ማለት ነው።

የምሁራኑ ቁንጮ የነበረው ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ‹‹አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ›› የተሰኘውን አጭር ግን ብዙ ቁም ነገር ያዘለ መጣጥፍ ሲጽፍ የ26 ዓመት ወጣት ነበር። ተክለ ሐዋርያት ተክለ ማርያም ደግሞ ከሩሲያ ትምህርቱ ተመልሶ ስለ ከተማና አጠቃላይ አስተዳደር ማሻሻያ ሐሳቦቹን ለልጅ ኢያሱ ያቀረበው በሀያዎቹ ዕድሜ ክልል እያለ ነው። ይልቁንም ‹‹ሁለተኛው ትውልድ›› ብዬ የፈረጅኳቸው ምሁራን እንዲሁ በለጋ ዕድሜያቸው ነው በአገር ጉዳይ ፋይዳ ያለው ሥራ

መሥራት የቻሉት። ይህ አባባል የጎሩይ ወልደ ሥላሴ ልጆች የነበሩትን ፈቃደ ሥላሴና ሲራክን፣ የሐኪም ወርቅነህ ልጆች የነበሩትን ዮሴፍና ብንያም ወርቅነህን፣ መጀመሪያ አሜሪካ ተልከው ከፍተኛ ትምህርት ከቀመሱት መካከል አውራ የነበረውን መላኩ በያንን ያጠቃልላል። ዮሴፍ፣ ብንያምና ፈቃደ ሥላሴ የጥቁር አንበሳን ጦር ተቀላቅለው ለነፃነት ከታገሉ በኋላ ጎጀብ ላይ ተማርከው በግራዚያኒ ላይ የተደረገውን የቦምብ ጥቃት ሙከራ ተከትሎ በግፍ ተጨፈጨፉ። መላኩ በያን ከንጉሠ ነገሥቱ ጋር ከተሰደደ በኋላ በደንብ ወደሚያውቀው ኒው ዮርክ ተሸጋግሮ በግፍ ለተወረረች አገሩ የአፍሪካን-አሜሪካውያንን ድጋፍ በማሰባሰብ አኩሪ ገድል ሠራ።

በወጣትነት ዕድሜ ክልል የሚገኙት ምሁራኑ ብቻ ሳይሆኑ የለውጥ ሐሳባቸውን እንዲያስፈጽሙላቸው ይጎተጉቷቸው የነበሩት ልዑላንም ነበሩ። በዚህም ረድፍ የሚገኙት በተከታታይ ልጅ ኢያሱና ራስ ተፈሪ መኰንን ናቸው። ገብረ ሕይወት ‹‹አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ››ን ሲጽፍ ኢያሱን እያሰበ እንደሆነ ውስጡ ካሉ አንዳንድ ዐረፍተ ነገሮች በግልፅ መረዳት ይቻላል። ተክለ ሐዋርያትም የአስተዳደር ማሻሻያ ማኑዋሎቹን ለኢያሱ ነው የጻፈው። እንደዚሁ ሁሉ፣ የገብረ ሕይወት *መንግሥትና የሕዝብ አስተዳደር* ከራስ ተፈሪ የአስተዳዳር ማሻሻያ እርምጃዎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። እነዚህ የሪፎርም ሐሳቦች ለልዑላኑ በሚቀርቡበት በሀያኛው መቶ ዓመት መባቻ ላይ ኢያሱ በዐሥራዎቹ ዕድሜ፣ ተፈሪ ደግሞ በሀያዎቹ መጀመሪያ ላይ ነበር የሚገኙት።

### የፖለቲካ ዐውዱ

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄን ልደትና ዕድገት በዝርዝር ከማየታችን በፊት ለመፈጠሩ ምክንያት የሆነውን የፖለቲካ ዐውድ በመጠኑ እንቃኛለን። ምክንያቱም ምንም እንኳን ንቅናቄው የ‹‹ሉላዊ ስድሳዎቹ›› አካል ቢሆንም፤ ለየት ያለ ባሕሪ ያላበሰው አገራዊ ዐውድም ነበር። ከሌሎች የተማሪዎች ንቅናቄዎች ሲነፃፀር ሥር-ነቀል ያደረገውም ይኸው አውድ ነው።

የአፄ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ምንም እንኳን ብዙ የዘመናዊነት መሠረት የተጣለበት ዘመን ቢሆንም ሁለት መሠረታዊ ሕፀፆች ነበሩበት፤ አንዱ ፖለቲካዊ፣ ሁለተኛው ደግሞ ማኅበራዊ-ኤኮኖሚያ። በፖለቲካው ረገድ መለያ ባሕሪው ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝና በእጅጉ የተማከለ አስተዳደር ማስፈኑ ነው። ሥልጣን በንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተጠቃሎ የተያዘ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ አገልጋይ እንጂ የፖለቲካ መሪ አልነበረም። ፓርላማውም ቢሆን ለጌጥ የተቀመጠ ተቋም እንጂ መንግሥትን ሞጋችና ለሕዝብ ጠበቃ የቆመ አልነበረም። ንጉሠ

ነገሥቱ ዕድሜያቸው እየገፋ ሲሄድ እንኳ በሕገ መንግሥት የተገደበ የዘውድ አገዛዝ (constitutional monarchy) የመመሥረት ሐሳብ ውልም አላለባቸውም። ይህን ያደርጉ ይሆናል ሲባል በጉጉት ከተጠበቀው የሰማኒያኛ የልደት በዓላቸው አገሪቷ ያተረፈችው የመናገሻ ከተማዋ በኒዎን መብራት ማሽብረቅ ብቻ ነው።

በኤኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ረገድ ደግሞ የሥርዓቱ ትልቁ ድክመት የመሬት ይዞታን ፍትሓዊ ለማድረግ ይህ ነው የሚባል እርምጃ ለመውሰድ አለመፈለጉ ወይም አለመቻሉ ነው። በተለይም በደቡቡ የአገሪቱ ክፍል የተንሠራፋው የጭሰኝነት ሥርዓት ወይ እንዲሻሻል ወይ እስከናካቴው እንዲወገድ ያልወተወተ ምሁር ወይም ኤክስፐርት አልነበረም። ሌላው ቀርቶ የዓለም የምግብ ድርጅት (ፋኦ) ሁለት ኤክስፐርቶች ጭሰኝነት እንዲቀር በአጽንኦት አሳስበዋል። ይሁን እንጂ የዘመኑ ፓርላማ እንኳን ጭሰኝነትን የሚያስወግድ አዋጅ ሊያወጣ፣ የቀረበለትን ጭሰኝነትን የሚደነግገውን ረቂቅ ሕግ እንኳ ማፅደቅ ተሳነው። ይህን ክስተት ካዩ በኋላ ነው ተማሪዎች ‹‹መሬት ላራሹ›› የሚለውን መፈክር አንግበው አደባባይ ለመውጣት የተገደዱት።

በተለይም በፖለቲካዊው ምኅዳር መጥበብ ምክንያት ተቃውሞ መጀመሪያ መሰማት የጀመረው ከራሱ ከገዢው መደብ አባላት ነው። በዚህ ረገድ የንጉሠ ነገሥቱ የዕድሜ ልክ ባላንጣ ሆነው የተገኙት ደጃዝማች ታከለ ወልደ ሐዋርያት ናቸው።ታከለ ምንም እንኳ ከኢጣልያ ወረራ በፊት የንጉሠ ነገሥቱ ታማኝ አገልጋይ የነበሩ ቢሆንም ወረራውን ተከትሎ ንጉሠ ነገሥቱ ስደትን ሲመርጡ የሁለቱ መቃቃር ጀመረ። ከነፃነት መልስ ወዲህ ታከለ በተከታታይ በንጉሠ ነገሥቱ ላይ ማመፁን ሥራዬ ብለው ተያያዙት። በሹመት ለማባበል ወይ በጋብቻ ለማሰር ሙከራ ቢደረግም አሻፈረኝ አሉ። በመጨረሻ በኅዳር 1961 ዓ.ም. ንጉሠ ነገሥቱን ለመግደል ሲያሴሩ ተደርሶባቸው እጅ አልሰጥም ብለው አፍንጮ በር አካባቢ በሚገኘው ቤታቸው መሽገው ተታኩሰው ሞቱ።

ሌላ የአፄያዊውን አገዛዝ የተፈታተነው በ1951 በቢትወደድ ነጋሽ በዛብህ የተመራው አመፅ ነው። የአመፁ ዋና ዓላማ ንጉሠ ነገሥቱን አስወግዶ ሬፐብሊክ መመስረት ነበር። ሆኖም መንግሥት ጉዳዩን ከጥንስሱ ስለደረሰበት ሴረኞቹ ምንም እርምጃ ሳይወስዱ ተይዘው የሞት ፍርድ ከተፈረደባቸው በኋላ ወደ ረጅም ጊዜ እስራት ተለውጦላቸዋል። ከዘጠኝ ዓመት በኋላ በ1960 መንግሥትን በብርቱ የፈተነው በክብር ዘበኛው አዛዥ በብርጋዴር ጄኔራል መንግሥቱ ንዋይ የተመራው መፈንቅለ መንግሥት ተከሰተ። አመፁን መንግሥቱ ይምራው እንጂ ዋና ጠንሳሹ ታናሽ ወንድሙ ገርማሜ ንዋይ ነበር። ገርማሜ አሜሪካ ከፍተኛ ትምህርቱን

በሚከታተልበት ወቅት የሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን በፕሬዚዳንትነት የመራ መሆኑ ሲታወቅ፤ በዚህ ጽሑፍ በዝርዝር ከምናየው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው ማለት ይቻላል::ይሁን እንጂ ጄኔራሉና ምሁሩ የጦር ሠራዊት ከፍተኛ መኰንኖችን ወይ ከጎናቸው ሳያሰልፉ ወይ ሳያግቱ ስለቀሩ መፈንቅለ መንግሥቱ ከሸፎ እነሱም ለሞት ተዳረጉ::

መፈንቅለ መንግሥቱ ይክሸፍ እንጂ አሻራው በቀላሉ አልጠፋም:: ጄኔራል መንግሥቱ የሞት ፍርድ ሲፈረድበት የተናገረው ትንቢታዊ ቃል ለዚህ የመጀመሪያው አመልካች ነበር:: ‹‹ዋ! ዋ! ዋ! ለእናንተና ለገዥአችሁ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ሐሳቤ በዝርዝር ገብቶት በአንድነት በሚነሳበት ጊዜ የሚወርድባችሁ መዓት የሚያሰቅቅ ይሆናል::›› ይህ ማስጠንቀቂያ በሕዝቡም በገዥው መደብ አባላትም ዘንድ ለማስተጋባት ብዙም ጊዜ አልፈጀበትም:: ሕዝቡ በመፈንቅለ መንግሥቱ መክሸፍ ተሸማቆ ዝም በማለት ፈንታ የአመፅ ጥሪን ማስተላለፍ ያዘ:: ‹‹ደም ካልፈሰሰ ስርየት የለም!››፤ ‹‹በግ ሆኖ ሺ ቀናት ከመኖር፣ አንበሳ ሆኖ አንድ ቀን ኖሮ መሞት ይሻላል››፤ ‹‹ይህ ትውልድ በባርነት ከሚኖር በደም ያልፋል፣ የሚመጣው ትውልድ ግን ያለ ደም በነፃነት ይኖራል››የሚሉ እና መሰል መፈክሮች በጎቡዕ መሠራጨት ጀመሩ::

ከገዥው መደብ አባላት መካከልም ነቃ ያሉት መፈንቅለ መንግሥቱን እንደ አንቂ ደወል በማየት ንጉሠ ነገሥቱ አስፈላጊውን አስተዳደራዊ ማሻሻያ እንዲያደርጉ አሳሰቡ:: በዚህ ረገድ ግንባር ቀደም ሚና የተጫወቱት የትምህርት ሚኒስትር የነበሩት አቶ ሐዲስ ዓለማየሁ ናቸው:: መፈንቅለ መንግሥቱ በከሸፈ ሁለት ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ለንጉሠ ነገሥቱ በጻፉት ማስታወሻ፣ መክሸፉ በጎ ቢሆንም ‹‹ያለ እሳት ጪስ አይኖርምና›› ክስተቱን እንደ ቀይ መብራት በማየት አስፈላጊውን የአስተዳደር ማሻሻል እንዲያደርጉ ምክራቸውን ለገሡ:: ድፍረት የተሞላበት ማስታወሻቸውንም በሚከተሉት ቃላት ደመደሙ::-

> በዚህ ማስታወሻ የገለጽኋቸው አንዳንድ ነገሮችና የገለጽሁበት ቋንቋ ትንሽ መረር ያሉ መሆናቸው ይሰማኛል:: እንዲሁም ሰው ሆኖ ለተፈጠረ ሁሉ ከመራራ እውነት የተቀመመና የለዘበ ከንቱ ውዳሴ እንደሚጣፍጥ አውቃለሁ:: ነገር ግን ዞሮ ዞሮ ከንቱ ውዳሴ የሚያፈራውን ጣፋጭ ፍሬ የሚለቅሙና በሱም የሚጠቀሙ አሞጋሾቹ ብቻ በመሆናቸው ተሞጋሾች ሁልጊዜም ቢሆን ከመራራው እውነት ጋር ቀሪዎች ናቸው::

ሚኒስትሩ ለዚህ ልፋታቸው ያገኙት ዋጋ ከሚኒስትርነት ወደ እንግሊዝ አምባሳደርነት መጋዝ ነው። ደግነቱ በአምባሳደርነት ዘመናቸው ለሳቸው ሐውልት፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ደግሞ ቋሚ ቅርስ የሆነውን ‹‹ፍቅር እስከ መቃብር›› የተሰኘውን መጽሐፍ ለመጻፍ በቂ ጊዜ አገኙ!

እንደዚሁ ከአንድ ሁለት ዓመታት በኋላ አምስት የሥርዓቱ ጉምቱ መሣፍንትና መኳንንት በላንጋኖ ሐይቅ ዳርቻ ለጥቂት ቀናት ዘግተው ተመሳሳይ ምክረ ሐሳብ አቀረቡ። እነሱም የመሣፍንቱ አውራ የነበሩት ልዑል ራስ ዐሥራተ ካሣ፣ የንጉሠ ነገሥቱ አማች ሌተና ጄኔራል ዐቢይ አበበ፣ የመከላከያ ሚኒስትሩና የ1960ውን መፈንቅለ መንግሥት በማክሸፍ ቁልፍ ሚና የተጫወቱት ሌተና ጄኔራል መርዕድ መንገሻ፣ የሐረር ጠቅላይ ግዛት እንደራሴ የነበሩት ኮሎኔል ታምራት ይገዙ እና የማስታወቂያ ሚኒስትሩ ደጃዝማች ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ነበሩ። እነዚህም ያገኙት መልስ ተመሳሳይ ነበር፤ በሹመት ስም መጋዝ። እንዲያውም ሌተና ጄኔራል መርዕድ መንገሻ ማስታወሻውን ከፈረሙ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ድንገት በመሞታቸው ተመርዘው ሳይሆን አይቀርም የሚል ሐሜት ሰፍኖ ነበር።

ሥርዓቱ ምን ያህል በቀውስ ውስጥ እንደነበረ የሚያመለክተው በተከታታይ በተከሰቱት ሴራዎችና አመፆች፣ እንዴት በአንድ ወቅት ሴራውን ወይም አመፁን ለማክሸፍ ቁልፍ ሚና የተጫወቱ ሰዎች በሚቀጥሉት ዓመታት በተራቸው በሥርዓቱ ላይ እንዳመፁ ነው። መንግሥቱ ንዋይ የቢትወደድ ነጋሽን ሴራ እንዳላከሸፈ ሁሉ፣ ከዘጠኝ ዓመታት በኋላ የመፈንቅለ መንግሥት መሪ ሆነ። የርሱን መፈንቅለ መንግሥት በማክሸፉ መሪ ተዋናይ የነበረው ጄኔራል መርዕድ መንገሻ ከሁለት ዓመታት በኋላ የለውጥን አስፈላጊነት ተገንዝቦ ከሌሎች አራት መሣፍንትና መኳንንት ጋር በመሆን ለንጉሠ ነገሥቱ ማስታወሻ ለመጻፍ በቃ። እንደዚሁ የነመንግሥቱን መፈንቅለ መንግሥት በማክሸፉ ወሳኝ ድርሻ የነበረው የፈጥኖ ደራሹ አዛዥ ኮሎኔል ታደሰ ብሩ የሜጫ ቱለማ ኦሮሞ ማኅበር መሪ በመሆን ሥርዓቱን ተገዳደረ።

## የተማሪው ንቅናቄ ማቆጥቆጥ

እንግዲህ ሥርዓቱ በዚህ ዓይነት ሁኔታ መጠነኛ ማሻሻያዎችን እንኳ ለማስተናገድ ባልቻለበት ሁኔታ ነው እያደር አብዮታዊ ባሕሪ እየያዘ የመጣው የተማሪዎች ንቅናቄ ያቆጠቆጠው። በተለይም የከሸፈው መፈንቅለ መንግሥት ከተማሪው ንቅናቄ መነሳሳት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ነበረው ማለት ይቻላል። መፈንቅለ መንግሥቱ እንደተከሰተ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ተማሪዎች ፈራ ተባ እያሉም ቢሆን ድጋፋቸውን በሰላማዊ ሰልፍ ገልጸዋል። በአውሮፓ የሚገኙ የኢትዮጵያ ተማሪዎችም የአመፁን

መሪዎች ‹‹ታኅሣሣውያን››[7] በማለት አቆላምጠዋቸዋል፡፡ በተጨማሪም ከ1958 ዓ.ም. ጀምሮ ንጉሠ ነገሥቱ ባስጀመሩት የስኮላርሺፕ መርሀ ግብር መሠረት ከሌሎች አፍሪካ አገሮች የመጡ ተማሪዎች በዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የትምህርት ዕድል ማግኘት የኢትዮጵያውያን ተማሪዎችን የፖለቲካ ንቃተ ኅሊና በማሳደጉ ረገድ ጉልህ የሆነ ሚና ተጫውቷል፡፡ የስኮላርሺፕ ተማሪዎቹ ባንፃሩ ከዳበረ የፖለቲካ ባህል የመጡ በመሆናቸው (የፖለቲካ ፓርቲ፣ የሠራተኛ ማኅበር፣ ንቁ ፕሬስ፣ ወዘተ ካለበት) ለኢትዮጵያውያኑ ዐይን ገላጭ ነበሩ፡፡

ቤተ መንግሥትና ካምፓስ መቃቃር የጀመሩት መፈንቅለ መንግሥቱ ከተከሰተ ከጥቂት ወራት በኋላ ነበር፡፡ በየዓመቱ ንጉሠ ነገሥቱ በክብር እንግድነት በሚገኙበትና በድምቀት በሚከበረው ‹‹የኮሌጅ ቀን›› ዐቢዩ ክንዋኔ ቀደም ሲል በተደረገ የግጥም ውድድር አሸናፊ የሆኑት ሦስት ግጥሞች የሚነበቡበት ፕሮግራም ነበር፡፡ በዚያን ዓመት አሸናፊ ሆኖ የቀረበው ግጥም በታምሩ ፈይሣ የተደረሰው ‹‹ድሀው ይናገራል›› በሚል ርዕስ የአንድ የድሀ ኢትዮጵያዊን ሰቆቃዊ ኑሮ በስዕላዊ መንገድ የሚተርክ ግጥም ነበር፡፡ ንጉሠ ነገሥቱ በዚህ ከተለመደው በተለየ ርዕስ እንዳልተደሰቱ ግልጽ ነበር፡፡ በሚቀጥለው ዓመት እንዲሁ ለኮሌጅ ቀን ሲጋበዙ የፕሮቶኮል ሹሞቻቸው ‹‹ጃንሆይን እየጠራችሁ መስደብ አትችሉም፤ መጀመሪያ የሚነበቡትን ግጥሞች ለኛ አሳይታችሁ ስንፈቅድ ነው የምታነቡት›› በማለት ቅድመ-ሁኔታ አስቀመጡ፡፡ የተማሪዎቹ መሪዎችም ይህን ከሳንሱር ያልተለየ አካሄድ መቀበል ስላልፈለጉ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የኮሌጅ ቀን ንጉሠ ነገሥቱ በሌሉበት ተከበረ፡፡ በዚያን ዓመት የተነበቡትም ግጥሞች ከታምሩ ፈይሣም ግጥም በላቀ ሁኔታ ሥርዓቱን የሚጠይቁ ነበሩ፡፡ በዚህም ምክንያት መንግሥት የበቀል እርምጃ ወሰደ፡፡ የግጥም ደራሲዎቹን ለአንድ ዓመት ከትምህርት ከማገድም አልፎ እስከዚያ ድረስ ለተማሪዎች በሙሉ ይሰጥ የነበረው የአዳሪ ተማሪነት ዕድል ተሰረዘ፡፡ ይህ እርምጃ ግን ተማሪዎችን ከማኅበረሰቡ ጋር ይበልጥ በማቀራረብ ሥርዓቱን ይበልጥ እንዲሞግቱ አበረታታቸው እንጂ አላለዘባቸውም፡፡

ሌላ ተማሪዎቹ አብዮታዊ አቅጣጫ እንዲይዙ ያደረጋቸው በ1964 ‹‹አዞዎቹ›› (The Crocodiles) በሚል ስም የተመሠረተው ኅቡዕ የፖለቲካ ቡድን ነው፡፡ የማርክሲስት ርዕዮት ወደ ተማሪው ንቅናቄ መስረግ የጀመረውም በዚህ ቡድን አማካይነት ነው፡፡ በተለይም በ1965 ተማሪዎች ‹‹መሬት ላራሹ›› የሚለውን መፈክር አንግበው ሠልፍ የወጡትና የተማሪው ንቅናቄም ላይመለስ አብዮታዊ አቅጣጫ የያዘው በነዚሁ

[7] በታኅሣሥ 1825 የሩሲያውን ንጉሥ (ዛር) ቀዳማዊ ኒኮላስን ለመገደል ያልተሳካ ሙከራ ካደረጉት የጦር መኰንኖች ጋር በማመሳሰል፡፡

በአዞዎቹ ጉትጎታ እንደሆነ ይታመናል። የ1965ቱ ሰላማዊ ሰልፍ ለተማሪው የተቃውሞ ታሪክ ፈር ቀዳጅ ሆነ። ከዚያ በኋላ በየዓመቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የተለያዩ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን ስሜት ኮርኳሪ በሆኑ መፈክሮች ሽልመው ሰላማዊ ሰልፍ ወጡ፦‹‹ድኅነት ወንጀል ነው ወይ?›› ‹‹ትምህርት ለሁሉም!››፣ ወዘተ። ይህ ዓመታዊ ተቃውሞ በ1969 ዓ.ም. ከፍተኛ ደረጃ ደረሰ። በዚያን ዓመት የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችም ንቅናቄውን ተቀላቀሉ። እንዲያውም ከዚያ በኋላ ግንባር ቀደም ሥፍራውን ያዙ።

የ1969ኙ አገር አቀፍ የተማሪዎች ተቃውሞ ንቅናቄው ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ነበር ማለት ይቻላል። የ1968ቱ ሉላዊ አመፅ ዓለም አቀፍ ሥርዓቱን ባናጋው ሁኔታ አገራዊ ሥርዓቱን በብርቱ ፈትኖታል ማለት ይቻላል።[8] ተቃውሞው ለሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና የሚጠየቀው ክፍያ እንዲሰረዝና የአሜሪካ ሰላም ጓድና ሕንድ መምህራን እንዲወገዱ፣ የትምህርት ሚኒስትሩ እንዲነሳ በመጠየቅ ጀምሮ ጠቅላላ የትምህርት ሥርዓቱ እንዲከለስ ወደመጠየቅ ተሸጋገረ። ንጉሠ ነገሥቱ ተማሪዎቹ እንዲረጋጉና አደብ እንዲገዙ ላደረጉት ንግግር ዋለልኝ መኰንን ታይቶ በማይታወቅ ድፍረት አብጠለጠላቸው። እርሱና ግብረ አበሮቹ ናቸው የተባሉት ተማሪዎችና ሠራተኞች ረጅም እስር ተፈርዶባቸው እስር ላይ እያሉ ክረምቱ ላይ ሰባት ተማሪዎች አውሮፕላን ጠልፈው ሱዳን ገቡ። ይህም በተከታታይ ለተደረጉት ተመሳሳይ ጠለፋዎች በር ከፋች ሆነ። ይባስ ብሎ ደግሞ በጥቅምት ወር ረጅም የእስር ፍርዱ ተሰርዞለት በምህረት የተፈታው ዋለልኝ መኰንን አይነኬ የነበረውን የብሔረሰቦች ጥያቄ አፈነዳው።

ይህ ለመንግሥት የማይታለፈው ቀይ መስመር ነበር። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የመንግሥት ሚዲያው በተማሪዎች ላይ ‹‹አሁንስ አበዙት!›› የሚል ቅኝት ያለው የተቀነባበረ ዘመቻ ከፈተ። ዘመቻውም በታኅሣሥ 19፣ 1962 ዓ.ም. ምሽት ላይ የተማሪዎቹን መሪ ጥላሁን ግዛውን በመግደል ማሳረጊያውን አገኘ። በማግስቱ አስከሬኑን አናስረክብም ብለው ስድስት ኪሎ በተሰበሰቡ ተማሪዎች ላይ የመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች ተኩስ ከፍተው ሦስት ተማሪዎችን ሲገድሉ ዐሥራ ስድስት ተማሪዎችን አቆሰሉ። ተማሪና መንግሥት እንዲህ ደም ከተቃቡ በኋላ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች እንደ ቀድሞው በሰላማዊ ሰልፍ መታገል እንደማያዋጣ ተረዱ። ገሚሶች ወደ ውጭ አገር በመሰደድ አውሮፓና አሜሪካ ያለውን የተማሪ ንቅናቄ ተቀላቀሉ።

---

[8] ይህን ንጽጽር በሚከተለው ጽሑፌ በስፋት አትቼዋለሁ፦ "1969: Ethiopia's 1968", in Chen Jian et al, eds., *The Routledge Handbook of the Global Sixties* (London and New York: Routledge, 2018), 356-366.

አገር ቤት የቀሩት በኅቡዕ የፖለቲካ ቡድኖች መደራጀት ጀመሩ:: የአደባባይ ትግሉን አርማ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ተረከቡ::

## አደረጃጀት

በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ የሚኖሩ ተማሪዎች እንቅስቃሴያቸውን የሚመሩ ድርጅቶች ነበሯቸው:: በአዲስ አበባው ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ መጀመሪያ የተቋቋመው ድርጅት ‹‹የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ኅብረት›› (University College Union, UCU) ይባል ነበር:: ማኅበሩ ከሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች ውስጥ የኮሌጁን መጽሔት ማሳተሙ ዋነኛው ነበር:: ይህም በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ስሞች ነበሩት፡- መጀመሪያ UC Calls፣ ቀጥሎ UCAA Newsletter፣ በመጨረሻም ረጅም ጊዜ የቆየውና ዝነኛ የነበረው News and Views::

በ1965 ስድስት ኪሎ የሚገኘው አዲሱ የመማሪያ ሕንፃ ተመርቆ የአርትስና ኢጁኬሽን ተማሪዎች ወደዚያ ሲዘዋወሩ የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ከስሞ ‹‹የዋናው ግቢ ተማሪዎች ማኅበር›› (Main Campus Student Union, MCSU) የሚባል ኅብረት ማቋቋም አስፈለገ:: የትምህርት ዘመኑ ሳይገባደድ፣ አዲስ አበባ የሚገኙትን የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በሙሉ በአንድ ማኅበር ስር ማሰባሰብ ያስፈልጋል የሚል ከፍተኛ ግፊት ተፈጥሮ ‹‹የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማኅበር›› (University Students Union of Addis Ababa, USUAA) ተቋቋመ:: የማታ ማታ፣ የኡዝዋ መመሥረት የድርጅታዊ መጠናከር መገለጫ ብቻ ሳይሆን የማርክሲስት ርዕዮት የበላይነት ማስመስከሪያም ሆነ:: ይህም ማኅበሩ በሚያሳትመው ‹‹ታገል›› (Struggle) በተሰኘው አዲስ መጽሔት ገሀድ ሆነ::

ከኡዝዋ መመሥረት በፊት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በሙሉ (ማለትም ከአዲስ አበባ ውጭ ያሉትን የዓለማያ ኮሌጅንና የጎንደር ጤና ኮሌጅን ጨምሮ) የሚያካትት ማኅበር ስላስፈለገ ‹‹የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ብሔራዊ ኅብረት›› (National Union of Ethiopian University Students, NUEUS) የተሰኘ ድርጅት ተቋቁሞ ነበር:: ይሁን እንጂ ይህ ድርጅት መጀመሪያ በኮሌጆች ማኅበር፣ ቀጥሎ ደግሞ በኡዝዋ ጥላ ስር ስለነበር ከአጋዥነት የዘለለ ብዙ ፋይዳ ሊኖረው አልቻለም::

በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን[9] ደግሞ በሁለት ታላላቅ አህጉራዊ ድርጅቶች የታቀፉ ነበሩ:: እነሱም ‹‹በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ኅብረት›› (Ethiopian Students Union in Europe, ESUE) እና ‹‹በአሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች

[9]ተማሪዎች ያላልኩት ተማሪ ያልሆኑ አባላትም ስለነበሯቸው ነው::

ኅብረት›› (Ethiopian Students Union in North America, ESUNA) ነበሩ። የአውሮፓው ድርጅት *ታጠቅ* እና *ትግላችን* (የመጀመሪያው የርዕዮተ ዓለማዊ ትንታኔ፣ ሁለተኛው የዜና ዘገባ) የሚባሉ መጽሔቶችን ሲያሳትም፣ የሰሜን አሜሪካው ደግሞ *Challenge* እና *Combat* የሚባሉ መጽሔቶችን ያወጣ ነበር። በአውሮፓ በየአገራቱ፣ በሰሜን አሜሪካ ደግሞ በየግዛቱ (ስቴቱ) ቅርንጫፍ ማኅበራት ነበሯቸው። የኅብረቱ አመራርም በፈረቃ ከቅርንጫፍ ቅርንጫፍ ይሸጋገር ነበር። ሁለቱን አህጉራዊ ኅብረቶችና የአገር ቤቱን ማኅበር የሚያስተባብር ደግሞ ‹‹ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ኅብረት›› (World Wide Union of Ethiopian Students, WWUES) የሚባል ድርጅት አቋቁመው ነበር። ይሁን እንጂ WWUESም እንደ NUEUS ውጤት አልባ እየሆነ ስለመጣ ጠንከር ባለ ድርጅት ለመተካት ታስቦ በ1972 ‹‹ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ፌዴሬሽን›› (World Wide Federation of Ethiopian Students, WWFES) ተመሠረተ። ይሁን እንጂ የተማሪዎችን ኅብረት ይበልጥ ያጠናክራል የተባለው ድርጅት የማታ ማታ ተማሪውን ሁለት ቦታ ሰነጠቀው። ኋላ ግልፅ እየሆነ እንደመጣው በፌዴሬሽን ጉዳይ ከተፈጠረው የከረረ ልዩነት ጀርባ በመኢሶንና በኢሕአፓ ስም የተከሰቱት ኅቡዕ የፖለቲካ ድርጅቶች የተማሪውን ንቅናቄ ለመቆጣጠር የሚያደርጉት የሥልጣን ሽኩቻ ነበር።

በነዚህ የተማሪዎች ድርጅቶች ዕድገት ውስጥ ጎልቶ የሚወጣው አንዱ ነገር የውኅደትና የመሰነጣጠቅ ተቃርኖያዊ ሂደት ነው። በአገር ቤት ውስጥ የተሞከረው አንዱ የውኅደት እርምጃ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎችን በሙሉ የሚያቅፍ ብሔራዊ ኅብረት (NUEUS) መፍጠሩ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ድርጅት የተፈለገውን ያህል ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። በ1965 የአርትስና ኢዱኬሽን ፋክልቲዎች ከአራት ኪሎ ወደ ስድስት ኪሎ ሲዘዋወሩ የዋናው ካምፓስ ተማሪዎችን በሙሉ የሚያቅፍ ኅብረት ተመሠረተ። ነገር ግን ቀደም ብለው እዚያው የተደራጁት የሕግ ፋክልቲና የቢዝነስ አስተዳደር ተማሪዎች የራሳችን ማኅበር ይበቃናል ብለው በካምፓሱ ኅብረት አንታቀፍም አሉ። በዚያው ዓመት የተቋቋመው ኡዝዋ የተማሪውን ሙሉ ድጋፍ አላገኘም ነበር። በተደረገው ሬፈረንደም ሊያሸንፍ የቻለው በአንድ ሦስተኛ ድምፅ ብቻ ነበር። ከዚያም በኋላ በኡዝዋ ምትክ የካምፓስ ኅብረቶችን ለመመለስ ጠንካራ እንቅስቃሴ ተጀምሮ እየጎለበተ ሲሄድ የኡዝዋ ደጋፊዎች ረብሻ በመፍጠር አጨናገፉት።

በውጭ አገርም የታየው ተመሳሳይ ክስተት ነበር። ጠንካራ የነበረው ኤዙና በ1971 በብሔረሰብ ጥያቄ ላይ በተፈጠረው አለመስማማት ምክንያት ለሁለት ተሰንጥቆ

‹‹የቀድሞው ኤዙና›› እና ‹‹አዲሱ ኤዙና›› በሚል መጠሪያ መለየት ተጀመረ። ይህም አልበቃ ብሎ ከአብዮቱ መፈንዳት በኋላ ልክ እንደ መኢሶን ለደርግ ሂሣዊ ድጋፍ እሰጣለሁ የሚል United Progressive Ethiopian Students Union in North America (UPESUNA) የሚባል ድርጅት ይፋ ወጣ። በአውሮፓ ደግሞ ቀስስተኛ የነበረውን የዓለም አቀፍ ተማሪዎች ማኅበር ነፍስ ይዘራበታል ተብሎ በ1973 የተመሠረተው ፌዴሬሽን እስከናካቴው ኅብረቱን ሁለት ቦታ ሰነጠቀው። አብዮት ሲፈነዳ በአብዮቱ ሂደትና የወደፊት አቅጣጫ ላይ ተጨማሪ ልዩነቶች ተፈጥረው ሁለቱ ወገኖች መቼም ላይገናኙ ተለያዩ።

እነዚህ የተማሪዎች ማኅበራት፣ በተለይም ውጭ አገር ያሉት፣ የተደራጀ የፖለቲካ ፓርቲ ባሕርያት ነበሯቸው። ዓመታዊ ጉባዔ ያካሂዱ፤ በአገራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉዳዮች ላይ የአቋም መግለጫ ያወጡ፣ ውሳኔዎች ያስተላልፉ፤ አባሎቻቸውን ለትግል የሚቀሰቅሱበት የተለያዩ መዝሙሮች ነበሯቸው። ከሁሉም በላይ አባሎች በርዕዮተ ዓለም እንዲበስሉ በየቅርንጫፍ ማኅበራት የጥናት ቡድኖች አቋቁመው ነበር። በዚህ ረገድ በተለይ ኤዙና ብዙ መንገድ ተጉዞ ነበር ማለት ይቻላል። አባላት በንቃት የሚሳተፉበት Political Education Program (PEP) የሚባል የጥናት መርሀ ግብር ዘርግቶ ነበር።

**ርዕዮተ ዓለም**

ኋላ ጭልጥ ብሎ ማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮት ውስጥ ሊገባ፣ የተማሪዎች ንቅናቄ አጀማመሩ ላይ ገራገር ነበር። ለዚህም ነው በ1950ዎቹ የተማሪዎች መሪ የነበሩት አቶ አስፋው ዳምጤ እነዚያን ዓመታት ‹‹የገር ዘመን›› የሚል ስያሜ የሰጡት።[10] ተማሪዎች ያተኩሩ የነበሩት ከፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ይልቅ በስፖርትና የክርክር ባህልን በማስረጽ ላይ ነበር ማለት ይቻላል። እንዲህ በግልፅ አይቀመጥ እንጂ የጊዜው መርህ ‹‹ራስህን እወቅ››፣ ‹‹አገርህን እወቅ›› የሚል ነበር። ዓላማው በትምህርት የመጠቀ፣ በስፖርት የላቀ እና በክርክር የሰላ ስብዕናን መፍጠር ነበር። ለዚህም ነው በተለይ ‹‹የክርክር ክበብ›› እና የግጥም ውድድር በተማሪዎች ሕይወት ውስጥ ጉልህ ስፍራ ሊይዙ የቻሉት።

‹‹አገርህን እወቅ›› በሚለው መርህ ደግሞ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች Ethnological Society የተሰኘ ማኅበር በማቋቋም በተለያዩ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ባህላዊ ዕሴቶች (ምግብና መጠጦች እምነቶች፣ የበዓላት አከባበር፣ ጋብቻ፣ የቀብር ሥነ ሥርዓት፣

---

[10] Bahru Zewde, ed., *Documenting the Ethiopian Student Movement: An Exercise in Oral History* (Addis Ababa: Forum for Social Studies, 2010), pp. 19-23.

ወዘተ...) ላይ ጥናት በማድረግ በማኅበሩ ቡለቲን ላይ አሳተሙ:: ይህ መጽሔትም በተከታታይ ለስምንት ዓመት ሊወጣ የቻለ ነው:: ከማኅበሩ መሪዎቹ መካከል ኋላ የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ለመሆን የበቁት ዶ/ር አክሊሉ ሀብቴ እና ዶ/ር ዱሪ መሐመድ ይገኙበታል::

የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮተ ዓለም ወደ ተማሪው ንቅናቄ መስረግ የጀመረው በ1960ዎቹ አጋማሽ ገደማ ነው:: ለዚህም ትልቁን አስተዋጽኦ ያደረገው ቀደም ሲል የተጠቀሰው ‹‹አዞዎቹ›› የተባለው ቡድን ነው:: የቡድኑ መሥራቾች ተብለው የሚወሱት ከዓለማያ ኮሌጅ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የተዛወሩት ገብሩ ገብረ ወልድና ዘርዐ ክሽን ናቸው:: ግንባር ቀደም የተማሪዎች መሪና የኢሕአፓ መሥራች የነበረው ብርሀነ መስቀል ረዳ ቡድኑን የተቀላቀለው ቆየት ብሎ እንደነበር ይገመታል:: ያም ሆነ ይህ እነዚህ የኅቡዕ ቡድኑ አባላት ናቸው ዩኒቨርሲቲውን የተቀላቀሉ አዲስ ተማሪዎችን እየመለመሉ የማርክሲስት ሌኒኒስት ርዕዮት በአብዛኛው ተማሪዎች ዘንድ እንዲስፋፋ የሠሩት::

ርዕዮተ ዓለሙ የተስፋፋበት መንገድ ሁለት ገጽታ ነበረው:: የመጀመሪያው ‹‹ኦርቶዶክስ›› ማርክሲስት የሚባሉትን የነማርክስ፣ ሌኒን፣ ስታሊንና ማኦን ሥራዎች በማሠራጨትና በማንበብ ነው:: በወቅቱ የነዚህን ጉምቱ የማርክሲስት መሪዎች የመጻሕፍት ስብስብ ቤቱ የማያከማችና የማያነብ ተማሪ አልነበረም ማለት ይቻላል:: በሌላ በኩል ደግሞ ትሮትስካይት ዝንባሌ የነበራቸው ‹‹አዲሱ ግራ›› (The New Left) የሚባሉት ማርክሲስቶች ሥራዎች እያደር ተወዳጅና ተፈላጊ እየሆኑ መጡ:: በተለይ በምዕራቡ ዓለም (አውሮፓና አሜሪካ) የተንሠራፋውን ይህን የ‹‹አዲሱ ግራ›› አመለካከት የሚያሠራጩ ሁለት ዝነኛ መጽሔቶች ነበሩ፡- Monthly Review እና New Left Review:: ከመጽሔቶቹም ባሻገር ያንኑ ስም የያዙት አሳታሚዎች የሚያወጧቸው መጻሕፍትም በጣም ተነባቢ ነበሩ:: አንዳንዶቹን ለመጥቀስ ያህል በአይዛክ ዶቸር የተደረሰው ባለ ሦስት ቅጽ (ትራይሎጂ) የትሮትስኪ የሕይወት ታሪክ፣ ፓል ባራን እና ፖል ስዊዚ የጻፏቸው የካፒታሊስት ማኅበረ ሰብ ትንተናዎች፣ አንድሬ ጉንደር ፍራንክ ያጠነጠነው የጥገኝነት ቲዎሪ ከዚህ ተርታ የሚገኙ ነበሩ:: የአዲሱ ግራ ትንተና መነሻ የማርክስና ኤንግልስ ጽሑፎች ነበሩ:: ሌኒን በነሱ ዘንድ ይህ ነው የሚባል ሥፍራ አልነበረውም::

ዞሮ ዞሮ በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ርዕዮተ ዓለማዊ ቀረጻ ወሳኙን ሚና የተጫወተው ማርክስ ሳይሆን ሌኒን፣ እሱንም ተከትሎ ስታሊን ነው:: ይህም ገሀድ የወጣው በተለይ ንቅናቄው የብሔረሰብን ጥያቄ ለመፍታት በሄደበት መንገድ ነው:: ችግሩ የተፍታታበትም ሆነ መፍትሔው የተፈለገበት መንገድ የኢትዮጵያን ታሪክና

ኤትኖግራፊ ባገናዘበ መልኩ ሳይሆን ለሌኒኒስትና ስታሊኒስት ቀኖና ታማኝነትን ባስመሰከረ ዓይነት ነው:: ይህንንም ለመረዳት በጉዳዩ ላይ የመከራከሪያ ሰነድ ለመሆን የበቁትን ሁለቱን ተፃራሪ ጽሑፎች ማየቱ ይበቃል:: የመጀመሪያው በጥላሁን ታከለ (ማለትም በብርሀነ መስቀል የሚመራው የአልጄሪያው ቡድን) በ1970 የኤዙናን መሪዎች አቋም በመተቸት ያወጣው ጽሑፍ ሲሆን፤ ሌላው ደግሞ ቱምቱ ሌንጮ በሚል የብዕር ስም አንድርያስ እሸቴ የሰጠው አፀፋ መልስ ነው:: የመጀመሪያው እስካሁንም አብሮን የዘለቀውን ‹‹የብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት እስከመገንጠል›› መርህ ሲያቀነቅን፣ ሁለተኛው መገንጠል ላይ ‹‹ሙጭጭ›› ማለትን ተቸ:: ምንም እንኳ የኋለኛው ስለ ተጨባጩ የኢትዮጵያ የብሔረሰብ ስብጥር የተሻለ ግንዛቤ ቢያሳይም፣ የሁለቱም ዋና ማጣቀሻ የሌኒንና የስታሊን ሥራዎች (በተለይም የሁለተኛው) ነበሩ::

ተፋላሚዎቹ ከሌኒን የወረሱት ቀኖናውን ብቻ ሳይሆን ምኅረት የለሽ የአተቻቸት ስልቱንም (ፖለሚክሱን) ጭምር ነበር:: ይህ በተለይ በጥላሁን ታከለ ጽሑፍ በጉልህ ይንፀባረቃል:: የኤዙና መሪዎችን ያብጠለጠለበት መንገድ የሐሳብ ልዩነትን ለማስረዳት ሳይሆን ከንቅናቄው ጎራ ጨርሶ ለማስወጣት የታለመ ነበር የሚመስለው:: ይህ ስልት በተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ሐሳብን ከልክ በላይ አክርሮ የማቅረብ ባህል በማስረግ ለመጠፋፋት ፖለቲካ መንገድ ከፈተ:: በቃላት የጀመረው ጦርነት ውሎ አድሮ ወደ መሣሪያ ጦርነት ተሸጋገረ:: በዚህም ሁኔታ የኢትዮጵያ ግራ ክንፍ እርስ በርሱ ተጠፋፍቶ ለደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ ምቹ ሁኔታን ፈጠረለት::

የተማሪው ንቅናቄ ከተሰለፈበት ተልእኮም ባሻገር ለኢትዮጵያ ግራ ክንፍ ድርጅቶች ምሥረታ ዋነኛው መረማመጃ ነበር:: የመላው ኢትዮጵያ ሶሻሊስት ንቅናቄ (መኢሶን) የተመሠረተው በ1968 በኤዙዌ መሪዎች ሲሆን ኋላ ስሙን ወደ የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) የቀየረው የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዮታዊ ድርጅት (ኢሕአድ) ደግሞ በ1972 በአልጄሪያው ቡድንና በኤዙዌ ቅርንጫፍ መሪዎችና የኤዙና መሪዎች ነው:: ይህ ኅብረ ብሔራዊ የሆኑትን የግራ ክንፍ ድርጅቶች የሚመለከት ሲሆን፣ ብሔርተኛ ድርጅቶቹም ቢሆን በከፊል የወጡት ከዚሁ ከተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ ነው:: የሕወሓት መሪዎች መጀመሪያ ላይ በአገር ቤቱ የተማሪ ንቅናቄ (በተለይም በኡዝዋ) ውስጥ ግንባር ቀደም ተዋናይ የነበሩ ናቸው:: ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር መሪዎች መካከልም ጥቂት የማይባሉት በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ ንቁ ተሳታፊ ወይም አመራር ላይ የነበሩ ናቸው:: በሁለቱ ክንፎች፣ ኅብረ

ብሔራዊና ብሔርተኛ፣ መካከል ያለው ልዩነት የመጀመሪያዎቹ የመገንጠልን ጽንሰ ሐሳብ ሲከልሱት፣ የኋለኞቹ ግን ገፉበት።

**አሻራው**

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በሀያኛው ክፍለ ዘመን በአገሪቱ ከታዩ ክስተቶች በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀስ ነው። አሻራው እስካለንበት ዘመን ድረስ ዘልቋል። የኢትዮጵያን ሕይወት ላይመለስ የቀየረው የ1974ቱ አብዮት ከሁሉም በላይ የንቅናቄው ውጤት ነው። የተማሪው የአንድ ዐሠርት ሙሉ ያላባራ ተቃውሞ ነው አፄያዊውን ሥርዓት ሰልስሎ በአብዮት ማዕበል እንዲጠራረግ ያደረገው። ከዚያም አልፎ አብዮቱ በወታደራዊው አገዛዝ የሄደበት መንገድ በተዘዋዋሪም ቢሆን ተማሪዎቹ የቀየሱት ነው። የደርግ አባላት ወደ ሥልጣን ሲመጡ ግፋ ቢል አገር ወዳድ ቢባሉ እንጂ ብዙዎቹ ከሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ጋር እምብዛም የሚተዋወቁ አልነበሩም። ለዚህም ነው የመጀመሪያ መፈክራቸው ‹‹ኢትዮጵያ ትቅደም›› የሆነው።

ይሁን እንጂ በሂደት ሥልጣናቸውን ለማረጋገጥ ይህ ዓይነት መፈክር ብዙም እንደማያስኬዳቸው ለመረዳት ብዙ ጊዜ አልወሰደባቸውም። ለመግዛት ገዥውን ርዕዮተ ዓለም፣ ማለትም ማርክሲዝም-ሌኒኒዝምን፣ መቀበል እንዳለባቸው ተረዱ። ተማሪዎችንና ከነሱ አብራክ የወጣውን ግራ ክንፍ ለመብለጥ ርዕዮታቸውን መንጠቅ። እሱንም ቢሆን በአንዴ አላደረጉትም። መጀመሪያ ‹‹ኅብረተሰባዊነት›› የሚል ለዘብተኛ ሶሻሊዝም መመሪያችን ነው አሉ። እንደ ታንዛኒያ ባሉት አገራት የሚቀነቀነውን የአፍሪካን ሶሻሊዝም ዓይነት መሆኑ ነው። ከዚያ በ1968 ‹‹የብሔራዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት››ን አወጁ። በመጨረሻም በ1984 የኢትዮጵያ ሠራተኞች ፓርቲን ይፋ አድርገው ከኛ ወዲያ ማርክሲስት-ሌኒኒስት ለአሳር ነው አሉ።

ከርዕዮተ ዓለም ባሻገር በ1975 የታወጀው ሥር-ነቀል የመሬት አዋጅ ከዐሥር ዓመት በፊት ተማሪዎች ‹‹መሬት ላራሹ›› በማለት ሠልፍ የወጡበት ጥያቄ ማሳረጊያ ሆነ። አዋጁ በተለይ በደቡባዊ የአገሪቱ ክፍል ተንሠራፍቶ የነበረውን ጭሰኝነት ለአንዴም ለሁሌም አስወገደ። ይሁን እንጂ መሬት እንደተፈከረው ለአራሹ አልተሰጠም። የተሰጠው ‹‹ለሕዝብ›› ነው። የሕዝቡም ወኪል መንግሥት፣ በተዋረድም የገበሬ ማኅበራት ሆኑ። ስለዚህ የታለመው ሙሉ የመሬት ባለቤትነት መብት ለገበሬው አልተሰጠም። ይህ ጉዳይ እስካሁንም እልባት ሳያገኝ የመከራከሪያ ነጥብ ሆኖ ቆይቷል።

ምናልባትም ከሁሉም በላይ የንቅናቄው አሻራ የሚታየው እስካሁንም በሚያስተጋባውና በሚያበጣብጠው በብሔረሰቦች ጥያቄ ነው። በ1969 እንደ ዱብ

ዕዳ የወረደው የብሔረሰቦች ጥያቄ ኤዙናን ለሁለት ሰነጠቀ። ከጊዜ በኋላም ኅብረ ብሔራዊውን ግራና ብሔርተኛውን ግራ ከፋፈለ። ከአገራዊ ዕውቀት ይልቅ በማርክሲስት ቀኖና ላይ የተመሠረተው ‹‹የራስን ዕድል በራስ የመወሰን፣ እስከመገንጠል›› መርህ የአገሪቱን ብሔረሰቦች ታሪካዊ ትስስርና መስተጋብር አደባብሶ ልዩነታቸውን የሚያከር ነበር። ይሁን እንጂ መርሁ የግራ ክንፎች ጉንጭ አልፋ ክርክር ከመሆን አልፎ ለብሔርተኛ ድርጅቶች መቀስቀሻና ማስተባበሪያ ሆኖ አገለገለ። ከዚያም አልፎ በ1995 የአገሪቱ ሕገ መንግሥት ዋነኛ አካል ለመሆን በቃ። መርሁ እንዲህ ገኖ ሊወጣ የቻለው ለመብት ከመቆርቆር ነው ወይስ ሥልጣን ለማደላደልና ሀብት ለማጋበስ ነው የሚለው ጥያቄ እስካሁንም የሚያጠያይቅ ጉዳይ ነው።

ሌላው የተማሪዎች ንቅናቄ ቅርስ ደግሞ የጽንፈኝነት ባህል ነው። በጥላሁን ታከለ የተጀመረው የምኅረት የለሽ ሬቶሪክ የተማሪው የአጻጻፍ ወግ ሆነ። ፋና ወጊዎቹ ሐሳባቸውን የሚገልጹበት መንገድ ልዝብና ትኅትና የተመላበት ነበር። ሌላው ቀርቶ በንቅናቄው ‹‹የገር ዘመን›› እንኳ በጣም ተወዳጅ የነበረው የአጻጻፍ ወግ ‹‹መቼ ይሆን?›› (That will be the day when ...) የሚል ነበር። ከ1970ዎቹ በኋላ ግን የኔ ሐሳብ ብቻ ነው ትክክል በሚል ቅኝት የተለየ ሐሳብን የማብጠልጠል ባህል ተዛመተ። ኤዙዌ ለሁለት ከተከፈለ በኋላ በተፃራሪዎቹ ወገኖች የሚወረወሩት የነቀፋ ቃላት የተለየ ሐሳብ ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚደረግ ክርክርን ሳይሆን ጦር የተማዘዙ ደመኛ ባላንጣዎችን የሚያስታውስ ነበር። ይህ የዜሮ ድምር ባህል እስካሁንም ድረስ የኢትዮጵያን ፖለቲካ ተጠናውቶት ቆይቷል። ለተጀመረው አገራዊ ምክክርም አንዱ ትልቅ እንቅፋት የሚሆነው ይኸው አመለካከት ሳይሆን አይቀርም።

በነዚህ ሁለት አሻራዎቹ ምክንያት (ማለትም በብሔረሰብ ጥያቄና የጽንፈኝነት ባህሉ) ኢትዮጵያ አሁን ለምትገኝበት ውስብስብ ችግር የተማሪውን ንቅናቄ ተጠያቂ የማድረግ አዝማሚያ በስፋት ይታያል። የንቅናቄው አዎንታዊ ባሕሪው ደብዝዞ አሉታዊ ጫናው ብቻ ጎልቶ ይወጣል። ነገር ግን ንቅናቄውን አለቅጥ ማወደስም ሆነ መኮነን አግባብ አይደለም። ትክክለኛው መንገድ ንቅናቄውን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መገምገም ነው። ይህንንም ስለ ንቅናቄው በጻፍኩት መጽሐፌ በሚከተለው መንገድ ገልጨዋለሁ።--

> ሲጠቃለል፣ ከሉላዊም ሆነ አገራዊ አውዱ ሲታይ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ማቆጥቆጥ የአይቀሬነት ባሕሪ አለው። ጊዜ የማይሰጡ የፖለቲካና ኤኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች ለማድረግ የተሳነውን መንግሥት የሚገዳደር የፖለቲካ ተቃዋሚ ቡድን በሌለበት ሁኔታ፣

ተማሪዎች ያንን ኃላፊነት ወሰዱ። ብዙዎቹ የማታ ማታ የማይጨበጥ ሕልም ለሆነ ጉዳይ የወደፊት ዕድላቸውን ብቻ ሳይሆን ሕይወታቸውን ገበሩ። አነሳሳቸውን አይቀሬ ያደረገው የአገራቸው የፖለቲካ ባህል አካሄዳቸውንም ገደበው። ከበሰለ ክርክርና የሰጥቶ መቀበል ባሕሪ ይልቅ ቀኖናዊ ግትርነት መለያቸው ሆነ። ይህ ችግር በተለይም ጎልቶ የወጣው የብሔረሰብ ጥያቄን ለመፍታት በሄዱበት መንገድና በድርጅታዊ አሠራራቸው ነበር። በዚህ ረገድ የተውት አሻራም ከሁሉም የበለጠ ጠንቀኛው ሳይሆን አይቀርም። አገሪቷ ከዚህ አሻራ መውጣት ካልቻለች መዳኛም የላትም። ይሁን እንጂ ተማሪዎች ያደረጉትን ነገር ያደረጉት በቅን ልቦና መሆኑን ልንረዳ ይገባል። ምንም ድብቅ አጀንዳ አልነበራቸውም። የሚገፋፋቸው ወጣቶችን የትም ሆነ መቼም የገፋፋቸው አንድ ጉዳይ ነው፡- ማኅበራዊ ፍትሕንና የተመጣጠነ ዕድገትን መሻት።[11]

## ድኅረ ጽሑፍ (Postscript)

ማርክ አንቷን ጁልያ የተባለ ፈረንሣዊ አብዮተኛ ‹‹በእሳተ ገሞራ ውስጥ ተወለድኩ፣ ፍንዳታውን ኖርኩት፣ በአመዱ ተቀበርኩ›› ሲል አብዮታዊ ሕይወቱን በስዕላዊ መንገድ ገልጾታል።[12] አብዮት ልጆቿን ትበላለች የሚባል ብሂልም እየተለመደ መጥቷል። በእርግጥም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ያቀጣጠሉት አብዮት ሰለባ ነው የሆኑት። በ1969 እንደ ዋዛ በአንድ ተማሪ እልፈተ-ሕይወት የጀመረው መስዋዕትነት በዘመነ አብዮት ዕልፍ አዕላፍ ወጣቶችን ቀጠፈ። በተለይም ቀይ ሽብር በተባለው የጅምላ ጭፍጨፋ አገሪቱ ብዙ አይተኬ ወጣቶችን አጣች። በሕይወት መስማማት ያልቻሉት መኢሶንና ኢሕአፓ በመቃብርና በእስር ቤት ተገናኙ። ገናና የነበረው የተማሪው የውጭ ክንፍም ተከፋፍሎና ተስፋ ቆርጦ ተበተነ። ወጣቱ ፖለቲካን ሕይወቱ ያላደረገውን ያህል ‹‹ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቅ›› በማለት ራሱን ከአገራዊ ጉዳዮች ገሸሽ አደረገ።

ደርግ የተማሪ ንቅናቄውን ካመከነ እና ከዚያም የፈለቁትን የግራ ኃይሎች ካስወገደ በኋላ ወጣቱን በራሱ አምሳያ ለመፍጠር መዋቅር ዘረጋ። በተለይም የወዝ አደር ፓርቲውን (ኢሠፓን) ካቋቋመ በኋላ ሕዝቡን የሚቆጣጠርባቸው የብዙኃን ድርጅቶችን በየፈርጁ መሠረተ። ገበሬውን በመላ ኢትዮጵያ ገበሬዎች ማኅበር

---

[11]The Quest for Socialist Utopia, pp. 279-80.

[12]Ibid, p. 263.

(መኢገማ)፣ ሠራተኛውን በመላ ኢትዮጵያ ሠራተኞች ማኅበር (መኢሠማ)፣ ሴቶች በአብዮታዊ ኢትዮጵያ ሴቶች ማኅበር (አኢሴማ)፣ ወጣቶችን ደግሞ በአብዮታዊ ኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበር (አኢወማ)። በዚህ ሂደት ወጣቱ ነፃነቱን ተነፍጎ የኢሠፓ ጉዳይ አስፈፃሚ ሆነ።

ወጣቱ ከዚያ በኋላ አንፃራዊ ነፃነት ያሳየው ሁለት ጊዜ ብቻ ነው፦ በምርጫ 97 ወቅትና በቅርቡ ደግሞ የመንግሥት ለውጥ ባመጣው አገር አቀፍ ንቅናቄ። የምርጫ 97ቱ መነቃቃት በወጣቱ የታጠረ ሳይሆን ብዙ የኅብረተሰብ ክፍሎችን ያዳረሰ ነበር። የ2018ቱን የመንግሥት ለውጥ የወለደው ንቅናቄ ግን በመሠረቱ በወጣቶች የሚመራ ነበር። በየክልሉም እስካሁንም የዘለቀ የራሱ መጠሪያ አውጥቶ ነበር፦ በኦሮሚያ ቄሮ፣ በአማራ ፋኖ፣ በጉራጌ ዘርማ። የተማሪዎች ንቅናቄ ሳይሆን የወጣቶች አመፅ ነበር። ከፖለቲካ ዓላማውም ባሻገር በአገሪቱ የተንሠራፋው ሥራ-አጥነት ውጤትም ነበር ማለት ይቻላል።

ምንም እንኳን የቅርቡ የቄሮዎች እንቅስቃሴ ገና በስፋትና በጥልቀት የሚጠና ጉዳይ ቢሆንም፤ ርዕሰ ጉዳያችን ከሆነው ከተማሪዎች ንቅናቄ ጋር አንዳንድ የንጽጽር ሐሳቦች በማስፈር ጽሑፌን እደመድማለሁ።[13] በተለይ በውጭ አገሩ እንቅስቃሴ ተማሪዎች ያልሆኑም የማኅበራት አባላት ቢኖሩም፤ የተማሪዎቹ ንቅናቄ በአብዛኛው፣ በተለይ በአገር ቤት ውስጥ፣ በተማሪዎች ላይ የተመሠረተ ነበር። በአንፃሩ፣ የ2015-18ቱ አመፅ ከትምህርት ቤቶች ወይም ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አውድ ውጪ ነው የተካሄደው። ሁለተኛ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ ይታገል የነበረው አብዮት ወይም ጠቅላላ ኅብረተሰባዊ ሹም ሽር ለማምጣት ሲሆን፣ የኋለኛው ዓላማ ግን ግፋ ቢል የመንግሥት ለውጥ ለማምጣት ነበር። በውጤት ደረጃ ግን ሁለቱም እንቅስቃሴዎች ተመሳሳይነት አላቸው። ተማሪዎቹ አብዮት አቀጣጥለው ለደርግ አስረከቡ። የወጣቶቹ አመፅም የአመፁ ዒላማ ከነበረው ኢሕአዴግ መሀል የወጣ ቡድንን ለሥልጣን አበቃ። ይህ ደግሞ በብዙ አብዮታዊ እንቅስቃሴዎች የታየ ጉዳይ ነው። ወጣት ይታገላል፣ የተደራጀ ቡድን ሥልጣን ይዛል። ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው በኢራን የሆነው ይህ ነው፤ በግብፅም የ2011ዱ ሕዝባዊ አመፅ (‹‹የአረብ ጸደይ›› በመባል የሚታወቀው) መጀመሪያ ለሙስሊም ወንድማማቾች፣ ቀጥሎ ደግሞ ለአል ሲሲ ወታደራዊ አገዛዝ መንገድ ጠረገ።

---

[13]እነዚህ ሐሳቦች ውይይቱን ለመጀመር ያህል እንጂ እንደ አለቀላቸው ነገሮች ሊታዩ አይገባም። በዚህ ረገድ በዚሁ የውይይት መድረክ ዶ/ር አስናቀ ከፋለ እና አማኑኤል ተስፋ የቀረቡት ጥናታዊ ጽሑፎች የተሻለ ግንዛቤ ይሰጣሉ።

ሌላ የሁለቱ እንቅስቃሴዎች ልዩነት ደግሞ ከአደረጃጀትና ርዕዮተ ዓለማዊ ዝግጅት ጋር የተያየያዘ ነው። ከላይ እንዳየነው የተማሪዎቹ ንቅናቄ፣ የአገር ቤቱም ሆነ የውጪው፣ ጠንካራ የአደረጃጀት መሠረት ነበረው። ቀኖናዊ በሆነ መንገድ ቢተገበርም ግልጽ የሆነ የርዕዮተ ዓለም ትጥቅ (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም) ነበረው። የተራማጅነትና የአብዮታዊነት መለኪያውም እሱ ነበር። ከሁሉም በላይ ተማሪዎቹ ስለዓላማቸውና አገሪቱ ልትሄድበት ስለሚገባው አቅጣጫ በስፋት ጽፈዋል። ከራሴ ልምድ መረዳት እንደሚቻለው በንቅናቄው ላይ ምርምር ለማድረግ የሚፈልግ ሰው የመረጃ ጎርፍ እንጂ ዕጥረት አያጋጥመውም።

በአንፃሩ የቅርቡ ዘመን አማፂ ወጣቶች የድርጅት መረብ እንደዘረጉ ቢታወቅም ትክክለኛ መልኩና ይዘቱ ለተመልካች ያን ያህል ግልጽ አይደለም። ትግላቸው በርዕዮተ ዓለም ሳይሆን ወቅታዊ ጉዳዮችና ችግሮችን በመፍታት የሚመራ ነበር። የትግል መሣሪያቸውም ብዕር ሳይሆን ሞባይል ስልካቸው ነው። ስለሆነም እርምጃቸው ፈጣን፣ ተደራሽነታቸው ሰፊ፣ ውጤቱም ሳይውል ሳያድር የሚታይ ሆነ። ትልቁ ችግር ግን ወደፊት ይህን አመፅ የሚያጠና የታሪክ ተመራማሪ በምን ሰነድ ላይ ተመርኩዞ ሊያጠና ይችላል የሚለው ነው። በአጠቃላይ ግን የተማሪዎቹ ንቅናቄ ከከሰመ ከአንድ አርባ ዓመት በኋላ የተከሰተው የወጣቶች አመፅ የሚያሳየው አንድ ነገር ቢኖር በደል እስካለ ድረስ ወጣቱ ምንጊዜም ከመቃወም ወደኋላ እንደማይል ነው። ይህ የወጣት ሉላዊና ዘላለማዊ ባሕርይ ነውና።

# ትምህርትና የወጣት ስብዕና ልማት በኢትዮጵያ

**የቆየዓለም ደሴ**

## 1. መግቢያ

የአንድ ሀገር ሁለንተናዊና ውጤታማ ዕድገት በወጣቶቿ ጥራት ላይ ይወሰናል:: ወጣቶች ለሀገር ዕድገት ወሳኝ ሚና የሚጫወቱ የማህበረሰብ ክፍሎች ናቸው:: ይህንንም በመረዳት ሀገራት ያላቸውን ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ሀብት ወጣቶችን ለማሳደግ፣ ለማስተማርና ለማብቃት ያውሉታል::

ኢትዮጵያ የወጣቶችና የህፃናት ሀገር ናት:: ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት 80% የሚጠጋው የማህበረሰብ ክፍል ከ35 ዓመት የዕድሜ ክልል በታች ነው:: እንዲሁም ከአጠቃላይ የህዝብ ብዛት 40% የሚሆነው ከ10-29፤ 26% የሚሆነው ደግሞ ከ10-19 የዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛል:: ይህም ወጣቱ ለኢትዮጵያ ዋነኛ እና የማይተካ ሀብት እንደሆነ ያሳያል:: እንዲሁም የኢትዮጵያን የዲሞግራፊ ሽግግር በቅርበት በምናጤንበት ጊዜ የወጣቱ ቁጥር ወደፊትም እየጨመረ እንደሚሔድ ያስረዳል:: ይህም ኢትዮጵያ ከምንም ነገር ቅድሚያ በወጣቶቿ ላይ መሥራት እንዳለባት ያስገነዝባል::

በኢትዮጵያ በተለይ ባለፉት ሦስት አሥርት ዓመታት በወጣቶች ዕድገትና የስብዕና ግንባታ ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ለውጦች ተካሂደዋል:: በተለይ ደግሞ ከ1983 ዓ.ም. የመንግስት ለውጥ በኋላ ወጣቶችን የተመለከቱ ዘርፈ ብዙ ለውጦች ተከናውነዋል:: በግንቦት 1983 ዓ.ም. የኢህአዴግ መንግስት ወደ ስልጣን መምጣቱን ተከትሎ የመጣው ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም እና ያልተማከለ አስተዳደር በአጠቃላይ በወጣቶች አደረጃጀት፣ ስነልቦናዊና የማንነት ዕድገት ላይ የራሱን የሆነ ተፅዕኖ አሳድሯል:: በ1986 ዓ.ም. የፀደቀውን ህገ-መንግስት መሠረት በማድረግ የተቀረፁት የትምህርት ፖሊሲ (1987 ዓ.ም.)፣ የወጣቶች ፖሊሲ (1986 ዓ.ም.)፣ የተለያዩ (የከተማ፣ የገጠር፣ የአርብቶ አደር)፣ የወጣቶች የልማት ፖኬጆች፣ የሥነ-ተዋልዶና የጤና ፖሊሲዎች፣ የማህበራዊና የቴክኒክና ሙያ እና የሥራ ፈጠራ፣ የአደገኛ ዐዘኔ ፖሊሲዎችና አዋጆች ከብዙ በጥቂቱ በወጣቶች የስብዕና ዕድገትና ልማት ላይ የራሳቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ ካሳደሩት መካል በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ::

የዚህ ፅሁፍ ዋና ዓላማ ግን በአጠቃላይ በድህረ 1983 ዓ.ም. በነበረው የፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ዐውድ ውስጥ የትምህርት ሥርዓቱ በወጣቶች ስብዕና

ዕድገትና ልማት ላይ ያመጣውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖ መዳሰስ ነው:: ለዚህም ፅሁፉ በስምንት ዋና ዋና ክፍሎች የተዋቀረ ነው:: የመጀመሪያው ክፍል ስለወጣትነትና የወጣት ስብዕና ዕድገት ምንነት አጠር አድርጎ ያስረዳል:: ሁለተኛውና ሦስተኛው ክፍሎች ደግሞ በቅደም ተከተል የወጣቶች የስብዕና ዕድገት ስለሚካሔድበት አውድና በመልካም ወይም በአዎንታዊ የስብዕና ዕድገት ላይ ያሉ ወጣቶች የሚያሳዩዋቸው መገለጫ ባህርያትን የሚያስረዳ ሀሳብ ይዘዋል:: አራተኛው ክፍል ስለ ትምህርትና ወጣት መስተጋብር የሚያትት ነው:: አምስተኛው እና ስድስተኛው ክፍል ደግሞ የድህረ 1983ቱ የትምህርት ፖሊሲ ዋና ዋና ግንዛቤዎችና ያመጣቸውን ጉልህ ስኬቶችና የነበሩበትን ጉድለቶች በቅደም ተከተል ያቀርባል:: ሰባተኛው ክፍል የትምህርት ስርዓቱ በወጣቶች የስብዕና ግንባታ ላይ ያስከተለውን ተፅዕኖ ይቃኛል:: የመጨረሻው ክፍል አጠር ያለ ማጠቃለያና ወደ ፊት ምን መደረግ እንዳለበት የሚጠቁሙ ሀሳቦችን ያካተተ ነው::

## 2. የወጣትነት ምንነት

ወጣት ማለት ምን ማለት ነው? ወጣት የሚባለውስ ማን ነው? የሚሉት ጥያቄዎች በተደጋጋሚ የሚነሱ ነገር ግን አጥጋቢ ምላሽ ያላገኙ ጥያቄዎች ናቸው:: በዘርፉ ያሉ ምሁራን እንደሚገልፁት የወጣትነት ትርጉም እንደ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታው፣ ታሪካዊ ሂደት እና ከግለሰብ ግለሰብ ይለያያል:: እንዲሁም የወጣትነት ዘመንን መጀመሪያና መጨረሻ ለመረዳት የሚያስችል አንድ ወጥ መስፈርት የለም:: እንደየትምህርት መስኩ እና እንደየሁኔታው የተለያዩ ወጥ ያልሆኑ መስፈርቶች ይጠቀሳሉ:: ለምሳሌ አካላዊ፣ አዕምሮአዊ እና የስሜት ብስለት፣ ባህል፣ የሀገራት ህጎችና ፖሊሲዎች፣ እና ዕድሜ በተደጋጋሚ የሚጠቀሱ የወጣትነት ምንነትን ለመበየን የምንጠቀምባቸው መሥፈርቶች ናቸው:: ሆኖም ግን በአጠቃላይ የወጣትነት ዘመን የሚባለው በልጅነት እና በአዋቂነት ዘመን መካከል የሚገኝ እጅግ በጣም ፈጣን አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ሥነ-ግብራዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ እና ወሲባዊ ለውጦች ተያያዥነት ባለው ሁኔታ የሚካሔድበት ዘመን ነው:: በተለይ ደግሞ የአካላዊ፣ አዕምሯዊ እና ማህበራዊ ፈጣን ለውጦችን ተከትሎ በወጣቶች ላይ የሚታዩ አምስት ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ ለውጦች ለዕድገት ዘመኑ የተለየ ገፅታን ይሰጡታል:: ምንም እንኳ እነዚህ አምስት ለውጦች ማለትም የማንነት ጥያቄ (Identity)፣ ራስን የመቻል ፍላጎት (autonomy)፣ ከሌሎች ጋር በተለይ ከተቃራኒ ፆታ አቻዎች ጋር የመቀራረብ ፍላጎት (intimacy)፣ ወሲባዊ (sexuality), እና በትምህርት (achievement) ዙሪያ የሚታዩ ለውጦች በሌሎች የዕድሜ ዘመናትም

የሚታዩ ቢሆኑ በወጣትነት ዘመን ግን በተለየ እና ጠንከር ባለ ሁኔታ ስለሚከሰቱ ለወጣትነት ዘመን የተለየ ጣዕምና ገጽታ ያላብሱታል።

የወጣትነትን ትርጉም ለመረዳት የተለያዩ መስፈርቶች ቢኖሩም በአብዛኛው ወጣትነት የሚገለፀው ዕድሜን መሠረት ባደረገ ሁኔታ ነው። ለዚህም የተባበሩት መንግስታት ወጣትነትን ከ15-24፣ የአፍሪካ ወጣቶች ቻርተር ደግሞ ከ15-35 የዕድሜ ክልል የሚገኝ የህይወት ዘመን በማለት ያስቀምጡታል። በተመሳሳይ የኢትዮጵያ የወጣቶች ፖሊሲ ወጣትነትን ከ15-29 የዕድሜ ክልል እንደሆነ ይገልፃል። ሆኖም ግን ዕድሜን ብቻ መሠረት ያደረገ አተረጓጎም አንዳንዴ ትክክል ስለማይሆን የወጣትነት ትርጉምን በትክክል ለመረዳት ዕድሜንና ከላይ የተጠቀሱትን አካላዊ፣ ስነ-ልቦናዊና ማህበራዊ ለውጦችን ከግንዛቤ ማስገባት ያስፈልጋል።

ወጣትነት የመማሪያና የማደጊያ ዕድሜ ነው። ወጣቶች ብቁ ዜጋ የሚያደርጋቸውን ሁለንተናዊ ማለትም አካላዊ፣ አዕምሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ-ልቦናዊ ክህሎቶችን የሚማሩበትና ወደ አዋቂነት ዘመን የሚሸጋገሩበት ዕድሜ ነው። በዚህም መሠረት የወጣት ስብዕና ዕድገት ማለት ወጣቶች በዕድሜ ደረጃቸው የሚጠበቁባቸውን መሠረታዊ የዕውቀት፣ አመለካከት፣ ክህሎት እና ማህበራዊ ዕሴቶችን መማርና መላበስ ማለት ነው።

## 3. የወጣት የስብዕና ዕድገት የሚካሔድባቸው አውዶች

የወጣቶች ዕድገት በአጠቃላይ እና የስብዕና ዕድገት በተለይ ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር በእጅጉ የተቆራኘ ነው። የወጣቶችን ዕድገትና የሚላበሱትን ስብዕና ከአካባቢያቸው ገንጥሎ ለብቻው መረዳት አይቻልም። በዘርፉ ያሉ ምሁራን እንደሚያስረዱት የሰው ልጅ ዕድገት በኦና (Vacuum) ውስጥ የሚካሔድ አይደለም። ሰዎች ከሚኖሩበት ጂኦግራፊያዊ፣ ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ አካባቢ ጋር ቀጣይነት ያለውና ሁለትዮሻዊ መስተጋብር አላቸው። በዚህም የማያባራ ሁለትዮሻዊ መስተጋብር አካባቢያቸው እነርሱን፤ እነርሱ ደግሞ አካባቢያቸውን ወይም እነሱ አካባቢያቸውን አካባቢያቸው ደግሞ እነርሱን ይቀርፃል። ስለዚህም የወጣቶች ስብዕና ዕድገት የዚህ ሁለትዮሻዊ (ወጣት ↔ አካባቢ) መስተጋብር ውጤት ነው (Bronfenbrenner, 1979)።[14] በዚህም መስተጋብራዊ ሂደት ውስጥ ሦስት ነገሮችን ማስተዋል ያስፈልጋል። እነሱም፡-

[14] Bronfenbrenner, 1979


1ኛ. በወጣቶች የስብዕና ዕድገት ሂደት ውስጥ ወጣቶች እንዲሁ የአካባቢን ተፅዕኖ የሚቀበሉ ብቻ ሳይሆኑ ትርጉም ባለው መንገድ አካባቢያቸው ላይ የራሳቸውን ተፅዕኖ ወይም አሻራ በማሳረፍ የስብዕና ዕድገታቸውን ይቀርፃሉ፡፡ ይህም ማለት ወጣቶች በዕድገት ሂደታቸው የራሳቸው ንቁ ተሳትፎ ውጤቶች ናቸው ማለት ነው፡፡

2ኛ. ከሚያድጉበት አካባቢ ጋር የሚኖራቸው መስተጋብር ቢያንስ የሁለትዮሻዊ አቅጣጫ (ወጣት ↔ አካባቢ) እና በሰጥቶ መቀበል መርህ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡

3ኛ. አካባቢ ማለት በወጣቶች ዕድገት ላይ ቀጥተኛና ጠንካራ ተፅዕኖ ከሚያሳድሩ የቅርብ አካባቢዎች (immediate contexts) እስከ ሩቅ እና ቀጥተኛ ተፅዕኖ እስከሌላቸው አውዶች ማለት ነው፡፡

በአጠቃላይ የወጣቶች ስብዕና ዕድገት እጅግ ውስብስብ በሆነ እና በማያቋርጥ መስተጋብር የሚቀረፅ ሂደት ነው፡፡ በመሆኑም የወጣት ስብዕና ዕድገትን ለመረዳት ወጣቱ የሚኖርበትን ማህበራዊና ሥነ-ልቦናዊ አካባቢ መረዳት የግድ አስፈላጊ ነው፡፡ የሰውን ልጅ ባህርይና ስብዕና የሚያጠናው የሳይኮሎጂ ትምህርት ዘርፍ የሰው ልጅ የሚኖርበትንና የሚያድግበት አካባቢ በአምስት ዓውድ (Context) እንደሚከፈል ያስረዳል፡፡ እነሱም፡-

1. ማይክሮ ሲስተም (Microsystem)
2. ሜሶ ሲስተም (Mesosystem)
3. ኤክሶ ሲስተም (Exosystem)
4. ማክሮ ሲስተም (Macrosystem) እና
5. ክሮኖ ሲሰተም Chronosystem) ናቸው፡፡



**ሥዕል 1፡** የወጣቶች የስብዕና ዕድገት የሚካሄድባቸው አውዶች

ማይክሮ ሲስተም ታዳጊው ልጅ እጅግ ቅርብ የሆነና ታዳጊው ልጅ በቀጥታ የሚሳተፍበት አካባቢ ነው፡፡ በታዳጊው ልጅና በአካባቢው መካከል በጣም ጠንካራ የሆነ ቀጥተኛና የሁለትዮሽ መስተጋብር የሚኖር ሲሆን፤ አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርሰውም ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህ ሥርዓት እንደ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ ጓደኛ፣ የመጫዎች ቦታ፣ የዕምነት ተቋማት እና የመሳሰሉትን መሠረታዊ አካባቢዎች ይይዛል፡፡ ከእነዚህ ከእያንዳንዳቸው ጋር የሚኖር ቀጥተኛ የሁለትዮሽ መስተጋብር ለስብዕና ዕድገት ጉልህ የሆነ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የተቀመጠው ሜሶ ሲስተም ደግሞ በሁለትና ከዚያ በላይ ማይክሮ ሲስተሞች መስተጋብር የሚፈጠር ሆኖ ታዳጊው ልጅ ቀጥተኛ ተሳትፎ ይኖረዋል፡፡ ለምሳሌ በትምህርት ቤትና በቤተሰብ እንዲሁም በቤተሰብና በልጆች ጓደኞች መካከል የሚደረግ መስተጋብር ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ በሁለት አውዶች የሚደረግ መስተጋብር ወጣቶች በየሁኔታው የሚያሳዩትን ባህርይና ዕድገት ለመከታተል ይጠቅማል፡፡

የኤክሶ ሲስተም ግን ታዳጊው ልጅ ቀጥተኛ ተሳትፎ የማያደርግበት ነገር ግን በልጁ ላይ ተዘዋዋሪ ተፅዕኖ የሚያሳርፉ ሁኔታዎችን ያካትታል፡፡ ለምሳሌ የወላጆች ሥራ ቦታ ላይ የሚከሰቱ የሥራ ዕድገቶች ወይም ዝውውሮች፣ የወላጆች ጓደኞች፣ ተፅዕኖ ይጠቀሳል፡፡ አራተኛው አውድ እና ለታዳጊው ልጅ ራቅ ያለ እና ቀጥተኛ ተፅዕኖ የሌለው ነገር ግን በአዳጊው ልጅ ላይ የራሱን ተፅዕኖ የሚያሳድር አውድ ማክሮ ሲስተም ይሰኛል፡፡ ማክሮ ሲስተም በሀገር ደረጃ ያሉ ሰፋ ያሉ ነገሮችን (ለምሳሌ እንደ ፖሊሲ እና ባህል ያሉ ሁኔታዎችን) ይይዛል፡፡ በመጨረሻም ክሮኖ ሲስተም በታሪካዊ የጊዜ ሒደት የሚከሰቱ ለውጦችን ለምሳሌ የትምህርት ሥርዓት ለውጥ፣ አዳዲስ የቴክኖሎጅ ውጤቶች፣ የኢኮኖሚ ዕድገት ወይም ድቀት እና የመሳሰሉትን የሚያካትትና በትውልዶች መካከል ልዩነት የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን ያጠቃልላል፡፡ በአጠቃላይ የወጣቶች ስብዕና ዕድገት በታዳጊው ወጣት ንቁ ተሳትፎ እና ከላይ በተጠቀሱት የቅርብም ሆነ የሩቅ አካባቢዎች ጠንካራ መስተጋብር ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም የወጣቶችን ስብዕናም ሆነ ሁለንተናዊ ዕድገት ለመረዳት አካባቢን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል፡፡

## 4. የወጣት ስብዕና ዕድገት አዎንታዊ መገለጫዎች

በወጣቶች ጥናት መስክ ለረጅም ጊዜ በሰፊው ተንሰራፍቶ የነበረው እና እስካሁንም ሙሉ በሙሉ ያልከሰመው ወጣቶችን የምንረዳበት እና የምናጠናበት ንድፈ ሀሳባዊ እይታ በችግር ወይም በጉድለት (deficit-based) ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ እይታ

ሁልጊዜም የሚያተኩረው የወጣቶች ችግሮች ላይ ነው፡፡ ጠንከር ሲልም ወጣቶች ራሳቸው ችግሮች እና ዕዳዎች (liabilities) እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ ይህ እይታ ወጣቶች ሁልጊዜም ለችግር ቅርብ የሆኑ አስቸጋሪዎች፣ አመፀኞች እና በጥንቃቄ መታየት ያለባቸው የህብረተሰብ ክፍሎች እንደሆኑ ያስረዳል፡፡

ነገር ግን እ.ኤ.አ. ከ1980ዎቹ ጀምሮ ጎላ ብሎ የመጣው ዕይታ ወጣቶችን እንደ ችግር ሳይሆን እንደ ብርቅዬ ሀብት የሚቆጥርና ከችግራቸው ይልቅ ያላቸውን እምቅ ሀብትና ጥንካሬ ፈልፍሎ በማውጣት ማጠናከርና ማበልፀግ ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ ይህ እይታ በጥንካሬ ላይ የተመሠረተ (Strengths-based) ሲሆን ትርጉሙም አዎንታዊ የወጣቶች ዕድገት/ልማት እይታ (Positive Youth Development, PYD) በመባል ይታወቃል፡፡ የወጣቶችን ችግሮች ከመንቀስ እና ወጣቶችን ሙሉ በሙሉ ከችግሮች አንፃር ከማየት ይልቅ ያላቸውን ሀብት ማጎልበት ላይ መሥራት አዋጭ እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ችግር ላይ የምናተኩር ከሆነ መጀመሪያችንም መጨረሻችንም ችግር እንደሚሆን፤ ነገር ግን ጥንካሬ ላይ የምናተኩር ከሆነ ችግር እየቀጨጨ ጥንካሬ ግን የበለጠ እየዳበረ እንደሚሔድ ያስረዳል፡፡

በአወንታዊ የወጣቶች ዕድገት ዕይታ መሠረት የወጣቶች መልካም የስብዕና ዕድገት የሚገለፅባቸው የተለያዩ ንዑሳን እይታዎች አሉ፡፡ አንደኛውና በሰፊው የሚታወቀው የአምስቱ “መ” ዎች (The Five ‘C’s) ዕይታ ነው (Lerner et al 2005)፡፡ እነዚህ የአዎንታዊ ስብዕና ዕድገት መገለጫዎች በተለያዩ ሁኔታዎችና ሀገራት ወጣቶች ላይ በተሰሩ ጥናቶች ተፈትሸው ተቀባይነትን ያገኙ ናቸው፡፡ በአፍሪካም በብዙ ሀገራት ወጣቶች ላይ ተሞክረው ተቀባይነትን አግኝተዋል፡፡ በዚህ መሠረት አምስቱን አዎንታዊ የስብዕና ዕድገት መገለጫዎች የተላበሰ ወጣት ማለትም መብቃት (Competence)፣ መተማመን (Confidence)፤ መገናኘት (Connection)፤ መንከባከብ (Caring) እና ምግባራዊነት (Character) ሌላ ስድስተኛ መገለጫ ማለትም አስተዋፅኦ ማድረግ (Contribution) ይላበሳል ይባላል፡፡ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ሌሎች የወጣት አጥኝዎች ሁለት ተጨማሪ መገለጫዎችን ጨምረው በአጠቃላይ የአወንታዊ የወጣት ስብዕና ዕድገት መገለጫዎች ስምንት ደርሰዋል፡፡ አጠር ባለ መልኩ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ብቃት (Competence)፡- አንድ ወጣት የሚጠበቅበትን የትምህርት፣ ማህበራዊና ሙያዊ ክህሎት በተሟላና አጠናቅቆ መያዝን እና ሙያዊ ተግባሩን በተሟላ እና በቅልጥፍና ማከወንን ያካትታል፡፡
- መተማመን (Confidence)፡- አንድ ወጣት በራሱ ነገሮችን የማድረግ ችሎታ ላይ የሚኖረውን ውስጣዊ ዕምነት፣ ለራሱ የሚሰጠውን አዎንታዊ ግምትና

ፍቱንነት (efficacy) እና በወደፊት ሁኔታ ላይ ዕምነት ማሳደርን የሚያካትት ክህሎት ነው፡፡

- ❖ ግንኙነት (Connection)፡- ይህ ደግሞ አንድ ወጣት ከሌሎች ሰዎችና ተቋማት ለምሳሌ ጓደኛ፣ ቤተሰብ፣ ት/ቤት፣ ማህበረሰብ የሚኖረውን አዎንታዊና ጠንካራ ትስስርና ቁርኝት ያካትታል፡፡
- ❖ መንከባከብ (Caring)፡- አንድ ወጣት ለሌሎች ሰዎች፣ ተቋማት፣ ማህበራዊ ዕሴቶችና ህጎች የሚያሳየው ተቆርቋሪነት፣ አሳቢነትና እንክብካቤን ያካትታል፡፡
- ❖ ሥነ-ምግባራዊነት (Character)፡- መልካሙን ከመጥፎው የመለየትና የመያዝ፣ የማህበረሰቡን ባህልና ወግ ማክበር፣ በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን ባህርያት መላበስ፣ መንፈሳዊነትን (Spirituality) መላበስ፣ ሀቀኛ መሆንን እና የመሳሰሉትን የስብዕና ገፅታዎች ያካትታል፡፡
- ❖ አስተዋፅኦ ማድረግ (Contribution) - አንድ ወጣት ራሱንና ማህበረሰቡን ለማሳደግ የሚያደርገውን ጥረት፣ በማህበረሰቡ ዘንድ የሚያደርገውን ንቁ ተሳትፎና አመራር እና በአካባቢው ዘንድ ልዩነት ለመፍጠር የሚያደርገውን ትጋት ያካትታል፡፡
- ❖ መቋቋም (Coping)፡- ይህ ደግሞ አንድ ወጣት የሚገጥሙትን የህይወት ውጣ ውረዶች ጭንቀትና ውጥረት በብቃት መቋቋምን እና አልበገር ባይ የመሆን ችሎታን ያካትታል፡፡
- ❖ መቆጣጠር (Control)፡- አንድ ወጣት የሚያደርጋቸውን ድርጊቶችና የሚወስዳቸውን ውሳኔዎች መረዳትና በህይወቱ ላይ የሚያስከትሉትን ተፅዕኖ መገንዘብ መቻልን ያካትታል፡፡

## 5. ወጣትና ትምህርት

ወጣትነት የፈጣን ዕድገት ዘመን ነው፡፡ ወጣትነት ለቀጣዩ የአዋቂነት የዕድገት ዘመን የመዘጋጃ ዕድሜም ነው፡፡ በርካታ የወጣቶችን ባህርይና የስብእና ዕድገት የሚያጠኑ ምሁራን እንደሚገልፁት ወጣትነት የመማሪያ፣ አዳዲስ ነገሮችን የመሞከሪያ፣ በአካላዊም ሆነ በአዕምሯዊ ብስለት እና ዝግጁነት ለትምህርት ምቹ ሁኔታ የሚፈጠርበት የዕድሜ ዘመን ነው፡፡ በትምህርት ገበታ ላይ ያሉ ወጣቶች ከመኝታ ሰዓታቸው ውጭ ያለውን ረዥም ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት በትምህርት ቤት ውስጥ

ነው። ከሌላው የዕድገት ዘመን በተለየ መማር ጠንከር ባለ ሁኔታ የሚካሔደው በወጣትነት ዘመን ነው።

ስለዚህ ትምህርት ለወጣቶች አሁን ላሉበት የወጣትነት ዕድሜም ሆነ ለመጪው የአዋቂነት ዘመን አስፈላጊ የሆኑ ዕውቀት፣ አመለካከትና ክህሎት የሚያገኙበት ሒደት ነው። የትምህርት ዋና ዓላማ ወጣቶች ሁለንተናዊ በሆነ መንገድ ማለትም በዕውቀት፣ በአመለካከትና በክህሎት ብቁ እንዲሆኑ ማድረግ ነው። ስለዚህ በጥሩ ሁኔታ እና በጥንቃቄ የሚሰጥ ትምህርት ወጣቶችን ለማንበብ፣ ለመፃፍ እና ለማስላት ብቻ ማዘጋጀት ሳይሆን ወጣቶች አዎንታዊ አመለካከት እንዲላበሱ፣ ለራሳቸውም ሆነ ለሌሎች አሳቢና ተቆርቋሪ እንዲሆኑ፣ ብዝሀነትንና ልዩነትን አክባሪና አድናቂ እንዲሆኑ፣ በክህሎት ረገድም ተለምዷዊ አሠራሮችን በዘመናዊና በተሻሻለ አሠራር መተካት እንዲችሉ እና ሥራ ፈጣሪዎች እንዲሆኑ ያስችላል። ይህ ሲሆን የተማረ ወጣት የአንድ ሀገር መሠረት፣ ሀብትና ኩራት ይሆናል። በመደበኛው የትምህርት ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን ላልቻሉ ወጣቶችና ጎልማሶችም ከኑሯቸው ጋር የተዛመደ ተግባር-ተኮር እና የተቀናጀ ትምህርት ማዘጋጀት ለወጣቶች የኑሮ መሻሻልና ለሀገር ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አብዛኛው ወጣቶች የሁለተኛ እና የከፍተኛ ትምህርት ዕድል በማያገኙበት ሁኔታ ተግባር-ተኮር እና ከህይወት ጋር የተቀናጀ የወጣቶችና የጎልማሶች ትምህርት ለሀገር ከፍተኛ ትርጉም አለው።

ትምህርት የሀገር ዕድገት መሠረት ነው የሚባለው በወጣቶች ላይ በሚፈጥረው በጎ ተፅዕኖ ሳቢያ ነው። በተለይ በአሁኑ ዘመን የትምህርት ሚና ወጣቶችን አሁን ላሉበት ዘመን ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ዘመን ተሻጋሪ ዕውቀት፣ ፈጠራ፣ ዘመናዊ አስተሳሰብ፣ የመሪነትና ልዩነትን አክባሪነት የባህሪ ገፅታዎችን እንዲላበሱ ማስቻል ነው። በአጠቃላይ ትምህርት ለወጣቶች አዎንታዊ የስብዕና ዕድገት ማለትም ለአዕምሯዊ ብቃትና ፈጠራ በራስ መተማመን፣ ሥነ-ምግባራዊ እና የመልካም ግንኙነት ባህሪያትን ለመላበስ፣ ለራስም ሆነ ለሌሎች አስተዋፅዖ ለማድረግ፣ ዕለታዊ ችግሮችን ለመቋቋምና ህይወትን በአግባቡ ለመምራት የሚያስችሉ ክህሎቶችን ከምናዳብርባቸው ወሳኝ አውዶች (Contexts) መካከል አንዱ ነው።

## 6. ትምህርት በድህረ 1983 ዓ.ም. ኢትዮጵያ- መሠረታዊ ነጥቦች

ኢትዮጵያ ረዥም የትምህርት ታሪክ ያላት ሀገር ናት። በተለይ ደግሞ ሀይማኖታዊ ትምህርት ከረዥም ዓመታት በፊት በቤተ-ክርስትያናትና በመስጅድ ይሰጥ እንደነበር ይታወቃል። እንዲሁም የምዕራባዊያን ትምህርት ወይም በተለምዶ ‹‹ዘመናዊ›› ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ከአንድ ክፍለ-ዘመን በላይ አስቆጥሯል። በዚህ

ታሪካዊ ሒደትም የመንግስታትን ፖለቲካዊ ፍላጎት ተከትሎ የተለያዩ የትምህርት ሥርዓቶች ተቀርፀው ተተግብረዋል፡፡ ነገር ግን እነዚህ በተለያየ ዘመን የተተገበሩት የትምህርት ሥርዓቶች በአጠቃላይ ለሀገር ዕድገትና በወጣት አዎንታዊ የስብዕና ዕድገት ላይ ያመጡት ተፅዕኖ በጥናት በሚገባ ተፈትሾ አልተሰናዳም፡፡ የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ በድህረ 1983 ዓ.ም. ይሰጥ የነበረው የትምህርት ሥርዓት የሀገሪቱን ወጣቶች የስብዕና ዕድገት ከመቅረፅ አንፃር የነበረውን አስተዋፅዖ መፈተሽ ነው፡፡

## 6.1. የ1983 ዓ.ም. የመንግስት ለውጥን ተከትሎ የመጣው የትምህርት ሥርዓት ለውጥ

ፖለቲካ እና ትምህርት የሚነጣጠሉ ነገሮች አይደሉም፡፡ በበርካታ የዓለማችን ሀገራት እንደሚታየው የፖለቲካ የስልጣን ሽግግር መደረግን ተከትሎ የትምህርት ሥርዓት ለውጥ ይካሔዳል፡፡ እንደዚህ አይነት ሁኔታ በተለይ በደንብ ያላደገና የጠና የመንግስትና የዴሞክራሲ ባህል ባለባቸው ሀገራት ይከሰታል፡፡ የአንድ ሀገር የፖለቲካ ርዕዮትና ሥርዓት የሀገሪቱን የትምህርት ግብ ይወስናል፡፡ መንግስታት የትምህርት ሥርዓት የሚነድፉት የፖለቲካ አስተሳሰባቸውን እና መርሀ-ግብራቸውን ለመተግበር በሚያስችል መልኩ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ታሪክ እንኳን በምናይበት ጊዜ በዘውዳዊው ሥርዓት የነበረው የትምህርት ዋና ዓላማ ለስርዓቱ ታማኝ የሆነ ዜጋንና በሥርዓቱ በተከፈቱ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች የሚሠራ የሰው ኃይል ማፍራት ነበር፡፡ በደርግ ወቅት ይሰጥ የነበረው የትምህርት ሥርዓት ዓላማ ደግሞ በሶሻሊስት ርዕዮት የበለፀጉ ዜጎችን ማፍራት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በአጠቃላይ የአንድ ሀገር የትምህርት ሥርዓት ዋነኛው ምንጭ የፖለቲካ ሥርዓቱ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ የትምህርቱን ሥርዓት ጠንቅቆ ለመረዳት የፖለቲካዊ ስሪቱን ማወቅ የግድ ይላል፡፡

በኢትዮጵያ የመንግስት ታሪክ ውስጥ ለ17 ዓመታት የትጥቅ ትግል ሲያካሔድ የቆየው አንጃ በግንቦት 1983 ዓ.ም. የወታደራዊውን የደርግ መንግስት አስወግዶ ስልጣን ያዘ፡፡ አዲሱ መንግስትም በሐምሌ 1983 ዓ.ም. ለዘር ተኮር የፌደራሊዝም ሥርዓት መሠረት የጣለ የሽግግር መንግስት አቋቋመ፡፡ በታህሳስ ወር 1983 ዓ.ም. ሕገ-መንግስት አፀደቀ፡፡ በፀደቀው ህገ-መንግስትም የብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ሥርዓት የመንግስት ዋነኛ የፖለቲካ ርዕዮት እንደሆነ ታወጀ፡፡ ይህ ኢትዮጵያን ቀደም ሲል ባልታየ መልኩ በዘውግ ሥርዓት የመሥራት ሁኔታ የትምህርት ሥርዓቱን አቅጣጫ መሠረታዊ በሆነ መንገድ እንዲለወጥ አድርጎታል፡፡ ለዚህም ማስፈፀሚያ እንዲሆን በሚያዚያ 1987 ዓ.ም. አዲስ የትምህርት ፖሊሲ ተነድፎ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ በፖሊሲው በግልፅ እንደተገለፀው የትምህርት ሥርዓቱ ዋና

ዓላማ ከቀድሞው ሥርዓት የተወረሱትን አምስት ቁልፍ የትምህርት ችግሮች መፍታት ነበር። እነሱም፦

1. እጅግ ውስን የሆነውን የትምህርት ተደራሽነት ማሻሻል፤
2. ፍትሀዊ ያልሆነውን የትምህርት አገልግሎት ስርጭት ማሻሻል፤
3. የትምህርት ሥርዓቱን ውስጣዊና ውጫዊ ብቃት ማሻሻል፤
4. የትምህርት ጥራትና ተገቢነትን ማሻሻል እና
5. ዴሞክራሲያዊ ያልሆነውን የትምህርት ይዘት መለወጥ ናቸው።

እነዚህን ችግሮች ለማሻሻል መንግስት የተለያዩ ሥልታዊ ግቦችን ለምሳሌ የትምህርት ዘርፍ ልማት ፕሮግራም 1 (ESDP I) በ1989/90 ዓ. ም.፣ የአጠቃላይ ትምህርት ጥራት ማሻሻያ ፕሮግራም (GEQIP I) በ2001 ዓ. ም. እና ሌሎችንም መመሪያዎች አውጥቶ ነበር። እንዲሁም የትምህርት ፖሊሲው ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ሦስት ነገሮችን በመለየት ወደ ትግበራ ገባ። እነሱም፦

1ኛ. የሥርዓተ ትምህርት ለውጥ - በዚህ የትኩረት ነጥብ ውስጥ የመማሪያ ቋንቋ፣ የሲቪክስ ትምህርት፣ የልጃገረዶች ትምህርትና የትምህርት ምዘናና ግምገማ ቅድሚያ የተሰጣቸው ጉዳዮች ነበሩ።

2ኛ. የመምህራንን ችሎታና ብቃት ማሻሻል፤

3ኛ. የትምህርት አደረጃጀቱን እና መዋቅሩን ያልተማከለ (Decentralized) ማድረግ የሚሉት ናቸው።

## 6.2. የድህረ 1983 ዓ.ም. የትምህርት ሥርዓት ስኬቶች

### *ተደራሽነት*

የተለያዩ ጥናቶችና የፖሊሲ ትግበራ ፍተሻ ውጤቶች እንደሚያሳዩት በኢህአዴግ ዘመን የነበረው የትምህርት ሥርዓት በርካታ ለውጦችን አምጥቷል። ጎልተው ከሚጠቀሱ ስኬቶች አንዱ የትምህርት መስፋፋትና መዳረስ ነው። የኢህአዴግ መንግስት ስልጣን በያዘበት ወቅት ዕድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ህፃናት መካከል የመማር ዕድል ያገኙት ከ20% በታች ያህሉ ብቻ ነበሩ። የሁለተኛ ደረጃ እና የከፍተኛ ትምህርት አቅርቦትም በቅደም ተከተል ከ10 በመቶ እና ከአንድ በመቶ በታች ነበር። ይህ የትምህርት ተደራሽነት ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት አንፃር እንኳን ሲታይ እጅግ ዝቅተኛው ነበር። በተለይ ደግሞ የቴክኒክና ሙያ ስልጠና እጅግ በጣም ውስን እና እዚህ ግባ የማይባል ደረጃ ላይ ነበር።

ነገር ግን በተነደፈው ፖሊሲ እና እሱን ተከትለው በወጡ ማስፈጸሚያ ስልቶችና መመሪያዎች መሠረት የትምህርት ተደራሽነት በከፍተኛ ደረጃ ተሻሽሏል። በተለይ

የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለማዳረስ በነበራው ጠንካራ የተጠያቂነት ሥርዓት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከፍተኛ ዕመርታ አሳይቷል። በተመሳሳይ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናና የከፍተኛ ትምህርት መስፋፋትም ቀድሞ ከነበረበት ሁኔታ አንፃር ሲታይ እጅግ በጣም በከፍተኛ ፍጥነት አድጓል። በአጠቃላይ የትምህርት ተደራሽነት ዕድገት ከድህረ-1983 የትምህርት ስርዐት ስኬቶች መካከል በዋናነት የሚጠቀሰው ነው።

### *የአፍ መፍቻ ቋንቋ*

ሌላው የትምህርት ሥርዓቱ እንደ ትልቅ ስኬት የሚነሳው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ትምህርት ማስጀመር ነው። ልጆች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መማራቸው የትምህርት አቀባበላቸውንና ውጤታቸውን ከመጨመሩ ባሻገር በራሳቸው ማንነት እንዲኮሩ ያደርጋቸዋል። ምንም እንኳ ከሰው ኃይልና ቁሳቁስ አንፃር በቂ ዝግጅት ሳይደረግ በድንገት ወደተግባር ቢገባም ከስምንት በላይ በሚደርሱ ቋንቋዎች ማስተማር መጀመሩ በራሱ ይበል የሚያሰኝ ነበር። በአሁኑ ወቅት በየክልሉ በሚገኙ በርካታ ቋንቋዎች ህፃናት በራሳቸው ቋንቋ በመማር ላይ ይገኛሉ። ይህም የሥርዓቱ አንድ ጉልህ ስኬት ተደርጎ ይወሰዳል።

### *ፍትሀዊነት*

ሌላው የድህረ 1983 ዓ. ም. የትምህርት ሥርዓት ያስመዘገበው ለውጥ ከፍትሀዊነት ጋር የተያያዘ ነው። ምንም እንኳ እስካሁን ድረስ ችግሮች ቢኖሩም በወንድና በሴት እንዲሁም በገጠርና በከተማ ተማሪዎች መካከል ያለው ልዩነት እየጠበበ መጥቷል። በተመሳሳይም አካል ጉዳተኞች ከበፊቱ እጅግ የተሻለ የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ተደርጓል። ይህም ትምህርት ተደራሽ እንዲሆን ከማስቻሉ በተጨማሪ ፍትሀዊነቱ እንደተሻሻለ ያሳያል።

### *መማር-ማስተማር*

የባለፈው የትምህርት ሥርዓት ከመማር ማስተማር ሒደት ጋር በተያያዘ ያመጣቸው አዎንታዊ ለውጦች አሉት። ከእነዚህም መካከል ተማሪ-ተኮር የመማርና ማስተማር ሥነ-ዘዴን እና የተከታታይ ምዘናን (በተለይ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ) በመተግበር አበረታች ውጤቶች ታይተዋል።

### *የፖሊሲ መሣሪያዎች*

ከላይ ከተጠቀሱት ጠንካራ ጎኖች በተጨማሪ የድህረ-1983 ዓ.ም. የትምህርት ሥርዓት በጎ ለውጦች ከሚባሉት መካከል የትምህርቱን ሥራ የሚያቀላጥፉና የሚያበረታቱ የፖሊሲ መሣሪያዎች፣ ስልታዊ ሠነዶችና መመሪያዎች ማውጣቱ

ነው። ከነዚህም መካከል የአጠቃላይ ትምህርት የጥራት ማሻሻያ መርሀግብር፣ የትምህርት ዘርፍ ልማት መርሀ-ግብር፣ የአማራጭ መሠረታዊ ትምህርት መመሪያ፣ የአርብቶ አደርና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ስልት፣ የልዩ ፍላጎትና አካቶ ትምህርት ስልት፣ የቅድመ መደበኛ ትምህርት ፖሊሲና ስልት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልት እና የብሔራዊ የትምህርት ቤት ጤናና ምግብ ስልት የሚጠቀሱ ናቸው። እንዲሁም የትምህርት ሥርዓቱ የተለያዩ ዓለም አቀፋዊ ህጎችንና ስልቶችን (ለምሳሌ እንደ ትምህርት ለሁሉም እና የዘላቂ የልማት ግቦች) ጋር ራሱን አጣጥሞ መሔዱ በራሱ እንደ አንድ ጠንካራ ጎን ይወሰዳል።

## 6.3. የድህረ 1983 ዓ.ም. የትምህርት ሥርዓት ጉልህ ጉድለቶች

ጤናማ የትምህርት ሥርዓት የማህበረሰቡን አጠቃላይ ሁኔታና ፍላጎት መሠረት አድርጎ የሚነደፍ ነው። የድህረ-1983ቱ ትምህርት ሥርዓት አነሳስ ግን ሀገሪቱ በረጅም ታሪኳ የገነባችውን የኢትዮጵያዊነት እና የአንድነት ዕሴት በሚፃረር መልኩ የተቀረፀ ነው። በመሆኑም የዚህ ትምህርት ሥርዓት መሠረታዊ ችግር የሚጀምረው የትምህርት ፖሊሲው መነሻ ከሆነው የሀገሪቱ መንግስት ከሚመራበት የዘር ተኮር ፌደራሲዝም ፖለቲካዊ ሥርዓት ነው። ምንም እንኳን ፌደራሊዝም በዓለም የሀገራት የፖለቲካ ሥርዓትና አመራር የተፈተነ መንገድ ቢሆንም በዘውግ ላይ የተመሠረተ፣ የሀገርን ዜጋ ብሔር፣ ብሔረሰብ እና ህዝብ ብሎ በደረጃ ባስቀመጠ እና በተበዳይነትና በታችነት ስሜት ላይ በተመሠረተ የፖለቲካ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ የትምህርት ሥርዓት መሆኑ ነው። በእዚህ ዓይነት መነሻ የሚጠነሰስና የሚተገበር የትምህርት ሥርዓት ውጤት የዚሁ ነፀብራቅ ይሆናል። በኢትዮጵያ ከትምህርት ፖሊሲው የሦስት አሥርት ዓመታት ትግባራ በኋላ የሚታየው ሀገራዊ ሁኔታ በከፊል የዚህ ትምህርት ሥርዓት ውጤት ነው ማለት ያስደፍራል። ቀጥሎ የተዘረዘሩት የትምህርት ሥርዓቱ መሠረታዊ ችግር መገለጫውች (Symptoms) ከላይ ከተጠቀሰው ዋነኛ ችግር የመነጩ ናቸው።

### ተደራሽነትና ፍትሀዊነት

ምንም እንኳ የትምህርት ተደራሽነትና ፍትሀዊነት የድህረ-1983 ዓ.ም. ትምህርት ሥርዓት ዐበይት ጠንካራ ጎኖች ተደርገው ቢጠቀሱም፤ እስከ አሁንም ቢሆን የተደራሽነትና ፍትሀዊነት ችግር ሙሉ በሙሉ አልተፈታም። ለምሳሌ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ከተማዎችን ጨምሮ አሁንም ችግር እንደሆነ የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ የሚያወጣቸው ሪፖርቶች ያስረዳሉ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት አቅርቦት በተለይ ወደ ዝቅተኛ-መካከለኛ (lower-middle income) የገቢ ደረጃ እንገባለን ለሚሉት ሀገራት ከተቀመጠው መሠፈርት አንፃር

ሲታይ ኢትዮጵያ ገና ብዙ የሚቀራት ሀገር እንደሆነች ይታወቃል። ትምህርትን ለዜጎች በፍትሀዊነትና በዕኩልነት ለማዳረስ የሚደረገው ጥረት አበረታች ቢሆንም እስካሁንም ድረስ ቢሆን በከተማና በገጠር፣ በሀብታምና በደሀ ልጆች መካከል ያለው ልዩነት አሳሳቢ ነው።

## ብቃት

የድህረ 1983ቱ የትምህርት ሥርዓት ሌላ ጉልህ ችግር የብቃት (Efficiency) ችግር ነው። አንዱ የትምህርት ብቃት አመላካች ከሆነው ከግብዓትና ሒደት ጋር የተያያዘውን ሁኔታ በምናጤንበት ጊዜ የተማሪዎች በትምህርት ገበታ ያለመገኘት፣ ማቋረጥ፣ ክፍል መድገም ወይንም መውደቅ፣ የመማር ማስተማር ጊዜ ብክነት እና የተማሪዎችና የመምህራን ትጋት ማነስ ዋነኛ የትምህርት ሥርዓቱ የብቃት ችግር መገለጫዎች ናቸው። በሌላው የብቃት አመላካች ማለትም በተማሪዎች ውጤት፣ በተመራቂዎች ሥራ ፈጣሪነትና የቅጥር ምጣኔ አንፃር ሲታይም የትምህርት ሥርዓቱ ከፍተኛ የብቃት ችግር እንደነበረበት ይናገራል።

## የተጓዳኝ ትምህርት

የዚህ የትምህርት ሥርዓት አንዱ ጉድለት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚማሩትን የቀለም ትምህርት የሚደግፍና ለተማሪዎች የአመራር፣ ፈጠራ፣ ተግባቦት፣ እና ሁለንተናዊ ስብዕና ዕድገት አስተዋፅኦ የሚያደርገው የተጓዳኝ /Co-curriculor/ እና የተጨማሪ ትምህርት (extra curricular) ፕሮግራሞች፣ የተማሪዎች ክበቦች ያለመጠናከርና መጥፋት ነው። ይህም ሁኔታ ከታች ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ የዘለቀ መሠረታዊ ችግር ነው። የቀለም ትምህርት ብቻውን ወጣቶችን ብቁ ዜጋ ማድረግ እንደማይቻል ዕሙን ነው። ነገር ግን የድህረ 1983ቱ የትምህርት ሥርዓት ወጣት ተማሪዎች በክበቦች እየተደራጁ ራሳቸውን የሚገልፁበትና የሚያበቁበት ዕድል አይሰጥም ነበር። ይህም የትምህርት ሥርዓቱ የተሟላ እንዳይሆን አድርጎታል።

## ጥራትና ተገቢነት

የትምህርት ጥራትና ተገቢነት ችግሮች የድህረ-1983ቱ የትምህርት ሥርዓት ቁልፍ ችግሮች ናቸው። የትምህርት ጥራት ችግር ከሚገለፅባቸው ነገሮች አንዱ ተማሪዎች በየደረጃው የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት ያለማሟላታቸው ነው። ይህም ለምሳሌ በርካታ 4ኛ ክፍልን ያጠናቀቁ ያውም በአፍ መፍቻ ቋንቋ የተማሩ ተማሪዎች በተማሩበት የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንኳን በሚገባ ማንበብና መፃፍ ያለመቻላቸው ነው። ይህ ችግር በቅብብሎሽ ወደ ሁለተኛ ደረጃ እና ከፍተኛ

ትምህርት ተመራቂ ተማሪዎች ላይ ይደርሳል:: የተለያዩ ጥናቶች እንዳሳዩት የ10ኛ እና 12ኛ ክፍልን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎችም ወይ በቀለም ትምህርቱ በጥሩ ሁኔታ ለመቀጠል ወይም ደግሞ ከደረጃቸው ጋር ተመጣጣኝ ወደ ሆነ የሥራ ዓለም ለመግባት ተፈላጊውን ብቃት ያለማሟላታቸው ነው::

ሌሎች የትምህርት ጥራት ችግሮችን ከሚያመላክቱ ጉዳዮች መካከል በመማር ማስተማሩ ሂደት ተማሪዎችና መምህራን ትርጉም ያለው ተሳትፎና ትጋት አለማሳየታቸው ነው:: በየደረጃው ያሉ ተማሪዎች የራሳቸውን የመማር ሒደት በባለቤትነት ወስደውና ኃላፊነት እንዳለባቸው ተረድተው በትምህርቱ ሒደት ያላቸው ተሳትፎ (engagement) እጅግ ዝቅተኛ ነው:: ይህም በተለያየ ደረጃና ሁኔታ ተማሪዎች በሚያሳዩት ዝቅተኛ ውጤት ይገልፃል:: በተመሳሳይም መምህራን በተመረቁበት ደረጃ እንዲያስተምሩ ሲመደቡ በግልፅ ከፍተኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ ማስተማር አልችልም ወደ ዝቅተኛ ክፍል መድቡኝ ማለት በየትምህርት ቤቶች የተለመደ ነገር ሆኗል:: እንዲሁም በቂ ያልሆኑ የትምህርት ግብዓቶች፣ መሠረተ ልማቶች፣ እና ቁሳቁሶች የኢትዮጵያን የትምህርት ጥራት ከቀነሱት ነገሮች መካከል ይጠቀሳሉ:: ከቅድመ መደበኛ እስከ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያለው የመማር-ማስተማር መሣሪያዎች ዕጥረት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ተማሪዎች ያለበቂ የተግባር ትምህርት ክፍል በመቁጠር ብቻ ያልፋሉ:: በእርግጥ የኢትዮጵያ የትምህርት ጥራት ችግር ከመንግስት መንግስት በቅብብሎሽ የቀጠለና መሠረቱም ሀገራዊ የሆነውን የካበተ የትምህርት ሥርዓት መሠረት ካለማደረግ ይጀምራል::

ሌላው ከትምህርት ጥራት ጋር አብሮ የሚነሳው የተገቢነት ጉዳይ ነው:: የኢትዮጵያን የትምህርት ሥርዓት በአጠቃላይ የፈተሹ ጥናቶች የሚያሳዩት የኢትዮጵያ ትምህርት የተውሶ እና ከአገሬው ወግና ባህል የተጣላ ከፍም ሲል የሚንቅ እና ወጣቶችን ሌላ ዓለም ናፋቂ አንዲሆኑ የሚያዘጋጅ ነው ይላሉ:: ከዚህም በተጨማሪ የኢትዮጵያ ትምህርት እጅግ በጣም ቀለም ተኮር፣ ከባድ፣ በይዘት የታጨቀና በብዙ አላስፈላጊ ነገሮች የተሞላ ነው:: ለምሳሌ በ2013 እ.ኤ.አ. በዓለም ባንክ የተጠናው የኢትዮጵያ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ግምገማ እንደሚያሳየው በተለይ የሳይንስ ትምህርቶች ከሌሎች ሀገራት ሥርዓተ-ትምህርቶች ጋር ሲነፃፀር አስቸጋሪና ከልጆች የመረዳት አቅም ጋር የማይጣጣም፣ በብዙ ይዘቶች የተሞላ፣ በርካታ የትምህርት ዓይነቶችን በቂ ባልሆነ የክፍለ ጊዜ ምደባ የያዘ እና ከዘመኑ ጋር የማይሔድ እንደሆነ ያስረዳል:: ይህ ጥናት እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ በ9ኛ እና 10ኛ ክፍሎች ይሰጥ የነበረው የአጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በበርካታ ሌሎች ሀገራት በ11ኛ እና 12ኛ ክፍል የሚሰጠው ነው::

ሌላው የድህረ-1983ቱን የትምህርት ሥርዓት ተገቢነት ጉድለት የሚያሳየው ነጥብ ሥርዓተ ትምህርቱ በዓለም እየተካሔደ ካለው ፈጣን የሳይንስና ቴክኖሎጅ ለውጥ ጋር ዕኩል ራሱን አብሮ የማያሻሽል መሆኑ ነው:: የትምህርቱ ይዘት በአብዛኛው ተለምዷዊ ነገሮች ላይ ያተኮረ እንጅ ወጣቶችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች የሚያዘጋጅ አልነበረም:: በአጠቃላይ የድህረ-1983ቱ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት በሁሉም ደረጃ ትምህርትን ተደራሽ ለማድረግ የነበረው ጥረትና ስኬት ምስጋና ቢያስገኝለትም፤ በተገቢነት፣ ጥራትና፣ ብቃት መሥፈርቶች ግን ብዙ ነቀፌታዎች አሉበት::

## 7. የድህረ 1983 ዓ.ም. የትምህርት ሥርዓትና የወጣቶች ስብዕና ግንባታ

የድህረ 1983 ዓ.ም. የትምህርት ሥርዓት ከተደራሽነት አንፃር ጉልህ ስኬቶች ቢኖሩትም በብዙ ውጣ ውረዶች እና በበርካታ ችግሮች የተተበተበ ነበር:: በዚህም ምክንያት የትምህርት ሥርዓቱ በወጣቶች የስብዕና ዕድገትና ግንባታ ሂደት ላይ አዎንታዊም አሉታዊም ሚና ነበረው:: በእርግጥ የወጣቶች የስብዕና ዕድገትና ግንባታ የበርካታ ውስብስብ ነገሮችና ሒደቶች ውጤት ነው:: ትምህርት ከነዚህ ነገሮች መካከል አንዱ ግን ትልቅ ሚና ያለው ነው::

በወጣቶች ስብዕና ዕድገት እና በትምህርት መካከል የአንድ ለአንድ ቁርኝት መፍጠር አዳጋች ቢሆንም የትምህርት ሥርዓቱ ከተቀረፀበት መሠረታዊ መነሻ እና አውድ፣ ከነበረው አጠቃላይ ዓላማ ወይም ምን አይነት ወጣቶችን ለማፍራት አልሞ እንደነበረ፣ ከሥርዓተ ትምህርቱ አደረጃጀትና ይዘቶች፣ ከመማር ማስተማርና ከተማሪዎች ግምገማ ሂደት፣ ለተማሪዎች ከቀለም ትምህርቱ ባሻገር ሌሎች ወሳኝ ክህሎቶችን ለማዳበር ይሰጥ ከነበረው ዕድል፣ በየደረጃው ያሉ መምህራን አሰለጣጠንና የሙያ ዕድገት እና ሌሎችም ተያያዥነት ካላቸው የፖሊሲና የትግበራ ሂደቶች በመነሳት አንድ የትምህርት ሥርዓት በወጣቶች ላይ የሚኖረውን አዎንታዊና አሉታዊ ተፅዕኖዎች መተፈሽ ይቻላል:: የዚህ ክፍል ዋና ዓላማ የድህረ-1983ቱ የትምህርት ሥርዓት በወጣቶች የስብዕና ግንባታ ላይ የነበረውን በጎ እና አሉታዊ ተፅዕኖዎችን መቃኘት ነው::

### ሀ. አዎንታዊ አስተዋፅዖ

ትምህርት በወጣቶች ላይ ምን በጎ ለውጥ አመጣ ብሎ መጠየቅና ለመመለስ መዳዳት የትምህርት ዓላማ ምንድን ነው? ትምህርት ለምን? የሚሉትን ትልልቅ ጥያቄዎች መመለስን ይጠይቃል:: በአጠቃላይ ትምህርት ወጣቶችን ለህይዎት፣ ለሥራ ዓለም እና መልካም ዜጋ እንዲሆኑ የማድረግ ትልቅ ሚና አለው:: የትምህርት

ውጤታማነት የሚለካው በሚያፈራቸው ወጣቶች ጥራትና በማህበረሰቡ ዘንድ በሚያመጣው ትርጉም ያለው የኑሮ መሻሻል ነው። ትምህርት ወጣቶች ጥልቅ አሳቢዎች፣ ፈጣሪዎች፣ ችግር ፈችዎች፣ ተግባቢዎችና ማህበራዊ ኃላፊነት የሚሰማቸው ዜጎች እንዲሆኑ የማድረግ ግዴታ አለበት። አንዳንድ ምሁራን የትምህርት ዓላማን ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገልፁ የትምህርት ዓላማ መልካም ዜጋን (Good Citizenship) ማፍራት ነው ይላሉ።

በድህረ-1983 ዓ.ም. የተነደፈው የትምህርት ሥርዓት ከምንም ነገር በላይ የኢትዮጵያ ህፃናትና ወጣቶች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል። በገጠርም ይሁን በከተማ የትምህርት ዕድል ማግኘት ለተቸገሩ ህፃናት ትምህርት በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቷል። ይህም በወንዶችና በልጃገረዶች መካከል የነበረውን የትምህርት ዕድል አቅርቦት ልዩነት እንዲቀንስ አድርጓል። በርካታ የአካል ጉዳት ያለባቸው ህፃናትና ወጣቶች የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ አድርጓል። በዚህ ዕድል ምክንያት ራሳቸውን የረዱ፤ ያሻሻሉ፤ ቤተሰቦቻቸውን የገዙ፤ ለአካባቢያቸው እና ለሀገራቸው ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ያደረጉ ወጣቶች ቁጥር ስፍር የላቸውም። ኢትዮጵያ ከነችግሩም ቢሆን የሚያስፈልጋትን የሰው ኃይል እያመረተችና በየዘርፉ እያሰማራች አንደሀገር እንድትቀጥል ረድቷታል።

በተጨማሪም ከጅምሩ ከፍተኛ የዝግጅትና የአፈፃፀም ችግር ቢኖርበትም ህፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ትምህርት መማራቸው ከሚያገኙት የአዕምሮና የአስተሳሰብ ዕድገት በተጨማሪ በቋንቋቸው መጠቀማቸው በራሳቸው እንዲኮሩ፣ እንዲተማመኑ እና ጤናማ የማንነት ዕድገት (identity development) እንዲኖራቸው አድርጓል።

### ለ. አሉታዊ አስተዋፅዖ

በበርካታ ምሁራን ተደጋግሞ እንደሚገለፀው ከሀብት (capital) ሁሉ የላቀው ሀብት የሰው ኃብት ነው ይላሉ። አስተማማኝና ጥራት ያለው የሰው ኃይል የሚመነጨው በጥራት ከተቀረፀ እና በትክክል ከሚተገበር የትምህርት ሥርዓት ነው። በአንድ ወቅት ፕሬዜዳንት ማንዴላ እንደተናገሩት ዓለምን ለመለወጥ ወሳኙ ትጥቅ ትምህርት ነው። የትምህርት ሥርዓት ውድቀት የሀገር ውድቀት ነው።

የትምህርት ሥርዓት ሲቀረፅ አንዱ ታሳቢ የሚያደርገው ጉዳይ የሀገርን ችግር በሰለጠነ የሰው ኃይል ለመፍታት ማስቻልን ነው። ስለዚህ ትምህርት ሁለናተናዊ ብቃት ያላቸው ዜጎችን ማፍራት ላይ ያተኩራል። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ የትምህርት ሥርዓት ከመነሻው በሚኖር የተንሻፈፈ ዕይታና በአፈፃፀም ሒደት በሚፈጠር ጉድለት በትምህርት ሥርዓቱ አልፈው የሚወጡ ወጣቶች ተገቢውን ጥራትና ብቃት

አሚልተው ከመውጣት ይልቅ በተቃራኒው የሚጠበቅባቸውን ዝቅተኛ የመማር ብቃት የማያሚሉ፣ ከማህበረሰቡ ወግና ባህል ያፈነገጡ፤ ጥገኛ እና አደገኛ የሆኑ ወጣቶችን ይፈጥራል። በኢትዮጵያም ለባለፉት በርካታ ዓመታት ይሰጥ የነበረው ትምህርት በወጣቶች ወይም በዜጎች ላይ ትርጉም ያለው አዎንታዊ የባህሪ ለውጥ እንዳላመጣ በሰፊው ይነገራል። ይህንን ሁኔታ ሲያስረዱ የሚችሉ የተወሰኑ ነጥቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## የብቃት ማነስ

የድህረ-1983 ዓ.ም. የትምህርት ሥርዓት ዋነኛ ችግር ማሣያ በየደረጃው የትምህርት እርከኖቻቸውን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች የብቃት ማነስ ነው። ይህ ችግር የተለያዩ መገለጫዎች አሉት። አንደኛው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ እና በብሔራዊ ደረጃ በሚሰጡ ፈተናዎች እጅግ ዝቅተኛ እና አስደንጋጭ ውጤት ማስመስገባቸው ነው። ለምሳሌ በሁለተኛና ሦስተኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተሠራው የማንበብ ብቃት ፈተና (Early Grade Reading Assessment) እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ የሚያሳየው ሁለተኛ ክፍል ካጠናቀቁት መካከል 70%፣ ሦስተኛ ክፍል ካጠናቀቁት መካከል ደግሞ 50% ያህሉ ምንም ማንበብ (Zero readers) የማይችሉ ናቸው። በተመሳሳይም ከ2000-2020 እ.ኤ.አ. በ4ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሔደው ብሔራዊ የመማር ምዘና (National Learning Assessment) ውጤት እንደሚያሳይው በ2000 እ.ኤ.አ. የተፈተኑት ተማሪዎች አማካይ ውጤት 47.9% ሲሆን፤ በ2020 እ.ኤ.አ. የተፈተኑት ደግሞ አማካይ ውጤታቸው 37.7% ነው። ይህ ውጤት በየትኛውም መመዘኛ እጅግ በጣም ዝቅተኛ እና የሀገራችን ትምህርት የደረሰበትን ከፍተኛ ዝቅጠት የሚያሳይ ነው። ሌላው አሰደንጋጩ ነገር ውጤቱ ከዓመት ዓመት እያሽቆለቆለ መምጣቱ ነው።

**ሠንጠረዥ 1፡** <u>በብሔራዊ ፈተናዎች ከ50% በታች ያመጡ ተማሪዎች በመቶኛ 2010 እ.ኤአ (2002 ዓ.ም)</u>

| የትምህርት ዓይነት | የክፍል ደረጃ | |
|---|---|---|
| | 10ኛ | 12ኛ |
| | ከ50% በታች ያመጡ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ | ከ 50% በታች ያመጡ ተማሪዎች ብዛት በመቶኛ |
| እንግሊዝኛ | 82.2 | 74.1 |
| ሒሳብ | 85.3 | 42.3 |
| ፊዚክስ | 89.9 | 83.3 |
| ኬሚስትሪ | 82.9 | 56.6 |

| | | |
|---|---|---|
| ባዮሎጂ | 75.2 | 39.3 |

ምንጭ፡- NEAEA 2010[15]

በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች የታየው አነስተኛ የመማር ውጤት በሁለተኛና በከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ላይም ያለ ልዩነት ይታያል፡፡ ለምሳሌ ከላይ በቀረበው የ10ኛና 12ኛ ክፍል ተማሪዎች የ2010 እ.ኤ.አ. የብሔራዊ ፈተና ውጤት እንደሚያሳየው በሚያስደነግጥ ሁኔታ በርካታ ተማሪዎች ከሚጠበቀው ዝቅተኛ የማለፊያ ውጤት (50%) በታች አስመዝግበዋል፡፡

ሌላው ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በየትምህርት ዘርፉ ተመርቀው የሚወጡ ምሩቃን በመውጫ ፈተና የሚያስመዘግቡት ዝቅተኛ ውጤት ነው፡፡ በተለይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ይሰጥ የነበረው የጤና እና የህግ ትምህርት ዘርፍ ተመራቂዎች የሚያስመዘግቡት የመውጫ ፈተና ውጤት አሳሳቢ ነው፡፡ እንዲሁም በየደረጃው ትምህርታቸውን አጠናቀው የሙያ ብቃት ፈተና ከሚወስዱት ተማሪዎች መካከል በመጀመሪያው ፈተና የማለፊያ ውጤት የሚያስመዘግቡት የተማሪዎች ቁጥር እጅግ አነስተኛ ነው፡፡

እንዲሁም ለተማሪዎች እና ለምሩቃን ብቃት ማነስ እንደማስረጃ ሊጠቀስ የሚችለው ነገር ከቀጣሪዎች የሚመጣ የእርካታ ማነስ ነው፡፡ በርካታ ቀጣሪ መስሪያ ቤቶች በተደጋጋሚ ሪፖርት ሲያደርጉ እንደሚታየው ከዩኒቨርስቲ ተመርቀው ወደ ሥራ ዓለም የሚሠማሩት ወጣቶች ከፍተኛ የሆነ የአቅም ችግር እንደሚስተዋልባቸው ነው፡፡ ይህም የሚሆንበት አንዱ ምክንያት ይሰጥ የነበረው ትምህርት ቀለም እና ንድፈ ሀሳብ-ተኮር እና ትምህርትና የሥራው ዓለም ወይም ትምህርት ቤቶችና ኢንዱስትሪዎች ትርጉም ያለው ቁርጠኝነት ስለሌላቸው ነው፡፡

የዓለም ባንክ በ2013 እ.ኤ.አ. ባስጠናው የኢትዮጵያ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ጥናት ሪፖርት በግልፅ እንደተጠቀሰው በአጠቃላይ በድህረ-1983 ዓ.ም. ይሰጥ የነበረው የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ንድፈ-ሀሳብ ላይ ትኩረት ያደረገ እና ከተግባር ጋር ብዙ ያልተዛመደ በመሆኑ በየደረጃው የትምህርት እርከን የሚያጠናቅቁ ተማሪዎች አስፈላጊ የህይወት ክህሎቶችን እንዳይላበሱ እና ብቁ ተቀጣሪዎችም ሥራ ፈጣሪዎችም እንዳይሆኑ አድርጓቸዋል፡፡

**የሥነ-ምግባር መላላትና መውረድ**

[15] NEAEA 2010

የልጆችና የወጣቶች ሥነ-ምግባር የሚቀረፀው በብዙ ነገሮች መስተጋብራዊ ሂደት ነው:: ሂደቱ ከቤተሰብ ይጀምርና በጎረቤት፣ በአካባቢ፣ በዕምነት ተቋማት፣ በሚዲያዎች ተፅዕኖ፣ በትምህርት ቤት እና በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ በሚንፀባረቁ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ስራቶች ይወሰናል:: የትምህርት ተለምዷዊው ሚና ወጣቶችን በቀለም ትምህርትና ክህሎት ማብቃት ተደርጎ ቢታይም ትምህርት ቤት ለወጣቶች ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ መማሪያ ትልቁ አውድ ነው:: በትምህርት ቤት ውስጥ በሚሰጡ ቀጥተኛ የትምህርት ይዘቶች ወይም ደግሞ በተጓዳኝ ለወጣቶች ስብዕና ግንባታ በሚቋቋሙ ክበቦች የወጣቶች ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ ይገነባል::

በድህረ-1983 ዓ.ም ይሰጥ በነበረው ሥርዓተ-ትምህርት ውስጥ መብቱንና ግዴታውን የሚያውቅ ብቁ ዜጋን ማፍራት በሚል ዕሳቤ የዜግነትና የሥነ-ምግባር ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ (5ኛ ክፍል) እስከ ከፍተኛ ትምህርት ድረስ ራሱን ችሎ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጥ ነበር:: ይሁን እንጂ የትምህርቱ ሁኔታ እና አሰጣጡ ፖለቲካዊ ዝንባሌው ያመዝናል በሚል በበጎ የሚታይ አልነበረም:: የትምህርት ሚኒስቴር እ.ኤ.አ. 2010 ባወጣው ዓመታዊ ሪፖርት ላይ እንደተገለፀው ይህ ትምህርት በወጣቶች ማህበራዊና ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ ላይ የፈጠረው ተፅዕኖ እጅግ አናሳ እና የሚጠበቀውን ያህል እንዳልሆነ ተገልጿል::

በእርግጥ የወጣቶች የሥነ-ምግባር ግንባታ በአንድ የትምህርት ዓይነት ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ወይም በትምህርት ቤት ብቻ የሚገነባ እንዳልሆነ ዕሙን ነው:: ቢሆንም ግን ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ እስከ ዩኒቨርስቲ የሚሰጠው የዜግነትና ሥነ-ምግባር ትምህርት እንዴት ትንሽ እንኳን መልካም ውጤት አላመጣም ብሎ መጠየቅ ግን ተገቢ ነው:: ከትምህርቱ ባሻገር ትርጉም ባለው ሁኔታ የወጣቶችን ስብዕና እና ሥነ-ምግባራዊ ባህርይ ለማሳደግ የተጓዳኝ (Co-curricular) እና የተጨማሪ (Extra-curricular) ተግባራት ወሳኝ ሚና አላቸው:: ወጣቶች በራሳቸው በሚያቋቁሟቸው እና በሚመሯቸው ክበባት ውስጥ መሳተፍ በክፍል ውስጥ በሚሰጠው የቀለም ትምህርት የማይዳሰሱ ግን እጅግ ወሳኝ ክህሎቶችን ይማራሉ:: ነገር ግን ባለፈው የትምህርት ሥርዓት ምክንያቱ ግልፅ ባልሆነ ሁኔታ እነዚህ ለስብዕና ዕድገትና መዳበር ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ አውዶች በጣም ተቀዛቅዘውና ተዳክመው ታይተዋል::

በአጠቃላይ በወጣቶች ላይ የሚታዩትን ገንቢ ያልሆኑ ሥነ-ምግባራዊ ባህርያት ማለትም እንደ ባቋራጭ የመበልፀግ ፅኑ ፍላጎት፣ ዘረኝነትና ጎሰኝነት፣ የቀዘቀዘ የሀገርና ብሔራዊ ስሜት፣ ስርቆትና አሰቃቂ ወንጀል፣ የፈተና ማጭበርበርና ስርቆት እና ሌሎችም ችግሮች ከነበረው የትምህርት ሥርዓት ሁለንተናዊ ጉድለት ጋር

ማያያዝ ይቻላል። በጥሩ ሁኔታና በአግባቡ ያልተማረ፣ በቀለም ትምህርትም ሆነ በተግባራዊ የሙያ ክህሎት ያልሰለጠነ፣ ተመርቆ ሥራ መፍጠር ወይም መቀጠር ያልቻለ ወጣት ምን ሊያደርግ ይችላል ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው።

## የዘመናዊ ክህሎቶች ማነስ

ቀደም ባለው ክፍል እንደተገለፀው የድህረ-1983ቱ የትምህርት ሥርዓት ከላይ እስከ ታች በይዘት የታጨቀ፣ ዘመናዊና ወቅታዊ ዕውቀቶችንና ክህሎቶችን ያላካተተ በብዙ ግብዓቶች ዕጥረት የተተበተበ የትምህርት ሥርዓት ነበር። አንዳንዶችም እንደሚሉት የኢትዮጵያ ትምህርት ሥርዓት በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ሥርዓተ ትምህርት፣ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ክፍልና ቁሳቁስ ወጣቶችን ለ21ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ክህሎቶች (21st Century Skills) ለማዘጋጀት የሚሞክር ነው ይላሉ። ይህ እንደሚያሳየው ከትምህርቱ ኋላቀርነትና አሰጣጥ ሂደት በመነሳት የኢትዮጵያ ወጣቶች ምን ያህል ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች ቅርብ አለመሆናቸውን ነው።

ወጣቶች በፍጥነት እየተለወጠች ባለችው ዓለም ውስጥ ተወዳዳሪ እና ውጤታማ ሆኖ ለመቀጠል የሚያስችሉ 12 የሚሆኑ ዘመናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ክህሎቶችን መላበስ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ክህሎቶች የ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች በመባል ይታወቃሉ። ሀገራትም የትምህርት ሥርዓቶቻቸውን እነዚህ የዘመኑ የሥራ ዓለምና ዘመናዊነት ከሚፈልጋቸው ብቃቶች አንፃር በመቃኘት የወጣቶቻቸውን አለም አቀፋዊ ተወዳዳሪነት እያሳደጉ ይገኛሉ። እነዚህ 12ቱ አጠቃላይ ክህሎቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. በጥልቀት ማሰብ (Cnitical thinking)፤
2. ፈጠራ (Creativity)፤
3. መተባበር (Collaboration)፤
4. ተግባቦት (Communication)፤
5. የመረጃ ዕውቀት (Information Literacy)፤
6. የሚዲያ ዕውቀት (Media literacy)፤
7. የቴክኖሎጂ ዕውቀት (Technology literacy)፤
8. ተለማጭነት (Flexibility)፤
9. መሪነት (Leadership)፤
10. ተነሳሽነት (Initiative)፤
11. ውጤታማነት/ምርታማነት (Productivity)፤

12. ማህበራዊ ክህሎት (Social skills) ናቸው።

በአጠቃላይ የድህረ-1983 ዓ.ም. የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት መፈተሽ ያለበት ምን ያህል ወጣቶችን ከላይ ለተጠቀሱት ዘመናዊ እና ዓለም አቀፋዊ ክህሎቶች አዘጋጅቷቸዋል በሚል አጠቃላይ ጥያቄ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን የትምህርት ሥርዓቱ ፍተሻዎች ለምሳሌ በ2013 እ.ኤ.አ. በዓለም ባንክ የተሰራው የ2ኛ ደረጃ ትምህርት የግምገማ ጥናት ሪፖርት እንደሚያሳየው የኢትዮጵያ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ወጣቶችን በእነዚህ ክህሎቶች ሊቀርፅ የሚችል እንዳልሆነ ነው።

## 8. ማጠቃለያ

ምንም እንኳ የወጣቶች ስብዕና በብዙ ሒደቶችና በበርካታ ዐውዶች መስተጋብር የሚገነባ ቢሆንም ትምህርት የጎላ ድርሻ ይጫወታል። የትምህርት ዋነኛ ግብ ወጣቶችን ለህይወት፣ ለሥራ እና ለሀገር መልካም ዜጋ እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነው። በዚህም ሒደት የማህበረሰቡን ህይወት ማሻሻልና ማሳደግ ነው። ከዚህ አጠቃላይ ግብ አንፃር ሲታይ የድህረ-1983ቱ የኢትዮጵያ የትምህርት ሥርዓት በወጣቶች የሥብዕና ግንባታ ሒደት ውስንነቶች እንደነበሩበት ይታመናል። በተለይ ወጣቶች በየደረጃው የሚጠበቅባቸውን የዕውቀት አመለካከትና ክህሎት ጠንቅቀው አሟልተው ከመገኘት እና ሥራ ፈጣሪዎች ወይም ብቁ ተቀጣሪዎች ከመሆን አንፃር ክፍተቶች ይታያሉ። ለዚህ ክፍተት ደግሞ የትምህርት ሥርዓቱ አጠቃላይ አቅጣጫ፣ ይዘት፣ የመማር-ማስተማርና የግምገማ ሂደት፣ የትምህርት ግብዓቶች ውስንነት፣ የመምህራን ጥራትና ብቃት፣ የተማሪዎች ተነሳሽነትና ትጋት ማነስ እና የባለድርሻ አካላት ንቁ ተሳትፎ ያለመኖር የሚጠቀሱ ምክንያቶች ናቸው።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ትምህርት በወጣቶች የስብዕና ግንባታ ላይ ያመጣውን ተፅዕኖ በተደራጀ መልኩ ማጥናት እጅግ አስፈላጊ ነው። ትምህርቱም ትኩረቱን ከቀለምና ንድፈ-ሀሳብ ባሻገር ከህይወት ጋር የተዛመደ ተግባር ተኮር እንዲሆን ማድረግ ጊዜ የማይሰጠው ተግባር ነው። የትምህርቱ ይዘትና አሰጣጡም ወቅቱን የዋጀ እና ወጣቶችን ለ21ኛው ክፍለ ዘመን ክህሎቶች የሚያዘጋጅ አለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያደርግ መሆን ይገባዋል። የትምህርቱ ትኩረትም በክፍል ውስጥ ብቻ የታጠረ ሳይሆን ወጣቶች ተፈላጊ የሥነ-ምግባር፣ ስብዕና እና የመሪነት ክህሎቶችን የሚያዳብሩባቸውን ተጓዳኝ ፕሮግራሞችን ማካተት ይገባዋል።

በመጨረሻም የኢትዮጵያ ወጣቶች በዚህ ሁሉ ያልተመቸ እና ባልተሟላ ሁኔታ ውስጥ ቢያልፉም ፈተናን ተቋቁሞ የማለፍ (coping) እና በፍጥነት የማገገም

(resilience) ብሎም የመበልፀግ (thriving) ችሎታቸው ግን ከምንም ነገር በላይ ያስገርማል።

# ወጣትነት፣ግብረገብና ሥነ-ምግባር በኢትዮጵያ

ጠና ደዎ

## 1. መግቢያ

በሀገራችን ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዘው የሕብረተሰብ ክፍል ወጣት ነው ተብሎ ይታሰባል። ይህ ባንድ በኩል ፀጋ፤ ውበትና ሀብት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአግባቡ ካልተያዘ የሚፈታተን ተግዳሮትና ሥጋት መሆን ይችላል። በሌላ መልኩ ሲታይ ደግሞ ወጣቱ የሀገር ባለቤት በመሆኑ በሀገር የሚሰራና ሀገርን የሚሰራ ነው። ስለዚህ ይህ ወጣት ዛሬ ያለው የት ነው? እንደተባለው የሀገር ፀጋ፤ ውበትና ሀብት ሆኖ ነው ወይስ ተግዳሮትና ሥጋት? ሕብረተሰቡስ መያዝ በሚገባው መልክ ይዞታል ወይስ እንደነገሩ ሆኖ የሚኖር ነው? የሚሉት መሠረታዊ ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው። የዚህ ጽሑፍ ዋና ትኩረት የኢትዮጵያን ወጣቶች በግብረገብና በሥነ-ምግባር መነፅር በመዳሰስ ቁመናቸውን ማሳየት ነው።

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የተገነቡ ብዙ መልካም ነገሮች አሉ። በዚያው ልክ በሕዝብ አዕምሮ፤ ሕይወትና ግንኙነት ላይ የተሰሩ መጥፎ ነገሮችም አሉ። መልካም ነገሮቻችን ወደ ፊት ሲወስዱን፤ መጥፎ ነገሮቻችን ደግሞ በራሳቸው መንገድ ወደ ኋላ ሲመልሱን ኖረናል። ታሪካችን ወደፊትና ወደኋላ ከመንገራገጭ አልፎ መዝለቅ ያልቻለው በዋናነት የመጥፎ ድርጊቶቻችን ጉልበት የመልካም ባሕርዮቻችንን አቅም በእጅጉ የሚገዳደሩ ሆነው በመገኘታቸው ነው። መልካም ድርጊቶችን የሚፈጽመው ሰው ነው፤ መጥፎ ነገሮችን የሚሰራውም ያው ሰው ነው። ለምንድነው ሰው መጥፎ መጥፎውን እየተወ መልካም መልካሙን ነገር ብቻ መርጦ የማይሰራው? ለምንድነው መጥፎ ነገሮችን ከመሥራት መታቀብ የማይችለው? የግብረገብና የሥነ-ምግባር ዋና ትኩረት መልካምን ከመጥፎ፤ ትክክል የሆነውን ነገር ትክክል ካልሆነው ለይቶ ማሳየት ወይም መፈረጅ ነው።

ወጣቶች እነዚህን ችግሮች እንደየ ባሕርያቸው ለይተው ለመረዳት ያላቸው ሞራላዊና ሥነ-ምግባራዊ አቅም ምን ያህል ጠንካራ ነው? የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚመጥን የግብረገብና የሥነ-ምግባር ትምህርት የማግኘት ዕድል ነበራቸው ለማለት አያስደፍርም። በዚህ ምክንያት ለሰው የሚበጀውን ለማድረግና ለማሳደግ፤ የማይበጀውን ላለማድረግና ለማስወገድ ያላቸው አቅም፤ ፍቃድና ጽናት ውስን ነው። በመሆኑም ለሚጠቅመውም ሆነ ለሚጎዳው ሁሉ የአዕምሮአቸው በር ክፍት ሆኖ ቆይቶአል። ለዚህ ነው የማንፈልገው የጥላቻ ጉልበት ከምንፈልገው የፍቅር ጉልበት በላይ ሆኖ ሲያደማን የኖረው። ባጠቃላይ ስለ ወጣትነት፤ በተለይ ስለ ኢትዮጵያ

ወጣቶች መነጋገር፤ መወያየት፤ መመካከር ከጀመርን ቆይተናል፡፡ እኛም ወጣቶች ሆነን በዚያው መንገድ ስላለፍን ስለወጣትነት በጊዜው ቋንቋና ትርክት ብዙ አውርተናል፡፡ በተለይ ከ1967 አብዮታዊ ለውጥ ጊዜ ጀምሮ ወጣትነት የምክክር፤ የክርክርና የውይይት አጀንዳችን ሆኖ ቆይቶአል፡፡ የወጣት ነገር ሁሌም ወጣት እንደሆነ ቀጥሎአል፤ ይቀጥላልም፡፡

የእነዚህ ሁሉ ጥረት ዋና እምብርት ዞሮ ዞሮ አንድ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቶች በመልካም ዜግነት መልካም ነገር እንዲያስቡ፤ እንዲሰሩና በአጠቃላይ በሀገር ደረጃ መልካም ሕብረተሰብ መስርተን መልካም ሕይወት እንድንመራ ነው፡፡ መልካም ዜጋ መሆን የሚቻለው ደግሞ መልካም ነገር በማሰብና በመሥራት ብቻ ሳይሆን ከመጥፎ አስተሳሰብ፤ ድርጊትና አመል በመራቅም ጭምር ነው፡፡ መጥፎ ነገሮችን ከማድረግና መጥፎ ነገሮችን ከመላመድ የታቀበና የሚታቀብ ስብዕና እንድንጎናጸፍ ነው፡፡

## 2. መነሻ ሐሳብ

የውይይታችን ርዕስ ‹‹**ወጣትና ሥነ-ምግባር በኢትዮጵያ**›› የሚል ሲሆን፤ በዚህ ርዕስ ሥር ሦስት መሠረታዊ ጽንሰ-ሐሳቦችን እናነሳለን፤ ወጣት፤ ሞራል (ግብረገብ) እና ሥነ-ምግባር፡፡ ወጣት ማለት ምን ማለት ነው? ከተቀረው ሕብረተሰብ በምን ይለያል? በግርድፉ ወጣት ማለት የተወሰነ ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው ነው፡፡ የሕብረተሰብን ደህንነትና ምቾት ለመጠበቅ፤ ሰላሙንና ደህንነቱን ለማስከበርና ልማቱን ለማፋጠን በተለያዩ የዕድሜ እርከኖች ውስጥ ያሉ ሰዎች የሚኖራቸውን ማንነትና ባሕርይ ማወቅ አስፈላጊ ነው፡፡ ሕብረተሰብ በሕፃናት፤ በወጣቶች፤ በጎልማሶችና በአዛውንቶች የተገነባና የሚገነባ ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ሲታይ ‹‹**ወጣት ማለት ከሕፃናትና ከጎልማሾች ዕድሜ ክልል መካከል በሚገኝ ዕድሜ ውስጥ ያለ ሰው ነው**››፡፡

ከላይ የተጠቀሰው ትርጉም ምን ዓይነት ወጣት የሚለውን ጥያቄ ግን አይመልስም፡፡ በእርግጥ የምንፈልገው ወጣት መልካም ወጣት ነው፤ ካልተገደድን በቀር የማንፈልገው ደግሞ መጥፎ ወጣት ነው፡፡ ይህን አስመልክታ አንዲት ፀሐፊ ስትገልጽ ‹‹ **በወጣቶቻችን ውስጥ እጅግ ከፍተኛ ኃይል አለን፡፡ ይህን ኃይል ለመልካም ግቦች ማዋል እንድንችል አሮጌ አስተሳሰቦችንና ልማዶችን የመለወጥ ጀግንነት ሊኖረን ይገባል**››ትላለች፡፡ (Mary McLeod Bethune) ኢትዮጵያ ዛሬ የምትፈልገው ምርጥ የሆኑ ወይም በየትኛው ሁኔታ መልካም ማንነት ያላቸው ወጣቶችን ነው፡፡ ግን ደግሞ መልካም ወጣት ማለት ራሱ ምን ማለት ነው የሚለውንም ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው፡፡

አንድ ፀሐፊ ሲጽፉ ‹‹መልካም ወጣት ፈጣሪን መፍራት አለበት፤ ለወላጆቹ መታዘዝ አለበት፤ ታላላቆቹን ማክብር ይጠበቅበታል፤ ለራሱ ንጹህ መሆን ይኖርበታል፤ ትዕግስትንና ትህትናን የሚወድ/የተላበሰ መሆን አለበት:: እነዚህ ሁሉ የወጣትነት ዘመን ጌጣጌጦች ናቸው›› ይላሉ (St. Ambrose) :: ሕብረተሰብና ሀገር የሚኖሩትና የሚገነቡት በትውልዶች ቅብብሎሽ ነው:: የዚህ ቅብብሎሽ ሰንሰለት አንዱና ዋና ቀለበት ደግሞ ወጣቱ ነው:: ወጣት አሁን ላለው ትውልድ እጅግ አስፈላጊ አካል ነው፤ በሚቀጥለው ትውልድ ውስጥ ደግሞ የጊዜው ዋና ተዋናይ፤ ባለቤት ወይም ታሪክ ሠሪ ነው:: ወጣትነት በራሱ ማንነት ነው - በመሆን ወይም በመታነፅ ላይ ያለ ማንነት::

ይህ ማንነት በሦስት ደረጃዎች ውስጥ ያልፋል:: አንደኛው ቀደም ሲል የነበረው ጊዜ፤ ሁለተኛው አሁን ያለበት ጊዜና ሦስተኛው ወደፊት የሚደረስበት ጊዜ ነው:: ማንነት የሦስቱም ድምር ውጤት ነው:: አንደኛውና ሁለተኛው ደረጃዎች በተጨባጭ የተኖረና በመኖር ላይ ያለ ሲሆን ሶስተኛው ወደፊት ይደረስበታል ተብሎ የሚታሰብ ማንነት ነው:: ወጣትነት ያለቀለት ማንነት ሳይሆን በመሰራትና በመሆን ሂደት ውስጥ ያለ ነው:: በመሆኑም የሚለማ፤ የሚገነባ ወይም የሚታነፅ ማንነት ነው:: የሚታነፀው በራሱና በሌሎች ነው:: (ሌሎች ማለት ወላጅን ወይም ቤተሰብን፤ ጎሮቤትን፤ ሕብረሰብን፤ የዕምነት፤ መንግስት፤ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችን ወዘተ) ለማለት ነው:: ሂደቱ ከሕፃንነት ወደ ወጣትነት፤ ከወጣትነት ወደ ጎልማሳነት የሚወስድ የሽግግር ጊዜ አለው::

አሁን በተጨባጭ ያለው በሆነውና መሆን በሚፈልገው፤ በያዘውና መያዝ ወይም ማግኘት በሚመኘው ማንነት መካከል ነው:: የመጀመሪያው አሁን የሚገኝበት ሲሆን ከመድረሻው አንጻር ሲታይ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ነው:: ሁለተኛው የሚደርስበት ነው፤ ከርቀት የሚታይ ግብ ነው:: ሽግግሩን ለማሳካት ያለውን አቀበትና ቁልቁለት መውጣትና መውረድ፤ መውደቅና መነሳት የግድ ይላል::

ወጣትነትና ፍልስፍናእንደ አስተሳብ የሚመሳሰሉበት አንድ ባሕርይ አላቸው:: ፍልስፍና እውነትን ለማወቅ ያለመታከት ይሰራል:: ሁሉንም ነገር ለመፈተሽ በተለያየ አቅጣጫ ይቧጥጣል፤ ይቆፍራል:: በባሕርይው ጠያቂ፤ ምክንያታዊና ሂሳዊ ነው፤ አንዳች ዓይነት ውጤት ካላገኘ ፍተሻውን አያቆምም:: ወጣትነትም የማያውቀውን ለማወቅ፤ ያላገኘውን ለማግኘት፣ ካልደረሰበት ለመድረስ ያለ መታከት የሚጥር ነው:: በባህርይው አዳዲስ ነገር ለማወቅና ለመስራት፤ ለመፍጠር ወይም ለማግኘት፤ ፈትሾና አረጋግጦ ለማሳየት ይጓጓል:: ከዚህ አንጻር ወጣቶች በሚኖሩበት ሕብረተሰብ ውስጥ ሰፊና ውስብስብ ኃላፊነት አላቸው:: በዛሬ ውስጥ ሆነው

ራሳቸውን ለነገ የማዘጋጀት ኃላፊነት አለባቸው፡- በአካልና በመንፈስ፤ በዕውቀትና በሥራ። ነገ ግን ሙሉ የትውልድ ኃላፊነትን ይረከባሉ።

## 3. መሠረታዊው ጥያቄ የሕይወት ስለመሆኑ

የሰው ልጅ ጉዳዮች ሁሉ ዋና መነሻና መድረሻ ሕይወት ነው። የሰው ልጅ ሕይወት በሁለት ተቃራኒ ነገሮች መካከል ትገኛለች፡- አንዱ የሚያበለጽግ ወይም የሚያስደስት፤ ሌላው የሚያቀጭጭ ወይም የሚያሳዝን ነው። የምንፈጠረው እነዚህን ሁለት ተቃራኒ የሆኑ እምቅ ገጽታዎችን ይዘን ነው። በተለያዩ ምክንያቶች አንዱ በሌላው ላይ ዓና የመፍጠር አቅም አለው። የመጀመሪያው ጫና በሁለተኛው ላይ አይሎ ሲገኝ የሕይወት ደስታ ከፍ ይላል። በተቃራኒው የሁለተኛው ጫና በመጀመሪያው ላይ ሲበረታ ሕይወት መከራን ለመቀበል ትገደድ ይሆናል። ስለዚህ የሰው ልጅ ሕይወት ያለችው በደስታና በመከራ መካከል ሆና አንዳንዴ በደስታ ወጀብ ትቀዝፋለች፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ በሐዘን ማዕበል ውስጥ ትደፈቃለች።

እኛ ሰዎች ግን የምንፈልገው፤ የምንፈቅደው ወይም የምንመርጠው ደስታን እንጂ መከራን (ወይም ሐዘንን) አይደለም፤ የሚያሳድገን እንጂ የሚያቀጭጨን አይደለም። ይህ ማለት መልካምነት ለሕይወታችን የምንጊዜም ምርጫችን ነው። ይሁን እንጂ ሕይወት አንዳንዴ እንደፈለግናትና እንደተመኘናት አትሆንልንም። ዓለም እንደ ምርጫችን እንድንኖር የማትፈቅድበት ጊዜና ሁኔታ አለ። አንዳንዴ የማንፈልገውን፤ የማንፈቅደውን ወይም የማንመርጠውን ነገር ትጭንብናለች፤ የምንመርጠውን ነፍጋን የማንመርጠውን ታሸክማናለች። እኛ የፈለግነውን ነፍጋን እርስዋ የፈለገችውን ትመርጥልናለች፡ እዚህ ጋ ዋናው የችግር ምንጭ ግን እኛው ሰዎች መሆናችንን መረዳት እጅግ ጠቃሚ ነው። ስለዚህ እኛ ሰዎች የመረጥነውን ወይም የምንፈቅደውን ሕይወት ለማግኘት ወይም ለመኖር ፈተናን ማለፍ ወይም መከራን መቋቋም የሚያስችል አቅም መፍጠር አለብን።

እዚህ ጋ ነው የሰው ልጅ ሕይወት ከግብረገብና ሥነ-ምግባር ጋር መተሳሰር የሚኖርበት። ሁለቱም የሰውን ባሕርይ መገንባትና ማልማት፤ ማነጽና ማረቅ የሚያስችሉ ናቸው። ሰው በደስታ ይኖር ዘንድ መከራን ማራቅ ያስፈልጋል፤ በፍቅር ይኖር ዘንድ ጥላቻን ማስወገድ ይጠበቅበታል፤ በሰላም ይኖር ዘንድ ጦርነትን ማቆም የግድ ይላል። ባጭሩ የሰው ልጅ ችግሮችን በመመከት ሕልውናን ማስቀጠል ከሚችልባቸው መንገዶች አንዱና ዋነኛው በግብረገብና በሥነ-ምግባር መታገዝ ነው። ሰው ሁሌም መልካም ነገርን የሚመርጠውና መጥፎ ነገርን የሚጠላው ለሕይወት ባለው ፍቅርና ክብር ነው። የሰው ተፈጥሮ ራሱ ውስብስብ ነው። ማሕበራዊ እንስሳ ነው፤ የፖለቲካና የግብረገብ ኑባሬ ነው። የማሰብና የመመራመር፤ የመሥራትና

የመፍጠር ችሎታ አለው:: በዚህ ምክንያት ባንድ ወይም በሁለት ነገሮች ብቻ የሚገለጽ ፍጡር አይደለም::

አንዳንድ ሰዎች ሰው በሳይንስና ቴክኖሎጂ ግኝቶች ብቻ ሊገለጽ የሚችል ነው ይላሉ:: ነገር ግን ሕይወቱና ማንነቱ የተገነባው በቁሳቁስ ብቻ አይደለም- በዋነኛነት በዕሴት፤ በሐሳብ፤ በመንፈስ፤ በሕሊና፤ በአዕምሮም ነው:: እነዚህ ፀጋዎች ወይም ችሎታዎች ሁሉ ለሰው ብቻ የተሰጡ ናቸው:: ማንኛውም ሕብረተሰብ የዕሴት ሥርዓት (value system) አለው:: ዕሴት (value) የሰው ልጅ ለድርጊቶች፤ ለባሕርያትና ለነገሮች ጠቀሜታ የሚሰጠው ዋጋ ነው:: ልክ እንደማንኛውም ነገር የሰው ልጅ ዕሴትም አለው:: ይኸ ዕሴት ልዩ ነው:: ገዢ ዕሴት ነው:: በነገራችን ላይ ሁለት ዓይነት ዕሴቶች አሉ - አንደኛው ዕሴት የመሣሪያነት/የማገልገያነት ዕሴት (extrinsic value) ሲሆን ሁለተኛው ዓይነት ዕሴት በራሱ ግብ የሚሆን ዕሴት (intrinsic value) ነው:: ለሰው ልጅ ሕይወት የተሰጠው ዕሴት ራሱን የቻለ ዕሴት (intrinsic value) ነው:: ለተለያዩ መገልገያዎች የሚሰጠው ዕሴት ራሱን ችሎ የሚቆም ሳይሆን ገዢ የሆነውን ዕሴት በመሣሪያነት የሚያገለግል (extrinsic value) ዕሴት ነው:: ለምሳሌ ለብር ወይም ለዶላር የተሰጠው ዕሴት የመገልገያ ዕሴት ነው:: የሚሸጥ እና የሚለወጥ ነገር ባይኖር ኖሮ ብር፤ ዶላር ወይም ገንዘብ የሚባል ነገር አይኖርም:: ስለዚህ በዓለም ላይ ከፈጣሪ ቀጥሎ የመጨረሻ ከፍተኛ ዕሴት ያለው ነገር የሰው ልጅ ሕይወት ብቻ ነው:: ለዚህ ነው የሰው ሕይወት ክቡር ነው የሚባለው::

## 4. የግብረገብና ሥነ-ምግባር ምሰሶዎች

የሰው ልጅ በታሪክ ሂደት ውስጥ ጥያቄዎቹን የሚመልሰባቸውና ችግሮቹን የሚፈታባቸው በርካታ የሥነ-ዕውቀት (epistemology) መስኮችን ፈጥሯል:: በእነዚህ መስኮች ውስጥ የሚያጠናቸው ነገሮች በዋነኛነት በሁለት ፈርጆች ይከፈላሉ፡- አንዱ ፋክት (fact) ሲሆን ሌላው ዕሴት (value) ነው:: ፋክት ወይም እውነታ ባብዛኛው በተጨባጭ የሚገለጽ ሲሆን፤ ዕሴት ግን መሠረቱ ሕሊናዊ ቢሆንም ነበራዊ ገጽታም አለው:: ብዙ ዓይነት ዕሴቶች አሉ- ከእነዚህ መካከል አንዱ የግብረገብ ዕሴት ወይም ግብረገብ (moral value or morality) የምንለው ነው:: ግብረገብ (Morality) የሰውን ድርጊትና ባሕርይ መልካም ወይም መጥፎ፤ ትክክለኛ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ፤ ፍታዊና ኢፍታዊ በማለት የምንለይበት፤ የምንዳኝበት ወይም የምንፈርጅበት ነው::

አንዳንዴ ግብረገብንና ሥነ-ምግባርን በተወራራሽነት እንጠቀምባቸዋለን:: ምክንያቱም ሁለቱም አንድና ተመሳሳይ የሆነ ትርጉም ሊይዙ ይችላሉ:: በዚህ ምክንያት ግብረገብ

ማለት ሥነ-ምግባር፣ ሥነ-ምግባር ማለትም ግብረገብ ይሆናል። ይሁን እንጂ ሥነ-ምግባር በዋናነት የጥናት መስክ ነው። በዚህ መሠረታዊ ባሕርይ (ጥናት መስክነቱ) ፍልስፍና ውስጥ ካሉት ትላልቅ ቅርንጫፎች መካከል አንዱ ነው። የሚያጠናው ደግሞ ግብረገብን (Morality) ነው። ግብረገብ ምንድነው? ከየት መጣ? ማን ያመጣው? ለምን መጣ? ጠቀሜታውስ ምንድነው? ምን ምን ጥያቄዎችን ይመልሳል? ምን ምን ችግሮችን ይፈታል? ምን ምን መረጃና ማስረጃ፣ ማረጋገጫና ማገናዘቢያ ይጠቀማል? የሚሉ ጥያቄዎችን በማንሳት ለመመለስ ይሞክራል፣ ሕግጋትን፣ መርህዎችንና ንድፈ-ሐሳቦችን በመቅረጽ ያበለጽጋል።

## 4.1. እውነታና እሴት

የሰው ልጅ በሥነ-ዕውቀት (epistemology) እንቅስቃሴው ውስጥ ሊያውቃቸው የሚገቡ ሁለት አበይት ነገሮች አሉ፡- አንደኛው ቀደም ሲል እንደተገለጸው እውነታ (Fact) ነው፣ ሁለተኛው ዕሴት (value) ነው። እውነታ የምንለው እውነት ወይም ውሸት ተብሎ ሊታወቅ የሚችል ነገር የምንገልጽበት ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ባብዛኛው የሚታይ፣ የሚዳሰስ ወይም የሚጨበጥ ነገር የሚገለጽበት ነው። ለምሳሌ ‹‹አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ነች›› የሚለው አረፍተ-ነገር እውነታን የሚገልጽ ነው። እውነት ወይም ውሸት ተብሎ ይገለጻል። እንደተባለው አዲስ አበባ የኢትዮጵያ ዋና ከተማ ከሆነች እውነት ነው። ያ መሆኑ ቀርቶ የኬንያ ዋና ከተማ ከሆነች ደግሞ ውሸት ይሆናል።

ዕሴት (value) ግን ከእውነታ ይለያል። ዕሴት የአንድ ድርጊት፣ ጠባይ ወይም ነገር ጠቀሜታ ወይም ዋጋ የሚገለጽበት ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ይህ ጠቀሜታ ወይም ዋጋ የምንለው በሐሳብ ደረጃ እንጂ በተጨባጭ ያለ አይደለም። ለምሳሌ ‹‹የአዲስ አበባ ነዋሪዎች መልካሞች ናቸው›› ሚል ዐረፍተ-ነገርን መውሰድ ይቻላል። ይህ ዐረፍተ-ነገር (factual statement) ሳይሆን (evaluative statement) ወይም (evaluative judgment) ነው። የሚገመገመው መልካም (ሰናይ) ወይም መጥፎ (እኩይ) ተብሎ ነው።

ዕሴት የሰውን የተለያዩ ፍላጎቶች የማርካት ጠቀሜታ ያላቸውን የተለያዩ ድርጊቶች፣ ባሕርያትና ነገሮች ፋይዳ ወይም ጠቀሜታ የሚገልጽ በመሆኑ በሰዎች ምርጫ፣ ውሳኔ፣ ድርጊት ወይም ጠባይ ላይ በጎ ወይም መጥፎ ጫና ማሳረፍ ይችላል። ዕሴት ያላቸው የተለያዩ ነገሮች ለምርጫ ይቀርባሉ። ሰው ከፍላጎቱና ግንዛቤው አንጻር አንዱን ነገር ትቶ ሌላውን የሚመርጠው፣ የሚመረጥ ዕሴት ስላለው ነው። ነገሮች ዕሴት ባይኖራቸው ኖሮ ምርጫ ማድረግና ውሳኔ መወሰን ባልተቻለ ነበር። ያለ ዕሴት ግብንና ከግብ የሚያደርስን ነገር መረዳት፣ መምረጥና መወሰን

አይቻልም። ለምሳሌ ታማኝነትና ደግነት፤ ታዛዥነትና ቅንነት፤ ጨዋነትና ታታሪነት፤ ርህሩህነትና ጀግንነት ወዘተ በውስጣችን ያሉ ዕሴቶች ናቸው። እነዚህ የሰውን ማንነት የሚቀርፁና የሚመሩ ናቸው። ባጭሩ ዕሴት የሰው ልጅ ሕይወት ትርጉም እንዲኖረው የሚያደርግ ነው።

በዚህ ባሕርያቸው ምክንያት እውነታና ዕሴት የተለያዩ የጥናት መስኮች አሏቸው። እውነታ በዋናነት የሚጠናው በሳይንስ ሲሆን፤ ዕሴት ግን በፍልስፍና ነው። ፋክትን የምናጠናው ለዕውቀት ሲሆን ዕሴትን የምናጠናው ለሁለት ነገሮች ነው። አንደኛው የግብረገብ ሕግጋት፤ የሥነ-ምግባር ንድፈ-ሐሳቦችና መርህዎች ያላቸውን ምክንታዊና ተዛምዶአዊ አቅም ለመረዳት ነው። ሁለተኛው ደግሞ ውበትና አስቀያሚነት በሰው ሕይወት ውስጥ ያላቸውን ፋይዳ ለመረዳት ነው። የኛ ጉዳይ የሚወስደን ወደ ግብረገብና ሥነ-ምግባር ነው። በዓለም ላይ የተለያዩ እምነቶች ወይም ሀይማኖቶች አሉ። እነዚህም እምነቶች ሰላምና ፍቅር፤ መፈቃቀድና መረዳዳት፤ ምቾትና ደስታ ለሰው ልጅ በዓለም ላይ እንዲሰፍኑ ይጸልያሉ፤ ያስተምራሉ፤ ይሰራሉም። ሀይማኖቶችም ከፈጣሪ ቀጥሎ በዓለም ላይ ከፍተኛ ዕሴት ወይም ዋጋ አለው ብለው የሚያምኑትና የሚያስተምሩት የሰው ልጅ ሕይወትን ነው። ግብረገብና ሥነ-ምግባርም የሰው ልጅ ሕይወት ያለውን ዕሴት ማክበር የሚጠበቅብን፤ ለሌላ ግብ የሚያገለግል ስለሆነ ሳይሆን፤ በራሱና ለራሱ ለራሱ መከበር የሚገባው ግብ ስለሆነ ነው በማለት ያስተምራሉ።

### 4.2. ‹‹መሆን ያለበት›› እና ‹‹መደረግ ያለበት›› (“Ought to be›› and ‹‹Ought to do”)

ከሞራል አንጻር ከሰው ልጅ የሚፈለጉ ሁለት ነገሮች አሉ። አንደኛው መሆን የሚገባንን መሆን (‘ought to be’) ነው። እያንዳንዳችን ከሞራል ሕግጋት አንጻር መሆን የሚጠበቅብን ነገር አለ፡- ደግ ሰው፤ ሰው አክባሪ፤ ታማኝ፤ ቅን፤ ትሁት፤ እውነተኛ ወይም ሐቀኛ፤ ለእውነት መስካሪና ታታሪ፤ አርቆ አሳቢ፤ ርህሩህ፤ ኀበዝ፤ ጨዋ፤ ጀግና፤ ትዕግስተኛ፤ ቅንና ቀና ሰው መሆን የሚጠበቅብን ግዴታ ነው። ባጭሩ ከማናቸውም መጥፎ ድርጊቶችና ጠባዮች የፀዳን መሆን ይጠበቅብናል። እነዚህ የተጣሉብን የሞራል ግዴታዎቻችን ወይም ኃላፊነቶቻችን ናቸው። ሁሉም የመልካም ሰው ማንነት መገለጫዎችም ሲሆኑ ጥቅም የሚሰጡ እንጂ ጉዳት የሚያስከትሉ አይደሉም። ለዚህ ነው የግብረገብ ተቋማትና ሕግጋት ሕይወትን በመልካምነት መምራት ግዴታችን መሆኑን የሚያስተምሩን።

በግልባጩ መሆን የማይገባውን (ought not to be) ነገሮች አሉ። ለምሳሌ ክፉ፤ ሞገደኛ፤ ተንኮለኛ፤ ሴረኛ፤ ትዕቢተኛ፤ እብሪተኛ፤ ሌባ፤ ውሽታም፤ አጭበርባሪ፤

አታላይ፤ ሙሰኛ፤ ምቀኛ፤ ቀናተኛ፤ ስግብግብ፤ ሰነፍ ወዘተ:: እነዚህ ድርጊቶችና ፀባዮች በመጥፎነት የሚፈረጁ ናቸው:: የሚጎዱ እንጂ የሚጠቅሙ፤ የሚያስወግዙ እንጂ የሚያስወድሱ አይደሉም:: በራስ ላይም ይሁን በሌላ ወገን ላይ የሆነ ጉዳት ወይም ስብራት ያስከትላሉ:: ለዚህ ነው ግብረገብ ከእነዚህ መጥፎ ነገሮች እንድንታቀብ የሚያስገድደን:: መልካም ሰው መሆን ወይም መጥፎ ሰው ከመሆን መታቀብ፤ ሰላምና መረጋጋትን፤ ፍቅርና አክብሮትን፤ መተማመንና መፈቃቀድን፤ አብሮ መኖርንና መስራትን፤ ማደግንና መልማትን ያጎለብታል፤ ያፋጥናል:: እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ማንና ምን መሆን፤ ማንና ምን አለመሆን እንደሚኖርብን የሚገልጹ የግብረገብ ሕግጋት ምሰሶዎች ናቸው::

ሰው በሕይወት ዘመኑ የሚጠበቅበት መሆንና አለመሆን ብቻ አይደለም:: ማድረግና አለማድረግም አሉ:: የምንፈልገውን ለመሆንና ለማግኘት በተግባር መንቀሳቀስ አለብን:: ከግብረገብ አንጻር ማድረግ የሚኖሩብን (ought to do) ነገሮች አሉ:: እነዚህ አዎንታዊ ስለሆኑ ተቀባይነት አላቸው:: ማድረግ የማይኖሩብን (ought not to do) ነገሮችም አሉ:: እነዚህ ደግሞ አሉታዊ ስለሆኑ ተቀባይነት የላቸውም:: ማድረግ ከሚገቡን ነገሮች መካከል ለሰው ማዘን፤ ሰውን ማክበርና መርዳት፤ እንዳይጎዳ ማድረግ፤ ከአደጋ መጠበቅና ማዳን፤ ማገልገልና መንከባከብ፤ ማናቸውንም መልካም ነገሮች መተግበር፤ ሀገርን መውደድ፤ ዜግነትን ማክበር፤ ሰዎችን ሁሉ በዕኩልነት ማየት ወዘተ በምሳሌነት ማንሳት ይቻላል:: እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ድርጊቶችን መፈጸም ከሚገቡን ተግባሮች መካከል ዋነኞች ናቸው:: እያንዳንዳችን እነዚህን መልካም ነገሮች ማድረግ ይጠበቅብናል - የግብረገብ ግዴታዎቻችን ናቸውና::

በግልባጩ ልናደርጋቸው የማይገቡ ነገሮች ወይም ድርጊቶች አሉ:: ጥቂት ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል ስርቆት፤ መዋሸት፤ ማጭበርበር፤ ሙስና፤ ውሸት፤ ሐሰት መመስከር፤ ሰውን በአካልም ሆነ በመንፈስ መጉዳት፤ የሰውን ሕይወት ማጥፋት፤ በሀገርና በሕዝብ ላይ ጥፋት መፈፀም ወይም ጉዳት ማድረስ ወዘተ. የተጠቃቀሱትን መልካም ነገሮችን ማድረግና መጥፎ ነገሮችን ከማድረግ መታቀብ ግለሰብንም ሆነ ሕብረሰብን የሚጠቅም ነው:: ጠቃሚ ወይም ገንቢ የሚሆኑት ሰላምና ፍቅርን ስለሚያሰፍኑ፤ መቻቻልና መደማመጥን ስለሚፈጥሩ፤ መፈቃቀድንና መተጋገዝን ስለሚያዳብሩ፤ ማመን፤መታማንና መተማመንን ስለሚያስችሉ ነው:: የግብረገብ ዋና ዓላማ ባለመተማመን አብሮ መኖር አስቸጋሪ ስለሆነ ማመንን፤ መታመንንና መተማመን መፍጠር ነው:: ይህ ደግሞ በተራው ለሌሎች ብዙ መልካም ነገሮች በር ከፋች ነው:: ባጭሩ የግብረገብ ሕግጋት፤

መርህዎች፤ አስተምህሮዎችና ንድፈ-ሐሳቦች ሁሉ መሠረት እነዚህ ሁለት ምሰሶዎች ናቸው።

ወደ ሌላ ርዕስ ከመሻገራችን በፊት ካነሳናቸው ጉዳዮች ጋር ተያያዥነት ያላቸው ሁለት ነገሮችን ማንሳት ተገቢ ይሆናል። በግብረገብ እሳቤ ውስጥ ሁልጊዜ ባንድ በኩል ቢያንስ ሁለት አማራጭ የማድረጊያ መንገዶች አሉ፤ በሌላ በኩል አድራጊው (ሞራል ኤጀንት) የሚፈልገውን ለማድረግ ከሁለቱ አማራጭ መንገዶች አንዱን የመምረጥ ሙሉ ነፃነት አለው። አንዱ መንገድ ከሞራል አንጻር ትክክለኛ፤ ተገቢ ወይም ተመራጭ መንገድ ነው። የሚጎዳ ሳይሆን የሚጠቅም፤ ለችግር የሚዳርግ ሳይሆን ችግርን የሚከላከል ነው። ሁለተኛው መንገድ በተቃራኒው ትክክለኛ፤ ተገቢ ወይም ተመራጭ ያልሆነ ነው። ምክንያቱም ራስን ወይም ሌላውን ወገን የሚጎዳ ነው። ስለዚህ ማንኛውም ሰው የመጀመሪያውን መንገድ የመምረጥና ሁለተኛውን ከመምረጥ የመታቀብ ሞራላዊ ግዴታ ግዴታ አለበት።

አንዱን ትቶ ሌላውን በመምረጥ ግዴታውን የሚወጣው ያለ ምንም አስገዳጅ ነገር ነው። የሆነ ነገር ይደርስብኛል ብሎ በመስጋት ወይም ቅጣት ይመጣብኛል ብሎ በመፍራት ሳይሆን ይህን መንገድ መምረጥ መልካም ነው፤ ያን አማራጭ መጠቀም ግን መጥፎ ነው በሚል ሕሊናዊ ብይን ነው። ይኸም ሆኖ ወደፊት እንደምናነሳው ሰው ግብረገባዊ ያልሆነ ድርጊት ይፈጽማል። ለጥቅም ያለው ፍላጎትና እኩይ ነገሮች ያልተባረኩ ጋብቻ የሚያደርጉባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ናቸው።

## 5. ግብረገብና ሥነ-ምግባር በኢትዮጵያ ወጣቶች ማንነት ውስጥ

የኢትዮጵያ ወጣቶች የኢትዮጵያ ሕዝብ ውጤትና ነፀብራቆች ናቸው። የሕብረተሰቡ ውጤቶች ቢሆኑም ከተቀሩት የሕብረተሰብ ክፍሎች የሚለዩአቸው በርካታ ነገሮች አሉ። በኢትዮጵያ ወጣትነት ለሕብረተሰቡ ምን ማለት ነው? ለወጣቶች ሕብረተሰብ ራሱ ምናቸው ነው? አንዳቸው ያላንዳቸው የሚኖሩ አይደሉም፤ አንዱ ሌላውን የግድ ይፈልጋል። ምክንያቱም አንዱ ያለ ሌላው ሙሉ አይሆንም። ግን ደግሞ አንዱ ስለሌላው የራሱ አረዳድ አለው።

### 5.1. ስለወጣቶች ግብረገብና ሥነ-ምግባር ያሉ ግምቶች

በርካታ ሰዎች ስለ ኢትዮጵያ ወጣቶች ሞራላዊና ሥነ-ምግባራዊ አቅምና አቋም የተለያዩ ሐሳቦች ይሰጣሉ። ጥቂቶቹን ለምሳሌ ያህል እንጥቀስ። የዛሬ ወጣቶች ግብረገብንና ሥነ-ምግባርን አያውቁም፤ ቢያውቁም ደግሞ አያከብሩም። ፈጣሪን አይፈሩም። ለወላጆቻቸው አይታዘዙም። ታላላቆቻቸውን አያከብሩም። ደካማን አያግዙም። የሀገር ፍቅር ስሜታቸው የተዳከመ ነው። ሥራ አይወዱም። ራሳቸውን

ችግር ፈጣሪ እንጂ ፈቺ ማድረግ አይመቻቸውም። ሌብነትን፣ ስንፍናን፣ ሙስናን፣ ልመናንና የመሳሰሉትን አይጠየፉም። ከግል ጉዳያቸው ውጭ ለሌሎች ኃላፊነት የመውሰድ ስሜት የላቸውም። አንዳንዶቹ ለግል ጉዳያቸውም ቢሆን እንኳን ጠንካሮች አይደሉም፣ በራሳቸው አይተማመኑም ወይም በጥገኝነት ስሜት ተጠቅተዋል። ባጭሩ ለግብረገብ ሕግጋትና ለሥነ-ምግባር መርህዎች አይታዘዙም ወይም አያከብሩም የሚሉ ጉምጉምታዎች በስፋት ይደመጣሉ።

እዚህ ጋ መነሳት የሚኖርበት የተባለው ሁሉ ለሁሉም እውነት ነው ወይ? የሚለው ጥያቄ ነው። እዚህ ላይ ‹‹አዎ እውነት ነው›› የሚያስብሉም፣ የማያስብሉም አሉ። ‹‹የለም፣ ውሸት ነው›› የሚያሰኙም የማያሰኙም አሉ። ከሁሉም በላይ በእንዲህ ዓይነት የጅምላ ፍረጃን እውነት ነው ብሎ ለመቀበልም ሆነ ውሸት ነው ብሎ ላለመቀበል አስቸጋሪ በመሆኑ መግባባት ላይ መድረስ አይቻልም።

በሌላ በኩል በቅርብ ጊዜ የተከሰቱት ችግሮች እንዳሉ ሆነው ሀገርንና ወገንን በማፍቀርና በማክበር ረገድ የኢትዮጵያ ወጣቶች አይታሙም የሚሉ ብዙ ወገኖች አሉ። ሀገራቸውንና ወገናቸው የሚያከብሩና የሚያፈቅሩ መሆናቸውን በከፈሉት የሕይወትና የአካል መስዋዕትነት አስመሰክረዋል። በንጉሣዊው፣ በደርግና በኢህአዲግ ሥርዓቶች ውስጥ ለኢትዮጵያ ልዕልናና ለሕዝብዋ ጥቅምና ፍላጎት፣ መብትና ክብር ሲሚገቱ በአደባባይ የተረሸኑ፣ ታፍነው በመወሰድ ደብዛቸው የጠፋ፣ በየእስር ቤቶች ውስጥ እየተንገላቱ ያለፉ፣ ቋሚ የአካልና የሥነ-ልቡና ጉዳት የደረሰባቸው፣ ከሚወዷት ሀገር የተሰደዱ ወጣቶች ቁጥር ቀላል አይደለም። የሀገራችንን ሕልውናና ልዕልና አስከብሮ የኖረው የመከላከያ ሠራዊት የተገነባው ባብዛኛው በወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ በሚገኙ ዜጎች ነው።

ይህን ሁሉ ግምት ውስጥ ስናስገባ የዚህች ሀገር ሕልውና ጸንቶ የቀጠለው በወጣቶቻችን መስዋዕትነት መሆኑን እንረዳለን። በየጊዜው በተከፈቱብን የወራሪ ጦርነቶች ውስጥ ግንባራቸውን ለጥይት ሰጥተው የሀገራቸውን ክብርና ነፃነት ያስከበሩ ወጣቶች ትላንት ነበሩ፣ ዛሬም አሉ። በተመሳሳይ ሁኔታ ለፈጣሪና ለወላጆቻቸው የሚታዘዙ፣ ታላላቆቻቸውን የሚያከብሩ፣ ደካሞችን ባላቸው አቅም የሚያግዙና ማናቸውንም መልካም ነገሮች የሚሰሩ ወጣቶች አሉ። በተለይ አሁን አሁን እየተለመደው የመጣው የበጎ አድራጎት ሥራዎች ውስጥ እጅግ የሚያኮራ አገልግሎት የሚሰጡ ወጣቶች ብዙ ናቸው።

በርካታ ዜጎችን ከወደቁበት አንስተውና ሰብስበው ደረጃውን በጠበቀ መንገድ የሚንከባከቧቸው ጀግና ወጣቶች በየቦታው አሉ። የሚፈለገውን ያህል አልሆነም ካልተባለ በቀር በና በሥነ-ምግባር በመታነጻቸው ምክንያት የተለያዩ መልካም

አገልግሎቶች የሚሰጡ በርካታ ወጣቶች አሉ። ይኸ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለውና የሚከፈለው ለሀገርና ለወገን ሲባል ነው። ይኸ ሁሉ የሆነው ለሀገርና ለሕዝብ መልካም ነገር ለማስገኘት ስለነበረ ግብረገባዊና ሥነ-ምግባራዊ አንድምታው ጉልህ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ‹‹አዎ፤ ጉምጉምታዎቹ እውነት ናቸው›› የሚል ግምት ያላቸው ወገኖች የሚቀርቧቸውን ምክንያቶች እናንሳ። ምክንያቱም እውነት ነው እንዳይባል ሐሰትም አለበት፤ ሐሰት ነው እንዳይባል እውነትም አለበት። ስለዚህ ይኸን ውዝግብ ለመፍታት ሐሳቡን ለሁለት ከፍለን እንይ። በመጀመሪያ ‹‹የለም፤ ጉምጉምታዎቹ ውሸት ናቸው›› የሚል ግምት ያላቸው ወገኖችን ምክንያት በዝርዝር ለማየት እንሞክር።

በማወቅ ወይም ባለማወቅ በሀገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጥፋት ያደረሱ የኢትዮጵያ ወጣቶች ነበሩ፤ አሉምም። መሠረቱ ከፖለቲካ ጥያቄዎች ወይም ችግሮች ጋር የሚያያዝ ነው። የመብትና የፍትህ፤ የጥቅምና የልማት በሚመስሉ ጥያቄዎች ውስጥ በመሸፈን የሀገርን ሕልውና የሚያፈርስና የሕዝብን ማሕበራዊ መሠረት የሚያናጋ ትርምስ የተካሄዱት ባብዛኛው በወጣቶች መሆኑ አይካድም። ይህ በይበልጥ ጎልቶ የታየው ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ነው። የሆነው ጥፋት ሁሉ የሆነው በፍጹም መገመት በማይቻልበት ሁኔታ ውስጥ ነው። በሀገርና በሕዝብ ላይ የደረሰው ዘግናኝ አደጋ በመጠንና ፍጥነት ሲለካ የኢትዮጵያ ወጣቶች ያደረጉት ነው ብሎ ማመን የሚከብድ ይመስለኛል።

ቀደም ሲል የተደረጉ የኢትዮጵያ ወጣቶች ፀረ-ጭቆና ትግሎች ያተኮሩት በሥርዓት ለውጥ ላይ ነው። አሁን አሁን የሚደረገው የትግል ትኩረት ግን በማውደም ወይም በማጥፋት ላይ ያነጣጠረ ይመስላል። ንጹሀን ሕፃናትና አዛውንቶች፤ ነፍሰ-ጡርና ጡት የሚያጠቡ እናቶች፤ አቅመ-ደካሞች ወዘተ ያለምክንያት ተገድለዋል፤ ሀብትና ንብረት ያለ በቂ ምክንያት ወድመዋል። ከግብረገብና ሥነ-ምግባር አንጻር ሲታይ ይህ የአውዳሚነትና ጨለምተኝነት ስሜት (nihilism) ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባንዳንድ የኢትዮጵያ ወጣቶች ዘንድ የታየው ኢ-ግብረገባዊና ኢ-ሥነ-ምግባራዊ እንቅስቃሴዎች መንስኤ ምንድነው ብለን መጠየቅ ይኖርብናል። ለዚህም ሦስት ነገሮች መንስኤ ሊሆኑ ይችላሉ ብለን ማሰብ እንችላለን። አንደኛው በግብረገብና በሥነ-ምግባር አለመታነፅ፤ ሁለተኛ በማያባራ ድህነትና ጦርነት ምክንያት ተስፋ ማጣት፤ ሦስተኛ የኢትዮጵያ ሕዝብ መነቃቃትና የባዕዳን በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ-ገብነት እየተጠናከረ መምጣት ናቸው።

ከላይ ላነሳነው አብይ ጥያቄ ዋና መልሱ በግብረገብና በሥነ-ምግባር አለመታነፅ ነው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ትርጉም ያለው የግብረገብና ሥነ-ምግባር ትምህርት

አልነበራቸውም፡፡ በዚህ ምክንያት በወጣቶች ላይ ከባድ ጉዳት ደርሶአል፡፡ እነርሱም በበኩላቸው ብዙ ጉዳት በሀገርና ሕዝብ ላይ አድርሰዋል፡፡ በብስለት ማጣትና በጥንቃቄ ጉድለት እጅግ የሚያስቆጩ ጉዳቶችና ጥፋቶች በመንግስት ተቋማትና በእርስ በርስ ግጭቶች የተነሳ በኢትዮጵያ ወጣቶች ላይ ተፈጽመዋል፡፡ በአፍላ ጊዜያቸው ለሀገራቸውና ለወገናቸው በነበራቸው ተቆርቋሪነትና በለውጥ ፈላጊነታቸው ከጨቋኝ ሥርዓቶች ጋር ባደረጉት ፍልሚያ ብዙ ወጣቶች እንደወጡ ቀርተዋል፡፡ ብሩህ አዕምሮ የነበራቸው የሁለትና የሦስት ትውልድ ልጆች ሌሎችን አጥፍተው፤ ለራሳቸውም ጠፍተውና ብዙ ነገራችንን አጠፋፍተው አልፈዋል፡፡ አነሳሳቸው ግን ባብዛኛው ለሀገርና ለወገን ቁጭትና መቆርቆር ነው፡፡ ‹‹ሀገር ለምን ደኸየች፤ ለምን ኋላ ቀረች፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን በአሳፋሪ ድህነት ውስጥ ተደፈቀ፤ ምን ጎድሎአቸው ነው ረሀብና ልመና መታወቂያቸው የሆነው?›› በማለት የሀገር ፍቅር ስሜት ያንገበገባቸውና ሀገራዊ ቀናኢነት ያነሳሳቸው ውድ ዜጎች ነበሩ፡፡

ባለማወቅ ግን ይህ ቁጭት መንገዱን ሳተ፡፡ ድህነትንና ረሀብን ለማጥፋት የተሳለው አዕምሮ የኢትዮጵያ ወጣት ምሁራን፤ ሠራተኞች፤ የሠራዊት አባላትና አርሶአደሮች እንዲጠፋፉ አደረጋቸው፡፡ በየጊዜው የነበሩት የሀገሪቱ የፖለቲካ ኃይሎች የተፈጠሩ ልዩነቶች በአግባቡ የመያዝ አቅም አልነበራቸውም፡፡ የሀገር ቀናኢነትና ተቆርሪነት ሀገር ማጣት የማይገባትን ልጆችዋን እንድታጣ አድርገዋታል፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ወጣቶች ይህን አስቀያሚ ታሪክ ማረም አለባቸው፡፡ ታሪኩ እንዴት እንደምንወድቅ አሳይቶናል፤ የዛሬ ወጣቶቻችን ግን እንዴት እንደምንነሳ የሚያሳይ መንገድና ታሪክ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የዛሬው ትውልድ ያለፈው ትውልድ የሰራውን ስሕተት የማረም እንጂ የመድገም ታሪካዊ ኃላፊነት የለበትም፡፡ ትልቁ ችግራችን ድክመቶችና ስሕተቶችን ለማረም ቶሎ የምንነቃ አለመሆናችን ነው፡፡ ስለዚህ መጥፎ ታሪክ ራሱን ሆኖ ይለፍ፤ የኢትዮጵያ ወጣቶች ግን መልካም ታሪክ ሰርተው ሀገራቸውን መካስ ይኖርባቸዋል፡፡

## 5.2. የኢትዮጵያ ፖለቲካና የኢትዮጵያ ወጣቶች

የኢትዮጵያ ወጣቶች በየዘመኑ በነበሩ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሥርዓቶች ውስጥ፤ የነበሩባቸውን ሕብረተሰብ ሆነውና መስለው በዋናነት በሁለት ጎራ ተከፍለው ተፋልመዋል ማለት ይቻላል፡፡ ይሁን እንጂ ወጣትነት የተለየ መደብ ነበረው ማለት ያስቸግራል፡፡ ከጨቋኝም ከተጨቋኝም መደብ አልነበሩም፡፡ ትግላቸው ለዚህኛው ወይም ለዛኛው መደብ ጥቅምና ፍላጎት ሳይሆን ሀገርን ለድህነት፤ ሕዝብን ለረሀብና እርዛት የዳረጉትን ሥርዓቶች ማስወገድ ነበር፡፡ በእርግጥ ትግሉ ግብታዊ ቢሆንም ለዚህ ወይም ለዚያ ወገን ሳይሆን ለእውነትና ለፍትህ መሆኑ ከሞራልና ሥነ-

ምግባር አንጻር የሚወደስ ነው:: ትግላቸው ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ፍላጎትና ጥቅም ያማከለ በመሆኑ በአሰላለፍ ረገድ ዛሬ ከምናየው ትርምስ የተሻለ ትርጉምና መልእክት ነበረው ማለት ያስደፍራል:: ጭቆና ከኢትዮጵያ ምድር መወገድ ያለበት መሆኑን የተረዳ ቢሆንም በሚወገደው የጭቆና ሥርዓት ምትክ ምን ዓይነት ሥርዓት መፈጠር እንዳለበት የሚያውቅ አልነበረም:: የጠራ እይታ ማጣቱ መስዋዕትነቱን በእጅጉ አገዘፈው::

ለሀገር ልዕልና፤ ለዜጎች መብትና ክብር፤ ለሰላምና ነፃነት በግንብር ቀደምትነት መታገሉ ግን ቋሚ ምስክር ነው:: ሥርዓቶችም ላለመውደቅ በሚያደርጉት መንፈራገጥ ወጣቱን በተለያዩ መንገዶች እየተጠለፉ ጥለዋል:: በእርግጥ ይህ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለነበራቸው የሞራል ልዕልና ቋሚ ምስክር የሚሆን ነው:: የነበረው ሁሉ ዥንጉርጉር ቢሆንም እኛ (ማለትም ከ1960ቹ ጀምረን እስካሁን ያለነው ተውልዶች) ለተተኪ ወጣቶች ጥሩ ምሳሌዎች እንሆናለን የሚል ዕምነት አለን ማለት ያስቸግራል:: ሁሉንም ነገር ከኛ ቅዱ ብለን አንመክራቸውም:: ግን ደግሞ ምንም በጎ ነገር አይገኝባቸውም ብላችሁ አትደምድሙ:: ግቡ ምንም ይሁን ምን፤ አነሳሳቸው ኢትዮጵያንና ሕዝብዋን ለመጉዳት ሳይሆን ለመጥቀም ነበር:: ሀገርንና ሕዝብን ለማዋረድና ለማጥፋት መነሳሳት የመጣው በቅርቡ ነው:: ስለዚህ የተተኪ ትውልድ ወጣቶች መልካም ከነበረውና ካለው ታሪክ መልካሙን ከመጥፎ ለይተው መውሰድ ይኖርባቸዋል::

## 5.3. የወጣቶች ኃላፊነት

ብዙ ጊዜ የአንድ ሀገር የወደፊት ዕጣ-ፋንታ በወጣቶች ትከሻ ላይ ያረፈ ነው ይባላል:: እርግጥ ነው - የነገ ሀገር መሪዎች የዛሬ ወጣቶች ናቸው:: የነገ መሪዎች ስንል የፖለቲካ መሪዎች ማለታችን ብቻ አይደለም:: በሁሉም የሕይወትና የሥራ ዘርፎች ኃላፊነት የሚረከቡ ዜጎች ማለታችን ነው:: ነገ ሀገርን የሚመሩት ግን ዛሬ በሚኖራቸው ወይም በሚያደርጉት ዝግጅት ነው:: ወገንን የሚያከብሩና የሚያስከብሩ፤ ሀገርን የሚፈቅሩና የሚያኮሩ፤ ለሰው ልጅ ሁሉ አክብሮትና ቅንነት ያላቸውን ወጣቶች ለማፍራት የምንችለው ማንነታቸውን በመገንባት ነው:: ዛሬ ያልሰጠናቸውን መልካምነት ነገ አምጣችሁ ውለዱ ልንላቸው አይገባም:: ዜጋን መቅረጽ ጥበብን ይፈልጋል፤ ሳይንሳዊ ዕውቀትን ይሻል፤ ግብረገባዊ ግንዛቤና ሥነ-ምግባራዊ ትጥቅን ይጠይቃል::

አሁን አሁን ‹‹ወጣት ድሮ ቀረ›› የሚል ብሶት-መሰል ነገር መስማት የተለመደ ነው:: ምን ማለት እንደሆነ በእርግጥ ማወቅ ያስቸግራል:: ስንገምተው ‹‹ከዛሬው ወጣት የድሮ ወጣት ይሻላል›› የሚል መልእክት ያለው ይመስላል:: ይህ እውነት

ነው ወይ? ይኸም በራሱ ወደ ሌላ ጥያቄ ይወስደናል - የድሮው ወጣት ከዛሬው ወጣት ተሽሎ የሚገኘው በምንድነው ወይም ለምንድነው ብሎ መጠየቅ ይቻላል - በትምህርት ነው፤ በሥራ ነው፤ በዲስፕሊን ነው፤ በባሕርይ ነው፤ በውጤት ወይም በስኬት ነው ወይስ በምን? ይኸ ጉዳይ በጣም ሰፊ ስለሆነ በማጥበብ፤ የድሮውንና የዛሬውን ወጣት ከግብረገብና ሥነ-ምግባር አንጻር ለማየት እንሞክራለን።

ቀደምት አባቶችና እናቶቻችን በነበራቸው አቅምና ዕውቀት እኛን አፍርተው፤ ከዚህ አድርሰውናል። እኛም በተራችን የሚቀጥለውን ትውልድ የማድረስ ኃላፊነት አለብን። እኛ መልካምም ሆነ መጥፎ ወርሰናል። መጥፎን ጭምር የወረስነው ቀደምት አባቶችና እናቶች የነበራቸው የሞራል ግንዛቤና ዕምነት ዝቅተኛ ስለነበር ነው። ለነገሩ ከእንከን ፍጹም የፀዳ ሕብረተሰብ ይኖራል ተብሎ አይታሰብም። የዛሬ ወጣቶቻችን የነበረውን ላለመቀጠል ራሳቸውን በግብረገብ ሕግጋትና በሥነ-ምግባር መርህዎች ማነጽና ማረቅ ይጠበቅባቸዋል። የኢትዮጵያ ወጣቶች የሚገባቸው የሞራልና የሥነ-ምግባር ትምህርት በሚፈለገው መጠንና ዓይነት በትምህርት ቤት የሚሰጣቸው አልነበረም። ትርጉም ባለው መንገድ በሞራል ዕሴትና በሥነ-ምግባር መርህዎች የመኮትኮትና የመታነፅ ዕድል አልነበራቸውም። ይህ ማለት ግን ገደብ የለሽ ወይም ልቅ ነፃነት ነበራቸው ማለት አይደለም። የራሱ ውስንነት ቢኖረውም በወላጆች ጥብቅ ቁጥጥር፤ በሕብረተሰቡ የዕሴት ሥርዓት (value system) ክትትል እና በመንግሥት አስተዳደራዊ ቁጥጥር ምክንያት በዲስፕሊን የታነጸ ማንነት ነበራቸው።

ይሁን እንጂ ይህም ራሱ በዜግነት በነበራቸውና ባላቸው መብት፤ ክብርና ነጻነት ላይ የተወሰነ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው። ይህ አያያዝ ምኞት የማይሰጥ በመሆኑ ወጣቶችን ወደ ብጥብጥና አመፅ ይገፋቸው ነበር። ውስን ወጣቶችን በማብቃት ረገድ ወላጆች/አሳዳጊዎች፤ ቤተ-እምነቶችና የመንግሥት ተቋማት በቅርበት እንደሚከታተሉ ቢታወቅም ቁጥጥሩ ነጻነትን የሚደፈጥጥ እንጂ የሚያከብር አልነበረም። የቁጥጥሩ እንጂ የነጻነቱ ጠቀሜታ ጎልቶ የሚታያቸው አልነበረም። ይህ በወጣቶች እምቅ ችሎታ ላይ የተወሰነ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው። በዚህ ምክንያት ችሎታቸውን በሚፈለገው መጠን አውጥተው መጠቀም ካለመቻላቸውም በላይ ብዙዎቹ ቁጥጥሩ በፈጠረው ፍርሀትና ሥጋት በመሸማቀቅ የሚኖሩ እንጂ በራሳቸው በመተማመን የሚንቀሳቀሱ አልነበሩም። ትግላቸውን መራር ከሚያደርጉ ነገሮች መካከል አንዱ ይህ ነው።

## 5.4. ስለወጣቶች የሚነሱ ጥያቄዎች

በመጀመሪያ ወጣቶች ስለራሳቸውና ስለ ሌሎች ምን ያህል ያውቃሉ? እናውቃለን ስለሚሉት ነገር ምን ያህል እርግጠኞች ናቸው? ማነው የሆኑትን እንዲሆኑ ያደረጋቸው ወይም ማነው ማንነታቸውን የቀረጸላቸው? መነሻቸውንና መድረሻቸውን በትክክል ያውቃሉ? ከመነሻቸው እስከ መድረሻቸው ያለውን የጉዞ ውጣ-ውረድ በትክክል ይረዳሉ? አንድ ወጣት በወጣትነት ዘመኑ ምን መስራትና ማን መሆን ይፈልጋል? ሕብረተሰቡ ራሱ ወጣቱ ማንና ምን እንዲሆን ይፈልጋል?

ማንኛውም ወጣት እንደማንኛውም ሰው ለራሱ የሚበጀውን ወይም የሚጠቅመውን ይመኛል፣ የሚጎዳውን ይጠላል:: ማንና ምን ሆኖ፣ እንዴትና በምን ሰርቶ ከተመኘው ደረጃ ይደርሳል? የኢትዮጵያ ወጣቶች ኢትዮጵያ ምን እንድታደርግላቸው ወይም ምን እንድትሆንላቸው ይፈልጋሉ? እነርሱስ ኢትዮጵያን ምን ቢያደርጉላት ይረካሉ? ስለቤተሰቦቻቸው፣ ስላሉበት ማሕረሰብ፣ ስለአካባቢውና ስለሀገራቸው ያላቸው ግንዛቤ ምን ያህል ምክንያታዊ ነው? ስለራቸው እንጂ ስለሌሎች ብዙ አያሳስባቸው ይሆን? እነዚህ ያነሳናቸው ጥያቄዎች ከግብረገብና ሥነ-ምግባር አንጻር መነሳት ያለባቸው ናቸው ለማለት እንጂ በዚህ ዝግጅት ለሁሉም ምላሽ የሚሰጣቸው ሆነው በመገኘታቸው አይደለም::

## 6. ወጣቶች መጠየፍ የሚገባቸው ድርጊቶችና ባሕርያት

ወጣቶች ከግብረገብና ከሥነ-ምግባር አንጻር ከመሆንና ከማድረግ መታቀብ የሚኖርባቸው ነገሮች በጣም ብዙ ናቸው:: አንገብጋቢ ከሆኑት መካከል ጥቂቶችን ለምሳሌነት ማንሳት ተገቢ ነው::

## 6.1. መገዳደል ለሰብአዊ ፍጡር አይመጥንም

ሁለንተናዊ ከሆኑ የግብረገብ ሕግጋት አንዱ ‹‹አትግደል›› ይላል:: ይህ በተለያዩ የቅዱሳን ወይም የዕምነት መጻሕፍት ውስጥ ተጽፎም እናገኛለን:: መገዳደል ፀረ-ግብረገብና ሥነ-ምግባር ስለሆነ ለሰው ልጅ የሚመጥን ተግባር አይደለም:: በፈጣሪ ፊትም ሆነ በሰው ዘንድ ወደር የማይገኝለት ጥፋት ወይም ኃጢአት ነው:: ጥፋት ጥበብ አይጠይቅም፣ ዕውቀት አይፈልግም፣ ጀግንነት አይደለም፣ ዝናም ሆነ ክብር አያስገኝም:: የሚያኮራ ሳይሆን የሚያሳፍር ነው:: ባጭሩ የሰብአዊ ፍጡር ዓይነተኛ ባሕርይ በእንዲህ ዓይነት ፀያፍ ተግባር አይገለጽም:: ጅላጅሎችና በደመ-ነብስ የሚንቀሳቀሱ እንስሳት ወይም ፍጡራን የሚደርጉት እንጂ ከሰው ተፈጥሮና በሰዎች ተጠብቆ ያደገና የኖረ ሰው ሊያደርገው የሚገባ አይደለም::

የሰው ልኩ ሰብአዊ ፍጡርነቱ ነው። የሰው ልኩ መልካምነትና ዕድገት ነው። የሰው ልኩ ሰላምና ፍቅር ነው። የሰው ልኩ ጥበብና ውበት ነው። የሰው ልኩ መከባበርና መደጋገፍ ነው። የሰው ልኩ ማመዛዘንና ማገናዘብ ነው። የሰው ልኩ ርህሩህነትና ጨዋነት ነው፤ የሰው ልኩ ዕውቀትና እውነት ነው። እነዚህን ሁሉ በጎ ነገሮች የምናገኘው በሰው ውስጥ ብቻ ነው። የማሰብ ችሎታ በሌላቸው ሌሎች ፍጥረታት ውስጥ ሳይሆን የማሰብ ችሎታ ባለው ሰው ውስጥ ብቻ ነው። የላቀ ፍጥረት መሆን የሚያስችለው አቅም እያለው የማሰብ ችሎታ የሌላቸው ፍጥረታት ከሚያደርሱት ችግር የከፋ ችግር ሆን ብሎ የሚያደርስ መሆኑ ሰውን በእጅጉ ያሳንሰዋል። የሰው ልጅ ሲገዳደል እነዚህ መልካም የሆኑ ሰውኛ ባሕርያቱ ወደ አራዊት ጠባይ ይቀየራሉ። ከሰብአዊ ሰገነት ይወርዳል። ስብዕናው የቁመና ብቻ ይሆናል። ስለዚህ መገዳደል ለሰው ልጅ በፍጹም የሚመጥን አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዓይነት ሰብአዊ ባሕርያት የጎደሉት ፍጡር ያደርገዋል።

በእርግጥ በአጋጣሚ የሰው ሕይወት በሌላ ሰው እጅ ሊጠፋ ይችላል፤ ሳይታሰብ ራስን ለመከላከል ሲባል የሰውን ሕይወት ማጥፋት ሊያጋጥም ይችላል። አሁን እያየን ያለነው መገዳደል ግን የሰውን ስብዕና ጥያቄ ውስጥ የሚከት ነው። በተለይ የኢትዮጵያ ወጣቶች ስለዚህ ነገር አጥብቀው ሊያስቡበት ይገባል። በአሰላለፋቸው ለጊዜው ለሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል። አንደኛው ከስብዕና፤ ከሀይማኖት፤ ከግብረገብና ሕጎች አንጻር ሰውን መግደል የመጨረሻው ከፍተኛ ወንጀልና ኃጢአት ነው ብለው የሚያምኑትን ባንድ በኩል፤ ‹‹የኔ ጉዳይ የተሰጠኝን ተልዕኮ መፈፀም እንጂ የሌላውን ሰው ሕይወት የማኖር ወይም ያለማኖር ጉዳይ አይደለም›› የሚል ዕምነት ያላቸውን በሌላ በኩል የሚይዝ ነው።

የመጀመሪያው መሆንና መደረግ የሚገባው ስለሆነ ግብረገባዊ ነው። ሁለተኛው ግን መሆንና መደረግ የሌለበት በመሆኑም ኢ-ግብረገባዊ ነው። ለወጣት ኢትዮጵያውያን ማስተላለፍ የምፈልገው መልእክት ግን አንድ ነው። ሰውን መግደል መገደልንም ይጋብዛል። ማብቂያ የሌላቸው ቂምና በቀሎች ሰንሰለት በመፍጠር የፍጅትና ውድመት መሠረት ይሆናል። ይኸ ለኢትዮጵያውን እንግዳ ነገር አይደለም። ከዚህ መጠፋፋት ውድቀት እንጂ ትርፍ እንዳላገኘን በዚህም ሆነ በዚያ የተሰለፉ ወጣቶች ያውቃሉ። ለመሆኑ ይህ የመጠፋፋት ምስጢር ለወጣቶቻችን ገብቶአቸው ይሆን? በመገዳደል ሰዎች ማንን ምን አሳጥተው ለማን ምን አስገኙ? ጉዳያችን ነው ብለው ተቀብለው ይሆን? እውነት ለዚህ ሁሉ እልቂትና ውድመት በቂ የሚሆን ምክንያት አለ? መቼ ነው የሚቆመው? ማነው የሚያቆመው? የኢትዮጵያ ሕዝብ በውል በማያውቀው ድብቅ ጉዳይ ወጣቶቻችንን በዚያና በዚህ የሚቃጠሉት እስከ መቼ

ነው? በዚህም ሆነ በዚያ ወገኖቻችንን እያቀጣጠሉ የራሳቸውን ዳቦ የሚጋግሩ ወይም ትርፍ የሚሰፍሩ ጥቂቶች እነማን ናቸው? እነርሱ ለክፋት ከነቁት በላይ ወጣቶቻችን ደግሞ ለመልካም ነገሮች ሁሉ ከእነርሱ በላይ ልቀው መገኘት አለባቸው።

## 6.2. ሀገራዊ ዕሴቶችን አለማክበር

በትዕግስት የመደማመጥ ልምዳችን በእጅጉ እየተዳከመ ነው። የኢትዮጵያ ወጣቶች የማዳመጥ፣ የመደመጥና የመደማመጥ ባሕላቸው መዳበር አለበት። መደማመጥ ከሌለ መረዳዳት፣ መግባባትና መስማማት አይኖርም። በተለይ ከሀገራችን የፖለቲካ ሊሂቃን መካከል ብዙዎቹና ቁንጮዎቹ መናገር እንጂ ማዳመጥ አይመቻቸውም። ይህ ችግር በሀገራችን ፖለቲካ ባሕል ውስጥ ያለ ካንሰር ነው ሊባል ይችላል። ለብዙዎቻችን እስከገባን ድረስ አንዱ የኢትዮጵያውያን የግብረገብና የሥነ-ምግባር ችግር ያለመደማመጥ ነው። ብዙዎቹ ተናጋሪ እንጂ አድማጭ መሆን አይፈልጉም። ንግግር ደግሞ የተፈለገውና የሚፈለገው ለመደማመጥ ነው። መደማመጥ አስፈላጊ የሚሆነው ለመግባባትና ለመተማመን ነው፣ ወደ አንድ የጋራ ስምምነትና አቋም ለመምጣት ነው። በተለይ ፖለቲከኞቻችን ብዙ መናገራቸውን እንጂ መደመጣቸውን አያረጋግጡም። የሚያዳምጥ በሌለበት መናገር ግን ምን ጥቅም የለውም። ተናጋሪ እንጂ አድማጭ በሌለበት ቦታ ሊኖር የሚችለው ከልክ ያለፈ ጩኸት ነው። መደማመጥ ለምን ተጠላ፣ አለመደማመጥ ለምን ተወደደ?

ለምሳሌ ያህል በቅርቡ በፌዴራል መንግስትና በትግራይ ክልላዊ መንግስት/ሕወሓት መካከል የተነሳውን አለመግባባትና ጦርነት እናስታውስ። አሁን የተፈጠሩት ችግሮች እንዳይፈጠሩ ጥረቶች ተደርገዋል። የሀይማኖት አባቶች፣ የሀገር ሽማግሌዎች፣ አባገዳዎች፣ ታዋቂ ዜጎችና ምሁራን ‹‹ግጭቶችና ችግሮች በሰላም ይፈቱ›› ብለው በተደጋጋሚ ተማጽነዋል። እናቶች ከተለያዩ የሀገራችን ክፍሎች ተወጣጥተው የእናትነትን ርህራሄና ዕሴት በሚገልጹ መንገዶች ለሰላም ሲሉ ከአንገታቸው ዝቅ ብለው ተማጽነዋል። ይህን ልብ የሚነካ ተማጽኖ በዓይናችን አይተናል። ይኸ ሁሉ ሆኖ ለሰላም የተደረገው ጥረት ፍሬ ሳያፈራ ቀረ። ትንሽ የግብረገብና የሥነ-ምግባር ንጥረ ነገሮች በውስጣችን ቢኖር ቢያንስ ቢያንስ ለእናቶች ክብርና ፍቅር ሲባል ከአንገት ዝቅ ብሎ ጥያቄያቸውን በአግባቡ ማስተናገድ በተገባ ነበር። በዚህ ምክንያት ብዙ ሕይወት አለቀ፣ ግዙፍ ሀብት ወደመ፣ ሚሊዮኖች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለመከራና ሥቃይ ተዳረጉ። ማን ምን አተረፈ? ማን ምን ከሰረ? ትልቅ ዋጋ የነበረውና ሀገርንና ሕዝብ ከደረሰው መከራ ሁሉ መታደግ የሚችለው የሀገር-በቀል የግጭት ማስወገጃ ጥረት ከግምት ሳይገባ ቀረ። ዋጋ አሳጣነው። ከዚህ ሁሉ

ከጠመንጃ ሻጮች በቀር የከሰረ እንጂ ያተረፈ የለም። አለመደማመጥ ያለመከባበርና አለመፈቃቀድ ማሳያ ነው።

በሀገራችን የሆነውና እየሆነ ያለው ፖለቲካ መሆኑን እጠራጠራለሁ። ፖለቲካ ውስጥ ሰውኛ ማንነት አለ። በሀገራችን በነበረውና ባለው የእርስ ጦርነት ከሰውኛ ማንነት ውጭ የሆነ ማንነት አለበት።

## 7. ወጣቶች መሆንና ማድረግ የሚኖርባቸው ነገሮች

የኢትዮጵያ ወጣቶች ከግብረገብ ሕግጋት አንጻር መሆን ያለባቸውንና መሆን የሌለባቸውን፤ ማድረግ ያለባቸውንና ማድረግ የሌለባቸውን ለይተው መረዳት አለባቸው። መሆንና ማድረግ የሚጠበቅባቸው በጣም ብዙ ነገሮች አሉ። በሀገራችን የዕሴት ሥርዓት (value system) ውስጥ ከወጣቶችም ሆነ ከሌሎቻችን የሚጠበቁ ግብረገባዊ ግዴታዎች መካከል ፈጣሪን መፍራትና ማመስገን፤ ወላጅን ማክበር መንከባከብ፤ ማንኛውንም ሰብዓዊ ፍጡር ማክበር፤ ለሀገርና ለዜግነት ፍቅርና ክብር መስጠት እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። እዚህ ለአብነት የምናነሳቸው ግን የኢትዮጵያ ወጣቶች ዛሬ በሀገሪቱ ውስጥ ከሚታዩ ሁኔታዎች ጋር የሚገናዘቡ ግብረገባዊና ሥነ-ምግባራዊ ኃላፊነታቸው መካከል ጥቂቶችን ነው። መሆንና ማድረግ ከሚጠበቅባቸው ነገሮች መካከል ጥቂቶቹን በምሳሌነት እናንሳ።

### 7.1. መልካምነትን መውረስና ማውረስ

ወጣቶች ከቀደምቶቻቸው መውረስ የሚገባቸውንና የማይገባቸውን ለይተው መረዳት ይጠበቅባቸዋል። የወጣቶች ግብረገባዊና ሥነ-ምግባራዊ፤ ትውልዳዊና ታሪካዊ ግዴታ መልካም መልካሙን መርጦ መውሰድ፤ መጥፎ መጥፎውን መርጦ መጣል ነው። በሕዝቦች መካከል የተዘረጉ የጥላቻ መረቦችን በመበጣጠስ ረገድ ግንባር ቀደሞች መሆን ይጠበቅባቸዋል። ነገ ከዛሬ የተሻለ መሆን የሚችለው ዛሬ በሚገነባው የፍቅር መሠረትና በሚፈርሰው የጥላቻ ግድግዳ ልክ ነው። እስካሁን እንደ ነበሩ ትውልዶች የመከራ ቀንበር ተሸካሚዎች ላለመሆን ወጣቶቻችን ልባቸውን ለፍቅርና ለሰላም፤ አዕምሮአቸውን ለዕውቀትና ለጥበብ ክፍት ማድረግ አለባቸው። ሀገርም ወጣት ዜጎችዋን ማዘጋጀት የሚኖርባት በአካባቢያቸው ለሚኖራቸው ግዴታ ብቻ ሳይሆን በሀገርና በዓለምአቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን የሚያስችል አቅም እንዲታጠቁ ለማድረግም ጭምር መሆን አለበት።

ዓለማችን ብዙ ፀጋዎች አሏት፤ ተግዳሮቶችም አሉባት። የኢትዮጵያ ወጣቶች ፀጋዎቹን መቋደስ እና ተግዳሮቶችን መቋቋም የሚያስችል ቁመና ሊኖራቸው ይገባል። በዚህ ረገድ የራስን አካልና አዕምሮ መጠበቅና መገንባት የምርጫ ሳይሆን

የግዴታ መሆን አለበት። ለምሳሌ በስፖርት ረገድ የኢትዮጵያ ወጣቶች እጅግ ከፍተኛ እምቅ ኃይል ወይም ችሎታ እንዳላቸው ይታሰባል። በዚህ ረገድ ሀገሪቱም ከፍተኛ ልምድና ተሞክሮ አላት። ዓለም ለኢትዮጵያ ወጣቶች ከምትሰጣቸው በርካታና ከፍተኛ ፀጋዎች መካከል አንዱ ነው። በትንሽ ነገርና መንገድ ራስን በማብቃት ዓለም ያለ ገደብና አድልዎ የምትሰጠንን ጸጋ መቋደስ ብልህነት ነው።

## 7.2. አካልንና አዕምሮን ከጉዳት መጠበቅ

የሰው ልጅ የሚጨበጥና የሚዳሰስ አካል አለው፤ የማይዳሰስ አዕምሮ ባለቤትም ነው። በተፈጥሮ ባሕርያቸው ተቃራኒ ቢመስሉም በሰው ማንነት ውስጥ አንዱ ያለሌላው ሊኖር አይችልም። ሁለቱም በግብረገብ ሕግጋትና በሥነ-ምግባር መርህዎች መጠበቅ አለባቸው። አካላቸውና አዕምሯቸው በስንፍናና በተንኮል ቁጥጥር ሥር እንዳይወድቁ መጠበቅ ግዴታቸው ነው። አዕምሮአችን አካላችንን፤ አካላችንም በተራው አዕምሮአችንን መጠበቅ አለበት። ያንዱ መቸገር ለሌላው ፈተና ነው። በአካል ብቻ ሳይሆን በመንፈስም ጤናማና ጠንካራ መሆን፤ በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በአካልም ብርቱ መሆን እጅግ አስፈላጊ ነው። አንዱ ያለሌላው ምሉዕ አይደለም። ስለዚህ ወጣቶች አካላቸውንና አዕምሮአቸውን ከማንኛውም ጉዳት መጠበቅ ቁጥር አንድ ግዴታቸው መሆኑን መረዳት አለባቸው። የመጡባትን ዓለም አጣጥመው ሊኖሩባት የሚችሉት ይህ ሲሆን ብቻ ነው።

በአካል ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ነገሮች በርካቶች ናቸው። ውጫዊ የሆኑትን በመተው ሰው በራሱ ውስጥ የሚፈጥራቸውን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። በተለያዩ ሱሶች መጠመድ አካልን ለጉዳት ይዳርጋል። አጫሽ መሆን፣ በመጠጥ፣ በአደንዛዥ ዕፅና በልቅ ወሲብ መጠመድና በስንፍና ቁጥጥር ስር መውደቅ ለተለያዩ አካላዊ አደጋዎች ያጋልጣሉ። የአካል ጉዳት ለመንፈስ ጉዳት ያጋልጣል። በመንፈስ መጎዳት በተራው ለአካል መዳከም ምክንያት ይሆናል። ሁለቱም ከገንዘብና ከተለያዩ ነገሮች ጋር በመወሳሰብ በበሽታ መለከፍን፣ አቅመ-ቢስነትን፣ የመንፈስ ስብራትንና ያለጊዜ መቀጨትን ያስከትላሉ። ስለዚህ ወጣቶች አካላቸውን ከተለያዩ ጉዳቶች፣ አዕምሮአቸውን ከእኩይ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች ጥቃት መጠበቅ የግብረገብ ግዴታቸው ነው።

ዓለም ብዙ የሚያብረቀርቁና ስሜትን የሚሰርቁ አታላይ ነገሮች የበዙባት ናት። ወጣትነት ደግሞ ለእንዲህ ዓይነት ዓለም ያለው ተጋላጭነት የሰፋ ነው። በዚህ ላይ ውስብስብ ፍላጎቶችና ድህነት ተጋብተው የሚፈጥሯቸው ፈተናዎች ብዙ ናቸው። በልካችን መኖር የምንችለው ከሚያሳስቱ ነገሮች መጠበቅ የሚያስችል አቅም ሲኖረን ነው። ምክንያታዊ አቅማችን ተጠቅመን ከኋላና ከፊት፣ ከላይና ከታች ያሉ ነገሮችን

መስተጋብር በትክክል በመረዳት መንቀሳቀስ ስንችል ሕይወት የሚገባትን ብርሀን ማግኘት ትችላለች። ወጣቶች ሕይወታቸውን መምራት የሚኖርባቸው በደመ-ነብስ ወይም በዘፈቀደ ሳይሆን በምክንያትና በዕውቀት፤ በጥበብና በሥነ-ምግባር መሆን አለበት።

## 7.3. ወጣትነትና ጊዜ

በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ የሚባክኑ ነገሮች አሉ። በዋዛ በፈዛዛ ከሚባክኑት ነገሮች መካከል አንዱ የሆነውን ጊዜን ወስዶ ማየት ይቻላል። ተፈጥሮ ከሰጠችን ብዙ ፀጋዎች መካከል ጊዜ አንዱ ነው። ጊዜ በሀገራችን እንደ ፀጋ ወይም እንደ ሀብት ስለማይታይ በእጅጉ ይባክናል። ሲባክን ደግሞ የምንጎዳው እኛ እንጂ ራሱ ጊዜ አይደለም። ጊዜ ለራሱ የሚገደው ነገር የለም። ጊዜ የሚኖረው ለኛ ሲል አይደለም፤ እግረ-መንገዱን ለእኛም ይኖራል። ለኛ መኖር ጊዜ ወሳኝ ነው። ያለ እርሱ እኛ ምንም ነን። ከመወለዳችን በፊት ጊዜ ነበር። ግን አልኖርንበትም፤ ምክንያቱም የኛ አልነበረም። እኛ ከሞትን በኋላም ጊዜ መኖሩን ይቀጥላል። እኛ ግን አንኖርበትም፤ ምክንያቱም በሕገ-ፍጥረት መሠረት ያ ጊዜ የሚገባን አይደለም። የኛ ጊዜ ዛሬ የምንኖርበት ነው። በምክንያት እንጠቀምበት። ስለሚገባን እንድንኖርበትና ታሪክ እንድንሰራበት የተሰጠን ነው።

እኛ ስንጠቀምበት ያለማናል፤ ስናባክነው ያጠፋናል። ወጣቶች የወጣትነት ጊዜያቸውን በአግባቡ መጠቀም አለባቸው። ማንምና ምንም በየትኛውም መንገድ የማይነጥቃቸው ነገር ቢኖር ጊዜ አንዱ ነው። ለሁሉም የተሰጠ ፀጋ ነው - ጊዜ። ይሁን እንጂ ለጊዜ የምንሰጠው ዋጋና ከጊዜ የምናገኘው ጥቅም በኛ አመለካከትና አጠቃቀም ይወሰናል። ጊዜ ምን ጊዜም ቢሆን የማናጣው ነው ብለን ማሰብ አይገባም። በእርግጥ በሕገ-ፍጥረት ያልነበርንበትና የማንኖርበት ጊዜ አለ። ይኽ የሚያሳስብ አይደለም። የሚያሳስበን በስንፍናችን ምክንያት የምናጣው ነው። ወጣትነት በራሱ ወርቃማ ጊዜ ነው። የሚያምርና የሚያጓጓ ብቻ ሳይሆን በተስፋና በትኩስ ጉልበት፤ የሚደምቅ ፍላጎትና ግለት ባለው መንፈስ የተሞላ ነው። በምክንያት ከሰራንበት ታሪክን እናንጽበታለን። በአግባቡ ጥቅም ላይ ካላዋልነው ግን የሚያሳዝን ዋጋ እንከፍልበታለን። የእያንዳንዱ ሰው ማንነት ወይም ዋጋ የሚታሰበው በተጠቀመበት ጊዜ ልክ ነው ማለት ይቻላል። ስለዚህ ወጣቶች መጪውን ጊዜ በብሩህ ተስፋ ግቡበት።

## 7.4. ወጣቶች ሀገራቸውን ማክበር

ሀገር እናትና ፍቅር ናት። ወልዶ ለማሳደግ እጅግ የሚከብድ መስዋዕትነት የሚጠይቅ ነው። ሀገር እያንዳንዱን ሰው ሁለት ጊዜ የምትወልድ ናት ብሎ ማሰብ ይቻላል። ምክንያቱም ወላጆቹን ወልዳችዋለች፤ እርሱንም ወልዳዋለች። የእርስዋ እናትነት ውስን ሳይሆን ተሻጋሪ፤ ነጠላ ሳይሆን ድርብ ነው። በእናትና በልጅ መካከል ያለው ፍቅር የፍቅሮች ሁሉ ገዢና ወሰን ነው። አፈር ይቅለላትና ራስዋ ፍቅር የሆነችው አርቲስት ብዙነሽ በቀለ ‹‹የእናት ውለታዋ …. ›› የሚለው ዘፈንዋ ይህን እውነት በሚገባ ይገልጻል። እናት ለልጅዋ ያላት ፍቅር ልክ የለውም። እጅግ በጣም ጥልቅ ነው። በዓለም ላይ ያለው መልካም ነገር ለልጅዋ መሆን ቢችል ፈቃድዋ ነው። ሀገርም ለልጆችዋ እንዲሁ ናት። አንድ የፈረንጆች አባባል አለ። ‹‹ዓለማችን እናቶቻችንን ትፈልጋለች››። እውነት ነው፤ ይህ መሆን አይችልም እንጂ፤ መሆን የሚችል ቢሆን ሕይወት ለሰው ልጅ ሁሉ መልካም ትሆን ነበር። እናቶች በእናትነት ንጹሕ አዕምሮ፤ ልብና ሕሊና እንዳላቸው ይታሰባል።

እናት ልጅዋን መጉዳት እንደማይታሰባት ሁሉ ልጅ እናቱን የሚጎዳ ድርጊት እንደማይፈፅም ይገመታል። ይልቁንም ሀገር በእናትነትዋ የሚያከብሯትና የሚንከባከቧት፤ የሚያለሟትና የሚሟገቱላት፤ የሚጠብቋትና የሚሞቱላት ናት። ሀገር ከወጣቶችዋ እነዚህን ሁሉ መልካም ነገሮች ትጠብቃለች። ይህን ማድረግ ለወጣቶች ግብረገባዊ መብትና ግዴታ ነው። ሀገርን ማፍቀርና ማክበር ከከንፈር ሳይሆን በልብና በሕሊና ነው። ፍቅር ከእናት ወደ ልጅ፤ ከልጅ ወደ እናት የሚፈሰው በልብ ነው። እናት ለልጅዋ የምትሰስተው እንደሌላት ሁሉ ልጅም ለእናቱ የሚሰስተው ነገር የለውም።

በዘመናዊ ታሪክዋ ውስጥ የኢትዮጵያ ወጣቶች ለሀገራቸው ያላቸው ፍቅርና ተቆርቋሪነት የጎላ ቦታ እንዳለው ይታወቃል። በተለይ በፖለቲካ ጥያቄዎችና ትግሎች ውስጥ ለተፈጠሩት ለውጦች አንቀሳቃሽ ሞተሮች ነበሩ። ሀገሪትዋን ተለይቷት የማያውቀውን ምስቅልቅልና ትርምስ የፖለቲካ ሁናቴ ዝም ብለው አልፈውት አያውቁም - ታግለውታል፤ ሕይወታቸውንና አካላቸውን ገብረውበታል። ለሀገር መቆርቆር ግን ብዙ በሆኑ መንገዶች የሚገለጽ ነው። ራስን መልካም ዜጋ ከማድረግ ይጀምራል። ራስን ማጠናከርም ሆነ ማዳከም የሚጀምረው በራስ ሥነ-ልቡና ወይም አዕምሮ ውስጥ ነው። ወጣቶች ለሀገራቸው የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ አሳንሰው ማየት የለባቸውም። ቢያንስ ራስን በአግባቡ መያዝና መቻል ራሱ አስተዋጽኦ ነው። ለሀገር የሚደመር አስተዋጽኦ ማድረግ ከተሳናቸው ቢያንስ ችግር ከመሆን መታቀብ ይገባቸዋል።

በመሠረቱ እያንዳንዱ ሰው ከሆነ ችሎታ ጋር የተፈጠረ ነው። የሚሆነውንና የሚችለውን ፈልጎ የማግኘት ጉዳይ ካልሆነ በቀር በተፈጥሮ ደካማ ሆኖ የተፈጠረ የለም። ወጣቶቻችን ስለሀገራቸው ለራሳቸው መንገር የሚኖርባቸው ብዙ መልካም ነገሮች አሉ። ኢትዮጵያ ራስዋን አስከብራ የኖረች ሀገር ናት። ይህ ብዙዎች ያላገኙት ፀጋ ነው። ለልማት፤ ለውበት፤ ለፈጠራ፤ ለፍቅርና ለሰላም የሚያመቹ በርካታ ሀብቶችና ዕሴቶች አሏት። የተፈጥሮ ሀብትዋ በንጽጽር ሲታይ ገና ቱባ ነው። አልተነካም ማለት ባይቻልም ብዙ የተጎዳ አይደለም።

ሥነ-ምህዳራዊ ሚዛኑ የተዛባ ቢሆንም፤ ወደነበረበት ለመመለስ ብዙ ርቀት መጓዝና ከባድ ድካም የሚጠይቅ አይደለም። በቋንቋ፤ በሀይማኖት፤ በብሔርና ብሔረሰብ፤ በባህልና በመሳሰሉት የሚለያዩ ሕዝቦች አሏት። ይህ ካወቅንበት ግዙፍ ሀብት፤ ማራኪ ውበትና የማይደፈር ጉልበት ነው። የሕዝቡ ባሕልና አኗኗር አሁንም ቢሆን ለተፈጥሮ ቅርብ ነው። በአንዳንድ መርዛማና ጎጂ ነገሮች ያልተበከሉ ብዙ የተፈጥሮ አካባቢዎች ለምሳሌ ወንዞች፤ ሐይቆች፤ የውኃና የየብስ አካላት አሉ። እምብዛም ያልተበከለ አየር አለ። የደን ሀብትን በብዛት በማልማት ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚመለሱ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች አሉ። የውኃ ሀብትን በአግባቡ በመጠቀም ከነዳጅ ሀብት ያልተናነሰ ገቢ ማግኘት ይቻላል። ሀብታም ሀገሮች አሁን ካሉበት የዕድገት ማማ የደረሱት ብዙ ነገሮች አጥፍተው ነው። ኢትዮጵያን ለማልማት ግን ብዙ ነገር ማጥፋት የሚያስፈልግ አይደለም።

የዚህ ሁሉ ፀጋ ባለቤት የሆነችው ኢትዮጵያ ምን ሆና ደኸየች? እስካሁን ይኸን ሁሉ ፀጋ ይዘን ሀብታም መሆን ያልቻልን እኛ ኢትዮጵያውያን መቸ ነው ሀብታም የምንሆነው? ይኸ ሁሉ ፀጋ ከወደመ በኋላ? እዚህ ጋ የወደፊት አቅጣጫችሁን መተለም እንድትችሉ ዘንድ የራሴን ልምድ ልንገራችሁ። እኔ ትምህርት ቤት ስገባ ረብሻ ነበር። የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪ ሆኜ ረብሻ ነበር።ዩኒቨርስቲ ስገባ ረብሻ ነበር። ስራ ይዤም ረብሻ ነው። እንደምታውቁት አሁንም ረብሻ አለ።

የኔ ጥያቄ አንድ ቀን ሥጋትና ፍርሀት የተለያት ኢትዮጵያን ሳላያት ልለያት ነው ወይ? ሰላምና ፍቅርዋን ሳላጣጥም ቀጠሮውን ረስቶ ወደማያውቀው ሞት እየዘለቅሁ ነው። የኔ ትውልድ ዕጣ-ፋንታ በዚሁ የመከራ ጉድጓድ ውስጥ ነው የሚያበቃው? ይኸን መንገድ አሁንም መቀጠል አለብን ወይ? የሀገራችን ዕጣ ፋንታ በሕዝብዋ ፍላጎትና ጥረት የሚወሰን መሆን አለበት። አሁን ያሉት ወጣቶች ከኛ በመማር ራሳቸውን መታደግ አለባቸው። በመንደር ፖለቲካ መጠለፍ የለባቸውም። የሚጠቅም እየመሰለ የሚጎዳ ነው። ይኸ ማለት ግን በፖለቲካ ውስጥ መሳተፍ የለባቸውም

ማለት አይደለም፡፡ ወጣትንና ሀገርን የሚያለማ እንጂ፤ እነርሱን እየበላ ለሚኖር ፖለቲካ መዋደቅ የለባቸውም ማለት ነው፡፡

ሁሉም ሰው ይህን ላይረዳው ይችላል፡፡ ከዚህ ሁሉ ትርምስ ማን ምን አተረፈ? ሀገር ያተረፈችው ነገር የላትም፤ ሕዝብ ወይም ትውልድ ምንም አልተጠቀመም፡፡ ለምንድነው አዕምሮ ያለው ሰው በማይጠቅመው ይልቁንም በሚጎዳው ነገር ተጠምዶ ይኸን ሁሉ ጊዜ የሚሰቃየው? አላዋቂነታችን ምን ያህል ቢሆን ነው ማንንም በማይጠቅም ወይም ሁሉንም ከሚጎዳ ትርምስና ንትርክ መውጣት ያልቻልነው? ጨቋኞች ተጨቋኞች ከፋፍለው ለመግዛት እንዲመቻቸው አንዱን የበላይ ሌላውን የበታች አድርገው የልዩነት ግድግዳ ሰሩ፡፡ ሕዝብ በዚህ ችግር ሲራኮት እነርሱ በሰላምና በምቾት ኖሩ - ለአጫጭር ጊዜያት ቢሆንም፡፡ ለዘላቂነት ያተረፉት አንድም በጎ ነገር የለም፡፡ ይልቁንም የሚወቀሱበት ታሪክ ትተው ነው የሄዱት፡፡

የኢትዮጵያ ወጣቶች ባንድ ጉድጓድ ውስጥ ብዙ ጊዜ እንደ ተጠቃው ሞኝ አውሬ መሆን የለባቸውም፡፡ እስካሁን ከነበረው የፖለቲካ ዜማና ቅኝት መውጣት መቻል አለባቸው፡፡ ከጦርነት ቀረርቶ ወደ ሰላምና ፍቅር ዝማሬ መሸጋገር አለባቸው፡፡ ትኩረታቸው በሀገራቸውና በራሳቸው ሰላምና ልማት ላይ መሆን አለበት፡፡ ራስን መውደድ የሰው ባሕርይ ነው፡፡ ከልክ ያለፈ ራስ-ወዳድነት ከብዙ ነገር ጋር ያጣላል፡፡ በመጨረሻም ራስን ከመጥላት ጋር የሚደመደም ይሆናል፡፡ ስለዚህ ራስን መውደድ ማለት ሌላውንም መውደድ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ሀገርን፤ ሰውን፤ ተፈጥሮንና የመሳሰሉትን መውደድ የሚያስከብር እንጂ የሚጎዳ አይደለም፡፡ በተለይ ሀገሩን የሚጠላ ሰው መከበሪያውና መቀበሪያው የት ነው?

## 7.5. ጦርነት - ያልተባረከ የእኩይና የጥቅም ጋብቻ

ባነሳነው የኢትዮጵያ ወጣቶች የሥነ-ምግባር ጉዳይ ጋር ስለጦርነት ማንሳት ለምን አስፈለገ ሊባል ይችላል፡፡ ያለ ምክንያት ነው ተብሎ እንደማይታሰብ ግልጽ ቢሆንም ለመንደርደሪያ ያክል አንዳንድ ነገሮችን ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ የዘመናዊት ኢትዮጵያ ታሪክ በዋናነት የጦርነት ታሪክ ነው፡፡ ትላንትም ሆነ ዛሬ ሕልውናውን ያፀናችው በልጆችዋ/ወጣቶችዋ ደምና አጥንት ነው፡፡ ፈልጋ የገባችባቸው ጦርነቶች የሉም፡፡ በሌሎች ፍላጎት (በእንግሊዝ፤ በግብፆች፤ በደርቡሾች፤ በኢጣሊያኖች፤ በሱማሌዎችና በሌሎች) የተከፈቱባትን ጦርነቶችን ግን ተራ በተራ ማስተናገድ ነበረባት፡፡ ሁሉንም ያጠናቀቀችው በአሸናፊነት እንጂ በተሸናፊነት አይደለም፡፡ አሁንም በጦርነት ውስጥ ትገኛለች፡፡

የተባበሩት መንግሥታትን ጨምሮ አድኃሪ የሆኑ የምዕራባውያን መንግሥታት ሁሉ ከውጭ፤ ከውስጥ ደግሞ በአንዳንድ ምዕራባውያኑ መንግሥታት የሚታገዙ ሀገር-በቀል የሽብር ቡድኖች አቅማቸውን አቀናጅተው እየወጓት ነው። ኢትዮጵያ በርካታ እምቅ ሀብቶችና ውበት ባንድ በኩል፤ እጅግ የገዘፈ ድህነትና ኋላቀርነት በሌላ በኩል አሉባት። እነዚህ እርስዋን በማዳከም በራሳቸው ቁጥጥር ሥር ሊያደርጓት ለቋመጡ ሁሉ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። በአልበገር-ባይነትዋ የተነሳ በቂም በቀል መንፈስ ጥርሳቸውን እንደነከሱባት የሚኖሩ ሁሉ በአራቱም ማዕዘናት በተናበበ መንገድ ተንቀሳቅሰው እየገዘገዟት ነው። በዚህ ውስብስብ ኩነቶች ውስጥ የኢትዮጵያ ወጣቶች ማንነትና ጥንካሬ ከግብረገብና ሥነ-ምግባር ሕግጋት አንጻር ነጥሮ እንደሚወጣ ይታሰባል።

ጦርነት የሰው ልጅ የእርስ በእርስ ፍጅት ነው፤ የሰው ልጅ የቅርስና የሀብት ውድመት ነው። በገራገር ዓይኖቻችን ስናይ ጦርነት አክሳሪ እንጂ አትራፊ አይደለም። ከሰው ልጅ ፍጅትና ከሀብት ውድመት ሰው ምን ያተርፋል? እንደ ሕዝብ፤ እንደ ሀገር ወይም እንደ ትውልድ ከጦርነት ማትረፍ አይታሰብም። ታዲያ የሰው ልጅ ጦርነትን ፈጥሮ የሚዋጋው ለምንድነው? በእርግጥ ጦርነት ከሚያስከትለው አሰቃቂ እልቂትና ከሚያስገኘው ውጤት አንጻር ሲታይ የጥያቄዎቹ መነሳት አግባብነት አለው። ይሁን እንጂ ከጦርነት ማንም ምንም አያተርፍም ብሎ መደምደም አይቻልም። ጥቂት ግለሰቦች፤ ቡድኖች፤ ለትርፍ የሚሰሩ ድርጅቶች፤ በተዘዋዋሪ መንገድ ቢሆንም ሀገሮችና መንግስታትም ከጦርነት ያተርፋሉ። ባብዛኛው የንጹሀን ሞትና እልቂት፤ የሀብትና የቅርሳቸው ውድመት ለጥቂቶች የማይነጥፍ የትርፍ ምንጭ ነው።

ከዚህ አንጻር ሲታይ ‹‹ዓለማችን ከጦርነት ነፃ የምትሆንበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል ወይ?›› ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። መልሱ ቀላል ሊሆን ባይችልም ቢያንስ በሐሳብ ደረጃ ‹‹አዎ፤ ይችላል›› ብሎ መመለስ አይከብድም። የሰው ልጅ እንደ ሰብአዊ ፍጡር መደማመጥና መከባበር፤ መተሳሰብና መተጋገዝ፤ መጋራትና መቻቻል፤ ከሕገ-አራዊት ተላቆ በሕገ-ሰው መገዛት ሲጀመር ጦርነት እየከሰመ ይሄዳል። ይህ ደግሞ የሚሆነው ሰው በውስጡ ያሉትን የአራዊት ባሕርያትን በራሱ ሰብአዊ ባሕርያት መተካት (humanize) ሲችል ነው። አሁን ባለው ሁኔታ ይህ ይሆናል ብሎ ማሰብ አይቻል ይሆናል።

እርሻ እንደማናርስበት ወይም ሕንፃ እንደማንገነባበት እየታወቀ ለምንድነው ሰው የጦር መሣሪያ የሚያመርተው? የጦር መሣሪያ ግዙፍ ትርፍ የሚያስገኝ የሰው ልጅ ሥራ ውጤት ወይም ምርት ነው። ጦርነት ደግሞ የጦር መሣሪያ መኖርን አስፈላጊ

የሚያደርግ የሞቀ ገበያ ነው። በጦር መሣሪያ ግብይት ደግሞ ግዙፍ ትርፍ ተጨምቆ ይወጣል። የጦር መሣሪያ የሚፈለገው ለአንድ ነገር ብቻ ነው - ለጦርነት። የጦርነት መሠረታዊ ተልዕኮ የልማት ሥራ ሳይሆን የጥፋት ነው። ብዙኃንንና ከጨዋታው ነጻ የሆነውን ሕዝብ አጥፍቶ ጥቂቶችን የሚያለማ ፕሮጀክት ነው። ሲጀመር የጦር መሣሪያ ሲመረት የጦርነትን አስፈላጊነት ታሳቢ የሚያደርግ በመሆኑ ፀረ-ግብረገብና ሥነ-ምግባር ነው። ጦርነት አውዳሚ በመሆኑ ከጅምሩ አይደለም መደረግ፤ ሊታሰብም አይገባውም ነበር። የጦር መሣሪያና ጦርነት ያንድ ነገር ሁለት ገጽታዎች ናቸው። የጦር መሣሪያ በገፍ እየተመረተ ጦርነት ከዓለም ይጠፋል ብሎ ማሰብ ያስቸግራል።

የጦር መሣሪያ የሚያመርተው ማነው? ያለ ምንም ጥርጥር ሰው ነው። ይህን መሣሪያ ማምረት የተፈለገው ለምንድነው? የመጀመሪያው ጥቅሙ ለአምራቹ ትርፍ የሚያስገኝ ሸቀጥ መሆኑ ነው። ገዢው ደግሞ ጦር መሣሪያን የሚፈልገው ሌላውን ሰው፤ ቡድን ሀገር ወይም መንግሥት ለማጥቃት ወይም ራሱን ከጥቃት ለመከላከል ነው። ራስን ከጥቃት መከላከል አግባብነት ያለው የሞራል ጉዳይ ሲሆን ከሚያስከትለው አስከፊ ውጤት አንጻር ሲታይ ግን ኢ-ሞራላዊ ነው። ይህ ሲታሰብ ዓለማችን ከጦርነት ነፃ የምትሆንበት ጊዜ ሊመጣ ይችላል ወይ ብሎ መጠየቅ ተገቢ ነው። በሐሳብ ደረጃ ሁለት የጦርነት ማስወገጃ መንገዶች አሉ። አንደኛው ጦርነትን በጦርነት መቋቋም ነው። ሁለተኛው ጦርነትን በሰላም ማቆም ነው። ከሞራል አኳያ የሰው ልጅ ምርጫ መሆን ያለበት ሁለተኛው ነው - ጦርነትን የትርፍ ማጋበሻ የሚያደርጉ ወገኖች በቀላሉ የሚቀበሉት ባይሆንም። በዚህ ምክንያት አሁን ባለው የዓለም ሁኔታ ጦርነትን በጦርነት መከላከል ብቸኛ ምርጫ የሆነ ይመስላል።

እያንዳንዱ ሀገር ራሱን የሚከላከልበት የጦር ሰራዊት የሚገነባው በዚህ ምክንያት ነው። ዛሬ የሰው ልጅ በሁለት መንገዶች ለዘላቂ ጦርነት መታገል ይጠበቅበታል - አንደኛው ራስን ለመከላከል ጦርነትን በጦርነት ማክሸፍ፤ ሁለተኛው ጦርነትን በሰላም ማሸነፍ ነው። ለዚህ ደግሞ በሰው ልጅ አዕምሮና ውስጣዊ ሕይወት (Internal Life) ላይ ከፍተኛ የሰላም ግንባታ መካሄድ ይኖርበታል።

የኢትዮጵያ ታሪክ ቀደም ሲል እንደተባለው ባብዛኛው የጦርነት ታሪክ ነው። ከውስጥ የሚነሳ የእርስ በእርስ ጦርነትና ከውጭ የሚመጣ የባዕዳን ጦርነት ሲፈራረቁባት ቆይተዋል። ስለዚህ ጦርነትና ሰላም በኢትዮጵያ ወጣቶች ታሪክ ውስጥ ልዩ ትርጉም አላቸው። በተለያዩ ተቃራኒ ጎራዎች በመቧደን እርስ በእርስ ተዋግተዋል። በተለያዩ ጊዜያት ከውጭ ከመጡብን ወራሪዎች ጋር በመፋለም ረገድም የወጣቶች ድርሻ በዋናነት ተጠቃሽ ነው። ከባዕዳን ወራሪዎች ጋር በገጠሙ ጦርነቶች ውስጥ

የተከፈለው ዋጋ እጅግ ግዙፍ ቢሆንም የማታ ማታ ድል አድራጊዎቹ ኢትዮጵያውያን ነበሩ። በዚህ ውስጥ ወጣቶች ታሪክ የማይዘነጋው ቦታ አላቸው።

ጦርነትን በጦርነት መከላከል ምርጫችን ባይሆንም ከጦርነት ማትረፍ ለሚፈልጉት ኃይሎች ደግሞ ሰላም ምርጫቸው ሊሆን አልቻለም። ታሪክ በተደጋጋሚ እንዳሳየን ሁሉ ለወደፊቱም ሳንወድ በግድ ወደ ጦርነት የምንገባበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ጥያቄው ከጦርነት ሥጋት ነፃ የሆነች ኢትዮጵያን ወይም የማትደፈር ኢትዮጵያን ለመፍጠር ምን መሰራት አለበት? የኢትዮጵያ ወጣቶች ስለዚህ ጉዳይ ምን ያስባሉ? ከዚህ አሳሳቢ ነገር አንጻር ኢትዮጵያ ግብረገብንና ሥነ-ምግባርን እንዴት መጠቀም አለባት? ግብረገብና ሥነ-ምግባር ለወጣቶች ልማት ምን መሆን አለባቸው? ወጣቶችም ለግብረገብና ሥነ-ምግባር ዕድገት ምን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል? የሚሉ አንገብጋቢ ጥያቄዎች መመለስ ይኖርባቸዋል።

የሰው ልጅ ሕይወት ክቡር መሆኑ ይታመናል። ይሁን እንጂ ዛሬ በዓለማችን ላይ ይህ ክቡር የሆነው የሰው ልጅ ሕይወት እጅግ እየተረገጠ ነው። ምን በመፈጠሩ ነው ይህ ሊሆን የቻለው ብለን መጠየቅ አለብን። ለዚህ ምክንያቱ ወይም መንስዔው እኛው ለመሆናችን ጥርጣሬ ሊገባን አይገባም። ሰላም በዓለም ላይ ማሸነፍ እንዲችል የሰው ልጅ አዕምሮ፣ ባሕርይና እንቅስቃሴ መቃኘት የሚገባው በግብረገብና በሥነ-ምግባር ነው። ዛሬ ራስን ለመከላከል ለጦርነት መዘጋጀትና መሰለፍ አስፈላጊ ነው። በጦርነት ዓለምን ከጦርነት ማላቀቅ ግን አይቻልም። ዓለምን ከጦርነት ነፃ ለማድረግና ሰላምን በዓለም ዙሪያ ለማስፈን በሰው ልጆች አካልና አዕምሮ ላይ ከፍተኛ የዕውቀት፣ የጥበብና የክህሎት ሥራ መሥራት አለበት። መልካምነት በዓለም ላይ ኃያል እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል።

በተለይ የሰላም መሠረት ወላጆችና ትምህርት ቤቶች ናቸው። የሰላም በሕፃናትና ወጣቶች አዕምሮ ውስጥ ማበብ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆን አለበት። ጦርነት ሰዎችና ሰዎች የሚበላሉበት ነው፣ በመሆኑም የሰው የአውሬነት መገለጫ ነው። ሕፃናት ስለ ጦርነት ሳይሆን ስለ ሰላምና ፍቅር፣ ስለመተጋገዝና መከባበር፣ ስለመስማማትና መተሳሰብ፣ ስለመፈቃቀድና መፈላለግ፣ ስለመጋራትና መቻቻል፣ ስለ መማርና መነጋገር ማወቅና መጠያየቅ አለባቸው። እነዚህ ሁሉ ‹‹መልካም›› በሚል አንድ ቃል የሚገለጹ ናቸው። ለምሳሌ ፍቅር ወይም መፈቃቀርን እንውሰድ። ፍቅር ወደር የማይገኝለት መልካምነት ነው።

በፍቅር ውስጥ አንዱ በራሱ ፍቃድና ምርጫ የሌላው አካልና እስትንፋስ፣ ዕውቀትና ጉልበት፣ ሀብትና ንብረት ይሆናል። የፍቅር መልካምነት የሚገለጸው ለክፋትና ጥፋት፣ ለጥላቻና ፍራቻ ቦታ የሌለው በመሆን ነው። ፍቅርና ሰላም ባሉበት ቦታ

ሌሎች መልካም ነገሮች ተከትለው ይመጣሉ። ስለዚህ ሕፃናትና ወጣቶች ስለ ፍቅር እየዘመሩና እየተማሩ ማደግ አለባቸው። በፍቅርና ሰላም አውድ ውስጥ ያደጉ ሕጻናትንና በጦርነትና ሁከት ውስጥ ያደጉ ሕጻናትን በምናባቸው የየራሳቸውን ዓለም ሰርተው እንዲያቀርቡ ቢደረጉ የመጀመሪዎቹ የፍቅርና የሰላም ዓለም፤ ሁለተኞቹ የጦርነትና የሁከት ዓለም እንደሚያቀርቡ ይታሰባል። መጀመሪያዎቹ ውስጣቸው በፍቅር መንፈስና ስሜት፤ ሁለተኞቹ በጦርነትና በሁከት የታነፀ ነው። ቤተሰብ ጥልቅና እውነተኛ ፍቅር የሰፈነበት፤ መተማመንና መመከባበር ያለበት ተቋም ወይም ድርጅት መሆን አለበት።

## 8. መልክቶቹ

❖ *መደማመጥ በእጅጉ ይጎድለናል*

እኛ ለመሆንና ለማድረግ የፈለግነውን እንዳንሆንና እንዳናደርግ ምን አነሰን ብለን ራሳችን እንጠይቅ። በእኔ ዕምነት መደማመጥ በእጅጉ ያንሳል። ይህ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚጎዳ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያ ታፍራና ተከብራ እንድትኖር ለማይፈልጉ አካላት መልካም አጋጣሚ ነው። ባለመደማመጣችን ብዙ ጉዳት አስተናግደናል። የኢትዮጵያን ችግሮች ለመፍታት ያልተነሳ በጎ ነገርና ያልቀረበ መልካም መፍትሔ አልነበረም። መደማመጥ ባለመቻላችን ግን የትኛውም መልካም የመፍትሔ ሐሳብ የተፈለገውን ውጤት አላመጣም። እኛም ወርቃማውን ዕድል አጥተን የሞት ዕዳ ከፋይ ሆነን ቀጥለናል። እውነት ሀገራችንንና ሕዝባችን የምንወድና የምናከብር ከሆነ መነጋገርና መደማመጥ አለብን። የሀገር ጉዳይ የግል ሳይሆን የሁላችን ጉዳይ መሆኑን ማመን ይጠበቅብናል። በተቻለ መጠን የመፍትሔ እንጂ የችግር አካል እንሁን። ቢያንስ ወጣቶቻችን መደማመጥ እንዲችሉ የቀደምቶቻቸውን መልካም ምክሮች ያድምጡ።

❖ *እርቅና ይቅርታን እንማር፤ እንማማር*

አንዱ ያጣነው ይኸን ምሰሶ ነው። የደረሱብን ጉዳቶች የፈለገውን ያህል እንኳን ዘግናኝ ቢሆኑም፤ ለፈጣሪ፣ ለሀገር፣ ለሕዝብ ክብርና ጥቅም ሲባል የራስን በደል ወደኋላ ትቶ ይቅር ማለት ተገቢ ይሆናል። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በአዶልፍ ሂትለር ምክንያት ስድስት ሚሊዮን አይሁዳን እንደተፈጁ ይነገራል። ‹‹ቅጣት ስጡት›› ተብለን ብንጠየቅ - ለዚህ ሰው ምን ተመጣጣኝ ቅጣት እናገኛለን? ለስድስት ሚሊዮን ሕዝብ መፈጀት ምክንያት ለሆነው አንድ ሰው የሞት ቅጣት ቢሰጥ ምን ትርጉም አለው? ነገሩ እጅግ በጣም የሚያም ቢሆንም ለዓለም የተሻለ መልዕክት ያለው እርምጃ መውሰድ ተመራጭ ይሆናል። ችግሩን በይቅርታ መፍታቱ ምናልባት ትልቅ መልዕክት ይኖረው ይሆናል።

### ❖ *ግብረገብና ሥነ-ምግባርን በመመሪያነት እንከተል*

*ግብረገብና ሥነ-ምግባርን እንማር፤ ራሳችንን፤ ልጆቻችን፤ ቤተሰቦቻችንን፤ ጎሮቤቶቻችንን እናስተምር። መማር ብቻ በቂ አይደለም - እንኑርባቸው፤ የዕለት ተዕለት መመሪያም እናድርጋቸው። ዓለምን ከመከራዎች ሁሉ ማውጣት ከተፈለገ ከግብረገብና ሥነ-ምግባር የተሻለ መፍትሔ አምጪ ነገር ያለ አይመስልም። ያደጉ ሀገሮች ለግብረገብና ሥነ-ምግባር የሚገባቸውን ትኩረት መስጠት አይፈልጉም። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ያለ እነርሱ አገልግሎት መኖር ስለሚችሉ ብቻ ሳይሆን ፍላጎቶቻቸውና ተግባሮቻቸው ከግብረገብና ሥነ-ምግባር ሕግጋት ጋር የሚጣጣሙ አይደሉም። ለኛና እንደኛ ላሉ ሀገሮች ግን እጅግ አስፈላጊዎቻችን ናቸው። ያሉብንን ውስብስብ ችግሮች ለመፍታት የቅርብ ደራሾቻችን ከመሆናቸውም በላይ ደረጃውን የጠበቀና የማይዋዥቅ መስመር ተከትለን እንድግ የሚያስችሉን ናቸው።*

*ይህ መልእክት ለወጣቶች ብቻ አይደለም - ለሁላችንም ነው። ወጣቶቻችን ልጆቻችን፤ ወንድምና እህቶቻችን ናቸው። ሀብትና ቅርሶቻችን፤ ውበትና ድምቀቶቻችን፤ ዕውቀትና ጉልበታችን፤ ተስፋና መተማመኛዎቻችን ናቸው። እነዚህ መልካሞቻችንና ፀጋዎቻችን በፖለቲካችን ልክፍት ምክንያት ሲባክኑ ዝም ብሎ ማየት ማብቃት አለበት። እኛ አባቶችና እናቶች፤ የሀይማኖት አባቶችና የሀገር ሽማግሌዎች፤ አባገዳዎችና ታዋቂ ሰዎች፤ ምሁራንና መምህራን ለወጣቶቻችን ሰላምና ደህንነት መጠበቅ የግብረገብና የሥነ-ምግባር ግዴታ አለብን። መነሻውን እንጂ መድረሻውን የማያውቀው የኢትዮጵያ ፖለቲካ የሀገር ተስፋ የሆኑ ወጣቶችን ትርጉም በሌለው ነገር ሊያስጨርስብን አይገባም። ‹‹በቃ›› ልንለው ይገባል።*

*በወጣቶች ላይ የደረሰው ተደራራቢና የማያባራ ጉዳት አሁን ከገቡበት ምሬት አድርሶአቸዋል። ለመልካም ግብ የተከፈለው መስዋዕትነት የተፈለገውን ፍሬ ባለማፍራቱ አንዳንድ ወጣቶች የገነቡትን ሁሉ እስከ ማፍረስ ደርሰዋል። እውነት እንነጋገር ከተባለ እኛም እንደ ሕዝብ መሮናል። በዚህም ሆነ በዚያ ሆነው የሚገድሉና የሚሞቱ፤ የሚጎዱና የሚጎዱ ቅጥረኛ ወታደሮች ሳይሆኑ ከአብራካችን የወጡ ልጆቻችን፤ እህቶቻችንና ወንድሞቻችን ናቸው። ይህ ፈጣሪ ሁሌ እንዳዘንና እንዳለቀስን መኖርን ፈቅዶ የሰጠን ዕጣ-ፋንታ አይደለም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ሰላምና መረጋጋትን መምረጡ መልካም ቢሆንም፤ ሞትን የሚያክል ዝምታ ይዞ መቀጠል ግን የለበትም። በየቦታው የሚደርሰውን የሕዝብ ጉዳትና የሀገር ጥፋት እንዲቆም በሰላማዊ መንገድ መንቀሳቀስ አለበት። ሁሉም ባለበትና በተሰማራበት ቦታ ሁሉ ለሀገሩና ለሰላም የመቆም ግብረገባዊና ሥነ-ምግባራዊ ኃላፊነቱን መወጣት አለበት።*

# ወጣቶች እና የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም በኢትዮጵያ


## ዑርጌሳ ዴሬሳ ጉቱ


## 1. መግቢያ

በአሁኑ ጊዜ ዘመኑ የደረሰበትን የኢንተርኔት አገልግሎት በመጠቀም ማንኛውም ሰው የፈለገውን መረጃ በፈለገው ሰዓት ከቤቱ ሆኖ ማግኘት ይችላል። ከመደበኛ መገናኛ ብዙኀን ይልቅም የማኅበራዊ ሚዲያ በብዙዎች ዘንድ ተመራጭ ሆነዋል። በተለይም ‹‹ስማርት›› ስልኮች ከተፈጠሩ ወዲህ የማኅበራዊ ሚዲያዎች አጠቃቀም በእጅጉን መጨመሩ የሚታይ እውነት ነው። በዓለማችን 4.57 ቢሊዮን ወይንም ከአጠቃላይ የዓለም ሕዝብ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ ሰዎች የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መሆናቸውን ሪፖርታል ዶት ኮም[1] መረጃ ያመለክታል። እንደ ድረ-ገፁ ዘገባ፣ በዓለም ላይ የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ባለፉት ዓመታት ከ10 በመቶ በላይ ጨምረዋል። ይህም የተጠቃሚዎቹን ቁጥር እስካለፈው የፈረንጆቹ ጁላይ 2022 ወር መጀመሪያ ድረስ 3.96 ቢሊዮን እንዳደረሰው ይጠቁማል። ይህም ዕድገት በአማካይ ከ1 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ሰዎች በየቀኑ፤ እንዲሁም ቢያንስ 12 አዳዲስ ሰዎች በየሰከንዱ ማኅበራዊ ሚዲያን መጠቀም እንደሚጀምሩ ይጠቁማል። ‹‹ስቴት ካውንተር›› የተሰኘ ድረ ገፅ ደግሞ በሚያወጣው ዓመታዊ መረጃ ላይ ከፈረንጆቹ ጁላይ 2019 እስከ ጁላይ 2020 ድረስ በዓለም ዙሪያ ካሉ ሰዎች 74.17 በመቶ የሚሆኑት የፌስቡክ ተጠቃሚዎች ናቸው ሲል፣ 6.78 በመቶ ትዊተር፣ 4.86 በመቶ ዩቲዩብ እንዲሁም 1.35 በመቶ የኢንስታግራም ተጠቃሚዎች ናቸው ይላል። ከአፍሪካ ሕዝብ 10 በመቶ የሚሆነው የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ እንደሆነ ጥናቶች የሚያሳዩ ሲሆን፣ እነዚህን የማኅበራዊ ሚድያዎች የሚጠቀሙ ሰዎች ቁጥር ከቀን ወደቀን እየተበራከተ ነው።

ኢትዮጵያ ውስጥ በማኅበራዊ ሚዲያ እና በወጣቶች ጉዳይ ላይ ትኩረት መደረግ ያለበት በሦስት ምክንያቶች ነው። አንደኛው የኃይማኖት እና የብሔር ማንነትን መጨመርን የሚመለከት ሲሆን ይህም በመሬት ላይም ሆነ በኦንላይን አከራካሪ ፖለቲካ እንዲፈጠር አድርጓል። ለዚህ ማሳያ የሚሆነን ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ተከታታይ የፖለቲካ ለውጦችን አድርጋ የነበረች ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የተቃውሞ ሠልፎች፣ የታጠቁ እና ያልታጠቁ ብሔር-ተኮር የወጣቶች ንቅናቄ፣ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ፣ መፈናቀል እና የሀይማኖት ግጭቶች

[1] https://datareportal.com/reports/digital-2022-july-global-statshot

ናቸው:: የማኅበራዊ ሚዲያ ተዋናዮች መሬት ላይ ያለውን አጨቃጫቂ የፖለቲካ ባህሪ ያንፀባርቃሉ:: ሁለተኛው ምክንያት የበይነ-መረብ እና የማኅበራዊ ሚዲያ ተደራሽነት በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ መምጣት ነው:: ኢትዮጵያ በዚህ ረገድ ከዓለም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ካሉ ሀገራት አንዷ ብትሆንም፣ የኢንተርኔት እና የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ላይ ትልቅ ዕድገት እየታየ ነው:: በሦስተኛ ደረጃ፣ በኢትዮጵያ ከፍተኛውን የህዝብ ቁጥር የሚይዙት ወጣቶች መሆናቸው (30 ሚሊዮን ገደማ) ሲሆን፤ 120 ሚሊዮን ከሚገመተው የኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከ28 በመቶ በላይ የሚሆነው ከ15 እስከ 29 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያለ ነው:: ከ10 እስከ 29 ዓመት የሆኑ ታዳጊዎች እና ወጣቶች ከጠቅላላው ህዝብ ብዛት 42 በመቶውን ይይዛሉ (CSA፣ 2013):: ይህ ተመራማሪዎች እና ፖሊሲ አውጪዎች ለወጣቶች የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ትኩረት እንዲሰጡ ያስገድዳል::

በመሆኑም ይህ ጽሑፍ በኢትዮጵያ የወጣቶች የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም አዝማሚያዎች እና ተያያዥ ችግሮች ላይ ከባለድርሻ አካላት ጋር ለመወያየት ዓላማ ይዞ የተዘጋጀ ሲሆን ጥናታዊ ጽሁፉ በሚከተሉት ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፤

- የወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ምን ያህል አዎንታዊ እና አሉታዊ ተፅዕኖ እንዳሳደረ መተንተን፤
- በኢትዮጵያ ወጣቶች የሚጠቀሙባቸውን ታዋቂ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን፣ የፍጆታ አዝማሚያን እና ፈተናዎቹን መዳሰስ፤
- በኢትዮጵያ የወጣቶች የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ችግሮችን የሚያባብሱ ምክንያቶችን መመርመር፤
- በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ሚዲያ ያልተፈለገ ውጤት ለማስወገድ ወይም ለመቀነስ እስካሁን የተወሰዱ እርምጃዎችን መለየት እና፤
- የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ለወጣቶች አዎንታዊ ዕድገት፣ የተሻሻለ የፖለቲካ ተሳትፎ እና የጋራ ተግባራት ለመጠቀም ሊወሰዱ የሚገባቸውን እርምጃዎች መጠቆም ናቸው::

## 2. የወጣት እና ወጣትነት ጽንሰ-ሐሳብ

ወጣት/ወጣትነት ለሚለው ቃል በሁሉም አውድ ውስጥ ሊተገበር የሚችል ተስማሚ ፍቺ ለማግኘት የሚስቸግር ጽንሰ-ሐሳብ ነው:: የወጣትነት ትርጉም እንደ አጠቃቀሙ ዓላማ እና እንደተገለጸበት ሁኔታ (ማኅበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ህጋዊ ሁኔታ) ይለያያል:: ይሁን እንጂ ቢያንስ ሁለት የወጣትነት

ማብራሪያ መንገዶች አሉ፡፡ እነሱም የጊዜ ቅደም ተከተል (chronological) እና ማኅበራዊ ደረጃ (social constructivism) ናቸው፡፡

ወጣት የሚለው ጽንሰ-ሀሳብ በጊዜ ቅደም ተከተል ሲገለጽ በተወሰነ ዕድሜ መካከል ያለ የዕድሜ ክልል (age range) ነው፡፡ ይህም የወጣትነት የዕድሜ ምድብን ከሥነ-ህይወታዊ ዕድገቶች ጋር ሊዛመድ የሚችል የዕድሜ ክልልን መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ምድብ ለተግባራዊ/መደበኛ እና ለስታቲስቲካዊ ዓላማዎች (ለምሳሌ የአቅም ህጋዊ መስፈርት፣ የልጅነት ዕድሜ እና የአዋቂዎች መደበኛ መለያየት) በስፋት አገልግሎት የሚውል ነው፡፡ በእርግጥ ለወጣትነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ተፈፃሚነት ያለው ዕድሜ-ተኮር ፍቺዎች የሉም፤ ይልቁንም ሀገራት ለወጣቶች የተለያየ ምድብ አላቸው፡፡ በዚህ ረገድ፣ ለምሳሌ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ለስታቲስቲክስ ዓላማዎች ወጣቶችን ‹‹በ15 እና 24 ዓመት መካከል ያሉ የዕድሜ ምድብ›› ብሎ ይጠቅሳል፡፡ በአፍሪካ ሁኔታ፣ የአፍሪካ ወጣቶች ቻርተር ወጣቶችን ከ15 እስከ 35 ዓመት ዕድሜ ያለው እያንዳንዱ ሰው ሲል ይገልፃል (የአፍሪካ ወጣቶች ቻርተር፣ 2006)፡፡ የኢትዮጵያ ወጣቶች ፖሊሲ ወጣቶችን ከ15 እስከ 29 ዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ የህብረተሰብ ክፍል አድርጎ ይገልፃል (ኢፌዲሪ፣ 2004)፡፡

ሌላው ከዘመን አቆጣጠር ምድብ ተቃራኒ የሚሰጠው ማኅበራዊ ትርጓሜ ነው፡፡ በዚህ ትርጓሜ ወጣትነት ከልጅነት ወደ ጉልምስና የመሸጋገር ሂደትን፣ በማኅበራዊና አምኮታዊ ሥርዓቶች (rituals) ወይም በአካላዊ ለውጦች እንዲሁም በባህል የተወሰነ ሚና ጋር በተያያዘ ግለሰቦች በተወሰነ ማኅበራዊ ሁኔታ ውስጥ የሚጫወቱት ነው፡፡ ይህ አካሄድ በህብረተሰቡ ውስጥ ካሉ ባህሪያት እና አመለካከቶች የሚወጣ ማኅበራዊ ክስተት ሆኖ ወደ ወጣትነት ይሸጋገራል፡፡ ስለዚህ እንደ ማኅበራዊ ደረጃ፣ ኀሳ እና ተለዋዋጭ ባህሪያትን በመገኛ ቦታ እና በጊዜያዊ ባህሪያት ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ለባህል ሊቃውንት፣ የወጣትነት ጽንሰ-ሐሳብ ምንም ዓይነት ሁለንተናዊ (wholistic) ምድብ የለውም፣ ይልቁንም በግለሰብ እና በማኅበራዊ ደረጃ እንደ ዘር፣ ጾታ፣ ኀሳ፣ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት እና ማኅበረሰብ ባሉ የተለያዩ የተጠላለፉ ምልክቶች ተለይቶ ይታወቃል፡፡ በማኅበራዊ ትርጓሜ ውስጥ ወጣቶች በሁለት የተለያዩ መንገዶች ይገለፃሉ - ለመረጋጋት የሚሳናቸው እና ለማኅበራዊ ደንቦች (norm) አስጊ የሆኑ አድርጎ ማየት እና በአንፃሩ እንደ አዎንታዊ ለውጥ እና የዕድገት ሞተር አድርጎ መመልከት፡፡

ኢትዮጵያ በወጣቶች ፖሊሲው ላይ እንደተገለጸው የወጣትነት ትርጓሜ በዕድሜ ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ምንም እንኳን ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ወጣትነትን ከ15 እስከ 29 ዓመት ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው በማለት

በዕድሜ ገድቦ ቢገልጽም፣ ወጣትነትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ለዋሉት እንደ ባህል እና ማኅበራዊ አውድ ለመሳሰሉ አቀራረቦች በግልፅ ዕውቅና ይሰጣል (FDRE፣ NYP Sec 1)። በአጠቃላይ 120 ሚሊዮን ከሚገመተው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል 30 ሚሊዮን ያህሉ በወጣትነት ዕድሜ ክልል ውስጥ ይገኛሉ (CSA፣ 2013)። ስለሆነም ወጣቱ ካለው ከፍተኛ የቁጥር ድርሻ አንፃር በአግባቡ ከተገራ እንደ መልካም አጋጣሚ ሊወሰድ ይችላል፤ ከተሳሳተ እና በአግባቡ ካልተያዘ ግን እንደ ስጋት ሊቆጠር ይችላል።

በ2004 እ.ኤ.አ መንግስት የወጣቶች ፖሊሲ በመቅረፅ ለኢትዮጵያ ወጣቶች የሰጠውን ትኩረት እና ለወጣቶች መብትና ጥቅም ዕውቅና ለመስጠት ያለውን ፍላጎት በግልጽ አሳይቷል ብሎ መከራከር ይቻላል። ነገር ግን አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የኢትዮጵያ ወጣቶች በማኅበራዊ አገልግሎት አቅርቦት እጦት ወይም ውስንነት፣ ስራ አጥነት፣ በራሳቸው ጉዳይ ላይ ትርጉም ያለው እና ነፃ ተሳትፎ ለማድረግ ባለመቻል እንዲሁም በአገሪቷ አስተዳደር ላይ ዘርፈ ብዙ ችግሮች ገጥሟቸዋል።

ፖሊሲውን ተግባራዊ ለማድረግ የማስተባበር ሚናው የወጣቶችና ስፖርት ሚኒስቴር እንደሆነ ቢታቀድም በኋላ ግን ‹‹የወጣቶች ጉዳይ›› ወደ ሴቶች፣ ህጻናትና ወጣቶች ጉዳይ ሚኒስቴርነት ተላልፏል። አሁን ባለው የመንግስት ካቢኔ መዋቅር ውስጥ ‹‹የወጣቶች ጉዳይ›› በግልጽ ባይታወቅም ‹‹በሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ›› ሚኒስቴር ስር እንዲሆን ተደርጓል።

## 3. ማኅበራዊ ሚዲያ

### 3.1. የማኅበራዊ ሚዲያ፤ ትርጉም፣ ዝግመተ-ለውጥ እና ልዩ ገፅታዎች

#### 3.1.1. የማኅበራዊ ሚዲያ ትርጉም

ማኅበራዊ የሚለው ቃል ከሰዎች ጋር መገናኘት ወይም መሳተፍ ማለት ሲሆን፤ ሚዲያ የሚለው ቃል ‹‹መንገድ›› ወይም ‹‹መሣሪያ›› ማለት ነው። ስለዚህ ማኅበራዊ ሚዲያ ሰዎች ይዘቶችንና ሀሳቦችን እንዲፈጥሩና እንዲጋሩ የሚያስችል ወይም በማኅበራዊ በይነ-መረብ ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማስቻያ መድረክና ዘዴ ነው። ማኅበራዊ ሚዲያ በበኩሉ ተጠቃሚዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲገናኙ፣ እንዲተባበሩ እና እንዲግባቡ የሚያስችል ኢንተርኔት ላይ የተመሠረተ የግንኙነት መረቦች ስብስብ ተብሎ ይገለጻል። የሜሪያም ዌብስተር መዝገበ ቃላት ማኅበራዊ ሚዲያን ‹‹የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ዘዴዎች (እንደ ማኅበራዊ ድረ-ገጾች እና ማይክሮብሎግ የመሳሰሉ) ሆኖ ተጠቃሚዎች መረጃን፣ ሀሳቦችን፣ ግላዊ

መልዕክቶችን እና ሌሎች ይዘቶችን (እንደ ቪዲዮ ያሉ) በመለዋወጥ ኦንላይን ማኅበረሰቦች የሚፈጥሩበት›› ዘዴ/መንገድ በማለት ይገልፀዋል፡፡

እንደ ሜትዚገርና ተከር (Metzger እና Tucker 2017:171) አገላለጽ ማኅበራዊ ሚዲያ የሚያመለክተው ተጠቃሚዎች ይዘት እንዲያመነጩ እና እነዚህን መድረኮች ለመጠቀም በመረጡ ሰዎች አውታረ-መረቦች ውስጥ እንዲያካፍሉ የሚያስችሏቸውን ትስስር መፍጠር ነው፡፡ እንዲሁም ማኅበራዊ ሚዲያ በweb 2.0 ርዕዮተ ዓለም[2] እና ቴክኖሎጂ መሠረት ላይ የሚገነቡ እና በተጠቃሚ የሚመነጭ ይዘት ለመፍጠር እና ለመለዋወጥ የሚያስችሉ በይነ-መረብ ላይ የተመሠረቱ መተግበሪያዎች (applications) ስብስብ ስም ነው (Dhingraa and Mudgal, 2019: 1)፡፡ ማይክል ማንዲበርግ ‹‹የማኅበራዊ ሚዲያ›› ዕሳቤ ከበርካታ ፅንሰ-ሀሳቦች ጋር የተቆራኘ ነው በማለት ይከራከራሉ፡- ‹‹በተጠቃሚ የመነጨ ይዘት (user-generated content)፣ የመገናኘት ባህል (convergence culture)፣ ቀደም ሲል ተመልካች በመባል የሚታወቁት ሰዎች (the people formerly known as the audience)፤ በፖለቲካዊ መልኩ የተዋሀዱ ‹‹አሳታፊ ሚዲያ›› (participatory media)፣ ሂደት-ተኮር አቻ-ምርት (peer-production) እና በኮምፒዩተር-ፕሮግራሚንግ ላይ ያተኮረ ‹‹Web 2.0›› (Mandiberg፣ 2012፡ 2) በማለት ይገልጻል፡፡ ስለዚህ ማኅበራዊ ሚዲያ ኢንተርኔት ላይ የተመሠረተ ዘመናዊ የመገናኛ ዘዴ ነው ሊባል ይችላል፡፡ እሱም ‹‹ርቀትን የገደለ›› የመገናኛ ዘዴ ነው ይባላል፤ ይህም አካላዊ እንቅፋቶችን በመቀነስ ግንኙነቶችን አጠናክሯል ለማለት ነው፡፡

በማኅበራዊ ሚዲያ ውይይት ውስጥ ሌላ ተዛማጅ ጽንሰ-ሀሳብ የሆነውን የማኅበራዊ ትስስር ገፆች (Social networking sites) ጉዳይም ማንሳት አስፈላጊ ነው፡፡ በቀድሞ ጊዜያት በዋናነት ማኅበራዊ ሚዲያ መረጃን ለማሰራጨት የሚያስችል መድረክ የነበረ ሲሆን የማኅበራዊ ትስስር ገፆች ግን እርስ በርስ የሚግባቡበት መድረክ ነበር፡፡ ያም ማኅበራዊ ሚዲያ የመገናኛ ቻናል ሲሆን፤ ማኅበራዊ ትስስር ግንኙነቱ የሁለት አቅጣጫ ባህሪ ነበረው፡፡ ምንም እንኳን ማኅበራዊ ድረ-ገጾች በባህሪያቸው በተለምዶ የማኅበራዊ ሚዲያ መሣሪያዎች ቢሆኑም ሁሉም ማኅበራዊ ሚዲያዎች በተፈጥሯቸው የማኅበራዊ ድረ-ገጾች አይደሉም (ካር እና ሀይስ፣ 2015)፡፡ አሁን አሁን ግን ሁለቱ የማይነጣጠሉ እየሆኑ በመምጣታቸው እና የመሣሪያ ስርዓቶችን ቴክኖሎጂ በየጊዜው በማሻሻል ምክንያት ልዩነቱ በጣም ተለዋዋጭ (fluid) እየሆነ

---

[2]Web 2.0 በተጠቃሚ የመነጩ ይዘቶችን የሚደግፉ፣ ለአጠቃቀም ቀላል የሆኑ፣ አሳታፊ እና የተጠቃሚዎችን መስተጋብር የሚያጎሉ ድህረ ገጾችን ያመለክታል፡፡ ቀድሞው የነበረ በይነመረብ ስሪት Web 1.0 በመባል ይታወቃል፡፡

መጥቷል:: ማኅበራዊ ትስስር ገፆች በጣም ተለዋዋጭ ከሆኑ የግንኙነት መድረኮች መካከል አንዱ ናቸው:: በአጠቃላይ ማኅበራዊ ገጾች ከትናንሽ፣ ከተበታተኑ፣ ከአካባቢያዊ ማህበረሰብ ድረ-ገጾች፣ ወደ ዓለም አቀፋዊ ተደራሽነት ያላቸው የተዋሀዱ ኩባንያዎች በማደግ ለብዙ ጉልህ ለውጦች ተዳርጓል::

### 3.1.2. የማኅበራዊ ሚዲያ ባህሪያት (ልዩ ገፅታዎች)

ማኅበራዊ ሚዲያዎች የሚከተሉትን ሦስት የመግለጫ ባህሪያት አላቸው:: እነዚህም፡ -

1. እንደ ምስሎች፣ ጽሁፍ፣ ቪዲዮዎች እና ሁኔታዎች (እንደ ጂኦግራፊያዊ መመዝገቢያ ያሉ) በተጠቃሚ የመነጨ ይዘትን (user-generated content) ቅርጾች የመደገፍ ችሎታ፤
2. ተጠቃሚዎች እርስ በርስ የሚገናኙበትን መንገድ ማቅረብ (በትዊተር ላይ በመከተል ወይም በመውደድ፣ በፌስቡክ ላይ ያሉ የጓደኝነት፣ መከተል፣ መጋራት ወዘተ ግንኙነቶችን)::
3. አባላት በትብብር፣ በማህበረሰብ ግንባታ፣ በተሳትፎ፣ በመጋራት፣ በመተሳሰር እና በሌሎች መንገዶች እርስ በርስ እንዲግባቡ የተለያዩ መንገዶችን መደገፍ (intercative) ባህሪያት አላቸው::

### 3.1.3. የማኅበራዊ ሚዲያ ታሪካዊ ዳራዎች (ዝግመተ-ለውጥ)

የማኅበራዊ ሚዲያ አጀማመርን በተመለከተ ምሁራን በዋነኛነት የሚለያዩት በ‹‹ማኅበራዊ›› መድረክ ዋነኛ መለያ ምልክቶችና ከሌሎች ማኅበራዊ ሚዲያ የሚለዩባቸው ምክንያቶችን በተመለከተ ነው:: የግንኙነት ባህሪያት ያላቸው ተግባር ላይ ውለው የጠፉ ብዙ ፕላትፎርሞች ተፈጥረው ነበሩ:: የመጀመሪያዎቹ እንደ CompuServe ያሉ የኢንተርኔት ዓይነቶች በ1960ዎቹ የተፈጠሩ ሲሆን፤ በመቀጠልም የInternet relay chats ለመጀመሪያ ጊዜ በ1988 ጥቅም ላይ ውለው በ1990ዎቹ ውስጥም ታዋቂ ሆነው ቀጥለዋል:: እ.ኤ.አ. በ1980ዎቹ Bulletin Board Systems እንደ ቀደምት የማኅበራዊ ሚዲያ አይነት ተፈለሰፉ:: እነዚህ ሲስተሞች ተጠቃሚዎች ጨዋታዎችን (games) እና ሌሎች ፋይሎችን እንዲያወርዱ እና መልዕክቶችን ለተጠቃሚዎች እንዲተዉ የሚያስችል ‹‹የኦንላይን ስብሰባ ክፍል›› (online chatroom) ዓይነት ነበሩ:: ይሁን እንጂ ሰዎች በስልክ መስመር ሌላኛው ጫፍ ማን እንደተቀመጠ ስለማያውቁ ግንኙነቱ በጣም ውስን፣

ቀርፋፋ እና የዘፈቀደ ባህሪ ነበረው። በመቀጠልም በ1997 ሲክስ ዲግሪስ (Six Degrees) የተሰኘው ማኅበራዊ ሚዲያ መሰል መገልገያ ተፈጠረ።

ነገር ግን እውነተኛው የማኅበራዊ ድረ-ገጽ አብዮት የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ2000ዎቹ መጀመሪያ ላይ የፍሬንድስተር (Friendster) ድረ-ገጽ ሲጀመር ነው። ፍሬንድስተር በአንድ ዓመት ውስጥ ሦስት ሚሊዮን ተጠቃሚዎችን በማሰባሰብ ትልቅ ተመልካች ያለው የመጀመሪያው ጣቢያም ለመሆን ችሎ ነበር። ከዚያ በኋላ የተለያዩ ‹‹ማኅበራዊ›› ሞዴሎችን የሚጠቀሙ የተለያዩ መድረኮች ተመስርተውጥቅም ላይ ውለዋል። በዚህ ረገድ አስገራሚው ምሳሌ በ2003 የተከፈተው ሊንክድኢን (LinkedIn) የተሰኘው የፕሮፌሽናል ትስስር መድረክ ሲሆን በዚህ መድረክ የሰዎች ዕውቂያዎች (contacts) የጓደኝነት ሳይሆን የሙያዊ ግንኙነቶች ነበሩ። ትስስር መድረኩ ይህን ልዩ ባህሪውን እስከ ዛሬ ድረስ ጠብቆ ቆይቷል። ሊንክድኢን ከተከፈተ ከአንድ ዓመት በኋላ በ2004፣ ማርክ ዙከርበርግ እና የሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የክፍል ጓደኞቹ ፌስቡክ (thefacebook.com) የተባለውን ድረ-ገጽ ፈጥረው በዓለም ላይካሉ በጣም ጠንካራ እና ስኬታማ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች መካከል አንዱ ለማድረግ ችለዋል። እ.ኤ.አ. በ2006 ትዊተር ተፈጥሯል። በተመሳሳይ ጊዜ እንደ ማይስፔስ (Myspace)፣ ዩቲዩብ (YouTube)፣ ጎግል+ (Google+)፣ ኢንስታግራም (Instagram)፣ ስናፕቻት (Snapchat) እና ሌሎች በደርዘን የሚቆጠሩ መድረኮች መፈጠራቸውን ለመታዘብ ተችሏል።

በአሁኑ ጊዝ ማኅበራዊ ሚዲያዎች በቁጥርና በዓይነት በብዛት ተፈልፍለዋል። ከነዚህ መካከል ፌስቡክ፣ ዩቲዩብ፣ ቴሌግራም፣ ዋትስአፕ፣ ኢንስታግራም፣ ትዊተር፣ ኢሞ፣ ቫይበር፣ ስካይፕ፣ ዊቻት፣ ቲክቶክ፣ ሊንክድኢን፣ ማይስፔስ፣ ፍሬንድስተር፣ ጎግል+፣ ስናፕቻት፣ ኪውዞን፣ ተምብለር፣ ባይዱቴባ፣ ኪውኪው፣ ሲናዌቦ፣ ላይን፣ ዋይዋይ፣ ቪኮንታክት፣ ፓይተረስት፣ ሬድኢት፣ ታሪንጋ፣ ፎርስኩዌር፣ ሬንሬን፣ ታግድ፣ ባዶ፣ ስታምብለአፕ፣ ዘዶትስ፣ ኪዊቦክስ፣ ስካይሮክ፣ ዴሊሸየስ፣ ስናፕፊሽ፣ ሬቨርቢኔሽን፣ ኔክስትዶር፣ ዋይን፣ ኬር2፣ ካሬማም፣ ሬቨርሊ፣ ሴሉፉን፣ ቫይን፣ ክላስሜት፣ ማይሄሪቴጅ፣ ቪያዲዮ፣ ዣንጋ፣ ዡንግ፣ ላይቭጆርናል፣ ጋይያኦንላ፣ ዊኸርትኢት፣ ቡዝኔት፣ ቱቶክ፣ ዲቪየንትአርት፣ ፍሊክር፣ ሚትሚ፣ ሚትአፕ፣ ቶውት፣ ሚክሲ፣ ዶባን፣ ቬሮ፣ ቆራ፣ ስፕሪሊ፣ ዲስኮርድ፣ ላይኪ በዋናነት ይጠቀሳሉ።

ምስል 1፡ ታዋቂ ማኅበራዊ ሚዲያ አይነቶች በከፊል




ምንጭ፡- ከበይነ-መረብ የተወሰደ

ከነዚህ መካከል ፌስቡክ ከ2.8 ቢሊዮን በላይ ወርሀዊ ንቁ ተጠቃሚዎች በመያዝ በዓለም በብዛት ጥቅም ላይ የዋለ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረክ ሆኖ ቀጥሏል፡፡ (DataReportal, 2021)፡፡ በአሁኑ ሰዓት በስፋት ከመስፋፋቱ የተነሳ "በፌስቡክ ላይ ከሌለ ምናልባት በሕይወትም ላይኖር ይችላል" (if you are not on *Facebook,* very likely you don't exist) እስከመባል ተደርሷዋል፡፡

## 4. የማኅበራዊ ሚዲያ ሚናዎች፡ ባለ ሁለት አፍ ሠይፍ

በማኅበራዊ ሚዲያ ሚና ላይ የህዝብ እና የአካዳሚክ ክርክር እያደገ መጥቷል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባለው ዓለም ማኅበራዊ ሚዲያ የማይነጣጠል የህይወት አካል እየሆነ መጥቷል፡፡ ዛሬ በዓለም ዙሪያ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች ማኅበራዊ ሚዲያዎችን ይጠቀማሉ፡፡ በዚህም ባለፉት አስርት ዓመታት ውስጥ ሰዎች በአለም ዙሪያ የሚግባቡበትን እና መረጃን የሚያገኙበትን መንገድ በመሠረታዊ መልኩ ቀይሯል (Courtright, et al, 2020)፡፡ በቅርብ ጊዜ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ፖለቲከኞች፣ መሪዎች፣ አማፂዎች፣ ተቃዋሚዎች፣ አክራሪ እና አሸባሪ ቡድኖች ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ያሉ ተዋናዮች ማኅበራዊ ሚዲያን ለግንኙነት እና ግባቸውን ለማራመድ በመሣሪያነት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ እንደ ፌስቡክ እና ትዊተር ያሉ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች አዲስ ነገር ከመሆን ወደ የብዙ ሰዎች የግል እና ሙያዊ ህይወት ወሳኝ አካል ሆነዋል (Mills, 2015)፡፡ የሰዎች የማኅበራዊ ሚዲያ ምርጫ በአብዛኛው የሚመነጨው በዋጋ ፣በፍጥነት እና በቀላሉ መረጃን በማሰራጨት ካለው ጥቅም አንፃር ነው፡፡

ሆኖም የማኅበራዊ ሚዲያ በዘመናዊው ማህበረሰብ ውስጥ ባለው ህይወት ላይ የሚያሳድረውን ተፅዕኖ በተመለከተ የተለያዩ አስተያየቶች ይሰነዘራሉ። ስር የሰደዱ ተዋረዶችን የሚፈታተን፣ ሥልጣንን እንደገና የሚያከፋፍል፣ መረጃን ዴሞክራሲያዊ የሚያደርግ፣ የሕዝብን ንቅናቄ የሚደግፍ እና ለዓለም አቀፋዊ እንቅስቃሴዎች ግንባታ አስተዋፅኦ የሚያደርግ የለውጥ ኃይል ሆኗል ብለው የሚከራከሩ ብዙዎች ናቸው። በሌላ በኩል ‹‹የሐሰት ዜና›› መስፋፋትን የሚያመቻች፣ ለዜጎች ክትትል (survellance) መሣሪያ የሚያቀርብ እና የኒዮሊበራል የበላይነትን እንደገና የሚያፀድቅ ክፉ ኃይል ነው ብለው የሚተቹም ቁጥራቸው ቀላል አይደለም (ለምሳሌ McCabe እና Harris፣ 2021)። ይህን የማኅበራዊ ሚዲያ ድርብ ሚና በዝርዝር እንመልከት።

አንዳንድ ጥናቶች ባህላዊው ሚዲያ (traditional media) በሊቃውንትና ታዋቂ ሰዎች ብቻ የተያዘና ለሕዝብ ተደራሽ ያልሆነ ባለመሆኑ ማኅበራዊ ሚዲያ ተራ ዜጎች እንዲታዩና እንዲሰሙ ያስቻለ የዴሞክራሲ መሣሪያ ነው ሲሉ ያወድሱታል። ለምሳሌ፣ መርቲ (Murthy 2012) የተባሉ ፀሀፊ እንደ ትዊተር ያሉ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተራ ሰዎች ሰበር ዜናን እንዲያቀርቡ፣ የሚዲያ ይዘቶችን እንዲያዘጋጁ እንዲሁም ሀሳባቸውን በይፋ እንዲገልጹ ስላስቻሉ ‹‹የዲሞክራሲ መሣሪያን›› ይወክላሉ በማለት ይከራከራሉ። በተመሳሳይ፣ ማካቢ እና ሐሪስ (McCabe and Harris (2021፡319) የተባሉ ተመራማሪዎች የማኅበራዊ ሚዲያ ጥቅሞች ከሚከተሉት አቅሞቹ እንደሚመነጩ ይከራከራሉ። እነዚህም ድምጽን ዲሞክራሲያዊ ማድረግ፣ የሚዲያ ተደራሽነትን ለአማራጭ እና ለአናሳዎች ፍላጎት ማመቻቸት፣ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር መገናኘት የሚቻልበት ሁኔታ አንጻራዊነት ቀላል ማድረግ፣ እና ትብብርን በአካባቢያዊ፣ በአገር አቀፍ እና በዓለም አቀፍ ደረጃ የበለጠ ውጤታማ የማድረግ አቅም ናቸው። ከዚህ ቀደም በትልልቅ አታሚዎች እና ብሮድካስተሮች ብቻ ተገድቦ የነበረውን የጋራ አጀንዳ የማውጣት አቅምን በስልጣን ላይ ያሉ ሰዎችን በፍርሀት በሚያርድ ደረጃ ለተራ ሰዎች ያጎናጽፋል (Standage, 2013: 239)። ከጊዜ ወደ ጊዜ ማኅበራዊ ሚዲያ መረጃ ለማሰራጨት፣ የህብረተሰብን ግንዛቤ ለማዳበር እና የፖለቲካ ተሳትፎን ለማሳደግ፣ ራስን ለመግለፅ እንደ አማራጭ መሣሪያ ሆኖ በማገልገል ላይ ይገኛል አገልግሏል። ተጠቃሚዎች ከሌሎች ሰዎች ጋር ሀሳቦችን እና አስተያየቶችን እንዲጋሩ አስችሏቸዋል፣ እንዲሁም ከልጅነት ጓደኞቻቸው እስከ ፍፁም የማይተዋወቁ ሰዎች ድረስ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ካላቸው ሰዎች ጋር እንዲፈላልጉ እና እንዲግባቡ አግዟል (Sundaram, 2018)።

በተጨማሪም ማኅበራዊ ሚዲያ የዜጎችን ተሳትፎ እና የጋራ ተግባራትን (collective actions) ለማመቻቸት ሊያገለግል ይችላል። የህዝብ ፖሊሲ ሂደትን ማሳደግ፣ አምባገነንነትን ለመቃወም እና የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለማደራጀት (Metzger and Jucker, 2017) ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል። በአሁኑ ጊዜ ማኅበራዊ ሚዲያ በተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሚስተዋሉ የጋራ የፖለቲካ እርምጃዎች ውስጥ አስፈላጊ መሣሪያ ሆኗል።

እንደ አረብ የጸደይ (spring) አብዮት፣ ዩክሬን እና ሆንግ ኮንግ ሕዝባዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በመሳሰሉት የቅርብ ጊዜ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማኅበራዊ ሚዲያ ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። የማኅበራዊ ሚዲያው የአረብ አብዮትን በማስተባበር እና ለህዝብ ይፋ በማድረግ የተጫወተውን ወሳኝ ሚና በመጥቀስ አንዳንድ ተንታኞች በግብፅ፣ ኢራን እና ቱኒዝያ የተከናወኑ የተቃውሞ ድርጊቶችን ‹‹የትዊተር አብዮቶች›› በማለት ትዊተር የነበረውን ቁልፍ ሚና አጉልተው ይገልፃሉ (Hussain and Howard, 2013)። ማኅበራዊ ሚዲያ ግንኙነትን በማሳለጥ፣ የመረጃ ተደራሽነትን በማፋጠን እና የሰብዓዊ መብት ረገጣ ተጠያቂነትን በማሳደግ ረገድ ያለው ሚናም የሚካድ አይደለም።

መኬብ እና ሐሪስ (McCabe and Harris, 2021) የተባሉ ተመራማሪዎች እነዚህ ወቅታዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ቀደም ሲል ከነበሩ ተቃውሞዎች በዋነኛነት የሚለዩት ባላቸው የማኅበራዊ ድህረ-ገፆች ተፅዕኖዎች የተነሳ ነው የሚል አስተያየት ይሰጣሉ። በመሆኑም እንቅስቃሴዎቹ ቀደም ሲል እንደነበሩት እንደ የሠራተኛ ማኅበራት ወይም የፖለቲካ ፓርቲዎች በመሳሰሉ ‹‹ባሕላዊ›› የአደረጃጀት ዓይነቶች ላይ ጥገኛ አይደሉም። እንዲሁም ዕቅስቃሴዎቹ የጎንዮሽ (horizontal) ግንኙነት ያላቸውና ግርማ ሞገስ ባላቸው ‹‹ካሪዝማቲክ›› ግለሰቦች ላይ ያልተመሰረቱ ናቸው። እንቅስቃሴዎቹንና መረጃዎችን በፍጥነት ለማሰራጨት ከማስቻላቸው በላይ፣ ተቃዋሚዎችን በማደስ እና በማስታገስ፣ ሰፊ የ‹‹ጎዳና ላይ›› እርምጃዎችን በማባባስ ለረጅም ጊዜ እንዲቆዩ/እንዲቀጥሉ ማድረግ ይችላሉ።

በእርግጥ በፖለቲካዊ ተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የማኅበራዊ ሚዲያ ሚና አከራካሪ ነው። አንዳንድ ተንታኞች በማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ውስጥ ያለውን የተሳታፊዎች ትክክለኛ ማንነት የመታወቅ ዕድል አነስተኛነት በመጥቀስ ማኅበራዊ ሚዲያ ‹‹እውነተኛ›› እንቅስቃሴን በማዳከም እና እውነተኛ አንቂዎችን (activists) ባለመፍጠር ውድቀትን ያስከትላል በማለት ይገልፃሉ። ይህንንም ለማጠናከር በማለት

የክሊክቲቪዝም (clicktivism) ወይም ስላከቲቪዝም (slacktivism)[3] ክስተትን በመረጃነት ያመለክታሉ (Morozov, 2009; Harlow & Guo, 2014)፡፡

ምንም እንኳን የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ለግለሰቦች እና ቡድኖች አዲስ አዎንታዊ እና ገንቢ ዕድሎችን ቢያበረክቱም አያሌ ጨለማ ጎኖችም አሏቸው፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያውን አሸባሪ ድርጅቶች ተከታዮቻቸውን አክራሪ ለማድረግ እና አጥቂዎችን ለመመልመል ይጠቀሙበታል፡፡ በሳራ ፖንደር እና ጆናታን ማቱሲትዝ (2017) የተደረገው ጥናት አይ.ኤስ.አይ.ኤስ (ISIS) የተባለው የፖለቲካ ቡድን ብዙ ሰዎችን በተለይም ወጣቶችን በኢንተርኔት ቻት ሩም እና እንደ ትዊተር ባሉ የማኅበራዊ ሚዲያ ድረ-ገጾች በተሳካ ሁኔታ መመልመሉን አሳይቷል፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያ ‹‹በመረጃ ጦርነት›› ውስጥ በመንግስታት እና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ፕሮፓጋንዳ ለማሰራጨት እንደ ቁልፍ መሣሪያ ሆኖ ያገለግላል (Prier, 2017)፡፡ በዚህም ሳቢያ ተመራማሪዎችን ማኅበራዊ ሚዲያን ‹‹ልቦች እና አዕምሮዎች ላይ ከፍተኛ ውጊያ የሚካሄድበት የጦር ሜዳ›› በማለት ይገልጿቸዋል (Beata Bialy 2017)፡፡ ይህ ማለት ማኅበራዊ ሚዲያ ማለትም ማታለልን፣ የሀሰት መረጃን፣ ፕሮፓጋንዳን፣ ተቃዋሚዎችን ማስፈራራትን፣ ደጋፊዎችን ማሰባሰብ እና የድርጊት ማስተባበርን ጨምሮ የተለያዩ ወታደራዊ ስልቶችን እና ዘዴዎችን የምንታዘብበት የጦር ሜዳ ነው፡፡

በተጨማሪም ማኅበራዊ ሚዲያ ወሬዎችን ለማሰራጨት ጥቅም ላይ እየዋለ ሲሆን፤ እነዚህ መረጃዎች በአብዛኛው የተሳሳቱ እና ወደ ገዳይ ውጤቶች ሊያመሩ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ሕንድ ውስጥ በ2018 በርካታ የመንጋ (mob) ጥቃት ክስተቶች የተፈጸሙት በተለያዩ የሕንድ መንደሮች የሕጻናት ጠላፊዎች ኩላሊታቸውን ለመሰብሰብ ህጻናትን በመፈለግ ላይ ናቸው ተብሎ በዋትስአፕ ላይ በተወራው አሉባልታ ምክንያት ሲሆን በዚህም ሳቢያ የህክምና ባለሙያዎች በአሰቃቂ ሁኔታ ተገድለዋል፡፡

እንዲሁም ማኅበራዊ ሚዲያው የጥላቻ እና አደገኛ ንግግርን ኢንተርኔት ላይ በማሰራጨት መሬት ላይ ከባድ መዘዞችን ሊያመጣ ይችላል፡፡ ለምሳሌ፣ እ.ኤ.አ. በ2017 በማያንማር የሮሂንጊያ ግጭት በከፍተኛ ሁኔታ በመባባስ ለመቶ ሺዎች መሰደድ ምክንያት የሆነው በከፊል ቀስቃሽ ንግግሮች በማኅበራዊ ድረ-ገጾች በዋናነት

---

[3] ሁለቱም ሀሳቦች ምንም ወይም ጥቂት ቁርጠኛ ተሳትፎ በሚታይበት ሁኔታ የፖለቲካ እንቅስቃሴን ወይም ማኅበራዊ ጉዳይን በድረ-ገጽ ወይም ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ብቻ ድጋፍ የመስጠት ድርጊትን ያመለክታሉ፡፡

በፌስ ቡክ ላይ ከፍተኛ ሁኔታ በመደረጋቸው ነው። በዚህም ጽንፈኛ የቡድሂስት ቀሳውስት ፌስቡክን ፍርሀትን ለማነሳሳት፣ የጥላቻ አመለካከቶችን መደበኛ ለማድረግ በሮሂንጊያ እና በሌሎች ሙስሊም ማህበረሰቦች ላይ የሚፈጸሙ ጥቃቶችን ለማመቻቸት ተጠቅመውበታል።

ማኅበራዊ ሚዲያ ወደ ጥቃት እና የሰብአዊ መብት ጥሰት ሊያመራ የሚችል አመለካከቶችን ሀላፊነት በጎደለው ሁኔታ ለመለጠፍ ምቹ ቦታ ነው። በኢምራን አዋን (2016) የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው አንዳንድ የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች በማህበረሰብ ትስስር ላይ ጉዳት የሚያደርስ እስልምና-ጠልና ዘረኛ የሆነ አስፈሪ ምናባዊ አካባቢ የሚፈጠር ትርክት በማኅበራዊ ሚዲያ የሚያሰራጩ መሆኑን ያመለክታል።

ማኅበራዊ ሚዲያ የፖለቲካ መራራቅን (polarization) ያጎላል፣ ልወደድ ባይነትን (populism) እና የተሳሳተ መረጃ ስርጭትን ያበረታታል። ማርቲን ጉሪ (Martin Gurri) የተባለ ተመራማሪ በ2018 በታተመና "*The Revolt of The Public and the Crisis of Authority in the New Millennium*" በተሰኘ መጽሀፉ ማኅበራዊ ሚዲያዎች በሦስት መንገዶች ኢ-ፍትሀዊነትን እና የፖለቲካ ችግርን አምጥተዋል ሲል ይተነትናል። አንደኛ፣ ማኅበራዊ ሚዲያ ጥሩ ዜጎችን ዝም እያሰኘ ሆን ብለው መልካም ያልሆነ መረጃን ለሚያሰራጩ ተጠቃሚዎች (trolls) እና ለደጋፊዎቻቸው የበለጠ ኃይል ይሰጣል። በዚህ ረገድ በፖለቲካ ሳይንቲስቶቹ አሌክሳንደር ቦር እና ማይክል ፒተርሰን የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው በማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ላይ ያሉ አንዳንድ ጥቂት ግለሰቦች በማኅበራዊ ሚዲያ ውስጥ ተሰሚነት ለማግኘት የማይፈነቀሉት ድንጋይ የለም። በዚህም እስከ ጠበኝነት ድረስ ለመሄድ ፈቃደኞች ናቸው። ብዙ ሰዎች በኦንላይን በመሆናቸው ብቻ የበለጠ ጠበኛ ወይም ጠላት እንዳላደረጋቸው ቦር እና ፒተርሰን ደርሰውበታል። ይልቁንም ጥቂት ቁጥር ያላቸው ጠበኛ ሰዎች የብዙ ሰዎችን ስብስብ እንዲያጠቁ አስችሏቸዋል። ተጨማሪ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሴቶች እና ጥቁሮች ያልተመጣጠነ ትንኮሳ በማኅበራዊ ሚዲያ ይደርስባቸዋል።

ሁለተኛ፣ የማኅበራዊ ሚዲያው ለፖለቲካው ፅንፎች የበለጠ ሀይል እና ድምጽ ሲያጎናጽፍ፤ የለዘብተኛ ብዙሀኑን ኃይልና ድምጽ ይቀንሳል። የፖለቲካ ጽንፈኞች በጠላቶቻቸው ላይ ብቻ አይተኩሱም፣ ብዙ ጥይቶቻቸውን በራሳቸው ቡድን ውስጥ ባሉ ነገር ግን የተለዩ አስተሳሰቦች ላይ በማነጣጠር ያጠፋሉ። በዚህም ማኅበራዊ ሚዲያ የተለየ ሀሳብ ያላቸውን በማጥፋት በመግባባት ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ ሥርዓት እንዳይፈጠር ዕንቅፋት የመሆን መሣሪያ ይሆናል። በሦስተኛ ደረጃ፣

ማኅበራዊ ሚዲያ ለሁሉም ሰው ጥይት በማቅረብ፣ ማንኛውም ሰው ያለምንም ህጋዊ ሂደት ‹‹ፍትህን›› በገዛ እጁ እንዲፈልግ ያለከልካይ ይፈቅዳል፡፡

ከላይ የተብራራው እርስ በርስ የሚቃረኑ የሚመስሉት ሁለቱ አመለካከቶች በአንድ ጊዜ (simultinously) እውነት እና ትክክል ናቸው፡፡ ይህም ማኅበራዊ ሚዲያ ‹‹ባለ ሁለት ስለት ጎራዴ›› (double-edge sword) የተባለበትን ትክክለኛ ባህሪውን ያሳየናል፡፡ በዚህም ማኅበራዊ ሚዲያ በአንድ ጊዜ መልካምም (novel) ክፉም (evil) መሣሪያ ሊሆን ይችላል ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መሣሪያውን ለበጎም ሆነ ለመጥፎ፤ ለሰላምም ሆነ ለጥቃት፣ ለልማት ሆነ ለጥፋት የማዋል ፍላጎትና አቅም በተጠቃሚው ላይ ያረፈ ነው፡፡

## 5. ማኅበራዊ ሚዲያ ወጣቶች ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ

ማኅበራዊ ሚዲያ በወጣቶች ህይወት ውስጥ አዎንታዊም አሉታዊም ተፅዕኖ በመፍጠር ትልቅ ሚና ይጫወታል፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያ ወጣቶች እንደየፍላጎታቸው ቡድኖች እና ገፆች የሚፈጥሩበት እና የተለያዩ የውይይት ርዕሶችን በማዘመን ለትስስር ዕድል የሚፈጥሩበት መሣሪያ ነው፡፡ እንዲሁም በሚኖሩበት አካባቢ ከሰዎች ጋር ለመገናኘት ቀላሉ መንገድ ሆኗል፡፡ አሁን አሁን አዳዲስ መረጃዎችን ለማግኘት ወጣቶች በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የበለጠ ጥገኛ እየሆኑ መጥተዋል፡፡ የማኅበራዊ ሚዲያ ገፆች ፈጣን እና ቀልጣፋ በሆነ መንገድ እንዲግባቡ ከማስቻላቸው በተጨማሪ፤ ማኅበራዊ ግንኙነቶችን ለመገንባት እና ከአገር ውጭ ከሚኖሩ ጓደኞች፣ ቤተሰቦች እና እንዲያውም ከቅርብ የቤተሰብ አባላት ጋር በቀላሉ እንዲገናኙ አስችሏቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ማኅበራዊ ሚዲያ ለወጣቶች ሀሳባቸውን የሚገልፁበት ሰፊ ቦታም ሰጥቷቸዋል፡፡

ይሂን እንጂ ከላይ በክፍል 3 ከተጠቀሱት አጠቃላይ አሉታዊ ተፅዕኖዎች በተጨማሪ ማኅበራዊ ሚዲያ በተለይ በወጣቶች ላይ የሚያሳድራቸው ተጨማሪ አሉታዊ ተፅዕኖዎች ዘርፈ ብዙ ናቸው፡፡ እነሱም እንደሚከተሉት ለማብራራት ተሞክሯል፡፡

### ሀ. የማኅበራዊ ግንኙነትና የተግባቦት ክህሎት ችግር

ማኅበራዊ ሚዲያ ባልተከሰተበት ባለፉት ዘመናት ፊት ለፊት የሚደረግ ግንኙነት ብቸኛው የመገናኛ ዘዴ የነበረ ሲሆን፤ አሁን በኔትወርክ እና በቴክኖሎጂ ዘመን ይህ የግንኙነት ዘዴ በማኅበራዊ ሚዲያ መስተጋብር ውይይቶችን በመተካት ላይ ይገኛል፡፡ ዛሬ ኔትዎርኪንግ እና ይዘትን መጋራት ልማድ እየሆነ በመጣበት ጊዜ ወጣቶች ምናልባት ፊት ለፊት ከመገናኘት ይልቅ ከጓደኞቻቸው እና ከቤተሰቦቻቸው ጋር በማኅበራዊ ትስስር ገፆች የመነጋገር ዕድላቸው ሰፊ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ

በቤተሰብ ስብሰባዎች ላይ ሰዎች ስማርት ስልኮቻቸውን ሁኔታቸውን ለማዘመን (updating their status) ወይም ከርቀት (virtual) ጓደኞቻቸው ጋር ለመወያየት ሲተጉ ይስተዋላል:: በመሆኑም በዙሪያቸው ካሉ ግለሰቦች ጋር የመገናኘታቸው ዕድል እጅግ እየጠበበ መጥቷል:: ይህ ለውጥ ውጤታማ የተግባቦት ችሎታቸውን ሊያደናቅፍ ይችላል:: ብዙ ጊዜ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ የሚያጠፉ ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር የሚያሳልፉት ጊዜ የላቸውም፤ የቀረበላቸውን ተመግበው በቶሎ ወደክፍላቸው የመሮጥ ነገር ይታይባቸዋል::ማኅበራዊ ክህሎታቸው በጣም ዝቅተኛ የሚያደርግና አዲስ ሰውን የመተዋወቅ ችሎታቸውን የሚቀንስ ይሆናል::

ማኅበራዊ ሚዲያ በወጣቶች ማኅበራዊ ህይወት ዘይቤ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል:: ከባልንጀሮቻቸው ጋር በአካል ከመገናኘት ይልቅ ከምናባዊ ጓደኞቻቸው ጋር በቨርቿል:: በዚህም ማኅበራዊነታቸው እየቀነሰ በመምጣት ላይ ይገኛል:: ወጣቶች ከቤተሰቦቻቸው ጋር ከመገናኘት ይልቅ የሞባይል ስልኮቻቸውን፣ ዴስክቶፖችን፣ ላፕቶፖችን ወዘተ መጠቀምን ይመርጣሉ:: በመሆኑም ከእውነተኛ ህይወት ጓደኞቻቸው ጋር ከመገናኘት ይልቅ የኢንተርኔት አዋቂ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል::

### ለ. የስነልቦና ችግር

የማኅበራዊ ድረ-ገጾች ከፍተኛ ተጠቃሚ የሆኑ ወጣቶች መካከል አብዛኞቹ የመንፈስ ጭንቀት እና ብቸኝነት ይሰማቸዋል:: እንዲሁም በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ የሚጠፋው ጊዜ ወጣቶች በኢንተርኔት ላይ ተከታታይ የ‹‹ትሮሎች›› ሰለባ ስለሚያደርጋቸው በስነ ልቦና ችግር እንዲሰቃዩ በር ይከፍታል:: በፌስቡክ ‹‹መውደዶች›› (likes) እና የወጣቶች በራስ መተማመን መካከል ጠንካራ ግንኙነት አለ:: አብዛኛው ወጣት በማኅበራዊ ድህረ-ገፆች በ‹‹ህብረተሰብ›› የተቀመጠውን የውበት ደረጃ እንዲኖረው ጫና ይፈጠርበታል:: ወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያው ከመደበኛ ሰው ህይወት የተለየና ያልተለመደ የአኗኗር ዘይቤ ላላቸው ታዋቂ ሰዎች የሚጋለጡበት መድረክ መሆኑን ላያውቁ ይችላሉ:: ይህ ሁኔታ በወጣቶች ዘንድ በራስ ገጽታ አለመርካትን፣ የአመጋገብ ችግርን፣ ድብርት እና በራስ የመተማመን ስሜትን የማጣት ችግሮችን ሊያስከትል ይችላል:: ለራሳቸው ዝቅተኛ ግምት ያላቸው ወጣቶች፣ ሌሎች ስለ እነርሱ ምን ይላሉ ወይም ያስባሉ በማለት እጅግ ይጨነቃሉ፣ ያሰቡትን አይናገሩም፣ ምናልባትም ራሳቸውን ሁል ጊዜ ይነቅፋሉ ወይም ሌሎችን ያለ ምንም ጥፋት ይቅርታ የሚጠይቁ እና ከሁሉም በላይ በማያቋርጥ የሀዘን ስሜት፣ ድብርት፣ ጭንቀት እና ቁጣ ይኖራቸዋል:: በዳሰሳ ጥናቶች መሠረት ወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያን አብዝቶ መጠቀም፣ ከአንዱ የማኅበራዊ ትስስር ድረ-

ገጽ ወደ ሌላው መዘዋወር፣ ‹‹ሜም›› በፌስቡክ ላይ መለጠፍ፣ ተዋናዮችን በኢንስታግራም መከታተል እና በዋትስአፕ ቀኑን ሙሉ ማውራት ለራሳቸው ያላቸውን ግምት ዝቅተኛ ያደርጋል። ያለማቋረጥ ህይወታቸውን በውበት፣ በጤና እና በሀብት ከሚበልጧቸው ጋር ያወዳድራሉ በመሆኑም ምስጋና ቢስ ይሆናሉ፤ የበታችነት ስሜት ይሰማቸዋል። ይህ አሉታዊነትን (negativity) እና ተስፋ መቁረጥን ያበረታታል። በዚህም ሳቢያ ለሚኖሩበት ማህበረሰብ ምንም ዓይነት መልካም ነገር ማድረግ አንችልም የሚል ስሜት እንዲያድርባቸው ያደርጋል።

### ሐ. የጊዜ አጠቃቀም ችግር

በቅርቡ የወጡ ግኝቶች እንደሚያሳዩት ማኅበራዊ ሚዲያ አብዛኛውን ወጣት ከትምህርትና ከሥራ እየዘናጋ መሆኑን ያመለክታሉ። በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ የሚጠፋው ጊዜ ሰፊነት ከተማሪዎች የትምህርት ክንዋኔ ጋር ጠንካራ ግንኙነት አለው። ብዙ ጥናቶች እንዳረጋገጡት ወደ በአለም አቀፍ ደረጃ 50% የሚጠጉ ወጣቶች ሦስት ወይም ከዚያ በላይ የተለያዩ ማኅበራዊ ሚዲያ የሚጠቀሙ ሲሆን፤ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚያሳልፉት ጊዜም በአማካይ በቀን ለሦስት ሰዓታት ነው። ይህም ማኅበራዊ ሚዲያ ከወጣቶች ላይ ብዙ የስራ ጊዜ እንደሚወስድ ያመለክታል። ለትምህርትና መማር ጥቅም ላይ መዋል የነበረበት ጊዜ በኦንላይን አዳዲስ ጓደኞችን በማፍራት፣ መገለጫዎችን በማዘመን (updating profiles) እና ትርጉም በሌላቸው ጉዳዮች ላይ በመወያየት ያሳልፋሉ። በክፍል ውስጥ እንኳን በፌስቡክ፣ ትዊተር ወዘተ ላይ ሲጠመዱ ይስተዋላል። የትምህርት መጽሐፍቶችን በማንበብ ለዘለቄታ የሚሆን ዕውቀት መገብየት ሲገባቸው ከጠዋት እስከ ማታ፤ አንዳንድ ጊዜ ሌሊቱን ጭምር ጊዜያቸውን በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የሚያባክኑ ወጣቶች ቁጥር ቀላል አይደለም።

### መ. ለወንጀሎች ተጋላጭነት ችግር

በአሁኑ ጊዜ ወጣቶች የዕለት ተዕለት ኑሯቸውን እና የግል መረጃዎቻቸውን እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር እና ኢንስታግራም ባሉ ማኅበራዊ ሚዲያዎች ላይ መለጠፍና ማጋራት ይወዳሉ። የሰሩትን ሁሉ ለሰዎች ማሳየት አዲስና የተለመደ ዘይቤ ሆኗል። በማኅበራዊ ሚዲያ ውስጥ ያሉ የተጠቃሚዎች መረጃዎች፣ ፎቶዎች እና ቪዲዮዎች ላልተወሰነ ጊዜ በዚያው የሚቆዩ በመሆናቸው ማኅበራዊ ሚዲያን የሚጠቀሙ ወጣቶች ለሳይበር ወንጀሎች እና እንደ አፈና፣ ግድያ እና ዝርፊያ ላሉ አደገኛ ሁኔታዎች የመጋለጥ ዕድላቸው ከፍተኛ ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት የማኅበራዊ ሚዲያ አዘውታሪ ተጠቃሚዎች ብዙ የግል መረጃዎቻቸውን ስለሚለጥፉ እንዲሁም

ማኅበራዊ ሚዲያ ዝቅተኛ የደህንነት ሥርዓት ያለው በመሆኑ እነዚህ የግል መረጃዎቻቸውን በቀላሉ በማንኛውም ሰው እጅ መግባት ስለሚችሉ ነው።

### *ሠ. የማኅበራዊ ሚዲያ ሱሰኝነት*

የማኅበራዊ ሚዲያ ሱስ ወይንም በጠቅላላ ኢንተርኔት ሱሰኛነት የተለመደ ባይሆንም፤ ገደብ የለሽ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ‹‹የማኅበራዊ ሚዲያ ሱሰኝነት›› ተብሎ ሊገለፅ እንደሚችል ብዙ የመስኩ ተመራማሪዎች ይናገራሉ። የሥነ ልቦና ጥናቶች እንደሚያሳዩት በኅብረተሰቡ በተለይም ወጣቶች ውስጥ ‹‹የመረሳት ፍርሀት›› (Fear of Missing Out - FOMO) በፍጥነት በመስፋፋት ላይ ይገኛል። በዚህም ምክንያት የማኅበራዊ ሚዲያን ጉዳይ ከራሳቸው እና ከሕይወታቸው (እና የሌሎች ሕይወት) የበለጠ ያስቀድማሉ። በመሆኑም ወጣቶች እና ጎልማሶች መኪና በሚያሽከረክሩበት ጊዜም ሳይቀር የጽሑፍ መልእክት ይላላካሉ። ይህም የሚሆነው የበለጠ አስደሳች ወይም አዝናኝ የሆነ ነገር እየተከሰተ ሊሆን ይችላል ብለው ስለሚያስቡ ነው ተብሎ ይታመናል። ይህ ችግር በአብዛኛው ጊዜ በወጣቱ የማኅበረሰብ ክፍል ላይ መታየቱ ደግሞ ብዙ የመሥራት አቅም ያለውን ኃይል እያንኮታኮተ ጊዜውን በአግባቡ እንዳይጠቀም ማድረጉ የማኅበራዊ ሚዲያን አሉታዊ ጎን አጉልቶ ያሳያል ሲሉ ብዙዎች ይተቻሉ።

በአሁኑ ጊዜ በማኅበራዊ ሚዲያ በጣም የተጠመዱ፣ ሰፊውን ጊዜያቸውን በሞባይል ስልካቸው ወይንም በኢንተርኔት ላይ የሚያሳልፉ ወጣቶች በስፋት ይታያሉ። እነኚህ ወጣቶች በከፍተኛ ሁኔታ ከኢንተርኔት ጋር ቁርኝት ወይንም ሱሰኝነት እያጋጠማቸው ነው። በዚህም ሳቢያ የሚፈጠርባቸው ሥነልቦናዊ ጫና አለ። ይህ ስነልቦናዊ ጫና ከስሜት፣ ከአስተሳሰብ መዛባት እንዲሁም ከድርጊት ጋርም የሚያያዝ ነው። ለምሳሌ በማኅበራዊ ሚዲያዎች አማካኝነት የሚሰሙ ክፉ ዜናዎችን ወይንም መጥፎ ቪዲዮዎችን በመመልከት የመረበሽ የመጨነቅ ሁኔታ ያጋጥማቸዋል። ከዛም አልፎ ደግሞ ከወሲብ (pornographic) ፊልሞች ጋር ተያይዞ ወጣቶች የበለጠ ሱሰኛ የመሆንና ከዚያ ያላመላቀቅ ችግር ያጋጥማቸዋል።

## 6. በኢትዮጵያ የወጣቶች የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም እና ፈተናዎች

ኢትዮጵያ አስራ አምስት በመቶ የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽነት በመስጠት ከዓለም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ከሚገኙ አገራት መካከል ትገኛለች። እንደ DataReportal (2021) ሪፖርት በጥር 2021 እ.ኤ.አ በኢትዮጵያ 6.7 ሚሊዮን የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች አሉ። የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር በ2020 እና 2021 በ500 ሺህ (+8.1%) ጨምሯል። በኢትዮጵያ ያለው የማኅበራዊ ሚዲያ የስርጭት

መጠን ከኢንተርኔት አጠቃቀም ኂላ የቀረ ሲሆን የተጠቃሚዎች ብዛት ከጠቅላላው ሕዝብ 9.5 በመቶ አካባቢ እንደሚሆን ይገመታል። በአገሪቱ ያለው የማኅበራዊ ሚዲያ ገበያ በፌስቡክ የበላይነት የተያዘ ነው። ከፌስቡክ በተጨማሪ ዩቲዩብ እና ትዊተር በርካታ ተጠቃሚ ያላቸው ማኅበራዊ ሚዲያዎች ሲሆኑ በአሁኑ ወቅት ቴሌግራምም በስፋት ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ይገኛል።

በኢትዮጵያ ወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያን ለተለያዩ ዓላማዎች ይጠቀማሉ። ለግንኙነት (relation)፣ ለመዝናኛ (recreation)፣ ለመረጃ (information) (መረጃን ለመፍጠር፣ ለማሰራጨት እና ለመለዋወጥ ወዘተ) ማኅበራዊ ሚዲያው በዋናነት ጥቅም ላይ የሚውልባቸው ግልጋሎቶች ናቸው። ከነዚህ በተጨማሪም ዜና ለማንበብ፣ በራዲዮ እና በቴሌቭዥን ያመለጧቸውን ወይም የማይቀርቡትን መረጃዎች ለማግኘት፣ ስለ ቀድሞ ጓደኞቻቸው ህይወት ለማወቅ፣ በአካባቢያቸው እየተከሰቱ ስላሉት ክስተቶች ለመዘገብ እና በወቅታዊ አገራዊ ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስፖርት ጉዳዮች ላይ ራሳቸውን ለማዘመን (update ለማድረግ) ወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያን በስፋት ይጠቀማሉ። እንዲሁም ፎቶግራፎችን እና ተንቀሳቃሽ ምስሎችን ለማጋራት፣ የግል መልእክቶችን ለማስተላለፍና የተለያዩ አስተያየቶችን ለማካፈል የማኅበራዊ ሚዲያ አማራጮችን ይጠቀማሉ።

በተጨማሪም ባለፉት ሰባት/ስምንት ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ ወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለማደራጀት እና መንግስትን ለመቃወም ማኅበራዊ ሚዲያን በከፍተኛ ደረጃ ሲጠቀሙ ተስተውሏል። በእርግጥ በኢትዮጵያ ወጣቶች ዘንድ አዳዲስ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን ለፖለቲካዊ ዓላማ መጠቀም የ2008 ዓ.ም ህዝባዊ ተቃውሞ ከመፈንዳቱ በፊትም ለረጅም ጊዜ የነበረ ነው። የእነ ጋግሊያርዶን (Gagliardon 2019) ጥናት እንደሚያሳየው በ1997 ዓ.ም በተካሄደው አገራዊ ምርጫ ምንም እንኳን በጣም የተገደበ የበይነ-መረብ እና የሞባይል ስልክ ግንኙነት ቢኖርም ጋዜጠኞች እና አክቲቪስቶች አዳዲስ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ወቅታዊ ክርክሮችን ለብዙ ታዳሚዎች ለማሰራጨት ችለው ነበር። በኦንላይን የተለጠፉትን አስተያየቶች እና ጥሪዎችን በመተርጎምና እንደገና በማታም እንዲሁም የጽሑፍ መልእክቶች (text message) በመሬት ላይ ያሉ ድርጊቶችን ለማስተባበር ማኅበራዊ ሚዲያ በስፋት ጥቅም ላይ ውሏል።

ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም በሀገሪቱ በተደረጉ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ማኅበራዊ ሚዲያ ተግባራዊ መረጃዎችን በማስተላለፍ እና የጋራ እንቅስቃሴን በማስተባበር ቁልፍ ሚና ተጫውቷል። በዋናነት በብሔረሰብ የተደራጁ ወጣቶች እንደ ፌስቡክ እና ትዊተር ባሉ ማኅበራዊ ድረ-ገጾች የተቃውሞ ስልቶችን

ለማሰራጨት፣ አባላትን ለመመልመል እና ድጋፍን ለማጠናከር ተጠቅመውባቸዋል። የኦሮሞ ቄሮ፣ የአማራው ፋኖ፣ የሲዳማ ኤጄቶ የመሳሰሉ አደረጃጀቶች የመንገድ ላይ ሠልፍ፣ የፖሊስ ጥቃት እና የመሳሰሉትን የሚያሳዩ የተለያዩ ፎቶዎችና እና ቪዲዮዎች በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ በመለጠፍ እና በማጋራት ይለዋወጡ ነበር።

በቴዎድሮስ ወርቅነህ (2020) የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች የኢትዮጵያ ወጣቶች በፖለቲካዊ ንግግሮች ውስጥ እንዲሳተፉ በማድረግ፣ ቀድሞ የተገለሉ ቡድኖችን በፖሊሲ ላይ ተፅዕኖ እንዲያሳድሩ እና የቡድን (ingroup) የባህል/የፖለቲካ ትስስር እንዲጠናከር በማድረግ ወሳኝ ሚና ተጫውተዋል። ይሁን እንጂ መረጃዎች እንደሚያመለክቱት በማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች የተፈጠሩ የተሳትፎ ዕድሎች የጥላቻ ንግግሮች እንዲበዙ እና የፖለቲካ አክራሪነትም እንዲጨምር አድርገዋል።

በማኅበራዊ ድረ-ገጾች ላይ ዜናዎችን የሚያገኙ እና የሚያሰራጩ ወጣት ኢትዮጵያውያን ቁጥራቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱ ለተሳሳተ መረጃ መስፋፋት ዋነኛ ኢላማ ሆኗል። የማኅበራዊ ሚዲያ አውዶችን በመጠቀም የሚተላለፉ መልእክቶች ግለኝነትን የሚያንፀባርቁ ከመሆናቸው በላይ፤ መድረኮቹ የጥላቻ ንግግሮችን ለማስተላለፍ እና ሰዎችን ለጥፋት የማደራጃ መድረክ እየሆኑ መምጣታቸው እየተስተዋለ ነው። በሀገሪቱ የሚስተዋለው ስር የሰደደ የውስጥ ግጭት እና የፖለቲካ አለመረጋጋት የተሳሳቱ መረጃዎች ስርጭት እንዲስፋፋ ምቹ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። በተሳሳቱ መረጃዎች እና በማኅበራዊ ድረ-ገጾች በሚተላለፉ የፕሮፓጋንዳ ዜናዎች ምክንያት ግጭት በተከሰተባቸው አካባቢዎች የሚኖሩ ሰዎች ህይወት በእጅጉ ተጎድቷል። በተለይ ደግሞ ወጣቶች በማኅበራዊ ሚዲያ የተሳሳተ መረጃ ተገፋፍተው ያልተገባ አቅጣጫ በመያዝ ብዙ የብሔርና የሀይማኖት ግጭቶች እንዲከሰቱ ምክንያት ሆኗል።

በኢትዮጵያ አንዳንድ ወጣቶች ዘንድ ማኅበራዊ ሚዲያውን (ፌስቡክ ወዘተ) አግባብ ባልሆነ መንገድ ለአፍራሽ ተግባራት መጠቀም እየተለመደ መጥቷል። በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ የማይወጣ አሉባልታ፣ የ‹‹በሬ ወለደ›› የፈጠራ ወሬ፣ የተሳሳተ ዜና እና የግልና የቡድን ስሜት የለም። ይህም በአገሪቱ ውስጥ እየተባባሰ ለመጣው የፖለቲካ ተቃርኖ (polarization) የራሱን አስተዋጽኦ እንዳደረገ የብዙዎች ዕምነት ነው። ይህንን በተመለከተ በአንድ ወቅት የቀድሞ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ የማኅበራዊ ሚዲያውን ቀውስ ሲገልጹ ‹‹የእኛ ሀገር አንዳንድ የማኅበራዊ ሚዲያ ጦማሪዎችም ልክ እንደ መርፌ ናቸው። እነርሱ ሀገር በሚወጋ መርፌያቸው እየወጉን ሲጓዙ፤ እንደ ክር አያሌዎች መድረሻቸውን ሳይጠይቁ

ይከተሏቸዋል፡፡ ድረ-ገጻቸውን የሚያነብላቸው ተከታታይና ደጋፊ ማብዛታቸውን እንጂ ሀገርና ሕዝብ ላይ እያስከተሉ ያሉትን አደጋ፣ እየረጨት ያለውን መርዝ ሊያዩት አልቻሉም›› ብለው ነበር፡፡

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ማኅበራዊ ሚዲያዎች የወጣቶች የወሲብ መገበያያ ቦታዎችም ሆነዋል፡፡ በይነ መረብ እና ማኅበራዊ ሚዲያዎች ሰዎች ከዚህ በፊት ወሲብ ፍለጋ ወደ ምሽት ቤቶች ያደርጉት የነበረውን ጊዜ በማሳጠሩ የወሲብ ንግድን ቀላል እንዳደረገው የማህበረሰብ ጤና ባለሙያዎች ያመለክታሉ፡፡[4]

## 7. የወጣቶች የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ችግሮችን የሚያባብሱ ምክንያቶች

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚተዋለውን የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ችግር የሚያባብሱ አያሌ ምክንያቶች አሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ ወጥለው ተዘርዝረዋል፡፡

*ሀ. ከፍተኛ ስራ አጥነት እና በፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የተደራጁ ወጣቶች መኖር፡-*

እንደ የኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ በኢትዮጵያ የስራ አጥ ቁጥር በ2022 መጨረሻ 23 በመቶ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል፡፡[5] በተጨማሪም በአሁኑ ጊዜ በአገሪቱ ውስጥ በየቦታው በፖለቲካ የተደራጁ ብዙ ወጣቶችን ማየት የተለመደ ሆኗል፡፡ እ.ኤ.አ. በ2018 መጨረሻ አካባቢ እንደ ኦሮሞ ቄሮ እና የአማራው ፋኖ ያሉ የተቃውሞ ቡድኖች አባላትን ለመመልመልና እና ለማደራጀት ማኅበራዊ ሚዲያ እና የፈጣን መልእክት መድረኮች በስፋት ጥቅም ላይ አውለው ነበር፡፡ እነዚህ ቡድኖች በድህረ-ተቃውሞ ወቅትም ውስጥ በተበታተነ መልኩ ቢሆንም ንቁ ሆነው የቆዩ ሲሆን በአብዛኛው የፖለቲካ ድርጅት እንዲጨምር እና የብሄር ስልጣን እንዲጠናከር ይፈልጋሉ፡፡ እነዚያን ወጣቶች በፖለቲካ አራማጆች እና ፖለቲከኞች ለጠባብ የቡድን ጥቅሞቻቸው እና ለጥቃት/ግጭት በማኅበራዊ ሚዲያ በቀላሉ እየንቀሳቀሱ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

*ለ. የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ግጭቶች እና የእርስ በርስ ጦርነት፡-*

በአሁን ሰዓት ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ አለመረጋጋት፣ ግጭቶች እና የእርስ በርስ ጦርነት መኖሩ ይታወቃል፡፡ በዚህም ምክንያት መንግስት እና ተቃዋሚዎች (ለምሳሌ የሕወሓት እና የኦሮሞ ነፃነት ሠራዊት አማፂ ተዋጊዎችን

---

4 https://am.al-ain.com/article/social-media-emerges-as-new-commercial-sex-platform-in-ethiopia

5 Statistical Report on the 2022 1st Round Urban Employment and Unemployment Survey available at: www.csa.gov.et

ጨምሮ) ማኅበራዊ ሚዲያን እንደ የጦር መሣሪያ (weaponisation of social media) እየተጠቀሙ ይገኛሉ። ለምሳሌ ከታች ያሉት ምስሎች ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ የማኅበራዊ ሚዲያ ምን ያህል የፖለቲካና የጦርናት እንደሆነ ያመለክታሉ። የፌስቡክ ሚሊሻዎች ማኅበራዊ ሚዲያን ‹‹የጥቃት ጥሪዎችን ለመዝራት›› እንደሚጠቀሙበት የፌስቡክ መረጃ አጋላጭ የሆነው የፍራንሲስ ሀውገን ሠነድ ያመለክታል።[6] እንደዚህ አይነት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ወጣቶች በማኅበራዊ ሚዲያ ፕሮፖጋንዳ እና ሀሰተኛ መረጃ ላይ በንቃት እንዲሳተፉ ይበረታታሉ፤ ይህም መጥፎ ልማዶችን ትቶ እንደሚያልፍ አያጠራጥርም።







ምስል 2፡ ዜጎች በማኅበራዊ ሚዲያ የጦር ፕሮፓጋንዳ እንዲሳተፉ የሚያበረታቱ መልዕክቶች

### *ሐ. ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ የመጣው የማኅበራዊ ትስስር (social cohesion) ዕሴቶች መሸርሸር፡-*

ኢትዮጵያውያን እርስ በርስ መተሳሰብን፣ አንድነትን፣ ሰላምን እና የቤተሰብን ስሜት ለማጠናከር የሚያስችሉ ለረጅም ጊዜ ያገለገሉ ሀገር በቀል ባህላዊና ልማዳዊ ዕሴቶች አሉን። ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ እነዚህ ዕሴቶች በተለያዩ ምክንያቶች የተሸረሸሩ ይመስላሉ። እንዲያውም በአንዳንድ ሁኔታዎች አንዳንድ ፀረ-ሰላም አካላት ሆን ብለው እነዚህን ሥር የሰደዱ ዕሴቶችን ለማዳከም እየሞከሩ፤ በተቃራኒው ውዝግብንና ጥላቻን እያስተላለፉ ይገኛሉ። በእንደዚህ ዓይነት አውድ ውስጥ ማኅበራዊ ሚዲያ ጥላቻን ለማራመድና እና ብሔራዊ መግባባትን የሚያደናቅፉ አለመግባባቶችን ለመዝራት እና ለማጉላት ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል።

### *መ. የብሔር፣ የሀይማኖት እና ‹‹የታሪክ›› ፖለቲካ መስፋፋት፡-*

[6]https://www.technologyreview.com/2021/10/05/1036519/facebookwhistleblower-frances-haugen-algorithms/

በማኅበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ምክንያት በአጠቃላይ በአለም ላይ የፖለቲካ ጽንፈኝነት፣ ጭፍን ወገንተኝነት እና የቁጣ ባህል እያደገ መምጣቱን ማስረጃዎች ያመለክታሉ። በኢትዮጵያ ነገሩን የሚያባብሰው የብሔር፣ የሀይማኖትና ‹‹የታሪክ›› ፖለቲካ (Politicisation of ethnicity, religion and history) ይበልጥ እየጎላ የመጣበት ወቅት ላይ የምንገኝ መሆናችን ነው። በኢትዮጵያ በብሔርተኝነት እና በሀገር ግንባታ መካከል ያለው የፉክክር ውጥረት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በኦንላይን በሚደረጉ ንግግሮች ብዙን ጊዜ ወደ ቀስቃሽ እና የጥላቻ ንግግሮች ተሸጋግረዋል።

## *ሠ. የባህላዊ ሚዲያዎች (ቴሌቪዥን ፣ ሬዲዮ ፣ ጋዜጣ ፣ ወዘተ) የተለያዩ አስተያየቶችን ማስተናገድ አለመቻል፡-*

ከዚህ በፊት መንግስት ሚዲያዎችን ሳንሱር ያደርግ ነበር። ጋዜጠኞችን እና የሚዲያ ተቋማትን ከማዋከቡ በተጨማሪ ሳተላይት ላይ የተመሠረቱ ሚዲያዎችን በማጨናነቅ (jam በማድረግ) ይታወቅ ነበር። በአንፃራዊነት የ2010 ዓ.ም የመንግስት ለውጥን ተከትሎ የሚዲያ ነፃነት ላይ መሻሻሎች ታይተዋል። ይሁን እንጂ ከለውጡ በኋላ መንግስት ቀስ በቀስ ወደ ቀድሞው ልምድ በመመለስ የከፈተውን በር መልሶ ለመዝጋት እየሞከረ ነው የሚል ወቀሳ በስፋት ይደመጣል። መንግስት ራሱ በባለቤትነት የሚቆጣጠረውን የኢትዮሳት የሳተላይትን ማስተላለፊያ ሳተላይት መፍጠሩ በብዙ አስተያየት ሰጪዎች ዘንድ መንግስት የሚዲያ ምህዳሩን በብቸኝነት የመቆጣጠር ፍላጎቱ መገለጫ ተደርጎ ይቆጠራል። እንደዚህ አይነት እርምጃዎች ወጣቶች አማራጭ መረጃ ፍለጋ ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ጥገኛ እንዲሆኑ ያስገድዳቸዋል።

## *ረ. የማህበረሰባችን የሚዲያ ባህል አለመዳበር፡-*

ኢትዮጵያ ውስጥ ባለን አጭር የሚዲያ ታሪክ ሳቢያ ሁሉንም ሚዲያዎች የማመን፣ የሚዲያ መረጃን ሳያጣሩ የመቀበል የመሳሰሉት ችግሮች ይስተዋላሉ። በተለይም ቀደም ሲል በነበሩት ጊዜያት የነበሩት የመገናኛ ብዙሀን በመንግስት ቁጥጥር ስር የነበሩ እና በጣም ጥቂት ውሳኔዎችን እና እውነታዎችን (ምንም እንኳን የአንድ ወገን ቢሆኑም) ያስተላልፉ ነበር። አሁን ግን የግል አስተያየቶችን የሚያስተላልፉ ብዙ የመገናኛ ብዙሀን እና በይነ-መረብ ላይ የተመሠረቱ ሚዲያዎች (ዩቲዩብን ጨምሮ) በስፋት ይገኛሉ። ካለፉት ጊዜያት ተፅዕኖዎች የተነሳ ኢትዮጵያውያን ማንኛውም በመገናኛ ብዙሀን የሚተላለፉትን መልእክቶች ትክክለኛ ናቸው ብለን የመቀበል ችግር እንዳለብን ይታመናል። ይህም ማኅበራዊ ሚዲያውን ለአፍራሽ ተልዕኮ አመቺ መድረክ አድርጎታል ተብሎ ይታመናል።

*ሰ. የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ግድየለሽነት፡-*

የማኅበራዊ ሚዲያ አገልግሎት ሰጪዎች በኢትዮጵያ ግጭት ቀስቃሽ የሆኑ ንግግሮችን ለመከላከል በቂ ትኩረት ባለመስጠት ይወቀሳሉ። ለምሳሌ ፌስቡክ አገልግሎቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ብጥብጥ ለመቀስቀስ ጥቅም ላይ እንደሚውል ያውቃል። ነገር ግን ይህንን ለመከላከል ብዙም ጥረት እንዳላደረገ ሰነዶች ያሳያሉ። ይህ አፍራሽ እና ግጭት ቀስቃሽ ንግግሮችና ምሽሎች በነፃ እንዲዘዋወሩ እና ጥላቻ ስር እንዲሰድ ሰፊ መንገድ ይከፍታሉ።

*ሸ. የማኅበራዊ ሚዲያን የንግድ ስራ ማድረግ (commercialisation)፡-*

ለማኅበራዊ ሚዲያ አሉታዊ ተፅዕኖዎች መባባስ አስተዋፅዖ የሚያደርገው ሌላኛው ምክንያት ማኅበራዊ ሚዲያው የንግድ ስራ መስክ *(commercialisation)* መሆኑ አንዱ ነው። ይህ ማለት የአንዳንድ ማኅበራዊ ሚዲያዎች (ለምሳሌ፤ ዩቲዩብ፣ ቲክቶክ) ይዘት ፕሮዲዩሰሮች ለቪዲዮዎቻቸው ተመልካቾች እስካገኙ ድረስ ለህብረተሰቡ ደህንነት ምንም ደንታ የሌላቸውም መሆናቸው ነው።

## 8. በኢትዮጵያ የማኅበራዊ ሚዲያን አሉታዊ ገጽ ለመቆጣጠር እስካሁን የተወሰዱ እርምጃዎች

መንግስት የማኅበራዊ ሚዲያን አሉታዊ ጎኖች ለመከላከልና ችግሩን ለመቅረፍ ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ ሕግ ማዘጋጀትና ማውጣት ነው። ከዚህ አንፃር የሚዲያ አዋጅ (ቁጥር 1238/2013) እና የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የወጣው አዋጅ (ቁጥር 1185/2012) በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። አዲሱ የሚዲያ ህግ የኦንላይን ሚዲያዎችን ህጋዊ ምዝገባ ለማድረግ የሚያስችል ማዕቀፍ አዘጋጅቷል። ይህ በተወሰነ ደረጃ ጦማሪዎችን (ዩቲዩበሮችን) ተጠያቂ ለማድረግ ያስችላል።

የጥላቻ ንግግርና የሀሰት መረጃ መከላከልና መቆጣጠር አዋጅ ማኅበራዊ የትስስር ድረ ገጾችን ለሐሰተኛ መረጃና ለጥላቻ ንግግር ማስተላለፊያነት የሚጠቀሙ ሰዎችን ተጠያቂ የሚያደርግ ነው። በአዋጁ ከተካተቱ ሕግጋት መካከል የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማኅበራዊ ሚዲያ ወይንም ሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎችን በመጠቀም ያስተላለፈ እስከ 2 ዓመት በሚደርስ እስራትና 100 ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ ቅጣት ይቀጣል የሚል ይገኝበታል። በተላለፈው የጥላቻ ንግግር ምክንያት በግለሰብ አሊያም በቡድን ላይ ጥቃት ከደረሰ፤ አልፎም መረጃው ከ5 ሺህ በላይ ተከታዮች ባሉት ገጽ ከተላለፈ ቅጣቱ እስከ 5 ዓመት ሊደርስ እንደሚችል አዋጁ ይደነግጋል። አዋጁ በማኅበራዊ ሚዲያ የጥላቻ ንግግሮችን በጽሑፍ፣

በምስል፣ በድምጽ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨትን ይከለክላል። ይሁን እንጂ አንዳንዶች ይህ ሕግ፣ መንግስት በሰበብ አስባቡ የማኅበረሰብ አንቂዎችን ያለጥፋታቸው ወደ እሥር ቤት እንዲልክ መንገድ ሊያመቻች ይችላል ሲሉ ይሰጋሉ።

ሌላው የኢትዮጵያ መንግስት የወሰደው ትልቅ ‹‹እርምጃ›› ኢንተርኔትን መዝጋት እና የማኅበራዊ ድረ-ገጾችን በጊዜያዊነት ማገድ ነው። የመንግስት ባለስልጣናት ብጥብጥን ለመከላከል እና ብሔራዊ ደህንነትን ለመጠበቅ በሚል ሰበብ ኢንተርኔትና የማኅበራዊ ሚዲያ ገፆችን በተደጋጋሚ ይዘጋሉ። በአገሪቱ ውስጥ ያለው የኢንተርኔት አገልግሎት አቅራቢ አንድ ለዚያውም በመንግስት ባለቤትነት የተያዘው ኢትዮ ቴሌኮም ብቻ መሆኑ፤ የተወሰኑ የኢንተርኔት ድረ-ገጾችን ማገድ ወይም የኢንተርኔት አገልግሎትን ሙሉ ለሙሉ መዝጋት ለመንግስት በጣም ቀላል ስራ ሆኖለታል። እንደ ፌስቡክ፣ ትዊተር፣ ስካይፕ እና ኢሞ ያሉ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች እና የግንኙነት መተግበሪያዎች በተለያዩ ጊዜያት በጊዜያዊነት ተዘግተዋል። ከ2008 እስከ 2010 ዓ.ም ብቻ በብሔራዊ ደኅንነት ስጋት ምክንያት ኢንተርኔት ከስድስት ጊዜ በላይ ተዘግቷል። መንግስት መሰል የኢንተርኔት አገልግሎትን እና የማኅበራዊ ድረ-ገጾችን የመገደብ እርምጃ ላልተረጋገጡ ዘገባዎች እና አሉባልታዎች ምላሽ ነው ሲል ይገልጻል።

በሌላ በኩል የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ራሳቸው የማህበረሰብ ደንቦቻቸውን በማጠናከር በመድረኮቻቸው ላይ ፀረ-ማኅበራዊ ባህሪያትን ለመቆጣጠር ይሞክራሉ። ለምሳሌ ፌስቡክ የራሱ ሕጎች ያሉት ሲሆን ከነዚህ መካከል አንዱ ‹‹ግለሰቦችና ድርጅቶችን ለማጥቃት የሚቃጡ፣ ጥላቻ የሚያስፋፉ እና የማይፈልጓቸውን ግለሰቦችና ቡድኖች እንዲገለሉ የሚያደርጉ በፌስቡክ ቦታ የላቸውም›› ሲል ይደነግጋል። ፌስቡክ እንዲህ አይነት ድርጅቶችና ግለሰቦች አገልግሎት እንዳያገኙ ከማድረግ በተጨማሪ አክራሪዎችን የሚያደንቁና የሚደግፉ ግለሰቦችና ቡድኖች አገልግሎቱን እንዳያገኙ ያግዳል።

እንደ ፌስቡክና ኢንስታግራም ባሉ የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮች ተጠቃሚዎች ጎጂ መልዕክት እንዳያስተላልፉ ጥረት እንደሚደረግ ይገልጻል። ይህን ሥራም ድርጅቶቹ ራሳቸው በቀጠሯቸው ሠራተኞች እና በአጋር ድርጅቶች አማካኝነት ያከናውናሉ። መቀመጫውን በኬንያ መዲና ናይሮቢ ያደረገው ሳማ ሶርስ የተባለ ድርጅት በአማርኛ፣ በኦሮምኛና በትግርኛ ቋንቋዎች የፌስ ቡክን የይዘት ቁጥጥር (content moderation) ያደርጋል። ነገር ግን ፌስቡክ የይዘት ቁጥጥር የሚያደርገው ተጠቃሚዎች ‹‹ሪፖርት›› ሲያደርጉ ብቻ እንደሆነ ይገልጻል። በተጨማሪም ፌስቡክ የቁጥጥር ቦርድ (oversight board) አቋቁሟል። ይሁን እንጂ እነዚህ ሁሉ

እርምጃዎች ምን ያህል ውጤታማ ናቸው የሚለው ጥያቄ ዛሬም በጣም አከራካሪ ነው።

## 9. መደምደሚያና ምክረ-ኃሳብ

በአሁን ጊዜ ነገሮችን በቅድመ-ዲጂታል ዘመን ወደነበሩበት ሁኔታ ለመመለስ የምንችልበት ሁኔታ ላይ አንገኝም። የቴክኖሎጂ በፈጣን ሁኔታ መዳበር ሁሉን ነገር ፈጣን እና ባለብዙ አቅጣጫ ስላደረገ በረዥም የመገናኛ ብዙኃን ዘመን የዳበሩት ልማዶች፣ ተቋማት እና የፖለቲካ ተሣትፎ ዓይነቶች አሁን በቀድሞው ሁኔታ ሊሰሩ አይቻላቸውም። በመሆኑም ጊዜውንና የማኅበራዊ ሚዲያ ሚናን መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። ለወደፊቱም ማኅበራዊ ሚዲያ በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የመግባቢያና የመገናኛ መሣሪያ ሆኖ እንደሚቀጥል ምንም ጥርጥር የለውም። በመሆኑም ማኅበራዊ ሚዲያ እንደ ወጣቶቻችን የአጠቃቀም ሁኔታ ጠቃሚም ጎጂም ጎን ያለው በመሆኑ ይህንን የዘመኑን ውጤት በመልካም ሁኔታ ለመጠቀም የሚከተሉት ምክረ-ሀሳቦ ተሰጥተዋል።

### 9.1. ከወጣቶች አጠቃቀም ጋር የተያያዘ

ወጣቱ ከተማረ ይቀየራል። ወጣቶችን ስለ ማኅበራዊ ድህረ-ገፆች አጠቃቀም በማስተማር ራሳቸውን እንዲያሻሽሉ መርዳት አስፈላጊ ነው። የማኅበራዊ ሚዲያ ሱሰኝነት ከመከሰቱ በፊት መቆጣጠር ይቻላል። በቤተሰብ ደረጃ ወላጆች በጎ የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን ለልጆቻቸው የማስተማር እና የማሳወቅ ኃላፊነት አለባቸው። በዚህም የልጆቻቸው የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም የማኅበረሰቡን ክብር፣ ባህል እና ወግ ያልጣሰ እንዲሆን፤ እንዲሁም ከጊዜም አንፃር የተገደበ እንዲሆን ማድረግ ይገባቸዋል። ለዚህም ወላጆች ከታዳጊዎችና ወጣቶች ጋር መመካከር እና መተማመን ላይ መድረስ ይጠበቅባቸዋል። በቀን ውስጥ ከተወሰነ ሰዓት ወይንም ደቂቃዎች በላይ በማኅበራዊ ሚዲያ ላይ እንዳያሳልፉ መምከር፣ ማሳወቅ እና መቆጣጠር ይኖርባቸዋል። ነገር ግን በማኅበራዊ ሳይንስ ውስጥ ‹who reforms the reformer› ወይንም ‹‹ለዋጩን ማን ይለውጠዋል›› የሚል አስተሳሰብ አለ። ስለዚህ ልጆቻቸውን ለመምከርና አቅጣጫ ለማስያዝ ወላጆች ራሳቸው ያ ዕውቀት እና ግንዛቤ ማዳበር ይጠበቅባቸዋል።

በመንግሥት ደረጃም ወጣቱን ማስተማር ያስፈልጋል። ወጣቶች ለምን ብዙ ጊዜያቸውን ማኅበራዊ ሚዲያ ላይ ያሳልፋሉ? የሚፈጥርላቸው ነገር ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት መንግስት በተለያዩ መንገዶች ከወጣቱ ሕይወት ጋር የተያያዘ ትምህርት ማስተማር እና ግንዛቤ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት። ስለዚህ

መንግስት የማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀምን እና ተያያዥ ጉዳዮችን በስርዓተ ትምህርት ውስጥ ማካተት ይጠበቅበታል (ለምሳሌ በዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ 'Introduction to Emerging technologies' የሚባል ኮርስ አለ፤ ነገር ግን ስለማኅበራዊ ሚዲያ ምንም ይዘት/ፖርሽን የለውም)። የተማሪዎችን ዕድሜና ብስለት በማገናዘብ የማኅበራዊ ሚዲያ ትምህርት ምናልባትም ከ9ኛ ክፍል ጀምሮ ቢሰጥ ይመረጣል።

የወጣቱን የማኅበራዊ ሚዲያ ዕውቀትን ለመስፋትና ግንዛቤን ለማዳበር ራሱ ማኅበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ማስተማርም ይቻላል። ይሁን እንጂ ብዙ የማኅበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች በባህሪያቸው ‹‹ስልቹ›› ስለሆኑ ለግንዛቤ ማዳበሪያ የሚዘጋጁት መልዕክቶች ፈጠራን መሠረት ያደረጉ፤ ሳቢ እና አጠር ያሉ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ማኅበራዊ ሚዲያ (ለምሳሌ ዩቲዩብ) ውስጥ ዕውቀት በተለያየ መስክ እንደልብ ይገኛል። ነገር ግን ያንን ዕውቀት ከአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ማገናዘብ እና መፈተሽ ያስፈልጋል። በርካታ የትምህርት የክህሎት ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ኢንተርኔት ውስጥ በብዛት ማግኘት ይቻላል።

ስለዚህ ወጣቱ ከራሱ ዝንባሌ አንፃር ወደፊት ከሚሆነው የሥራ ፍላጎቱ ጋር የተያያዙ በርካታ ዕውቀቶችን መርጦ የሚታመኑ ምንጮችን አውቆ እና ለይቶ ኃላፊነት የሚሰማቸው የሚዲያ አካላት የሚያወጧቸው ዜናዎች፣ መጽሔቶች ጋዜጦች ስላሉ፣ እነሱን ቢፈትሽ እና ቢያተኩር መልካም ይሆናል።

## 9.2. ከአውድ (የሀገሪቱ መዋቅራዊ ጉዳዎች) አንጻር

ከወጣቶች ማኅበራዊ ሚዲያ አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የሚፈጠሩ ችግሮችን ለመቆጣጠር አንዱ መንገድ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ አማራጭ መንገዶችን መጨመር እና ማጠናከር ነው። መገናኛ-ብዙሀኑ በአገሪቱ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ህዝቡን በማስተማርም ሆነ መረጃ በመስጠት ቁልፍ ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ፤ እንዲሁም የመከራከሪያ መድረክም በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ የግል መገናኛ ብዙሀንም በገቢ ዕጥረት ሳቢያ ለጋዜጠኞቻቸው ደሞዝ መክፈል እያቃታቸው ሲዘጉ እየታየ ነው። በእነዚህ መገናኛ ብዙሀን ውስጥ ሲሰሩ የነበሩ ጋዜጠኞችም ፊታቸውን ብዙም ወጪ ወደማይጠይቀው ማኅበራዊ ሚዲያ በማዞር በግልጽም ሆነ በድብቅ የመሰላቸውን ሲፅፉ እየታየ ነው። በመሆኑም መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት በሀላፊነት ስሜት የሚሰሩ ሚዲያዎችን በመደገፍና በማበረታታት የማኅበራዊ ሚዲያውን ተፅዕኖ መቀነስ ይቻላል። የሀገሪቱ የፀጥታ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በማሻሻል እና የፖለቲካ መራራቅን (polarization)

በማጥበብ ብሔራዊ መግባባትን ማስፈን ሌላኛ በመፍትሔነት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡

## 9.3. ማኀበራዊ ሚዲያን ከማሻሻል አንጻር

ማኀበራዊ ሚዲያን የማሻሻል (reforming social media) ጉዳይ በውስጡ ህጋዊ ምህዳርን፣ ስልተ-ቀመራዊ (algorithms) ስልትን እና ሌሎች ተመሳሳይ አያሌ ጉዳዮችን ያካተተ ነው፡፡ የማኀበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ማሻሻል በአጠቃላይ ለሀገራት፤ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ደካማ ሀገራት ቀላል ስራ አይደለም፡፡ አገልግሎት ሰጪዎቹ ግዙፍ ኢንተርናሽናል ኮርፖሬሽኖች ናቸው፡፡ ስለዚህ አስፈላጊውን ማሻሻያዎች ለማድረግ ከካምፓኒዎቹ አዎንታዊ ቀና ትብብርና መልካም ፈቃድ ያስፈልጋል፡፡ የኢትዮጵያ መንግስት ከፌስቡክ እና ጎግል+ ጋር በጋራ የመስራት ሂደት መጀመሩን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሊበረታታ ይገባል፡፡

በማኀበራዊ ሚዲያ መድረክ ላይ አሁን ከሚታዩት አጠቃላይ ለውጦች ባሻገር አንዳንድ ተጨማሪ ለውጦች ሊደረጉ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፤ ፌስቡክ በቅርቡ በኢትዮጵያ ሎክ ፕሮፋይል (Lock Profile) የተሰኘ አዲስ የደህንነት አሰራር (safety feature) ጀምሯል፡፡ ይህ አሰራር ሰዎች ጓደኛቸው ያልሆነ ሰው የመገለጫ (Profile) ፎቶቸውን እንዳያወርድ፣ እንዳያሳድግ ወይም እንዳያጋራ ለመገደብ ያስችላቸዋል፡፡ ማኀበራዊ ሚዲያ መሻሻያ /ለውጥ ሊደረግበት ከሚችሉት መካከል የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡፡

- ❖ *የማኀበራዊ ሚዲያ መተግበሪያ ባህሪ ማሻሻያ (feature reform)*

የማኀበራዊ ሚዲያ ዋናው ችግር አንዳንድ ሰዎች የውሸት መረጃና ዜና ወይም መርዛማ ነገሮችን ስለሚለጥፉበት ብቻ አይደለም፡፡ ይልቁንም የውሸት እና ቁጣ ቀስቃሽ ይዘት ያላቸው ዜናዎች አሁን እ.ኤ.አ ከ2009 የፌስቡክ 'like' እና 'share' ወይም የትዊተር 'retweet' መሣሪያዎች ከመፈጠሩ በፊት ከነበሩበት ደረጃ እጅግ መጨመራቸውና ተጽዕኗቸውም ከፍተኛ መሆን ችሏል፡፡ ይህንን ችግር ለማቃለል የተለያዩ ማሻሻያዎች ማድረግ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የፌስቡክ መረጃ አጋላጯ (whistleblower) ፍራንሲስ ሀውገን በማኀበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርም ላይ ቀላል የአርክቴክቸር ለውጦች ሊደረግ ይገባል ትላለች፡፡ ይህንም በምሳሌ ስታስረዳ በፌስቡክ ላይ ያለውን ‹‹የማጋራት›› (share) ተግባር በማሻሻል ማንኛውም ይዘት ሁለት ጊዜ ከተጋራ በኋላ በሦስተኛ ደረጃ በሰንሰለት ውስጥ ያለው ሰው ማጋራት ቢፈልግ ጊዜ ወስዶ ይዘቱን እንደ አዲስ ጽሁፍ ገልብጦ ለመለጠፍ የሚችልበትን ዘዴ በመተግበር

በጎ ያልሆኑ መረጃዎችና ዜናዎች በቀላሉ እንዳይሰራጩ ማድረግ ይቻላል ስትል ታስረዳለች። እንደዚህ አይነት ማሻሻያዎች (reforms) ሳንሱር ካለመሆናቸው በተጨማሪ፤ ማንኛውም ሰው የፈለገው ሀሳብ እንዳይገልጽ አያግድም፣ ነገር ግን እውነት የመሆን ዕድሉ አነስተኛ የሆነውን የይዘት ስርጭትን ብቻ ይቀንሳሉ።

❖ *የተጠቃሚ ማረጋገጫ (user verification)?*

ምናልባትም የማኅበራዊ ሚዲያ የፕላትፎርሞችን መርዛማነት ሊቀንስ የሚችለው አንዱ ትልቁ ለውጥ የተጠቃሚዎችን ማንነት ማረጋገጫ ማጠናከር ሊሆን ይችላል። ያ ማለት ግን ተጠቃሚዎች ሁሌም በእውነተኛ ስማቸው መጠቀም አለባቸው ማለት አይደለም። ማረጋገጫው እያለም የማኅበራዊ ሚዲያ ጽሁፎቻቸውን በብዕር ስም (pseudonym) ማቅረብ ይችላሉ። ይህን የማንነት ማረጋገጫ በማጠናከር አንድ ፕላትፎርም የተጠቃሚውን ፖስት (post) በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሰዎች ከማሰራጨቱ በፊት፣ ተጠቃሚው እውነተኛ ሰው መሆኑን እና ፕላትፎርሙን ለመጠቀም ዕድሜው የደረሰ መሆኑን ለማጣራት ያስችለዋል፤ ግዴታም ያስገባዋል። ይህ ለውጥ በአሁኑ ጊዜ ዋና ዋና የማኅበራዊ ሚዲያ መድረኮችን ከሚበክሉ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ቦቶች እና የውሸት መለያዎች (fake accounts) ለመከላከል ያስችላል። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ሰዎች ማንነታቸው የማይታወቅ እና የማይደረስበት እንደሆነ ሲሰማቸው በኦንላይን ጸረ-ማህበረሰብ (anti-social) ባህሪ ማሳየትና ማንፀባረቅ ይበልጥ የተለመደ ነው።

❖ *የማኅበራዊ ሚዲያ ቁጥጥር?*

የማኅበራዊ ሚዲያው ጉዳት እያዳረሰ መሆኑን የሚያሳዩ መረጃዎች እየጨመሩ ስለመጡ የቁጥጥር አካላት ተገቢውን ቁጥጥር ማድረግ አለባቸው የሚሉ ወገኖች አሉ። በሌላ በኩል የማኅበራዊ ሚዲያ ቁጥጥርን የሚቃወሙ እና በአጠቃላይ በመንግስት የተደነገጉ የይዘት ገደቦች በተግባር ወደ ሳንሱር ይሸጋገራሉ በሚለው ተገቢ ስጋት ላይ ያተኩራሉ። ስለዚህ ቁጥጥሩ በማን እና እስከ ምን ድረስ መሆን ይገባዋል የሚሉ ጥያቄዎች ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልጋሉ።

**ዋቢ ጽሑፎች**

Biały, B. (2017), Social Media: From Social Exchange to Battlefield, *The Cyber Defense Review*, Vol. 2, No. 2, Pp. 69-90.

Courtright ,J. et al (2020), Dangerous Speech and Social Media Uncharted Strategies for Mitigating Harm Online, *Columbia University School of International and Public Affairs?*

DataReportal (2021), Digital 2021: Ethiopia, available on; https://datareportal.com/reports/digital-2021-ethiopia, accessed on 30 June 2021.

Gagliardone, I., Stremlau, N. & Gerawork A. (2019), A tale of two publics? Online politics in Ethiopia's elections, *Journal of Eastern African Studies*, Vol.13, No.1, 192-213, DOI: 10.1080/17531055.2018.1548208

Gurri, M. (2018), The Revolt of The Public and the Crisis of Authority in the New Millennium, Stripe Press.

Harlow, S. and Guo, L. (2014), Will the revolution be tweeted or Facebooked? Using digital communication tools in immigrant activism, *Journal of Computer-Mediated Communication*, Vol.19, No. 3, Pp.463–478.

Mandiberg, M. (2012), 'Introduction' in Michael Mandiberg (ed.), *The Social Media Reader*, New York: New York University Press, Pp. 1-10.

McCabe, A. & Harris, K. (2021), Theorizing social media and activism: where is community development?, *Community Development Journal,* Vol. 56, No.2, Pp. 318–337.

Mills, A. (2015), The law applicable to cross-border defamation on social media: whose law governs free speech in 'Facebookistan'?, *Journal of Media Law*, Vol.7, No.1, Pp.1-35.

Morozov, E. (2009) The brave new world of slacktivism. *Foreign policy blog*, http://www.npr.org/templates/story/story.php?storyId=104302141

Shafaat H. (2018), Patterns of Youths Communication on Social Media in Western Ethiopia, *International Journal of Research Publication* (Vol.: 4, Issue: 1), http://ijrp.org/paper_detail/143

Standage, T. (2013), Writing on the Wall: Social Media: the First 2,000 Years. Bloomsbury, London

Sundaram, A. (2018), The Dark Side of Social Media: A Reality Becoming More Contemporary by the Day, *Asian Social Science*, Vol. 14, No. 1.

Téwodros W. (2020), Social media, protest, & outrage communication in Ethiopia: toward fractured publics or pluralistic polity?, *Information, Communication & Society*, DOI: 10.1080/1369118X.2020.1811367.

# የወጣቶች ፖለቲካዊ አደረጃጀት እና የመንግስት ግንኙነት በድህረ-2010 ኢትዮጵያ[1]

አስናቀ ከፋለ እና አማኑኤል ተስፋዬ

## 1. መግቢያ

የዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ዓላማ በ2010 በኢትዮጵያ ከተደረገው የመንግሥት ለውጥ በኋላ በመንግሥትና በወጣቶች በተለይም በወጣት አደረጃጀቶች መካከል የተፈጠሩትን አዲስ ግንኙነቶች እንዲሁም መንግሥት ለወጣት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ምላሽ ለመስጠት የተጠቀመባቸውን ስልቶች ማብራራት ነው፡፡ ምንም እንኳን ጥናቱ የወጣቶችን የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችና የመንግሥት ምላሽ በአጠቃላይ የሚመለከት ቢሆንም፤፤ በቦታ እና በጊዜ የተገደበ መሆኑን መግለፅ እንወዳለን፡፡ በመጀመሪያ,፣ ጥናቱ የሚያተኩረው በኦሮሚያ እና በአማራ ክልሎች ላይ በመሆኑ በሌሎች አካባቢዎች የነበሩትን የወጣት እንቅስቃሴዎች አያካትትም፡፡ በሁለተኛ ደረጃ ጥናቱ በጊዜም የተገደበ ነው፡፡ ለጥናቱ ግብዓት የሆኑ መረጃዎች በሙሉ የተሰበሰቡት እና ትንተናውም የሚመለከተው ከ2007 እስከ 2014 ያለውን ጊዜ በመሆኑ 2014 በኋላ የተከሰቱ ሁነቶችን እና እንድምታዎች ጽሁፉ አይመለከትም፡፡

ወጣቶች በኢትዮጵያ የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ባልነበሩበት የንጉሣዊ አገዛዝ ዘመን የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የኃይለሥላሴን መንግሥት ከመቃወሙም ባሻገር ለዘውዳዊው ሥርዓት መገርሰስ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ‹‹መሬት ላራሹ›› በሚለው መሪ መፈክር ስር ወጣቶች በጊዜው የነበረው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ሥርዓት እንዲቀየር ከፍተኛ መስዋዕትነት ከፍለዋል፡፡ በመቀጠልም ዘውዳዊው አገዛዝ ከተገረሰሰ በኋላ ሥልጣን የተቆናጠጠውንና ከ1967 እስከ 1983 ዓ/ም ሀገሪቱን ሲመራ የነበረውን ወታደራዊ መንግሥት በመቃወም ወጣቶች ከፍተኛ ትግል አድርገዋል፡፡ የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶችን በማቋቋምና በመደራጀት ያለሙትን ዓላማ ለማሳካት ጥረት

[1] ይህ ጥናት እኤአ ከ2019 እስከ 2022 ኖርዌይ የሚገኘው ሲኤምአይ (ክር. ሚኬልሰን ኢንስቲትዩት) በኖር ግሎባል በመደገፍ "ወጣቶች በአፍሪካ፡ በአፍሪካ ከግጭት በኋላ የተነሱት መንግሥታት የአፍሪካን ወጣቶች እንዴት ይይዛሉ" የሚለው ፕሮጀክት ድጋፍ መሆኑን የሲኤምአይ ባልደረቦቻችንን በማመስገን እንገፃለን፡፡

አድርገዋል። ይሁን እንጂ ደርግን በመቃወም የተደረጉት ትግሎች በመጨረሻ ለወጣቶቹ ድልን አላስገኙም። እንዲያውም የደርግ መንግሥት ለነዚህ ተቃውሞች የሰጠው የመረረ ምላሽ ለአያሌ ወጣቶች እንግልት፣ ሞትና ስደት ምክንያት ሆነ። በዚህ ሳቢያ የወጣቶች (ተማሪዎች) የፖለቲካ እንቅስቃሴ እስከተወሰኑ ዓመታት ድረስ በከፍተኛ ደረጃ ተዳክሞ እንደነበረ ይነገራል[2]። ይሁን እንጂ ይህ የወጣቶች የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ዳግም የማንሰራራት ሁኔታ አሳይቷል። በተለይም የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባርን (ኢሕአዴግ) የፖለቲካ የበላይነትን ለመቃወም በተለያዩ ክልሎች በተደረገው ትግል ውስጥ የወጣቶች ሚና ከፍተኛ ነበር። በዚህ ከ2007 እስከ 2010 ባሉት ዓመታት በብዙ የኢትዮጵያ ክልሎች በወጣቶች የተመሩ ብሔር-አቀፍና በተለየዩ ስሞች የሚታወቁ የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች ተነስተዋል። ከነዚህ መካከል በኦሮሚያ የቄሮ፣ በአማራ የፋኖ፣ በጉራጌ የዘርማ እና በሲዳማ የኤጀቶ የወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በዋናነት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በአብዛኛው በወጣቶች ይደረግ የነበረው ተቃውሞና በኢሕአዴግ ውስጥ የተፈጠረው ክፍፍል በመጋቢት 2010 የፖለቲካ ለውጥና የአዲስ መንግሥት ምስረታ ቢያመጣም፣ አዲሱ መንግሥት በወጣቶች የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ የያዘው አቋምና ምላሽ አሻሚ ሆኖ ቆይቷል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዓብይ አህመድ ወደ ሥልጣን እንደመጡ በመጀመሪያዎቹ ወራት አዲሱ አስተዳደር ወጣቱን እንደ ቁልፍ የለውጥ ኃይል በመገንዘብ የሚያወድስ ነበር። ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣን እንደያዙ (ሚያዚያ 3፣ 2010) በአምቦ ከተማ ለተሰበሰበ ህዝብ ንግግር ሲያደርጉ ቄሮን ‹‹የሁሉም ህዝብ ጋሻ›› ሲሉ አወድሰውታል። በዚሁ ዝግጅት ላይ የቀድሞው ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ይህንኑ ቄሮ ‹‹የለውጥ መሐንዲስ›› ሲሉ አሞካሽተዋል።[3] በተመሳሳይ ሁኔታ የመንግሥት ሚዲያዎች እና ሌሎች ባለሥልጣናትም በአማራ ክልል ህዝባዊ ተቃውሞን በመቀስቀስና በማስፋፋት ውስጥ ግንባር ቀደም ሚና የነበራቸውን የወጣት ስብስቦች (ፋኖዎችን) ያወድሱ ነበር።

---

2 ስለ ድህረ አብዮት (ከ1966) በኂላ ስለነበረው የተማሪዎች የፖለቲካ እንቅስቃሴ አበባው ይርጋ እና ብላስቪክ ራንዲ ሮኒንግ ይመልከቱ፤ ስለ ፅሁፉ ሙሉ መረጃ በማጣቃሻ ጽሁፎች ዝርዝር ላይ በእንግሊዘኛ (Abebaw Y. Adamu, & Balsvik, R. R. 2017) ይመልከቱ። ሌሎች ማጣቀሻ ፅሁፎችም በዚህ መልክ ይቀርባሉ።

3 ስለ ጠ/ሚኒስትር ዓብይ አህመድና አቶ ደመቀ መኮንን የአንቦ ንግግር የአዲስ እስታንዳርድ የዜና ድረ ገጽን ይመልከቱ፤ (Addis Standard፤ 2018)

እነዚህ አስተያየቶች በወቅቱ ለወጣቶች የፖለቲካ እንቅስቃሴ የነበረውን አዎንታዊ አመለካከት ያሳዩ የነበረ ቢሆንም፤ መንግሥት እንቅስቃሴዎቹ ውለው አድረው መንግሥትን ሊቃወሙ ይችላሉ የሚል ስጋትም አድሮበት እንደነበርም መገመት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ቀስ በቀስ መንግሥት የፖለቲካ ለውጥ እንዲመጣ ያስቻሉ የወጣት የፖለቲካ አደረጃጀቶችንና እንቅስቃሴዎችን በሚመለከት ውዳሴን በመግታት ይልቁንም ቁጥብና አንዳንዴም ጠንከር ያሉ ትችቶችን ወደመስጠት አዘነበለ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው ከ2007 እስከ 2010 ወጣቶች በመንግሥት ላይ ተቃውሞዎችን አካሂደዋል፡፡ ህዝባዊ ተቃውሞው በስፋት በኦሮሚያ ክልል በ2007 የተጀመረ ሲሆን፤ የተቃውሞው እንቅስቃሴውን ያቀጣጠለው ምክንያት ለአዲስ አበባ ከተማ የታቀደው የተቀናጀ ማስተር ፕላን በከተማው ዙሪያ ያሉትን በአብዛኛው ኦሮሞ የሆኑትን ገበሬዎች ያፈናቅላል በሚል ቅሬታ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በማስተር ፕላኑ የተጀመረው ተቃውሞ እየሰፋ በመሄድ እንደ የፖለቲካ እስረኞች መፈታት፣ ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነትን ማስፈን የመሳሰሉ ሌሎች መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎችን በማካተት በመጨረሻም የመንግስት ሥርዓት ለውጥን የሚጠይቅ ሆነ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በ2008 በአማራ ክልል በወጣቶች የተመራ ተመሳሳይ የተቃውሞ እንቅስቃሴ ተከሰተ፡፡ ለተቃውሞው መነሳት ገፊ ምክንያት የነበረው የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች በሐምሌ 2008 በጎንደር ከተማ ‹‹የወልቃይት ጠገዴ የአማራ ማንነት እና ወሠን አስመላሽ ኮሚቴ›› ብሎ ራሱን ያደራጀው ቡድን አባል የነበሩትን ኮሎኔል ደመቀ ዘውዱን ለማሰር ያደረጉት ሙከራ ነበር፡፡ ኮሚቴው የቀድሞ የጎንደር ክፍለ ሀገር አካባቢ የነበሩትን የወልቃይትና ጠገዴ አካባቢዎች ወደ ትግራይ መካለል በመቃወም፤ አካባቢዎቹ ወደ አማራ ክልል እንዲካለሉ የሚጠይቅ ነበር፡፡ እያደር ግን ተቃዋሚዎች የሚያነሱዋቸው ጥያቄዎች እየተበራከቱ በመሄድ ከማንነት እና የወሰን ጥያቄ በተጨማሪ የፖለቲካ ነፃነት እና የፖለቲካ ለውጥ ጥያቄዎችን ማንሳት ጀመሩ፡፡ በሌላ በኩል የተቃውሞው ውጥረት በገዢው ግንባር ውስጥ መከፋፈልን በማስከተል በኢህአዴግ ውስጥ ለውጥን የሚደግፍ ኃይል መታየት ጀመረ፡፡ ይህ ቡድን ቀስ በቀስ በመጠናከር በግንባሩ ውስጥ ለውጥ በማምጣት በመጋቢት 2010 ዶ/ር ዓብይ አህመድን የኢህአዴግ ሊቀመንበር አድርጎ መረጠ፤ በመቀጠልም ዶ/ር ዓብይ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኑ፡፡

ከ2007-2010 ባሉት ዓመታት በኢትዮጵያ በተካሄደው የፖለቲካ ተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ የወጣቶች ሚና ከፍተኛ እንደነበረ መረዳት ይቻላል፡፡ ለወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴ መጀመር የወጣቱ ህብረተሰብ ክፍል በፖለቲካና ኢኮኖሚ መገለል በተለይም በወጣቶች ላይ የተንሰራፋው ሥራ አጥነትና ስለ ወደፊት

ህይወታቸው ተስፋ ማጣት በዋነኝነት ይጠቀሳሉ። በመሆኑም በእነሱ የተቃውሞ ማዕበል ወደ ሥልጣን ከመጣው መንግሥት ወጣቶች ብዙ ይጠብቁ እንደነበረ ግልፅ ነው። ይሁን እንጂ በሚገባ ያልተደራጀውና አንድ ዓይነት ግብና የሚመራበት ርዕዮተዓለም የሌለው የወጣቶች እንቅስቃሴ የሥርዓት ለውጥን ከማሳለጥ ባሻገር የሚፈልገውን ነገር ከአዲሱ መንግሥት ለመጠየቅና ለማስፈፀም በቂ አቅም እንደሌለው ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ያመለክታል።

ይህ ጥናት የመጀመሪያ ደረጃና እና ሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች በማጣመር በዓይነታዊ የጥናት ዘዴ የተከናወነ ነው። በዚህ መሠረት የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን በአዲስ አበባ እና ባህር ዳር ከተሞች ስለ ወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴና ወጣቱ የህብረተሠብ ክፍል ከመንግሥት ጋር ስላለው ግንኙነት በቂ ግንዛቤ አላቸው ተብለው ከሚገመቱ የገዥው እና ተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎች፣ ከወጣት ማኅበራት አመራሮች፣ ከሲቪክ ማኅበራት መሪዎችና ከማኅበራዊ ሚዲያ አንቂዎች (አክቲቪስቶች) ጋር በተደረጉ ቃለ ምልልሶች ለማሰባሰብ ተችሏል። በቃለ-መጠይቅ የተሰበሰበው የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ በሁለተኛ ደረጃ መረጃዎች ማለትም ህትመቶች፣ የመደበኛ መገናኛ ብዙሀንና የማህበራዊ ሚዲያ ዜና ዘገባዎች ጋር በማዳበር ለዚህ ፅሁፍ የመረጃ ግብአት ሆነዋል።

## 2. የወጣቶች ፖለቲካዊ ተቃውሞ

በኢትዮጵያ ቢያንስ ከ1950ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ወጣቶች በአገሪቱ የፖለቲካ ተቃውሞ እና ለውጥ ውስጥ ትልቅ ሚና ተጫውተዋል።[4] በዚህ ረገድ ከ1960ዎቹ ጀምሮ የንጉሠ ነገሥቱን ሥርዓት በመቃወም፤ በኋላም በ1966ቱ አብዮት የንጉሡን መንግሥት በማስወገድ ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና የነበረው የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በዋናነት ይጠቀሳል። ንቅናቄው መጀመሪያ ላይ ትኩረቱ የተማሪዎች ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ እና የመደራጀት ጥያቄዎች ላይ የነበረ ቢሆንም፤ ከጊዜ ወደ ጊዜ ሥር-ነቀል እየሆነ በመሄድ እንደ ‹‹መሬት ለአራሹ›› ያሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን በማንሳት ፍትሀዊ ያልነበረውን የመሬት ይዞታ ሥርዓት ተቃወመ። ንቅናቄው በተለያዩ ሠላማዊ ሠልፎች፣ መንግሥትን የሚሸነቁጡ ግጥሞች፣ ክርክሮች እንዲሁም በተማሪዎች መካከል በድብቅ በሚካሄዱ ጠንካራ የንድፈ ሀሳብ ውይይቶች የታጀበ ነበር። በዚህም የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ በአገሪቱ ፖለቲካ እና ሀገራዊ

[4]የኢትዮጵያ ወጣቶች (ተማሪዎች) የቅርብ ጊዜ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ታሪክን በተመለከተ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የባሕሩ ዘውዴን ጽሑፍ ይመልከቱ።

ጉዳዮች ዘላቂ ተፅዕኖ አሳድሯል ማለት ይቻላል።[5] የንጉሣዊ ሥርዓት ተገርስሶ በምትኩ ሥልጣን ላይ የወጣውን ደርግ በመቃወምም ወጣቶች በተመሳሳይ ሁኔታ ትግል አካሂደዋል። ትግሉና መስዋዕትነቱ ዘውዳዊውን ሥርዓት በወታደራዊ አገዛዝ ለመተካት ሳይሆን ዕውነተኛ ዲሞክራሲ ለማስፈን ነው በማለት ወጣቶቹ በተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች በመደራጀት ከደርግ ጋርም የከረረ ፖለቲካዊ ትግል አካሂደዋል፤ ከፍተኛ መስዋዕትነትም ከፍለዋል።

በጊዜው የነበሩት የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ አባላት ከፈጠሯቸው የፖለቲካ ድርጅቶች መካከል ከ17 ዓመታት የትጥቅ ትግል በኋላ በ1983 ዓ.ም ወታደራዊውን የደርግ ሥርዓት በተሳካ ሁኔታ ማስወገድ የቻለው ህዝባዊ ወያኔ ሐርነት ትግራይ (ህወሓት) መራሹ ኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ነበር ። ኢህአዴግ ሥልጣን ላይ ከወጣ በኋላም ወጣቶች በተለይም ተማሪዎች አገዛዙን ደጋግመው ተቃውመውታል። በ1993 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች የኤርትራን ከኢትዮጵያ መገንጠል አስመልክቶ ሊካሄድ የታቀደውን ህዝበ-ውሳኔ በመቃወም፤ እንዲሁም በ1989/90 የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማራ ተማሪዎች በክልላቸው የተደረገው የመሬት ክፍፍል ፍትሀዊ አይደለም በማለት የተቃውሞ አንቅስቃሴዎች አካሂደዋል።[6] በታህሳስ 1993 የዚሁ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በነፃ ለመደራጀትና የራሳቸው ጋዜጣ እንዲኖራቸው ያነሱት የመብት ጥያቄና ተቃውሞ በመዲናዋ የወጣቶች አመጽን ቀስቅሷል። በተጨማሪም አወዛጋቢውን የ1997 አገራዊ ምርጫን ተከትሎ ወጣቶች በመላ አገሪቱ በሚገኙ ትላልቅ ከተሞች ተቃውሞ በማሰማታቸው በመቶዎች የሚቆጠሩ ሰዎች መሞታቸውና በአስር ሺዎች የሚቆጠሩት ለእስር መዳረጋቸው ይታወሳል።

በመሆኑም በ2007-2010 በአማራ እና ኦሮሚያ ክልሎች የተቀሰቀሱት የወጣቶች ህዝባዊ ተቃውሞች በነዚህ ቀደምት የተቃውሞ ታሪኮች ላይ የተመሰረቱና በተሞክሮዎቻቸው ላይ የተንተራሱ ነበሩ ማለት ይቻላል። በኦሮሚያም ሆነ በአማራ ክልሎች የተቀሰቀሱት ተቃውሞዎች በአብዛኛው ህዝባዊ ማለትም ወጣቶች በሰፊው የተሳተፉባቸውና የህዝብ ጥያቄዎችን ያነሱ ቢሆኑም የተማከለ አደረጃጀት አልነበራቸውም። እነዚህን የወጣት እንቅስቃሴዎች ትክክለኛ ተፈጥሮ፣ ግብ፣ እና አወቃቀር እንደዚህ ናቸው ብሎ ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም፤ ቡድኖቹን በተመለከተ

---

[5] ስለ ኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ታሪክ፤ ባህሩ ዘውዴ (Bahru Zewde, 2014) ይመልከቱ።

[6] ስለ ተማሪዎች የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሶስት ተካታትይ የኢትዮጵያ መንግሥታት ብላስቪክን (Balsvik, R. R. 2007) ይመልከቱ።

ቢያንስ ሁለት ዋና ነጥቦችን ማንሳት ይቻላል። አንደኛው፤ ቡድኖቹ በአንድነት ‹‹ሆ›› ብለው አገዛዙን በመቃወማቸው በኢህአዴግ እና በተቀናቃኞቹ መካከል የነበረውን የኃይል ሚዛን በማዛባትና በገዢው ፓርቲ ውስጥም የነበረውን ክፍፍል በማስፋት በኢህአዴግ ይመራ ለነበረው መንግስት መውደቅ ከፍተኛ ሚና መጫወታቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ነጥብ ደግሞ የወጣት ቡድኖቹ እንቅስቃሴ ለአገዛዙ ማክተም ምክንያት ቢሆንም፤ ቡድኖቹ የጠራ የፖለቲካ ዓላማ፣ የተማከለ አመራርና መዋቅር ያልነበራቸው በመሆኑ በተቃውሞ ያገኙትን ውጤት ለላቀ ግብ ለመጠቀም ሳይችሉ ቀርተዋል። በመሆኑም ከመንግሥት ለውጥ በኋላ የእንቅስቃሴዎቹ መሪዎች በልዩ ልዩ ጥቅሞች ከመደለላቸው በላይ ለክፍፍል ተዳርገዋል። አንዳንድ በተቃውሞ ለመዝለቅ የሞከሩ ቢኖሩም ለጭቆና ተዳርገዋል። መንግሥት የተቃውሞ እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር የተጠቀመባቸውን ስልቶች ከመዳሰሳችን በፊት ቄሮና ፋኖ ማን እንደሆኑ በአጭሩ እንመልከት።

## 2.1 ቄሮ

በኦሮሚያ ውስጥ የነበረው የቄሮ እንቅስቃሴ በኢህአዴግ ውስጥ የአመራር ለውጥ እንዲመጣ በማድረግ ረገድ ዋነኛ ተዋናይ ነበር። ይሁን እንጂ ቄሮ እንዴት ተፈጠረ? አባላቱ እነማን ናቸው? ተዋረዳዊ አደረጃጀት ነበረው? መሪዎቹስ እነማን ናቸው? ለሚሉት ጥያቄዎች ግልጽ መልስ ማግኘት ያስቸግራል።

‹‹ቄሮ›› የሚለው ቃል በአፋን ኦሮሞ ትርጉሙ ያላገባ ወጣትን የሚያመለክት ቢሆንም፤ 2007-2010 ለተነሳው የኦሮሞ ወጣቶች እንቅስቃሴ የወል ስም በመሆን አገልግሏል። በቄሮ ስም የተደራጁ ወጣቶች የሥራ ማቆም አድማና የተቃውሞ ሠልፎችን በማደራጀት፣ መንገድ በመዝጋት የክልሉንና የፌዴራል የጸጥታ ኃይሎችን ተገዳድረዋል። አንዳንድ ፀሃፊዎች ቄሮ በድንገት የተፈጠረ፤ ምንም ዓይነት መደበኛ መዋቅር የሌለው እንደሆነ በማብራራት አደረጃጀቱ ሁለት ገፅታ የነበረውና በአንዱና በማይታየው ሁኔታ ብዙ የኦሮሞ ወጣቶችን የሚወክል፤ በሁለተኛውና በሚታየው ደግሞ ተቃዋሚ የኦሮሞ ወጣትንየሚወክል ነው ሲሉ ይገልጹታል።[7] በተቃራኒው ሌሎች ፀሃፊዎች ቄሮ ታስቦበት በመደበኛ ድርጅትነት የተፈጠረና እ.ኤ.አ በሚያዚያ በ2011 ‹‹Qeerroo Bilisummaa Oromoo (QBO)››

[7] ይሄን አመለካከት በተመለከት እስቴቦ የተባለው ፀሀፊ በ2020 አዲስ እስታንዳርድ የድረገፅ መፅሄት ላይ ያሳተመውን ይመልከቱ (Østebø, T. 2020).

(ወጣት ለኦሮሞ ነፃነት) በሚል ስያሜ የራሱን የተሟላ ማኒፌስቶ እና ድረ-ገጽ ይዞ የተቋቋመ መሆኑን ይገልጻሉ [8]።

ይሁን እንጂ የቄሮን እንቅስቃሴ ማን እንደሚመራው በትክክል የሚገልጽ እንዲሁም ሁሉንም የሚያስማማ መረጃ የለም። አንዳንዶች ታዋቂው አክቲቪስትና ፖለቲከኛ ጃዋር መሐመድ የንቅናቄው መሪ እንደነበረ ይናገራሉ ። በእርግጥ ጃዋር የቄሮን ተቃውሞ በርቀት ሆኖ መረጃና መመሪያ በመስጠት ያስተባብር እንደነበረ ይታመናል። አንዳንድ ፀሀፊዎች ጀዋር መመሪያዎች ይሰጥ ነበር ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሚናው ድጋፍ መስጠት ነበር በማለት የንቅናቄው መሪ ነበር የሚለውን ሃሳብ ይተቻሉ። ሌሎች መረጃ ሰጪዎችም እንዲሁ ቄሮና ጃዋር ግንኙነት ቢኖራቸውም ግንኙነቱ የሥልጣን ተዋረድ ያለው አመራር የመስጠትና የመቀበል ከመሆን ይልቅ መረጃ ልውውጥ ላይ ያመዘነ ነበር በማለት ጀዋር ከሚሊዮን በላይ ተከታዮች የነበሩት የፌስ ቡክ ገፁንና በራሱ አነሳሽነትና መሪነት የመሰረተውን የኦሮሚያ ሚዲያ ኔትዎርክ (OMN) የተባለውን የሳተላይት ቴሌቪዥን በመጠቀም የተቃውሞ እንቅስቃሴውን ለማቀጣጠል የተጫወተውን ሚና ያነሳሉ። አንድ ስሙ እንዳይጠቀስ የፈለገ ታዋቂ አንቂ በጃዋርና ቄሮ መካከል የድርጅት መዋቅር አልነበረም የሚለውን አመለካከት በማጠናከር የሚከተለውን ብሏል።

> [ቄሮ] ጃዋር እንደሚለው በደንብ የተደራጀ እና የተዋቀረ አይደለም... አዎ በእርግጥ በተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚሳተፍ የወጣት ኃይል ነበር። በተለያዩ የክልሉ አካባቢዎች ራሳቸውን ያደራጁ ተፅዕኖ ፈጣሪ ወጣቶችም ነበሩ። ከሀገር ውጪ የነበረው ዋና እንቅስቃሴ ገንዘብ ማሰባሰብ ነበር። ይህም ለገንዘብ ድጋፍ፣ ለተጎዱት የህክምና አገልግሎት ለመስጠት፣ ለትራንስፖርት፣ ለስልክ እና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ይውል ነበር። ነገር ግን ይህ በዋናነት ለተቃውሞ የተነሱትን ወጣቶችን ለመደገፍ የተደረገ ሲሆን፤ ያን ያህል ግን ወሳኝ አልነበረም። ነገር ግን የግንኙነት መረቡ ልትቆጣጠረውና እና ልታዘው በምትችለው መንገድ በተዋረድ የተዋቀረ እንቅስቃሴ አልነበረም።

[8] ከብዙዎቹ በተለየ ቄሮ ወጥ አደረጃጀትና ማኒፌስቶ ነበረው በማላት የፃፈው ሞሲሳ ኢጋ ነበር፤ (Mosisa, 2020).

እነዚህ ውዝግቦች ቢኖሩም፣ ቄሮ፣ እንደ ኦሮሞ ወጣቶች የተቃውሞ ንቅናቄ፣ በ2010 በተካሄደው የፖለቲካ ለውጥ ውስጥ ጉልህ ሚና የተጫወተ መሆኑ ግልጽ ነው።

## 2.2 ፋኖ

ፋኖ ማለት በሰፊው በሚታወቀው አረዳድ በሠላም ጊዜ አርሶ የሚኖር፣ በጦርነት ጊዜ ደግሞ አገሩን ለመከላከል የሚዋጋ ገበሬ ማለት ነው። አንድ ፀሀፊ ፋኖ ‹‹የራሳቸው መሣሪያ የነበራቸው እና በንጉሣዊ ወታደራዊ ዘመቻዎች የሚሳተፉ ነፃ ገበሬዎችን›› እንደሚያመለክት ጽፏል[9]። ፀሃፊው ፋኖ የሚለው ቃል ከ1928-1933 ከተደረገው ፀረ ፋሺስት ተጋድሎ ጋር ስለሚነሳ ቃሉ ጠንካራ የሆነ አገራዊ ስሜት አለው በማለትም ያክላል።

ከ2008-2010 በአማራ ክልል ከተደረገው የተቃውሞ እንቅስቃሴ አንጻር ፋኖ የሚለው ቃል የተለያየ ትርጓሜ ሊሰጠው ይችላል። ፋኖ የሚለው ከዚህ በላይ በተቀሰው ጊዜ የኢህአዴግን መንግሥት በመቃወም ራሳቸውን ያደራጁ የአማራ ወጣቶችን የሚያመለክት ነው። በተጨማሪም ይህ ስብስብ ከጥቅምት 2012 እስከ ጥቅምት 2014 ባለው ጊዜ ውስጥ ከህወሓት ጋር በተደረገው ለሁለት ዓመታት በዘለቀው ጦርነት ከፌዴራል መንግሥት ጎን ተሰልፎ በጦርነቱ ትልቅ ሚና የተጫወተ ነው። ይህ አረዳድ ፋኖን መንግሥታዊ ያልሆነ ሕዝባዊ ሚሊሻ አደርጎ ይመለከተዋል።

በሌላ በኩል ፋኖ በህወሓት የሚመራውን አገዛዝ በመቃወም የተቃውሞ ሠልፎች ማድረግን ጨምሮ የተለያዩ እርምጃዎችን የወሰዱ ወጣቶች እንቅስቃሴተደርጎ ይታያል። ይህ አገላለጽ ፋኖን እንደ ቄሮ ሁሉ የኢህአዴግን አምባገነናዊ ፖለቲካ በመቃወም ብሔርን መሠረት አድርጎ የተደራጀ የወጣት ማኅበራዊ ንቅናቄ አድርጎ ይመለከተዋል። ሦስተኛውና ሰፊው የቃሉ ፅንሰ-ሀሳብ አረዳድ በአብዛኛው መብቱን ለማስጠበቅ የሚያምፅ፤ በጭቆና የተከፋ/ጎልማሳአድርጎ ይመለከተዋል። እንደአተረጓጎሙና አረዳዱ ሁሉ በፋኖ ምንነት ላይም ልዩነቶች ይንጸባረቃሉ። እንድ አብዛኛዎቹ የዚህ ጥናት ተሳታፊዎች፤ ከ2008-2010 በነበረው የተቃውሞ እንቅስቃሴ ፋኖ እንደ ሰፊ የወጣቶች የተቃውሞ ማኅበራዊ እንቅስቃሴ መታየት የሚችል ሲሆን፤ በዚህ ወቅት ሠላማዊ ሠልፍ በማድረግና መንገድ በመዝጋት አገዛዙን ሲፈታተኑ የነበሩ ወጣቶች በሰፊው ፋኖ ይባሉ ነበር።

---

[9] ለዚህ አመለካከት ላብዛኤ ኤምን ይመልከቱ፤ (Labzaé, 2022)

# 3 የወጣቶች እና መንግስት ግንኙነት ከ2010 በኋላ

ከ2010 ለውጥ በኋላ ሥልጣን የያዘው ‹‹የለውጥ አመራር›› ፤ የወጣቱንና የሌላውን ማህበረሰብ ጥያቄ በፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ማሻሻያዎች እንደሚመልስ ቃል በመግባት ጉልህ እርምጃዎች በተለያዩ መስኮች መውሰድ ጀመረ። የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ውስጥ በርካታ የፖለቲካ እስረኞች ተፈትተዋል፣ በስደት ላይ የነበሩ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ታጣቂ ቡድኖች ወደ ሀገር ቤት እንዲመለሱ ተጋብዘዋል። የመገናኛ ብዙሀንም የተሻለ ነፃነት አግኝትዋል።

በለውጡ የመጀመሪያ ጊዜያት በአዲሱ የለውጥ አመራርና በወጣቶቹ መካከልየነበረው ግንኙነት ቀናና አዎንታዊ ነበር። አዲሱ የመንግሥት አመራር በሽግግሩ የመጀመሪያ ጊዜያት ለውጥ ለማምጣት የተንቀሳቀሱትን ወጣቶች ከማድነቅ አልፎ ራሱን ከቄሮ እና ፋኖዎች ጋር አንድ አድርጎ ለማቅረብ ሞክሯል። በተለይም የትግራይ ጦርነት ወቅት (2013-2015) የአማራ ፋኖ ከፌዴራል መንግሥት ጎን በመቆሙ በልዩ ሁኔታ አድናቆት ይሰጠውና ድጋፍም ይደረግለት ነበር።

በሌላ በኩል አዲሱ አመራር በመጀመሪያ አካባቢ በአማራ ክልል ከፍተኛ የህብረተሰብ ድጋፍ አግኝቶ ነበር። መንግሥትን በመደገፍ በክልሉ ዋና ዋና ከተሞች ታላላቅ ሠልፎች ተካሂደዋል። አንድ አንቂ ጋዜጠኛ በሚከተለው ሁኔታ ገልጾታል።

> ከፖለቲካ ተሀድሶው ማግስት ወጣቱ በአዲሱ አመራር እጅግ በጣም ደስተኛ ነበር። በተለያዩ ቦታዎች ለአመራሩ የድጋፍ ሠልፎች የተደረጉ ሲሆን የወጣቱ ጥያቄዎችም መልስ እንደሚያገኙ ተስፋ ተጥሎ ነበር። አዲሱ ‹‹የለውጥ›› አመራርም የህዝቡ ጥያቄዎች የራሱ የአመራሩ እና የፓርቲውም ጭምር እንደሆነ ሲገልጽ ነበር። ይህም ከእስረኞች መፈታት እና ይህንኑ ተከትሎ ከተንጸባረቀው ሀሳብን በነጻ የመግለጽ ሁኔታ ጋር ተዳምሮ የወጣቱን ተስፋ ይበልጥ ከፍ ያደረገ ነበር።

በኦሮሚያም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሄዱባቸው ከተሞች ሁሉ በብዙ ሕዝብ አቀባበል ይደረግላቸው ነበር። የአዲሱ አመራር መምጣት በወጣቶች እና ህብረተሰቡ ዘንድ ለአገሪቱ እንደፈነጠቀ አዲስ የብርሀን ጅማሮ ተደርጎ ተወስዶም ነበር።

ይሁን እንጂ በወጣቱ እና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች መቀየሩ አልቀረም። በመጀመሪያ፣ መንግሥት የወጣቶቹ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በሌሎች ተቀናቃኝ ኃይሎች ተፅዕኖ ስር ወድቋል የሚል ጥርጣሬ ማሳየት ጀመረ። ይህንን ጥርጣሬ የሚያጠናክሩ የተለያዩ ሂደቶችም ተስተውለዋል።

በዚህ ረገድ የኦሮሞ ብሔርተኛ አንቂ የሆነው ጃዋር መሐመድ ከአዲሱ የለውጥ አመራር ጋር የገባበት እሰጣ ገባ በመንግሥትና በቄሮ ግንኙነት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ የነበረው ይመስላል፡፡ ጃዋር በቄሮ ውስጥ የነበረው ከፍተኛ ተሰሚነት በሁለት ምክንያቶች ጎልቶ የወጣ ነበር፡፡ የመጀመሪያው (በኋላ ላይ እንደታየው) ወደ 1.75 ሚሊዮን የሚጠጋ ተከታይ ባለው የማኅበራዊ ሚዲያ (ፌስ ቡክ) ገፁ ላይ የሚያወጣቸው መልዕክቶች ወደ አብዛኛው የኦሮሞ ወጣት በቀላሉ የሚደርሱና ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ሲሆን፤ በሁለተኛነት በ2006 በአሜሪካ የተመሰረተውና በጃዋር ዳይሬክተርነት የሚመራው የኦሮሞ ሚዲያ ኔትወርክ (Oromo Media Network-OMN) ቴሌቪዥን ጠንካራ፣ ኮርኳሪ እና ስሜት ቀስቃሽ መልእክቶችን ያስተላልፍ ነበር፡፡ በቴሌቪዥን ጣብያው አማካይነት ጃዋር በብዙ ቄሮ ልብ ውስጥ ሊገባና እንዲያውም በአንዳንዶች የቄሮ መሪ እስከመባል ደርሶ ነበር፡፡

አዲሱ መንግሥት ከወሰዳቸው ዕርምጃዎች መካከል አንዱ ቀደም ሲል አሸባሪ ተብለው የተፈረጁ ቡድኖች ወደአገር ተመልሰው በሠላማዊ ትግል እንዲሳተፉ የሚለው ነበር፡፡ በዚህም ጃዋር ከኦ.ኤም.ኤን ቴሌቪዥን ጣቢያው ጋር በነሐሴ 2010 ወደ አገር መመለስ ችሎ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በጃዋርና በመንግሥት መካከል የነበረው መልካም ግንኙነት በነበረበት መቀጠል አልቻለም፡፡ በጥቅምት 23 ቀን 2012 የመንግስት የፀጥታ ኃይሎች የመኖሪያ ቤቴን ከብበዋል የሚል ፁሁፍ በፌስቡክ ገፁ መለጠፉን ተከትሎ በአዲስ አበባና በመላው ኦሮሚያ የተነሳው ሁከት የግንኙነቱ መደፍረስ ዋና መገለጫ፤ እንዲሁም በመንግስትና በቄሮ ግንኙነት መለወጥ ላይ አንን ነጥብ ተደርጎ ይጠቀሳል፡፡ በጃዋር የፌስቡክ መልዕክት የተነሳ የተቆጣው ቄሮ በየከተማው የተቃውሞ ሠልፍ ከማድረግ አልፎ መንገዶችን ዘጋ፤ አገሪቱም በከባድ ቀውስ ውስጥ ገባች፡፡ ይህ ተቃውሞ ከሚያዝያ 2010 ወዲህ በኦሮሚያ ክልል የተካሄደ የመጀመሪያው የተቃውሞ ሠልፍ ሲሆን፣ በመንግሥትና በቄሮ መካከል ከፍተኛ ክፍተት ፈጥሮ አልፏል፡፡

በነውጡ በወጣቶችና በመንግሥት የፀጥታ ኃይሎች መካከል በተከሰተው ግጭት የብዙ ዜጎች ሕይወት ማለፉን መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በዚህም ብዛት ያላቸው ወጣቶች በጥፋት ተጠርጥረው በቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡ ሁኔታው መንግሥት የወጣቶች የተቃውሞ እንቅስቃሴ በሌሎች ኃይሎች ተጠልፏል የሚለውን አመለካከት ያጠናከረ ነበር፡፡ እንዲሁም በግጭቱ የጠፋውን የሰው ህይወትና የወደመውን ንብረት በመመልከት በቄሮ ስም ጠባብ ብሔርተኝነትን የሚራምዱ፣ ሠላም የሚነሱ እና ዘረፋ የሚያስፋፉ ወገኖች አሉ የሚል ወቀሳ በስፋት ተሰማ፡፡

በጃዋርና በመንግሥት መካከል የነበረው ልዩነት እየሰፋ መጥቶ ጃዋር የመንግሥት ተቃዋሚ የሆነውንና በፕሮፌሰር መረራ ጉዲና እና አቶ በቀለ ገርባ የሚመራውን የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) መቀላቀሉ፤ ፓርቲው በበኩሉ የ2012ቱ ምርጫ በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት መራዘሙን በመቃወም የወሰደው ጠንካራ አቋም፣ እንዲሁም ሰኔ 2012 የአርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳን መገደል ተከትሎ በአዲስ አበባ እና በተለያዩ የኦሮሚያ ከተሞች የተከሰተው አመፅን የቀላቃለ ተቃውሞና ያስከተለው የንብረት ውድመትና የሰው ህይወት መጥፋት በቄሮና በመንግሥት መካከል የነበረውን ግንኙነት ቀድሞ ወደነበረበት በማይመለስበት ሁኔታ የቀየረው ይመስላል:: በተለይ በተለያዩ ከተሞች ብዛት ያላቸው ወጣቶች ሁከትን በቀላቀለ ተቃውሞ ውስጥ በመሳተፋቸው ቄሮ ‹‹ለሥልጣን የቋመጡ ክፍሎች መጠቀሚያ ሆኗል››፣ የሚለውን ክስ የሚያጠናክር ሁኔታ ፈጥሯል:: ይህም በቄሮና በመንግሥት መካከል የነበረው ግንኙነት ወደማይመለስበት ደረጃ ያወረደው ይመስላል::

በተመሳሳይ ሁኔታ መንግስት ከትግራይ ክልል ጋር በነበረው ጦርነት ውስጥ ፋኖ ከመንግሥት ጦር ጋር ተሰልፎ መንግሥት በአሸናፊነት እንዲወጣ አስተዋጽኦ ቢያደርግም፤ “አንዳንድ እራሳቸውን ፋኖ ብለው የሰየሙ ክፍሎች ሕገ ወጥ ተግባራት ላይ ተሰማርተዋል፣ የመንግሥት መዋቅርን ተገዳድረዋል” በማለት መንግሥት እንደ ፋኖ ያሉ ኢመደበኛ አደረጃጀቶች ለማክሰም የተላያዩ እርምጃዎች መውሰድ ጀመረ:: እያደረ በመንግሥትና በፋኖ መካከል የነበረው ቅራኔ እየሰፋ ሄዶ ወደ ግጭት አመራ::

በአጠቃላይ ሲታይ በሁለቱም ክልሎች የወጣት አደረጃጀቶችና እንቅስቃሴዎች የመንግሥት አካላትን ሥልጣን መገዳደርና አንዳንድ የወጣት ቡድኖች በሕገ-ወጥ ተግባራት መሳተፋቸው መንግሥት የወጣት አደረጃጀቶችን ለማዳከም እርምጃ እንዲወስድ በር ከፍቶለታል:: በሌላ በኩል፣ በሁለቱ የወጣት ተቃውሞ ቡድኖች መካከል የነበረው ግንኙነት ጠንካራ አልነበረም:: ቄሮና ፋኖ ከእነሱም ባሻገር በተቃውሞ ጎራ በነበሩ የኦሮሞና የአማራ የፖለቲካ ልሂቃን መካከል ኢህአዴግን በመቃወም ለአጭር ጊዜ አንድ ላይ ቢቆሙም፣ ስለወደፊቱ የአገሪቷ ፖለቲካ ግልጽ የሆነ የጋራ ራዕይ አልነበራቸውም:: ከዚህም በላይ፣ አንዳንድ ጥያቄዎቻቸው እርስ በርስ የሚጋጩ ነበሩ:: በዚህም ምክያት አዲሱ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ በአማራና በኦሮሞ ተቃዋሚዎች መካከል የነበረው ጥምረት በፍጥነት ተዳክሟል:: ይህ በሁለቱ ቡድኖች መካከል የተፈጠረው መለያየት በማህበራዊ ንቅናቄው ውስጥ እንደ የመጀመሪያውን ትልቅ ስንጥቃት ማየት ይቻላል::

ከዚህ በታች መንግሥት የወጣት እንቅስቃሴዎችን ለመቆጣጠር የተጠቀመባቸውን ስልቶች በአጭሩ እናብራራለን፡፡

## 3.1 ማባበል

መንግሥት የወጣቶችን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር የተጠቀመበት አንዱ መሣሪያ ማባበል ነበር፡፡ በኦሮሚያ፣ መንግሥት የቄሮ አመራሮችን ከክልሉ አዲሱ አመራር ጋር ለማስተሳሰር በትኩረት ሰርቷል፡፡ አዲሱ መንግሥት የኦሮሚያ ተቃዋሚ ወጣቶችን፣ አክቲቪስቶችን እና ተፅዕኖ ፈጣሪዎ ግለሰቦችን ድጋፍ ለማግኘት ከፍተኛ ጥረት አድርጓል፡፡ ይህንንም ለማረጋገጥ መንግሥት ለእነዚህ ቡድኖች የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን በመደለያነት አቅርቧል፡፡ ለምሳሌ፣ የኦሮሚያ ክልል መንግስት የለውጡ እንቅስቃሴ ከፍ ባለበት ወቅት በመጋቢት 2009 ‹‹የኦሮሞ ኢኮኖሚ አብዮት›› በሚል የሰየመው እርምጃ በተቃውሞ እንቅስቃሴ ውስጥ ጉልህ ሚና የነበራቸው ወጣቶችን በኢኮኖሚው ውስጥ ለማሳተፍ ብድር፣ የሥራ እድል፣ እና የንግድ ፈቃድ እንዲሁም በባለሃብቶች ይዞታ ሥር የነበሩ የማዕድን ማውጫ ቦታዎችን እየነጠቀ ለተደራጁ ወጣቶች ሰጥቷል፡፡[10]

ከመንግሥት ለውጥ በኋላም አዲሱ አስተዳደር በተለያዩ መንገዶች የተደራጁ ወጣቶች የኢኮኖሚ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይሰራ ነበር፡፡ ተቃዋሚ ፓርቲ የሆነው የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) አካሄድኩት ባለው የምርመራ ዘገባ ምንም እንኳ መንግሥት ህጉን በተከተለ መንገድ ለተመዝጋቢ እድለኞች ኮንዶሚኒየም ቤቶችን እንደሚያስተላልፍ ቃል ቢገባም በተግባር ግን ቤቶቹ "ለራሳቸው አባላት፣ ለሹማምንቶች፣ ለማይታወቁ ግለሰቦች እና ቡድኖች" መታደላቸውን ገልጿል፡፡[11] ሌላው የማባበያ መንገድ ተዘዋዋሪ ብድር መስጠት ሲሆን፤ ምንም እንኳን ቀደም ሲል የተሰጡ ብድሮች አብዛኛው ያልተመለሱ ቢሆንም፣ መንግሥት ከ2013ቱ አገራዊ ምርጫ ዋዜማ በወጣቶች ተዘዋዋሪ ፈንድ ፕሮግራም አማካኝነት ለተደራጁ ወጣቶች ብድርን በስፋት ሰጥቷል፡፡ ሆኖም፣ ብዙዎቹ በብድር የተቋቋሙት ንግዶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ተዘግተዋል፡፡

ከቁሳዊ ማባበያ በተጨማሪ መንግሥት ተቋማዊና መዋቅራዊ ማባበያዎችንም በስፋት ተጠቅሟል፡፡ አክቲቪስቶች፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮች፣ የዲያስፖራ

---

[10] ስለ ኦሮሚያ የኢኮኖሚ አብዮት የአዲስ አድማስ ሚያዚያ 3፤ 2010 ዘገባን ይመልከቱ፤(አዲስ አድማስ 2010)፡፡

[11] የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ) በ2012 የወጣውን ሪፖርት ይመልከቱ (ኢዜማ 2012)፡፡

ተመላሾች እና በወጣቶች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የተቃዋሚ ፓርቲ አመራሮችና አክቲቪስቶች በክልልና በፌደራል ደረጃ ተሹመዋል፡፡ በተጨማሪም የአማራ ክልላዊ መንግሥት በወጣቶች ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትና ድጋፍን እያገኘ የነበረውን የአማራ ወጣቶች ማኅበር (አወማ) አመራሮች በማባበል ወደራሱ ለማምጣት ረዥም መንገድ ተጉዟል፡፡ ባለሥልጣናቱ በተለያዩ ከተሞች የሚገኙ የማህበሩ መሪዎችን እና አባላትን በመንግሥት በሚደገፈው የአማራ ክልል ወጣቶች ማኅበር ውስጥ ሥራ እንደሚሰጣቸው ቃል በመግባት እና ጥቅማ ጥቅሞችን በማቅረብ መሪዎቹ ወደ መንግሥታዊው ማህበር እንዲገቡ በማድረግ ማህበሩን አዳክመዋል፡፡

በአማራ ክልል የወጣቶችን ድጋፍ ለማግኘት ገዢው ፓርቲ የቃላት ሽንገላን ውጤታማ በሆነ መንገድ ተጠቅሟል ማለት ይቻላል፡፡ በመሆኑም መንግሥት በመጀመሪያዎቹ ሁለት የሥልጣን አመታት የማንነት ፖለቲካን በማጣጣል ላየኢትዮጵያን አንድነት የሚያጎሉ ትርክቶችን በሰፊው አራምዷል፡፡ ይህም ያለፈውን የሀገሪቱ ታሪክ ባብዛኛው በአዎንታዊ መልኩ የሚመለከቱትን፤ እንዲሁም በህዝባቸው ላይ ደርሷል ለሚሉት ችግር በማንነት ላይ የተመሠረተውን የፌዴራል ሥርዓት ተጠያቂ የሚያደርጉትን የአማራ ወጣቶች እና የአማራ ልሂቃንን ድጋፍ ለማግኘት ረድቷል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይህም ሆኖ ገዢው ፓርቲ ከቃላት ሽንገላ ባለፈ ከማንነት ተኮር ፖለቲካ ለመራቅ እዚህ ግባ የሚባል ጥረት ሲያደርግ አልተስተዋለም፡፡

## 3.2 ተፅዕኖ/ጭቆና

ለወጣት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በተለይም መዳከም ሌላው ምክንያት መንግስት በተለያዩ መንገዶች በእቅስቃሴዎቹ ላይ የወሰዳቸው ጨቋኝ እርምጃዎች ናቸው፡፡ በአማራ ክልል እነዚህ የተፅዕኖ ዘይቤዎች የተለያዩ መልኮች ነበሯቸው፡፡ ከላይ እንደተገለጸው ከ2010 በኋላ የነበሩት የመጀመሪያ ጊዜያት በቀደመው ሥርዓት የነበረው አፈና በእጅጉ የቀነሰባቸው ‹‹የጫጉላ ወቅት›› ሊባሉ የሚችሉ ነበሩ፡፡ ወጣቶቹ ለአዲሱ አስተዳደር ቀና አመለካከት የነበራቸው ሲሆን፤ በጊዜው በክልሉ የተካሄዱት ሠላማዊ ሠልፎችም በዋናነት አዲሱን አመራር በመደገፍ የተካሄዱ ነበሩ፡፡ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ የማህበረሰብ አንቂዎችና ወጣቶች በአዲሱ መንግሥት የመጀመሪያው ዘመን ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ እና የመደራጀት እንዲሁም የቅስቀሳ ነጻነት ይንፀባረቅበት እንደነበረ ያምናሉ፡፡ የመደራጀት ነፃነት መረጋገጡ የተለያዩ ድርጅቶች፤ በተለይም የአማራ ወጣቶች ማኅበር (አወማ) እና የአማራ ተማሪዎች ማኅበር (አተማ) እንዲጠናከሩ ሲያደርግ፤ ፋኖዎችም ከመደበቅ ይልቅ በከተሞች በግልጽ መደራጀት የጀመሩበት ወቅት ነበር

ሆኖም አዲሱ አመራር ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ከክልሉ ውጭ ባሉ የአማራ ተማሪዎች፣ አብያተ ክርስቲያናት እና የአማራ ተወላጆች ላይ የሚደርሰው ጥቃት እየጨመረ መምጣቱ በአዲሱ መንግሥት ላይ ቁጣና ጥርጣሬ እንዲበረታ አድርጓል:: በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በአማራ ተወላጆች ላይ ጥቃቶች እየደረሱ ነው በሚል ምክንያት የወጣቶች ቁጣ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጣ:: በመሆኑም በክልሉ በሰፊው ሲካሄዱ የነበሩት የድጋፍ ሠልፎች በተቃውሞዎች ተተኩ:: በ2012 በተለያዩ ክልሎች ለሚገኙ የአማራ ተወላጅ የዩንቨርስቲ ተማሪዎች መንግሥት ጥበቃ አላደረገም በሚል በአማራ ክልል ከተሞች ሰፊ ተቃውሞዎች ተቀሰቀሱ:: ለእነዚህ ተቃውሞዎች መቀስቀስ ዋና ምክንያት የነበረው በርካታ የአማራ ተወላጅ የሆኑ ሴት ተማሪዎች ከደምቢ ዶሎ ዩኒቨርሲቲ በታጠቁ ግለሰቦች ታግተው መወሰዳቸው ነበር:: በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች (በተለይም በኦሮሚያ ክልል) የአማራ ተወላጆች ላይ ከደረሱ ጥቃቶች በኋላ ተመሳሳይ ተቃውሞ ተካሂዷል::

የአማራ ወጣቶች መንግሥትን ክፉኛ መተቸት በመጀመራቸው መንግሥትም በበኩሉ በተለያዩ መልኮች በሚገለጽ ሁኔታ ቁጥጥሩንና እርምጃውን አጠናከረ:: በዚህም ሂደት ውስጥ የአማራ ወጣቶች ማኅበር የመጀመሪያው ዒላማ ነበር ማለት ይቻላል:: መንግሥት በማኅበሩ ላይ ጫና መፍጠር ሲጀምር ማኅበሩም እየተዳከመ ሄደ:: የክልሉ መንግሥት በመዋቅሩ ስር የተደራጀውን የአማራ ክልል ወጣቶች ማህበርን በማጠናከር ወደ ተቃውሞ ያደላውን የአማራ ወጣቶች ማኅበርን የማያስፈልግ መሆኑን ገለጸ:: በሰኔ 2011 የአማራ ክልል ፕሬዜዳንት እና የፀጥታ ዘርፍ ሀላፊ መገደል ለአፈናው መጠናከር ምቹ ሁኔታን ፈጠረ:: የፖለቲካ ቀውሱን ተከትሎ የወጣት ማኅበራት፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና የፋኖ አባላት ለእስር ተዳርገዋል::

ነገር ግን በጥቅምት 2013 በሰሜን ኢትዮጵያ በፌዴራል መንግሥት እና በህወሓት መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት በመንግሥት እና በአማራ ወጣቶች መካከል ያለው የግንኙነት ሁኔታ እንዲለወጥ አደረገ:: መንግሥት በጦርነቱ ድል ለማግኘት የአማራ ልዩ ኃይል እና የአማራ ወጣቶች (በተለይም የፋኖዎች) ድጋፍ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘቡ ከእነሱ ጋር ያለውን ግኑኝነት ለማደስ ሞከረ:: በመሆኑንም ፋኖ በድጋሚ በመንግሥት መወደስ ጀመረ::

ነገር ግን ከህወሓት የመጣው ስጋት መቀልበስን ተከትሎ ነገሮች ወደ ነበሩበት የተመለሱ ሲመስል፣ መንግሥት ዳግም ወደ አፈና ስልቱ ተመለሰ፤ ፋኖንም ኢ-መደበኛ አደረጃጀት በማለት ትጥቅ ለማስፈታትና አደረጃጀቶቹን ለማፍረስ መንቀሳቀስ ጀመረ:: በወጣቶች ማኅበራት ላይ የሚደርሰው ተፅዕኖም ዳግም የቀጠለ

ከመሆኑ በተጨማሪ መንግሥት ከአማራ ተማሪዎች ማኅበር ጋርም ግጭት ውስጥ ገባ፡፡ ለምሳሌ የተማሪዎች ማኅበሩ ያልተለመደ ያለውን የፈተና ውጤት በመቃወም ሠላማዊ ሠልፍ ሲጠራ፤ መንግስት የሠላማዊ ሠልፍ ፍቃድ ከመከልከሉ በላይ በባህር ዳር እና በደብረማርቆስ ያሉ የማኅበሩ አመራሮችን ለአጭር ጊዜ ቢሆንም አስሮ ነበር፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ በወጣቶች እንቅስቃሴ ላይ በኦሮሚያም በተለያዩ ሁኔታዎች ተፅዕኖዎች ተካሂደዋል፡፡ ከአማራ ክልል ጋር ሲነፃፀር፤ በኦሮሚያ የነበረው ‹‹የጫጉላ›› ጊዜ በጣም አጭር የነበረ ሲሆን፤ ወጣቱን በጥቅማ ጥቅም ከማባበል ጎን ለጎን መንግስት የሀሳብ ልዩነቶችን በጉልበት የማፈን ተግባራት ሲያከናወን ቆይቷል፡፡ በሌላ በኩል በኦሮሚያ ተፅዕኖውን ያፋጠነው በመንግስትና ከኦሮሞ ነጻነት ግንባር በተከፈለው በኦሮሞ ነፃነት ጦር (ኦነግ-ሸኔ) የሚደረገው ግጭት ነው፡፡ የመንግስትና የቄሮን ግንኙነት ወሳኝ በሆነ ሁኔታ የተቀየረው በተቃውሞ ዜማዎቹ የሚታወቀው ዝነኛው የኦሮሞ አርቲስት ሀጫሉ ሁንዴሳ በሰኔ 2012 መገደሉን ተከትሎ በኦሮሚያ ክልል ባሉ በርካታ ከተሞች እና በመዲናዋ አዲስ አበባ ከተካሄደውና ከፍተኛ ጥፋት ካደረሰው የወጣቶች ተቃውሞ በኋላ ነው፡፡ መንግሥት በወሰደው እርምጃ በኦሮሚያ ክልል በሺዎች የሚቆጠሩ ወጣቶች ለእስር ተዳርገዋል፡፡

ከለውጡ አራት ዓመታት በኋላ አንዳንድ ዋና ዋና የቄሮ መሪዎች እና አስተባባሪዎች መንግስትን በተለያየ ደረጃ ሲቀላቀሉ፣ የተወሰኑት ሲሰደዱና ሌሎቹ ደግሞ የተቃውሞውን ጎራ ሲቀላቀሉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በተቃውሞ እንቅስቃሴ የተሳተፉ የኦሮሞ ወጣቶች ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ራሳቸውን አቅበዋል፡፡

## 4 ማጠቃለያ

በኦሮሚያና በአማራ ክልሎች ከ2008-2010 የተካሄዱት የወጣቶች የፖለቲካ ተቃውሞ አንቅስቃሴዎች የኢሕአዴግ መራሹ የፖለቲካ ሥርዓት እንዲያከትምና የፖለቲካ ተሀድሶ እንዲደረግ ዓይነተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ምንም እንኳን የጠራ አደረጃጀት ባይኖራቸውም ወጣቶቹ በከፍተኛ ፍጥነት በራሳቸው ቡድኖች ለመደራጀት ችለዋል፡፡ ቄሮና ፋኖ የነዚህ እንቅስቃሴዎች ውጤቶች ናቸው፡፡ በኢሕአዴግ ውስጥ ለውጥ ይፈልግ የነበረው ኃይል እነዚህን የተቃውሞ እንቅስቃሴዎች በሚገባ በመጠቀም የሚፈለገውን ለውጥ ለማምጣት ችሏል፡፡ ከላይ አንደተጠቀሰው አዲሱ መንግሥት ሥልጣን እንደያዘ የነዚህ የወጣት ቡድኖችና የመንግሥት ግንኙነት መልካም ሆኖ መቀጠል ችሎ ነበር፡፡

ይሁንና የቡድኖቹና የመንግሥት ግንኙነት ቀስ በቀስ በጥርጣሬና ባለመተማመን ተተካ። መንግሥትም ቡድኖቹና አባላቶቻቸው የጥፋት መሣሪያ ሆነዋል በማለት አንድም የቡድኖቹን መሪዎችና አባላት ልዩ ልዩ ጥቅማ ጥቅሞች በመስጠትና በማባበል ወደራሱ በማምጣት እንዲሁም በኃይል በማፈን ቡድኖቹ እንዲዳከሙና እንዲከፋፈሉ አድርጓል።

የእንቅስቃሴዎቹ መሪዎች ለመንግሥት እርምጃዎች የተለያዩ ምላሾችን ሰጥተዋል፤ አንዳንዶቹ የመንግሥትን ማባበያ በመቀበል በአዲስ መልክ በተደራጀው የክልል እና የፌዴራል አስተዳደር መዋቅር ውስጥ ሲገቡ፤ ሌሎቹ ተሰደዱ፣ ከፖለቲካ ራቁ ወይም የተቃዋሚ ቡድኖችን (አማፂ ቡድኖችን) ጨምሮ ተቀላቀሉ።

ይሁን እንጂ ለቡድኖቹ መዳከምና በፖለቲካ መስመሮቻቸው አለመቀጠል ይህ የመንግሥት እርምጃ ብቸኛና ዋና ምክንያት አይደለም። ቡደኖቹ ከመጀመሪያው ሲነሱ የነበረውን ሥርዓት ከመቃወምና ለውጥ ከመፈለግ ባሻገር የሚያስተሳስራቸው ርዕዮተ-ዓለምና የጋራ ርዕይ አልነበራቸውም። ሁለቱም የወጣቶች ንቅናቄዎች ልክ እንደ አብዛኞቹ አዳዲስ ማኅበራዊ ንቅናቄዎች የሥልጣን ተዋረድ ያለው ድርጅታዊ መዋቅር የሌላቸው ሲሆኑ፤ በአመዛኙ በአካባቢ ደረጃ፣ ማንነት ላይ በመመስረት፣ በፈቃደኝነት እና በራሳቸው የተደራጁ እንዲሁም ወጥነት የሌላቸው ነበሩ ማለት ይቻላል። ይህም በአንድ በኩል እንቅስቃሴዎቹ ከሁኔታዎች ጋር በቀላሉ ራሳቸውን ማጣጣም እንዲችሉ እና ተለዋዋጭ እንዲሆኑ ስላስቻላቸው አገዛዙን በመገዳደር ረገድ ስኬታማ እንዲሆኑ ረድቷቸዋል። በሌላ በኩል ግን ድርጅታዊ መዋቅር እና ግልጽ ርዕእዮተ ዓለምና አመራር አለመኖር ከተቃውሞው በኋላ ለሚኖረው ሁኔታ የጠራ አጀንዳ እንዳይኖራቸው አድርጓቸዋል። በዚህ ሳቢያ በኋላ እንደታየው እንቅስቃሴዎቹ በፖለቲካ ልሂቃን እንዲጠለፉ ምክንያት ሆኗል። በመሆኑም ወጣቶች የተቃውሞ ትሩፋቶቻቸውን ወደ እውነተኛ የፖለቲካ ትርፍ መተርጎም ሳይሳካላቸው ቀርቷል ማለት ይቻላል። በአዲስ መልክ የተቋቋመው መንግሥትም ከላይ እንደተብራራው ማባበያንና አፈናን በማጣመር እንቅስቃሴዎቹን መቆጣጠር ችሏል።

## ዋቢ ጽሑፎች

Abebaw Y. Adamu, & Balsvik, R. R. (2017). Students' Participation in and Contribution to Political and Social Change in Ethiopia. In C. Gunderson & B. E. Crawford (Eds.), What Politics? (pp. 265-284). Brill: Nijhoff.

Addis Standard (2018), "Feature: PM Abiy Ahmed visits Ambo, protest epicenter in search of answers", April 12, 2018, https://addisstandard.com/feature-pm-abiy-ahmed-visits-ambo-the-epicenter-of-the-oromo-struggle-in-search-of-answers/

Bahru Zewde, (2014). The Quest for Socialist Utopia: The Ethiopian Student Movement, c. 1960-1974. James Currey

Balsvik, R. R. (2007), The Quest for Expression: The State and the University in Ethiopia under Three Regimes, 1952-2005. Addis Ababa: Addis Ababa University Press

Labzaé, M (2022), "The war in Tigray (2020–2021): Dictated truths, irredentism and déjà-vu", in Routledge Handbook of the Horn of Africa, London: Routledge

Mosisa Aga, (2020). Qeerroo: A regimented organization or a spontaneous movement?. Ethiopia Insight. https://www.ethiopia-insight.com/2020/08/21/qeerroo-a-regimented-organization-or-a-spontaneous-movement/

Østebø, T. (2020), "Analysis: The role of the Qeerroo in future Oromo politics", Addis Standard, https://addisstandard.com/analysis-the-role-of-the-qeerroo-in-future-oromo-politics/

አዲስ አድማስ (2010), "የኦሮሚያ "የኢኮኖሚ አብዮት" እና ባለሀብቶችን ያሰጋው እርምጃ"፣ ሚያዚያ 3፣ 2010 ፤ https://www.addisadmassnews.com/index.php?option=com_k2&view=item&id=19902:የኦሮሚያ-"የኢኮኖሚ-አብዮት"-እና-ባለሃብቶችን-ያሰጋው-እርምጃ&Itemid=232

ኢዜማ (2012)፣ "በአዲስ አበባ ከተማ የመሬት ወረራ እና የጋራ መኖሪያ ቤቶች ኢፍትሃዊ ዕደላን አስመልክቶ የተደረገ ጥናት ውጤት"።

## ጥናታዊ ጽሁፍ አቅራቢዎች

**ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ፡-** ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ተመራማሪ፥ የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ መስራች እና ዋና ምክትል ፕሬዝዳንት እንዲሁም የአፍሪካ ሳይንስ አካዳሚ አባል ናቸው። በተለይም ስለ ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ በሰፊው የፃፉት ፕሮፈሰር ባህሩ ዘውዴ፤ በአሁኑ ወቅት የመልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-ምሥራቃዊ አፍሪካ የቦርድ ሰብሳቢ ናቸው።

**ዶ/ር የቆየአለም ደሴ፡-** ዶክተር የቆየአለም ደሴ የሶስተኛ ዲግሬያቸውን በደቨሎፕመንታል ሳይኮሎጂ (Developmental psychology) ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ያገኙ ሲሆን በስርዓተ ትምህርት እና በስነ-ልቦና-ማህበራዊ ፕሮግራም ዲዛይን፣ ልማት፣ ትግበራ እና ግምገማ ላይ ሰፊ ልምድ አላቸው። በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የትምህርትና የባህርይ ጥናት ኮሌጅ ዲን ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

**ዶ/ር ጠና ደዎ፡-** ዶ/ር ጠና ደዎ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፍልስፍና ትምሕርት ክፍል በረዳት ፕሮፌሠርነት ማዕረግ በመምህርነትና ተመራማሪነት በመሥራት ላይ የሚገኙ ሲሆን፤ ‹‹ሰው፤ ግብረገብነትና ስነምግባር፡- የዘመናችን ቁልፍ ጉዳዮች›› በሚል ርዕስ ካሳተሙት መጽሐፍ በተጨማሪ አያሌ የጥናትና ምርምር ወረቀቶችን በተለያዩ ሳይንሳዊ መፅሔቶች ላይ አሳትመዋል።

**አቶ ዑርጌሣ ደሬሳ፡-** አቶ ዑርጌሳ ደሬሳ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካ ሳይንስና አለም አቀፍ ትምህርት አግኝተዋል። አቶ ዑርጌሳ በአምቦ ዩኒቨርስቲ በመምሕርነትና ተመራማሪነት የሚያገለግሉ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ የዶክትሬት ትምሕርታቸውን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሰላምና ደህንነት ጥናት ኢንስቲትዩት በማጠናቀቅ ላይ ይገኛሉ።

**ዶ/ር አስናቀ ከፋለ፡-** ዶ/ር አስናቀ ከፋለ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን ከላይደን ዩኒቨርሲቲ (ኔዘርላንድስ) በፖለቲካል ሳይንስ ያገኙ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስ ትምሕርት ክፍል በተባባሪ ፕሮፌሰርነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ። ዶ/ር አስናቀ ሰፊ የጥናትና ምርምር ልምድ ያላቸው ሲሆን ፌዴራሊዝም፣ ግጭትና የግጭት አፈታት፣ ፍልሠት እና የወጣት ልማት ከምርምር መስኮቻቸው መካከል ይጠቀሳሉ።

**አማኑኤል ተስፋዬ፡-** አማኑኤል ተስፋዬ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳይንስና አለም ዓቀፍ ግንኙነት የማስተርስ ዲግሪ፤ እንዲሁም ከለንደን ስኩል ኦፍ ኢኮኖሚክስ በዴቨሎፕመንት ስተዲስ የማሰተርስ ዲግሪ ያገኙ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሄልሲንኪ ዩነቨርስቲ የዶክተሬት ትምሕርታቸውን በመከታተልመላይ ይገኛሉ። ማህበራዊ ንቅናቄዎች (social movements)፣ የብሔርና ብሔርተኛ እንቅስቃሴዎች እና ፖለቲካ ኢኮኖሚ ከጥናትና ምርምር ዘርፎቻቸው መካከል ዋናዎቹ ናቸው። ከጥናትና ምርምር በተጨማሪ አቶ አማኑኤል ቀደም ሲል በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በፖለቲካል ሳየኝስና አለም አቀፍ ግንኙነት ትምሕርት ክፍል በመምሕርነት አገልግለዋል።

አንድ መቶ ኃያ አምስት ሚሊዮን ገደማ ከሚገመተው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ሠላሳ ከመቶውን እንደሚደርስ የሚገመተው ወጣቱ የሕብረተሠብ ክፍል ፖለቲካዊና ማኅበራዊ ለውጦችን ለማምጣት በተለያዩ ጊዜያት በተደረጉ ትግሎች ውስጥ ጉልህ ሚና ተጫውቷል። የዘውዳዊውን ስርዓት ለመገርሰስ ከመታገል አንስቶ፣ በደርግ የአገዛዝ ዓመታት፤ በኋላም በኢሕአዴግ ዘመን ወጣቱ ማኅበራዊ ለውጥ እንዲመጣና ፍትሕ እንዲሰፍን ከፍተኛ መስዋዕትነት መክፈሉ ይታወቃል። በተለይ በ2008 ጀምሮ በአገሪቱ በተካሄደው የፖለቲካ ተሃድሶ ለውጥ ትግል ውስጥ ወጣቱ ራሱን በማደራጀት ከፍተኛ አንቀሳቃሽ ኃይል መሆኑን አሳይቷል፤ የመንግሥት ለውጥ በማምጣት በተደረገው ትግል ውስጥም ከፍተኛ ገንቢ ሚና ተጫውቷል። ይህ ጊዜ ምናልባትም ከ1966ቱ አብዮት በኋላ ቀደም ሲል ባልታየ ሁኔታ የወጣቱ የፖለቲካ ተሳትፎ ጎልቶ የታየበት ነበር ማለት ይቻላል።

ይህ መጽሀፍ ***መልካም አስተዳደር ለአፍሪካ-የአፍሪካ ቀንድ*** ቀጣናዊ ጽ/ቤት ***«ወጣትና ፖለቲካ በኢትዮጵያ»*** በሚል ርዕስ ባካሄዳቸው ተከታታይ ሕዝባዊ የውይይት መድረኮች ላይ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎችን አካትቶ ይዟል፡፡ ጥናታዊ ጽሁፎቹ በአገሪቱ በተለይም ከ2008 ጀምሮ በሚታዩት የወጣቱ ፖለቲካዊ አመለካከቶች እና ድርጊቶች ላይ ጉልህ ተፅዕኖ አሳድረዋል ተብለው የሚገመቱ ጉዳዮችን ይዳስሳሉ፤ ይተነትናሉ፤ የፖሊሲ ምክረ-ኃሳብም ያቀርባሉ።